# ዲስረፕቲንግ ሀርም በ ኢትዮጵያ፡

ስለ በይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የማስረጃ ድጋፍ




Funded by End Violence Against Children

Implemented by ecpat INTERPOL unicef Office of Research-Innocenti

**ማሳሰቢያ:**

*ዲስረፕቲንግ ሀርም* በባሕርይው ውስብስብ እና ስሱ (sensitive) በሆነው ርእሰ-ጉዳይ ላይ፤ ማለትም በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ላይ ያተኮረ የምርምር ሥራ ነው። ተጠቂዎቹ በራሳቸው አንደበት የተናገሩትን ጨምሮ፤ በሪፖርቱ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ስሜትን የሚፈታተኑ ድርጊቶች ተገልጸዋል። አንዳንድ አንባቢዎች፤ በተለይም የወሲብ ጥቃት ገጠመኝ የነበራቸው ሰዎች፤ የሪፖርቱን አንዳንድ ክፍሎች ማንበብ ሊረብሻቸውይችላል። የሚያሳድርብዎትን ስሜት እየተቆጣጠሩ፤ ሪፖርቱን ምቾት በሚሰጥዎ አኳኋን እንዲያነቡ ይበረታታሉ። ብርቱ መረበሽ ካሳደረብዎ ግን እባክዎ የሥነ-ልቦና ድጋፍ ለማግኘት ይሞክሩ።


**ዋቢ ድርሳናት፡**

ኢ/ሲ/ፒ/ኤ/ቲ/፣ ኢንተርፖል፣ እና ዩኒሴፍ (እ.ኤ.አ. 2022)። *ዲስረፕቲንግ ሀርም በኢትዮጵያ፡ ስለ በይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የማስረጃ ድጋፍ* ። ግሎባል ፓርትነርሺፕ ቱ ኢንድ ቫዮለንስ አጌይነስት ቺልድረን



የቅጂ መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው © ኢ/ሲ/ፒ/ኤ/ቲ/፣ ኢንድ ቫዮለንስ ፓርትነርሺፕ፣ ኢንተርፖል፣ እና ዩኒሴፍ። እ.ኤ.አ. 2022፤ ትርፍ ለሚያስገኙ ተግባራት እስካልዋለ ድረስ ይህንን ሕትመት ምንጩን በመጥቀስ መጠቀም ይቻላል።



በገንዘብ ያገዘው ግሎባል ፓርትነርሺፕ ቱ ኢንድ ቫዮለንስ አጌይነስት ቺልድረን (Global Partnership to End Violence Against Children) ‹ደኅንነቱ የተጠበቀ በይነ-መረብ› በሚሰኘው ውጥኑ አማካኝነት ሲሆን፤ በእገዛው የተሠራው ጥናት ላይ የተገለጸው ይዘትግን እንደ ድርጅቱ አቋም ሊቆጠር አይገባም።

# ማውጫ


ድርሞ (Executive Summary) 6

የዲስረፐቲንግ ሀርም የጥናት ዘዴዎች 9

ስለ በይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል 13

የሕግ ማእቀፍ እና የፖሊስ ዳሰሳ 15

## 1. የበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት በኢትዮጵያ 23

1.1 የበይነ-መረብ ተደራሽነት እና ማነቆዎች 24
1.2 የሕፃናት የበይነ-መረብ አጠቃቀም 27
1.3 አስጊ የበይነ-መረብ አጠቃቀምን የተመለከቱ እሳቤዎች እና ገጠመኞች 28

## 2. የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል በኢትዮጵያ 34

2.1 በኢትዮጵያ ስላለው የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የሕፃናቱ ገጠመኞች 36
2.2 ከበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጋር ምናልባት የሚገናኙ ሌሎች የሕፃናቱ ገጠመኞች 42
2.3 ከሚታወቁ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል እና የሕ/ወ/ብ/በደል ነገረ-ጉዳዮች መነሻነት ስለ ተጎጂዎች እና ስለ አጥፊዎች የተቀሰሙ ቁምነገሮች 56
2.4 የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ምላሽ አሠጣጥ በኢትዮጵያ 59

## 3. የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ምላሽ አሠጣጥ በኢትዮጵያ 61

3.1 መደበኛ የሪፖርት/የአቤቱታ ማቅረቢያ አሠራሮች 62
3.2 የሕግ አስከባሪው ምላሽ 65
3.3 የፍትሕ ተደራሽነት እና ማካካሻዎች 67
3.4 ቅንጅት እና ትብብር 68

## 4. በኢትዮጵያ እንዴት ጉዳትን መግታት እንደሚቻል 69

## ዐማርኛ 76

## ዕውቅና እና ምስጋና 77

# መቅድም

**ሕይወታችን ከበይነ-መረብ (ከኢንተርኔት) ጋር ያለው ትስስር በየጊዜው እያደረገ ይገኛል። በይነ-መረብ እና በፍጥነት የሚለዋወጡት የዲጂታል ተግባቦት (ኮሚዩኒኬሽን) መገልገያዎች፤ በየትም ቦታ ያሉ ሰዎችን እያቀራረቧቸው ነው። ሕፃናት በእነዚህ ቴክኖሎጂዎች የሚያደርጉት ግንኙነት እና ጥገኝነታቸውም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ሲሆን፤ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ደግሞ የሕፃናቱ በርካታ የኑሮ ዘይቤዎች ወደ በይነ-መረብ የተሸጋገሩበትን ሂደት አፋጥኖታል።**

በይነ-መረብ፤ ሕፃናት ግንኙነት እንዲፈጥሩ፣ አካባቢያቸውን እንዲመረምሩ፣ ዕውቀት እንዲቀስሙ፣ ብሎም ፈጠራ-አከል እና አቅማቸውን በሚያጎለብት አኳኋን መስተጋብር እንዲያደርጉ የሚያስችላቸው ብርቱ መገልገያ ነው። የዲጂታል ከባቢ ለሕፃናቱ ኑሮ እና መብት ስላለው ፋይዳ፤ የተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መብቶች ኮሚቴ እ.ኤ.አ. በ2021 በወጣው ጠቅላላ አስተያየት ቁ. 25 ላይ አጽንኦት ሰጥቶ ገልጾታል። በይነ-መረብን መጠቀም በጊዜ ሂደት ተቀባይነት የሌላቸው ስጋቶችን እና ጉዳቶችን ማስከተሉ አይቀሬ መሆኑን ጠቅላላ አስተያየቱ የሚያሳስብ ሲሆን፤ አንዳንዶቹ አደጋዎች ከዚህ ውጪ ባሉ ሁናቴዎች ውስጥም ሕፃናቱን የሚያጋጥሟቸው፤ አንዳንዶቹ ደግሞ በበይነ-መረብ ማእቀፍ/ድባብ ውስጥ ብቻ ያሉ ዓይነተኛ ችግሮች ናቸው።

ከስጋቶቹ መካከል አንዱ በይነ-መረብን እና የዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የሕፃናትን ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ለመፈጸም የሚደረግ ያልተገባ አጠቃቀም ነው። በበይነ-መረብ ማሽኮርመም (grooming)፣ የሕፃናት ወሲባዊ በደልን የሚያሳዩ ቁሳቁሶችን (child sexual abuse material) ለሌሎች ማጋራት፣ እና የሕፃናት በደልን በቀጥታ-ሥርጭት የማስተላለፍ ድርጊቶች፤ በሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ስለሆኑ አፋጣኝ፣ የዘርፈ-ብዙ አካላትን እና የዓለም-አቀፍ ምላሽን የሚሹ ናቸው። አዘውትሮ እንደሚስተዋለው፤ እነዚህ ወንጀሎች በዲጂታል መልክ የሚቀረጹ ምስሎች እና ቪዲዮዎች ሲሆኑ፤ በበይነ-መረብ ላይ እጅግ ተዘውትረው የሚሠራጩ እና ያለገደብ በቅብብሎሽ የሚናኙ በመሆኑ፤ ሕፃናትን በተደጋጋሚ መልሶ መላልሶ ይጎዳል። የአደጋው አስጊነት ባሕሪውን እየቀያየረ እና ዕድገቱም በእጥፍ ድርብ ፍጥነት እየገሠገሠ በሄደ መጠን፤ ለመንግሥታት፣ ለፖሊሶች፣ እና ለሕፃናት ሕዝባዊ አገልግሎቶችን ለሚሰጡ አካላት ብቻ ሳይሆን፤ ከሕፃናቶቻቸው የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ጋር አብሮ ለመራመድ ለሚጣጣሩት ወላጆች እና ተንከባካቢዎችም የመከላከል እና የጥበቃ ሥራው አዳጋችነቱ እየጨመረ እንዲሄድ አድርጎባቸዋል።

በይነ-መረብን ለመላው ዓለም ለማዳረስ የሚደረገው እንቅስቃሴ እመርታ እያሳየ እንደመሆኑ፤ ከመቼውም ጊዜ በላይ በሕፃናት የበይነ-መረብ ደኅንነት እና ጥበቃ ላይ መሥራት የወቅቱ አንገብጋቢ ጉዳይ ነው። በዓለም ዙሪያ ያሉ መንግሥታት በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ስለተጋረጠው ስጋት ይበልጥ እየተገነዘቡ የመጡ ሲሆን፤ አንዳንድ ሃገራት አስፈላጊ ሕጎችን ወደ ማውጣት እና የመከላከል እርምጃዎችን ወደ መተግበር ተሸጋግረዋል። በአንጻሩ፤ የቴክኖሎጂ ኢንደስትሪው የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ሲቀርጽ እና ሲያበለጽግ፤ ‹ችግሩ ሲከሠት ኋላ መፍትሔ ይፈለግለታል› ከሚል ዘይቤ ይልቅ፤ አገልግሎቶቹ ገና ከጅምሩ ሲቀረጹ የሕፃናትን ደኅንነት ያማከሉ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ አሠራርን እንዲከተል እየተደረገበት ያለው ጫና እየጨመረ ነው። ይህን መሰል ደኅንነትን ከጥንስሱ ያካተተ የቀረጻ ሂደት የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ክሥተትን በሚያመላክት ማስረጃ ሊደገፍ የሚገባ ሲሆን፤ *ዲስረፕቲንግ ሀርም* የዚህ ዓይነቱን የማስረጃ ፍላጎት በማሟላት ረገድ የላቀ አስተዋጽኦ ያበረክታል።

ግሎባል ፓርትነርሺፕ ቱ ኢንድ ቫዮለንስ አጌይነስት ቺልድረን (Global Partnership to End Violence Against Children) ‹ደኅንነቱ የተጠበቀ በይነ-መረብ› በሚሰኘው ውጥኑ አማካኝነት፤ ለ*ዲስረፕቲንግ ሀርም* ፕሮጀክት ሰባት ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር አውጥቷል። *ዲስረፕቲንግ ሀርም* ስለ ዘርፉ ማእቀፍ፣ ስላሉት ስጋቶች፣ እንዲሁም የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን በተመለከተ የሕፃናቱ አተያይ/እሳቤ ላይ ሁለንተናዊ ዳሰሳ ለማካሄድ ዙሪያ-መለስ እና ፈጠራ-አከል የጥናት ዘዴዎችን እና አካሄዶችን ተጠቅሟል። ይህ ፈር-ቀዳጅ ፕሮጀክት፤ የኢ/ሲ/ፒ/ኤ/ቲን፣ የኢንተርፖልን፣ የዩኒሴፍ የምርምር ጽ/ቤትን (ኢኖሰንቲ እና የጽ/ቤቱ አጋሮች) ያካበቱትን የምርምር ክህሎት ተጠቅሟል። ሦስቱ ዓለም-አቀፍ አጋሮች፤ በኢ/ሲ/ፒ/ኤ/ቲ አባል ድርጅቶች፣ ኢንተርፖል በየሃገሩ በከፈታቸው በ‹ሃገር-አቀፍ ማእከላዊ ቢሮዎች› (National Central Bureaus)፣ እንዲሁም በዩኒሴፍ ሃገር-አቀፍ እና ቀጣናዊ ቅርንጫፍ ጽቤቶች አማካኝነት እገዛ ተደርጎላቸዋል። አሁን የተቀረጸውን እና በተግባር የተፈተሸውን የጥናት ሥነ-ዘዴ፤ በዓለም ዙሪያ ባሉ ሌሎች ሃገራት ላይም ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዷል።

*ዲስረፕቲንግ ሀርም* በሃገር-አቀፍ ደረጃ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ላይ ከተካሄዱ የምርምር ፕሮጀክቶች ሁሉ በሁለንተናዊነቱ እና በግዝፈቱ ቀዳሚ ሲሆን፤ የየሃገራቱን ማለትም 13 ሃገር-አቀፍ ሪፖርቶችን እና ሁለት ቀጣናዊ/ክፍለ-አህጉራዊ ሪፖርቶችን ለማውጣት ችሏል፡ ፡ ሕፃናት በበይነ-መረብ ስለሚያገጥሟቸው አደጋዎች፣ ስጋቶቹ እንዴት እንደሚፈጠሩ፣ ከሌሎች የጥቃት ዓይነቶች ጋር ስላላቸው ቁርኝት፣ እንዲሁም ለመከላከል እና ለመቀነስ መደረግ ስላለባቸው ነገሮች ሁሉን-አቀፍ ማስረጃን ይለግሳል፡፡

መንግሥታት፣ የሚመለከታቸው ዘርፎች፣ ፖሊሲ አውጪዎች፣ እና ማኅበረሰቦች በይነ-መረብን ለሕፃናት ደኅንነቱ የሚያስተማምን ለማድረግ ትክክለኛውን እርምጃዎች እንዲወስዱ ግኝቶቹ እገዛ ያበረክታሉ፡ ፡ ይህም የሃገር-አቀፍ የመከላከል እና የምላሽ አሰጣጥ ስትራቴጂዎች ሲዘጋጁ እንደ መረጃ ግብዓት መጠቀምን፣ *የዲስረፕቲንግ ሀርምን* ተደራሽነት ወደ ሌሎች ሃገራት እና ቀጣናዎች ማስፋፋትን፣ እንዲሁም በጥናቱ ላይ ተመሥርቶ አዲስ መረጃዎችን እና ዕውቀቶችን ማዳበርን ያጠቃልላል፡፡

የሕፃናትን ጉዳት መግታት የሁሉም ኃላፊነት ነው፡፡



ዶክተር ሆዋርድ ቴይለር
የኢንድ ቫዮለንስ ፓርነርሺፕ
ዋና ዳይሬክተር

# ድርሞ

**ግሎባል ፓርትነርሺፕ ቱ ኢንድ ቫዮለንስ አጌይነስት ቺልድረን ‹ደኅንነቱ የተጠበቀ በይነ-መረብ› በሚሰኘው ውጥኑ አማካኝነት ባደረገው የገንዘብ ድጋፍ፤ *ዲስረፕቲንግ ሀርም ን፤* ማለትም በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ላይ ያተኮረውን የምርምር ፕሮጀክት፤ ኢ/ሲ/ፒ/ኤ/ቲ (በእንግሊዝኛው ምሕፃረ-ቃል ECPAT)፣ ኢንተርፖል (INTERPOL)፣ እና የዩኒሴፍ (UNICEF) የምርምር ጽሕፈት ቤት (ኢኖሰንቲ) በጋራ ቀርጸው ተግብረዋል። በዓይነቱ ልዩ የሆነው ይህ ጥምረት፤ ውስብስብ ይዘት ያለውን ጉዳይ ለመመርመር የሚችሉ ከበርካታ መስኮች የተውጣጡ ባለሙያዎችን ያሳተፈ ሲሆን፤ ይህም በሁሉም አቅጣጫዎች ያሉትን ችግሮች ለመቃኘት እንዲቻል ነው። የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል፤ የዲጂታል ወይም የተግባቦት (ኮሚዩኒኬሽን) ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም፤ የብዝበዛ እና የበደል ድርጊቱ እየተካሄደ በቀጠለበት የጊዜ ፍሰት ወስጥ *በአንዱ ነጥብ* ላይ ያለውን ሁኔታ የሚያመለክት ነው። በድርጊቱ ፈጻሚዎች እና በሕፃናት መካከል የሚደረገው ግንኙነት፤ ሙሉ በሙሉ በበይነ-መረብ ብቻ፤ አሊያም ሁለቱንም ማለትም በይነ-መረብን እና የአካል/ፊትለፊት ግንኙነትን ባጣመረ መልኩ ሊሆን ይችላል። *የዲስረፕቲንግ ሀርም* ምርምር ኢትዮጵያን ጨምሮ ሰባት የምሥራቃዊ እና የደቡባዊ አፍሪካ ሃገራትን፤ እንዲሁም ስድስት የደቡብ-ምሥራቃዊ የእስያ ሃገራትን የሸፈነ ነው። በተለያዩ ዘጠኝ ፈርጆች/ርእሰ-ጉዳዮች ላይ ከተካሄዱት ምርምሮች የተገኙት ጥሬ መረጃዎች ላይ ትንተና የተደረገ ሲሆን፤ ትንተናውም ለየሃገሩ በተናጠል የተሰናዱ ሃገር-አቀፍ ሪፖርቶችን ለማዘጋጀት ጥቅም ላይ ውሏል፤ ሪፖርቱም ስለ ስጋቶቹ በማውሳት የተብራሩ የትግበራ ምክረ-ሐሳቦችን ይለግሳል።**

***የዲስረፕቲንግ ሀርም* ምርምር የያዛቸው ግኝቶች እና የትግበራ ምክረ-ሐሳቦች ለሰፊው የዓለም ማኅበረሰብ የላቀ ፋይዳ ያለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በአንጻሩ የዚህ የኢትዮጵያ-ተኮር ሪፖርት ዓላማ ደግሞ መንግሥት፣ ሕግ አስከባሪው፣ የሲቪል ማኅበረሰቡ፣ እና ሌሎች የሚመለከታቸውን ጨምሮ በኢትዮጵያ ያሉ የጉዳዩ ባለድርሻዎች የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን በብቃት ለመቅረፍ የሚያስችላቸውን የመንደርደሪያ (baseline) ማስረጃ ለማስጨበጥ ነው።**

## የሕፃናት እና የተንከባካቢዎቻቸው የበይነ-መረብ ተደራሽነት

በኢትዮጵያ ከ12 እስከ 15 ዓመት ዕድሜ ካላቸው ከአራቱ ሕፃናት ውስጥ አንዳቸው የበይነ-መረብ ተጠቃሚ[1] ሲሆኑ፤ ከእነዚህ ውስጥ ዕድሜያቸው 16 እና 17 ከሆናቸው (46 በመቶዎቹ) ይልቅ ከ12 እስከ 13 ዓመት ዕድሜ ያላቸው (8 በመቶዎቹ) በይነ-መረብን የመጠቀም ዝንባሌያቸው እጅግ ያነሰ ነበር።  በገጠር እና በከተማ መካከል ግልጽ የዲጂታል ድንበር አለ። በከተሞች ውስጥ በአማካይ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ካላቸው መካከል 45 በመቶዎቹ የበይነ-መረብ ተጠቃሚዎች የነበሩ ሲሆን፤ የገጠሩ ድርሻ ግን 21 በመቶ ነበር።

በአባወራ/ቤተሰብ የዳሰሳ ጥናቱ ከተሳተፉት የበይነ-መረብ ተጠቃሚ የኢትዮጵያ ሕፃናት ውስጥ እጅግ የሚበዙት (98 በመቶ)፤ በበይነ-መረብ ለመገናኘት የሚጠቀሙት የስማርት ተንቀሳቃሽ ስልክ ቀፎን ሲሆን፤ በጣም ጥቂቶቹ ኮምፒዩተሮችን ወይም ታብሌቶችን ይጠቀማሉ። ከግማሽ በላይ የበይነ-መረብ ተጠቃሚ የኢትዮጵያ ሕፃናት በይነ-መረብን ለመጠቀም የሚገለገሉበት የራሳቸው መሣሪያ ባለቤት ሲሆኑ፤ 45 በመቶዎቹ ደግሞ የስማርት ስልክ ቀፎን ከሌላ ሰው ጋር በጋራ (በደባልነት) የሚጠቀሙ ነበሩ፡ ፡ በ16 እና 17 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ ካሉት ጋር ሲነጻጸር፤ በዕድሜ ያለሱት ሕፃናት ስማርት ስልክ ቀፎን በደባልነት የመጠቀም ዕድላቸው በእጥፍ ጨምሮ የታየ ሲሆን፤ በተመሳሳይም ከወንዶች ልጆች ይልቅ ልጃገረዶች መሣሪያዎችን በደባልነት የሚጠቀሙበት ሁኔታ የሰፋ ነበር።

የአባወራ/ቤተሰብ ዳሰሳ ጥናቱ እንደሚያመለክተው፤ ከኢትዮጵያ የበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት ውስጥ ያለ አንዳች ክልከላ በይነ-መረብን መጠቀም የሚችሉት 13 በመቶዎቹ ብቻ ናቸው። የበይነ-መረብ ተደራሽነት ላይ የተደቀኑት  ዋነኞቹ መሰናክሎች የመሠረተ-ልማት ችግሮች ሲሆኑ፤ ለአብነት ያህል ቀርፋፋ መስመር እና ደካማ ሞገድ/ሲግናል፤ በመቀጠልም የበይነ-መረብ የአገልግሎት ክፍያ ውድነት፣ እና የኤሌክትሪክ አቅርቦት ውሱንነት ናቸው።

## አስጊ የበይነ-መረብ አጠቃቀም ባሕርያት

በአባወራ/ቤተሰብ ዳሰሳ ጥናቱ ከተሳተፉት ተንከባካቢዎች መካከል እጅግ የሚያመዝኑት፤ በበይነ-መረብ አማካኝነት ልጆቻቸው ከባይተዋር (ከማይታወቅ) ሰው ጋር ግንኙነት ይጀምራሉ፤ ወይም ከወሲባዊ ምስሎች ጋር በድንገት ይገጣጠማሉ የሚል ከፍተኛ ፍራቻ አላቸው። 52 በመቶ የሚሆኑት እነዚህ ተንከባካቢዎች፤ ከባይተዋር ግለሰቦች ጋር በበይነ-መረብ መነጋገር ለሕፃናት ‹እጅግ አደገኛ› መሆኑን ገልጸዋል። መሰል ድርጊቶች ለሕፃናት ‹እጅግ አደገኛ› ስለመሆኑ የሚሰማቸው 26 በመቶዎቹ ብቻ እንደመሆናቸው፤ የበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት ለዚህ ጉዳይ ያላቸው ደንታ/ጥንቃቄ እምብዛም አለመሆኑ ተስተውሏል።

እውን ሕፃናት እንዲህ ባሉ አስጊ ድርጊቶች እየተሳተፉ ነውን? በዳሰሳ ጥናቱ ከተሳተፉት የበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት ውስጥ 42 በመቶዎቹ፤ በባለፈው ዓመት ውስጥ ከዚህ በፊት ጨርሶ አግኝተዋቸው የማያውቁ ሰዎችን አድራሻ፤ በአድራሻ መዝገባቸው ውስጥ ያካተቱ ሲሆን፤ ከእነዚህም ሕፃናት ውስጥ 33 በመቶዎቹ የግል መረጃዎቻቸውን አስቀድሞ በአካል/በፊትለፊት አግኝተው ለማያውቁት ግለሰብ ሰጥተዋል ወይም አጋርተዋል።

ይብሱንም፤ 80 በመቶ የሚሆኑት ተንከባካቢዎች በይነ-መረብን ፈጽሞ ተጠቅመው አያውቁም። *የዲስረፕቲንግ ሀርም* የአባወራ/ቤተሰብ ዳሰሳ ጥናቱ እንደሚያመለክተው፤ በጥቅሉ ተንከባካቢዎች በይነ-መረብን የሚጠቀሙት ከልጆቻቸው ባነሰ መጠን ሲሆን፤ ይህም የልጃቸውን የበይነ-መረብ አጠቃቀም ለመግራት እና ሊከሠቱ የሚችሉ አደጋዎችን ለማለዘብ ያላቸው አቅም ውሱን መሆኑን ያመላክታል። አንድ ሦስተኛ የሚሆኑት ተንከባካቢዎች፤

1. መይነ-መረብ ተጠቃሚዎች ማለት በይነ-መረብን ባለፉት ሦስት ወራት የተጠቀሙትን ያመለክታል (ብዛት = 5 ሺህ 938 ሕፃናት)

ልጆቻቸው ከበይነ-መረብ ጋር በተገናኘ ጉዳይ ከተረበሹ ወይም ስሜታቸው ከደፈረሰ፤ በሕፃናቶቻቸው የበይነ-መረብ ግንኙነት ላይ ዕቀባ ወደ ማድረግ እንደሚሄዱ ገልጸዋል።

ሁለት-ሦስተኛ የሚሆኑት የበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት፤ ደኅንነቱ የተጠበቀ የበይነ-መረብ አጠቃቀምን በተመለከተ ምንም ዓይነት ትምህርት አግኝተው አያውቁም። ሆኖም፤ አብዛኞቹ ሕፃናት አስጊ የሚባሉ አንዳንድ የበይነ-መረብ አጠቃቀም ልማዶችን እንደሚያውቁ አመልክተዋል፤ ለምሳሌ የግል መረጃቸውን ለሌሎች መስጠት፣ እና ወሲባዊ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን ለሌሎች መላክ አስጊ ድርጊት እንደሆነ። ይህም ሆኖ፤ ከእነዚህ መካከል አናሳ ቁጥር ያላቸው ሕፃናት፤ በባለፈው ዓመት ውስጥ አስጊ የሆነ የበይነ-መረብ አጠቃቀም ልማድ እንደነበራቸው ገልጸዋል። 14 በመቶዎቹ አስቀድሞ በበይነ-መረብ የተዋወቁትን ሰው ኋላ ላይ በአካል/ፊትለፊት ያገኙት ሲሆን፤ 6 በመቶዎቹ ደግሞ የገዛ ዕርቃናቸውን የሚያሳዩ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን ለሌሎች በበይነ-መረብ አማካኝነት አጋርተዋል። ዕርቃን ገላን የሚያሳዩ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን ለምን እንደላኩ ሲጠየቁ በሕፃናቱ የተሰጠው ዋነኛ ምክንያት፤ የቅብጠት (flirting) ስሜት ስላደረባቸው ወይም እንደ ጨዋታ ስላዩት (ልክ በፍቅረኞች መካከል እንዳለው ዓይነት) የሚለው ይጠቀሳል። በቁጥር አነስተኛ የሆኑ ሕፃናት በተደረገባቸው ጫና/ማስገደድ የተነሣ ወሲባዊ ይዘቶችን ልከዋል። ወሲባዊ ይዘቱ ከጅምሩ ከእጃቸው የወጣው ወይም ለሌሎች የተጋራበት አግባብ ምንም ይሁን ምን፤ ከአንዱ ወደ አንዱ እያለ ለብዙዎች በቅብብሎሽ የሚሠራጭበት አደጋ ተፈጥሯል ማለት ነው።

## ስለ በይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ላይ ያለው ግንዛቤ

*ዲስረፕቲንግ ሀርም* በኢትዮጵያ ያለውን የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን ምንነት እና የችግሩን አድማስ ለመረዳት፤ የመንግሥት ባለድርሻዎችን፣ ግንባር ቀደም የማኅበራዊ አገልግሎት ሰጪዎችን፣ ሕግ አስከባሪውን፣ እንዲሁም ሕፃናትን እና ተንከባካቢዎቻቸውን ጨምሮ ዘርፈ-ብዙ ባለድርሻዎችን አሳትፏል፡ ፡ በተደረጉት በሁሉም የጥናት ፈርጆች ላይ የወጡት ግኝቶች የሚጠቁሙት፤ በሃገሪቱ ውስጥ ስለ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ያለው ግንዛቤ እጅግ ውሱን መሆኑን ነው። ለአብነት ያህል የሕፃናት መብትን ለማስጠበቅ በኢትዮጵያ ኃላፊነት-ለተጣለባቸው (duty-bearers) ለዘጠኝ የመንግሥት ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ የተደረገላቸው ሲሆን፤ ሁሉም ኃላፊዎች እንዳሉት ምንም እንኳ ጉዳዩ ትኩረት ማግኘት የጀመረ ቢሆንም፤ በምልአተ-ሕዝቡ፣ በፖሊሲ አውጪዎች፣ እና በግንባር ቀደም ሠራተኞች ዘንድ ስለ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ያለው ግንዛቤ እጅግ ዝቅተኛ ነው። ተመሳሳዩ አስተያየት በግንባር ቀደም የማኅበራዊ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችም ተንጸባርቆ ነበር። ሆኖም ቃለ-መጠይቅ የተደረገላቸው የመንግሥት ኃላፊዎች፤ በመንግሥትም ሆነ በሕዝቡ ዘንድ ያለውን የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ግንዛቤ ለማሻሻል ስለሚቻልባቸው መንገዶች ሐሳባቸውን አካፍለዋል። እነዚህ አስተያየቶች በሁሉም የሪፖርቱ ክፍሎች ውስጥ ተመላክተዋል።

## የሕፃናቱ የበይነ-መረብ ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ተሞክሮዎች

*በዲስረፕቲንግ ሀርም* የአባወራ/ቤተሰብ ዳሰሳ ጥናት አማካኝነት፤ በባለፈው ዓመት ውስጥ ለልዩ ልዩ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ድርጊቶች የተዳረጉበት አጋጣሚ ስለመኖሩ ለሕፃናቱ ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር።የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ማለት፤ የዲጂታል ወይም የተግባቦት ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም፤ የብዝበዛ እና የበደል ድርጊቱ እየተካሄደ በቀጠለበት የጊዜ ፍሰት ወስጥ በአንዱ ነጥብ ላይ ያለውን ሁናቴ የሚያመለክት ነው። *በዲስረፕቲንግ ሀርም* የአባወራ/ቤተሰብ ዳሰሳ ጥናት አማካኝነት የተሰበሰበው ጥሬ መረጃ እንደሚያሳየው፤ በባለፈው ዓመት ብቻ በኢትዮጵያ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ካላቸው በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት መካከል፤ 10 በመቶዎቹ በዓይነታቸው እጅግ በከፋ የበይነ-መረብ ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ድርጊቶች ተጠቅተዋል። ይህም ሕፃናት በወሲባዊ ድርጊቶች እንዲሳተፉ በመያዣ ማስገደድን (blackmailing)፣ ወሲባዊ ምስሎቻቸውን ያለይሁንታቸው ለሌሎች ማጋራትን፣ ወይም በገንዘብ እና በስጦታ በመደለል በወሲባዊ ድርጊቶች እንዲሳተፉ የማስገደድ ድርጊቶችን ያካትታል።

ከበይነ-መረብ ውጪ (offline) በሕፃናት ላይ ጥቃቱን የሚፈጽሙት ሰዎች በሕፃናቱ አስቀድሞ የሚታወቁ ሰዎች እንደሆነው ሁሉ፤ የሚበዙት የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ድርጊቶችም በተመሳሳይ አካላት የተፈጸሙ ነበሩ፡ ፡ ከባይተዋር ሰዎች የተሰነዘሩት ጥቃቶች አነስተኛ ድርሻ (ማለትም እንደ የበ/መ/ሕ/ወ/ብ/በደሉ ዓይነት ከ2 እስከ 13 በመቶ) ይዘዋል፡ ፡ የበይነ-መረብ ደኅንነት ሥራዎች፤ ሕፃኑ አስቀድሞ በምታ/ሚያውቃቸው ሰዎች ላይ ከመሆን ይልቅ በባይተዋሮች ሊሰነዘሩ በሚችሉ ጥቃቶች ላይ በማነጣጠር ላይ የተቃኙ እንደመሆኑ፤ ይህ ግኝት ለመከላከል ሥራው ጠቃሚ አንድምታ አለው።

## የበይነ-መረብ ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ድርጊቶችን ማሳወቅ እና ለመደበኛ አደረጃጀት ማመልከት

አብዛኞቹ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ክሥተቶች የሚመለከተው አካል እንዲውቃቸው ሳይረደጉ እና በይፋ ወይም ለመደበኛ አደረጃጀቶች ሪፖርት ሳይደረጉ ቀርተዋል፡ ፡ በባለፈው ዓመት ውስጥ ክሥተቱ እንዳጋጠማቸው ከገለጹ ሕፃናት ወስጥ 25 በመቶ ገደማ የሚሆኑት፤ የደረሰባቸውን ነገር ለማንም ሳያሳውቁ ቀርተዋል። ክሥተቱን ካሳወቁት ወይም አቤቱታ ካቀረቡት መካከል፤ 33 በመቶዎቹ ክሥተቱን ያመለከቱት/ያሳወቁት በኢ-መደበኛ አኳኋን ነው፤ ለምሳሌ ለጓደኞቻቸው። ሁነቱን ለፖሊስ ያመለከተ ወይም እንደ የዕርዳታ መጠየቂያ መስመሮች (helplines) የመሳሰሉ መደበኛ አሠራሮችን ወይም አደረጃጀቶችን የተጠቀመ አንድም ሰው አልነበረም ለማለት ይቻላል። በመደበኛው የፍትሕ አደረጃጀቶች የተያዙ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል-ነክ ነገረ-ጉዳዮችን (case) ለማግኘት ጥረት ቢደረግም አልተሳካም፤ ይህም ለመደበኛው አሠራር ሪፖርቶች/አቤቱታዎች እየቀረቡ አለመሆኑን፤ ኢሊያም ቢያንስ መደበኛው አደረጃጀት አቤቱታዎችን እየተቀበለ አለመሆኑን ያረጋግጣል፡ ፡ እነዚህ አገልግሎት ሰጪዎች ሕፃናቱን የሚያግዱበት አቅም ላይኖራቸው እንደሚችል፤ ወይም ሕፃናቱ እነዚህ አገልግሎቶች ስለመኖራቸው የማያውቁ መሆኑን ግኝቶቹ ያመለክታሉ። በእርግጥም፤ ሕፃናት የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ሁነቶችን እንዳያሳውቁ ያገዳቸው ዋና እክል በማለት የጠቆሙት፤ የት ማመልከት እንደሚችሉ ወይም ለማን መንገር እንዳለባቸው የማያውቁ መሆኑን ነው። በተጨማሪም፤ አንዳንድ ሕፃናት ሪፖርት ያላደረጉት የኃፍረት ወይም የመሸማቀቅ ስሜት አድሮባቸው፤ ወይም ያለፉበትን አጋጣሚ መልሶ ለማሰብ እና ለማውሳት ስሜታቸውን እጅግ የሚፈታተናቸው በመሆኑ የተነሣ ነው። የግንባር ቀደም ሠራተኞችን ያሳተፈው ዳሰሳ እንደሚያሳየው፤ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ድርጊቶች ሪፖርት የማይደረጉበት ምክንያት በአገልግሎት ሰጪ አካላቱ (ለምሳሌ በፖሊስ፣ እንዲሁም በአደጋ ማሳወቂያ (hotline) እና በዕርዳታ መጠየቂያ መስመሮች) ላይ አመኔታ ባለመኖሩ የተነሣ

መሆኑን ሁሉም ምላሽ ሰጪዎች ያለልዩነት ገልጸዋል።

> **አኃዙ ከጠቅላላው የሕዝብ ብዛት አንጻር ሲሰላ፤ በአንድ ዓመት ውስጥ ብቻ 300 ሺህ የሚገመቱ ሕፃናት ከእነዚህ ጎጂ ድርጊቶች በአንዱ መጠቃታቸውን ያመለክታል።**

## የሕግ አስከባሪ ዘርፉ ምላሽ

ምንም እንኳ ኢትዮጵያ 180 አባላትን ያቀፈ፤ ብሎም የሕፃናት የወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጉዳዮችን የሚመረምር ፖሊሳዊ የሥራ ክፍል ያላት ቢሆንም፤ እነዚሁ ድርጊቶች ስልታቸውን ቀይረው በበይነ-መረብ መልኩ ቢፈጸሙ ግን የክፍሉ አባላት ምርመራ ለማካሄድ የሚያበቃ ዓይነተኛ ክህሎቶችን የሚያጨብጣቸውን ምንም ዓይነት የተለየ ሥልጠና አላገኙም። በ*ዲስረፕቲንግ ሀርም* የዝግጅት ሂደት ላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጠው መልስ በመነሣት፤ እ.ኤ.አ. ከ2017 እስከ 2019 ድረስ ባሉት ዓመታት ውስጥ በፖሊስ የተመዘገበ አንድም የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ነገረ-ጉዳይ አለመኖሩን ገልጸዋል። በጥናቱ የተሳተፉ የሕግ አስከባሪ አካላት፤ (በአካል የተፈጸመውን ጨምሮ) በደፈናው የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን ያጣቀሰ ጥቅል መረጃን የሰጡ ሲሆን፤ የተፈጸሙት ድርጊቶች ምናልባት በዲጂታል፣ በበይነ-መረብ፣ ወይም በተግባቦት ቴክኖሎጂዎች እገዛ ታክሎባቸው የነበረ እና መረጃውም እነዚህንም ጭምር አደባልቆ የያዘ ሊሆን እንደሚችል ጠቁመዋል። ሆኖም የተመዘገበው መረጃ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን ለብቻው ነጥሎ አላስቀመጠም ወይም አልመደበም።

ከ‹ጠፉ እና ለብዝበዛ የተጋለጡ ሕፃናት ብሔራዊ ማእከል (ጠ/ብ/የ/ሕ/ብ/ማእከል› (National Center for Missing & Exploited Children (NCMEC)) የተገኘው ኢትዮጵያን የሚያጣቅሰው መረጃ፤ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ለኢትዮጵያ አስፈሪ ጉዳይ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ይሰጣል። በእርግጥም እ.ኤ.አ. በ2019 ብቻ ማእከሉ ኢትዮጵያን ያጣቀሱ ከ15 ሺህ በላይ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን የሚመለከቱ የሳይበር ጥቆማዎችን ተቀማጭነታቸው አሜሪካ ከሆኑ የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች ተቀብሏል። ሙሉ በሙሉ ለማለት በሚያስችል መጠን፤ ጥቆማዎቹ የሕፃናት ወሲባዊ በደልን የሚያንጸባርቁ ቁሳቁሶችን ከመያዝ፣ ከማዘጋጀት፣ እና ከማከፋፈል ጋር የተያያዙ ነበሩ።

## የፍትሕ ተደራሽነት

ምንም እንኳ የጥናት ቡድኑ ለአብነት እንኳ አንድ ናሙና ለማግኘት ያልተቆጠበ ጥረት ቢያደርግም፤ ከበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጋር በተያያዘ የወንጀል ጉዳይ ላይ በመደበኛው የፍትሕ ሥርዓቱ አማካኝነት ፍትሕ ያገኘን አንድም ሕፃን ለማግኘት አልቻለም። በተመሳሳይም *ዲስረፕቲንግ ሀርም* ቡድን፤ በፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል-ነክ ነገረ-ጉዳዮች ላይ በቀጥታ የሚሠሩ ወይም ተሞክሮ ያላቸውን የፍትሕ ባለሙያዎች ለማግኘት አልቻለም። የተጠቃለለው

የ*ዲስረፕቲንግ ሀርም* ምርምር ጥሬ መረጃ እንደሚያመለክተው፤ ድርጊቱ እየተከናወነ ባለበት ሁኔታ እንኳ፤ ለበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የተዳረጉ ሕፃናት እስካሁን ድረስ መደበኛ የፍትሕ ሥርዓቱን የመገልገል ወይም የመጠቀም ዕድል የላቸውም።

## ቁምነገሮች

ኢትዮጵያን የተመለከተው *የዲስረፕቲንግ ሀርም ሪፖርት* የሚደመድመው፤ አራት ቁምነገሮችን አጽንኦት ሰጥቶ በማጉላት ነው፡-

1. በባለፈው ዓመት ብቻ፤ በኢትዮጵያ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ካላቸው በይነ-መረብ ተጠቃሚዎች ውስጥ፤ 10 በመቶዎቹ ዓይነታቸው በከፋ የበይነ-መረብ ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ድርጊቶች ተጠቂ ሆነዋል። ይህም በመያዣ በማስገደድ (blackmailing) ሕፃናት በወሲባዊ ተግባራት እንዲሳተፉ ማድረግን፣ እነሱን የሚያሳዩ የግዛ ወሲባዊ ምስሎቻቸውን ያለ ይሁንታቸው ለሌሎች መጋራትን፣ በገንዘብ እና በስጦታ በመደለል በወሲባዊ ተግባራት እንዲሳተፉ ጫና ማድረግን ይጨምራል። አኃዙ ከጠቅላላው የሕዝብ ብዛት አንጻር ሲሰላ፤ በአንድ ዓመት ውስጥ ብቻ 300 ሺህ የሚገመቱ ሕፃናት ከእነዚህ ጎጂ ድርጊቶች በአንዱ መጠቃታቸውን ያመለክታል።

2. በኢትዮጵያ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ከደረሰባቸው ሕፃናት ውስጥ፤ እንደ ዕርዳታ መጠየቂያ መስመሮችን ወይም ፖሊስን የመሳሰሉ መደበኛ የአቤቱታ/ ሪፖርት ማድረጊያ አሠራሮችን የተጠቀሙት በጣም ጥቂቶቹ ብቻ ነበሩ።

3. የፍትሕ ሥርዓቱ እስካሁን ድረስ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ሊባል የሚችል አንድም የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ነገረ-ጉዳይን አላስተናገደም። የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን ለሚመለከቱ ጉዳዮች የተሻለ ምላሽ ለመስጠት እንዲቻል፤ የሕግ አስከባሪውን እና የዳኝነት ሥርዓቶችን ዕውቀት፣ አቅም፣ እና አደረጃጀት የሚያጎለብት ማርሽ ቀያሪ ኢንቨስትመንት ማድረግ ይደር የማይባል አስቸኳይ ጉዳይ ነው።

4. ሥራን ለማሣለጥ እንዲቻል ከበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጋር የተያያዙ አስፈላጊ የሆኑ የሕግ ማሻሻያዎችን ማድረግ ያሻል።

በድምሩ ሲታይ፤ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ለተጠቁ ሕፃናት ጠንካራ ተቋማዊ ድጋፍ መስጠት የሚያሻ መሆኑን፤ እንዲሁም ሕፃናት እና ቤተሰቦቻቸው ችግሩ ሲፈጠር ወዲያዉኑ ለማወቅ እንዲችሉ ስለ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል አሁን ካለው የበለጠ የግንዛቤ ደረጃ መፍጠር የሚያስፈልግ መሆኑን እነዚህ ግኝቶች ይጠቁማሉ።

የዲስረፕቲንግ ሀርም በኢትዮጵያ ሪፖርት የሚቋጨው፤ ለመንግሥት፣ ለሕግ አስከባሪው፣ ለፍትሕ፣ ለማኅበራዊ አገልግሎቶች፣ ብሎም ለተንከባካቢዎች፣ ለመምህራን፣ ለማኅበረሰቦች፣ ለዲጂታል ፕላትፎርሞች፣ እና ለበይነ-መረብ አገልግሎት ሰጪዎች በየፈርጁ የተከፋፈሉ ተከታታይነት ያላቸውን እና ዝርዝር ምክረ-ሐሳቦችን በመለገስ ነው። የሪፖርቱ ምክረ-ሐሳቦች በገጽ 69 ይገኛሉ።

# የዲስረፕቲንግ ሀርም የጥናት ዘዴ

**ሕፃናት በሚኖሩባቸው እና በሚያድጉባቸው በሌሎች የኑሮ መቼቶች (settings) ወይም ከባቢዎች ላይ እንዳለው ሁሉ፤ የበይነ-መረብ ከባቢም ሕፃናት ለወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የሚጋለጡበትን ስጋት ያዘለ ሊሆን ይችላል፡ ፡ ሆኖም፤ ያለው ማስረጃ አነስተኛ ስለሆነ፤ የደረሰውን ጉዳት ምንነት በቅጡ ለመረዳት፤ ብሎም ችግሩን የመከላከያ እና የምላሽ አሠጣጥ ፖሊሲዎችን ለማውጣት የሚያግዙ ገንቢ ምክረ-ሐሳቦችን ለመሰንዘር አስቸጋሪ አድርታል። እ.ኤ.አ. በ2018 የወጣውን በእንግሊዝኛው ‹WePROTECT Global Alliance Global Threat Assessment›[2] የተሰኘ ጥናትን መነሻ በማድረግ፤ እንዲሁም አሁን እያደረጋቸው ያሉ ጥረቶች የሚያስገኙትን ፋይዳ ይበልጥ ጥልቀት ለመስጠት በማለም፤ ግሎባል ፓርትነርሺፕ ቱ ኢንድ ሻዮለንስ አጌይነስት ቺልድረን (Global Partnership to End Violence Against Children) ‹ደኅንነቱ የተጠበቀ በይነ-መረብ› በሚሰኘው ውጥኑ አማካኝነት፤ አሁን ያለውን ውስን የማስረጃ ቋት በሚያጎለብት የምርምር ሥራ ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ወስኗል፡ ፡ ምርምሩም በ13 የምሥራቃዊ እና የደቡባዊ አፍሪካ፤ እንዲሁም የደቡብ-ምሥራቃዊ የእስያ ሃገራት ላይ ያተኮረ ነው።**

ትኩረት የተደረገባቸው የምሥራቃዊ እና የደቡባዊ አፍሪካ ሃገራት ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ሞዛምቢክ፣ ናሚቢያ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ታንዛኒያ፣ እና ዩጋንዳ ናቸው። ጥናቱ ያተኮረባቸው የደቡብ-ምሥራቃዊ የእስያ ሃገራት ደግሞ ካምቦዲያ፣ ኢንዶኔዢያ፣ ማሌዢያ፣ ፊሊፒንስ፣ ታይላንድ፣ እና ቪየትናም ናቸው።

እ.ኤ.አ. ከ2020 መጀመሪያ እስከ 2021 መጀመሪያ ባሉት ጊዜያት ውስጥ ዓይነታቸው በተለያዩ በዘጠኝ የምርምር ተግባራት/ፈርጆች ላይ ያተኮረ ሰፊ የጥሬ መረጃ ማሰባሰብ ሥራ የተከናወነ ሲሆን፤ ጥሬ መረጃው ያነጣጠረው እ.ኤ.አ. ከ2017 እስከ 2019 ድረስ ባሉት ሦስት ዓመታት ላይ ነበር። መረጃው በጥልቀት በተተነተነበት ምዕራፍ ላይ፤ ከሁሉም የምርምር ተግባራት የተሰበሰበውን ጥሬ መረጃ በሦስትዮሻዊ-ንጽጽር (triangulation) የማመሳከር ሥራ የተከናወነ ሲሆን፤ በመቀጠልም የየ13ቱ ሃገራት ሃገር-አቀፍ ሪፖርቶች በተናጠል ተዘጋጅተዋል። ኢትዮጵያን የሚመለከተው መረጃ፤ ትንተናው በሐምሌ 2013 ዓ.ም. ተጠናቋል። ለሁሉም 13 ሃገራት ተመሳሳይ ዘዴ ጥቅም ላይ መዋሉ አንዱን ሃገር ከሌላው ጋር ለማነጻጸር የሚያስችል ሲሆን፤ ይህም በተከታታይ ሕትመቶች ላይ በሚወጡት በሁለቱ ቀጣናዊ ሪፖርቶች ላይ የሚገለጽ ይሆናል።

የዚህ ሪፖርት ዓላማ፤ የኢትዮጵያ ፖሊሲ አውጪዎች የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን ለመቅረፍ እና ለተጎጂዎች የሚሰጠውን ድጋፍ ለማጠናከር የሚያስችላቸውን መንደርደሪያ እና የማስረጃ ድጋፍ ለመስጠት ነው። አልፎ ተርፎም፤ ግኝቶቹ እና የቀረቡት ምክረ-ሐሳቦች ለሰፊው የዓለም ማኅበረሰብ ጭምር ፋይዳ ያዘሉ ናቸው። በሪፖርቱ የተሰነዘሩት ምክረ-ሐሳቦች በእንግሊዝኛው ‹WeProtect Model National Response›[3] በሚል ከወጣው ሰነድ ጋር የሚሰናኙ/አብሮ የሚሄዱ፤ እንዲሁም ለ‹ዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030›[4] አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ናቸው።

## ኢ/ሲ/ፒ/ኤ/ቲ ኢትዮጵያ የተጠቀማቸው ዘዴዎች በአጭሩ

### ኃላፊነት-ከተጣለባቸው የመንግሥት አካላት ጋር የተደረጉ ቃለ-መጠይቆች

የሥራ ድርሻቸው በብሔራዊ ደረጃ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን የሚመለከት በሃገር-አቀፍ ደረጃ በከፍተኛ እርከን ላይ ከሚገኙ ኃላፊነት-ከተጣለባቸው[5] አካላት ጋር ዘጠኝ ቃለመጠይቆች ከሐምሌ 2012 እስከ መስከረም 2013 ድረስ ባሉት ጊዜያት ተካሂዷል። በኮቪድ-19 ወረርሽኝ የተነሣ ቃለ-መጠይቆቹ የተካሄዱት በሩቅ-ለሩቅ ወይም በቨርቹዋል መገናኛ ዘዴዎች አማካኝነት ነው። በቅድሚያ ታቅዶ እንደነበረው ከ10 እስከ 12 ተሳታፊዎችን ማግኘት እጅግ አዳጋች የነበረ ሲሆን፤ አንዳንዶቹ የሥራ ክፍሎች ተደጋጋሚ ሙከራ ቢደረግላቸውም ምላሽ አልሰጡም። ይህን ተግባር ስለተከናወነበት ስልት ይህንን ማስፈንጠሪያ በመጫን የበለጠ መረጃ ማግኘት የሚቻል ሲሆን፤ የጥሬ መረጃው ቀዳሚ ሪፖርት ደግሞ በዚህኛው ማስፈንጠሪያ ይገኛል። ከእነዚህ ምላሽ ሰጪዎች የቀረቡ ጥሬ መረጃዎችን ለይተው የሚጠቅሱ ዋቢዎች በመላው ሪፖርት ውስጥ የተዘረዘሩ ሲሆን፤ እነዚህም የተራ ቁጥሩ መነሻ RA1 ከሚለው ጀምሮ ለእያንዳንዳቸው የተለየ መለያ አኃዝ ተሰጥቷቸዋል[6]።

### ሕግ አስከባሪ ካልሆኑ አካላት የተሰባሰበው ጥሬ መረጃ

ሕግ አስከባሪ ያልሆኑ የተለያዩ ባለድርሻዎች፤ ስለ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ምንነት እና ስለ ችግሩ አድማስ ጥሬ መረጃዎችን እና ሐሳባቸውን አካፍለዋል። በእንግሊዝኛው ‹ኢንተርናሽናል አሶሴሽን ኦፍ ኢንተርኔት ሆትላይንስ› (International Association of Internet Hotlines (INHOPE))፣ ‹ኢንተርኔት ዋች ፋውንዴሽን› (Internet Watch Foundation (IWF))፣ እና ‹ቻይልድ ሄልፕላይን ኢንተርናሽናል› (Child Helpline International (CHI)) ከሚባሉት ድርጅቶች ጥሬ መረጃ ተገኝቷል። የተጠቀሱት ጥሬ መረጃዎች ስለያዙት ገላጭ/ገለጻዊ (qualitative) ፍሬነገሮች ላይ በርካታ ዓለም-አቀፍ የቴክኖሎጂ ፕላትፎርሞች ማብራሪያዎችን ለግሰዋል፡ ፡ እንደ ጉዳዩ

2. WeProtect Global Alliance. (2018). Global Threat Assessment 2018: Working together to end the sexual exploitation of children online. London: WeProtect Global Alliance.
3. WeProtect Global Alliance. (2016). Preventing and Tackling Child Sexual Exploitation and Abuse: A model national response. London: WeProtect Global Alliance.
4. የተባበሩት መንግሥታት (ቀን አልተጠቀሰም)፤ የዘላቂ ልማት ግቦች፤ ግብ ተራ ቁጥር 5.2ን፣ 8.7ን፣ እና 16.2ን ይመለከቷል
5. በዚህ አገላለጽ ‹ኃላፊነት-የተጣለባቸው› ማለት፤ በሃገር-አቀፍ ደረጃ ለበ/መ/ሕ/ወ/ብ/በደል ስጋቶች ምላሽ የመስጠት ዓይነተኛ ኃላፊነት የተሸከሙትን ያመለክታል። የጥናቱ ተሳታፊዎች፤ የሴቶች፣ ሕፃናት፣ እና ወጣቶች ሚኒስቴር፤ የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ የትምህርት ሚኒስቴር፣ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ-ሕግ ጽሕፈት ቤት፣ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሕፃናት ፍትሕ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት፣ የባህል እና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ የሳይበር ወንጀል የሥራ ክፍል፣ እንዲሁም የተባበሩት መንግሥታት የአደንዛዥ ዕፆች እና ወንጀሎች ጽሕፈት ቤት (UNODC) ናቸው።
6. RA1-ET-01-A የሚለው ኮድ እንደ መታወቂያ ካርድ በተናጠል ለመለየት የሚያገለግል ነው። ‘RA1’ የጥናት ተግባሩን፤ ‘ET’ ኢትዮጵያን፤ ‘01’ የተሳታፊውን/የአስረጂውን ተራ ቁጥር ፤ እንዲሁም ‘A’ የሚለው በቃለ-መጠይቆቹ ከአንድ ሰው በላይ ተሳትፎባቸው ከነበረ የተሳተፈውን ተጨማሪውን ግለሰብ የሚያመለክቱ ኮዶች ናቸው።

# የዲስረፕቲንግ ሀርም የጥናት ዘዴ

አግባብነት፤ ይሄ መረጃ በኢንተርፖል የቀረበውን ትንታኔ ይበልጥ ለማዳበር ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

## የግንባር ቀደም ማኅበራዊ ሠራተኞች ዳሰሳ

በየምድቡ ያሉ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (መ/ያ/ድ/)ን በመጠየቅ በተገኘው የስም ዝርዝር መነሻነት፤ በ‹ግምት-አልቦ የምቾት ናሙና› የአመራረጥ (non-probability convenience sample) ዘዴ፤ 50 ናሙናዎች የተመረጡ ሲሆን፤ እነዚህም በኢትዮጵያ ውስጥ ከደንበኞቻቸው ጋር የገጽ-ለገጽ የሥራ ግንኙነት ያላቸው ግንባር ቀደም ሠራተኞች (ለምሳሌ ተጠቃሚ-ተኮር/አውትሪች ሠራተኞች፣ ማኅበራዊ ሠራተኞች፣ ኬዝ ማኔጀሮች፣ የሥነ-ልቦና ባለሙያዎች፣እንዲሁም ከሕፃናት ጉዳይ[7] ጋር የተያያዘ ቀጥተኛ ኃላፊነት ያለባቸው አንዳንድ የጤና እና የሕግ ባለሙያዎች) ከሐምሌ 2012 እስከ ጥቅምት 2013 ዓ.ም. ድረስ በበይነ-መረብ በተካሄደ ዳሰሳ ተሳታፊ ነበሩ፡፡ ይህ የጥናት አካሄድ፤ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት በማኅበራዊ ድጋፍ ላይ በግንባር ቀደምነት ተሰልፈው እየሠሩ ባሉት ዘንድ ያለውን ምልከታ ለማወቅ፤ ከዚህ አኳያም የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን አድማስ እና ማእቀፍ ለመረዳት ያለመ ነበር፡፡ ምንም እንኳ 50 ተሳታፊዎች በዳሰሳ ጥናቱ ውስጥ ተሳትፈው የነበረ ቢሆንም፤ ጥሬ መረጃው በሚጣራበት ወቅት ጥቅሉ ጥሬ መረጃ (dataset) አንዳንድ መጣረሶች እንዳሉበት ስለታወቀ፤ የ17ቱ ዳሰሳ ከትንታኔው ውስጥ ጨርሶ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡ በድምሩ 33 ዳሰሳዎች ተተንትነዋል፡፡ የተጠቀሱት መጣረሶች ምናልባት ከበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ግንዛቤ እጦት እና የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ተጎጂዎችን የመደገፍ የሥራ ልምድ እንዳላቸው የገለጹት በቁጥር በጣም አነስተኛ ስለሆኑ ይሆናል፡፡ በተጨማሪ፤ ተሳታፊዎቹ ዝርዝር ምላሾችን ያልሰጡ ሲሆን፤ ለዚህም ምናልባት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል በዳሰሳ ጥናቱ አካሂያጆች የተሰጠው ግምት፤ ምንም እንኳ ተሳታፊዎቹ የሚሰጡት ምላሽ ሚሥጥራዊነቱ እንደሚጠበቅ በአጽንኦት የተነገራቸው ሆኖ ሳለ፤ ተሳታፊዎቹ ግን ምናልባት ክትትል ሊደረግብኝ እና ማን ምን ምላሽ እንደሰጠ ሊታወቅ ይችላል የሚል ስጋት ስለነበራቸው ነው[8] ፡፡ ይህ ተግባር ስለተካሄደበት ስልት ይህንን ማስፈንጠሪያ በመጫን የበለጠ መረጃ የሚገኝ ሲሆን፤ የጥሬ መረጃው ቀዳሚ ሪፖርት ደግሞ በዚህኛው ማስፈንጠሪያ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ምላሽ ሰጪዎች የተሰጡ ጥሬ መረጃዎችን ለይተው የሚጠቅሱ ዋቢዎች በመላው ሪፖርት ውስጥ የተዘረዘሩ ሲሆን፤ እነዚህም የተራ ቁጥሩ መነሻ RA3 ከሚለው ጀምሮ ለእያንዳንዳቸው የተለየ መለያ አኃዝ  ተሰጥቷቸዋል፡፡

## የፍትሕ ተደራሽነት እና ሕጋዊ ማካካሻዎች - ከበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ተጎጂዎች እና ከተንከባካቢዎቻቸው ጋር የተደረጉ ቃለ-መጠይቆች

ይህኛው የምርምር ሥራ፤ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የተጠቁ ሕፃናት በኢትዮጵያ ፍትሕን እና ማካሻዎችን እንዴት እና እስከምን ድረስ ያገኛሉ በሚለው ርእስ ላይ የተሻለ ግንዛቤን ለማስጨበጥ ያለመ ነው፡፡ ዕድሜያቸው ከ15 እስከ 18 ላሉ ልጆች እና ለተንከባካቢዎቻቸው 10 ቃለ-መጠይቆችን ለማድረግ ታቅዶ ነበር፡፡ ይሁንና፤ ያልተቆጠበ ጥረት ቢደረግም፤ የዲስረፕቲንግ ሀርም በኢትዮጵያ ጥናት በሕግ ሥርዓቱ ያለፈ/ች አንድም የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ተጎጂን ማግኘት አልቻለም፡፡ ተጎጂዎችን ወይም አብነቶችን ለማግኘት የተለያየ ጥረት የተደረገ ሲሆን፤ ይህም በቁጥር ከ20 ከሚልቁ ሃገር-አቀፍ እና ዓለም-አቀፍ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ጋር የተደረጉ ውይይቶችን፣ እንዲሁም ሕፃናት ተጠቂ በሆኑበት በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ብሎም በወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ላይ ሰሠሩ ከነበሩ የፍትሕ ባለሙያዎች እና የሕግ አስከባሪ መኮንኖች ጋር የተደረጉ ግንኙነቶችን ይጨምራል፡፡ ለዚህም ከሚገመቱት መንሥኤዎች ውስጥ ለእውነትነት ይበልጥ የሚቀርበው ምክንያት፤ አንድም የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ተጎጂ የደረሰበ/ባትን ሪፖርት ለማድረግ የሚ/ምትችልበት ሁኔታ አለመኖሩ ነው፡፡ በመሆኑም፤ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ተጎጂዎች ስላገኙት ፍትሕ የሚመለከት ጥሬ መረጃ በዚህ ሪፖርት አልቀረበም፡፡ ይህንን ርእሰ-ጉዳይ የሚመለከተው መረጃ የተጓደለ መሆኑ፤ ከሌሎች   የመረጃ ሰጪ አካላት ከተገኙ የጥሬ መረጃ  ነጥቦች ጋር በሦስትዮሻዊ-ንጻጽር ለማመሳከር እንዳይቻል አድርጎታል፡፡ ይህም ቢሆን፤ ፍትሕ ያገኙ ሕፃናትን ማግኘት አለመቻሉ በራሱ እንደ አንድ ግኝት የሚታይ ነው፤ ምክንያቱም ተጎጂዎች የደረሰባቸውን ሪፖርት የማያደርጉ፤ እንዲሁም እነዚህ ነገረ-ጉዳዮች በመደበኛው የፍትሕ ሥርዓት የረባ ዕውቅና ያልተሰጣቸው መሆኑን ስለሚያመለክት ነው፡፡

## የፍትሕ ተደራሽነት እና ሕጋዊ ማካካሻዎች - ከፍትሕ ባለሙያዎች ጋር የተደረጉ ቃለ-መጠይቆች

ከ10 የወንጀል ሕግ ባለሙያዎች ጋር 11 በከፊል-የተዋቀሩ (semi-structured) ቃለ-መጠይቆችን በኢትዮጵያ ውስጥ ለማካሄድ ታስቦ ነበር፡፡ ናሙናው በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የወንጀል ጉዳዮች ላይ የሥራ ልምድ ያላቸውን የመንግሥት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ምላሽ ሰጪዎችን እንዲያካትት ዕቅድ ነበር፡፡ ሆኖም ልክ ከላይ እንደተጠቀሰው ሁናቴ፤ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ነገረ-ጉዳዮች ላይ የሥራ ልምድ ያላቸውን የወንጀል ሕግ ባለሙያዎችን ለማግኘት ያልተቆጠበ ጥረት ቢደረግም፤ የ*ዲስረፕቲንግ ሀርም* ቡድን መስፈርቱን የሚያሟላ አንድም ግለሰብ ማግኘት አልቻለም፡፡ ቡድኑ ያገኛቸው 20 የፍትሕ ባለሙያዎች በሙሉ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን የሚመለከቱ ጉዳዮችን በማስተናገድ ረገድ ምንም ልምድ እንደሌላቸው ገልጸዋል፡፡ በድጋሚ፤ ለችግሩ በመንሥኤነት ከሚገመቱት ውስጥ ለእውነትነት ይበልጥ የሚቀርበው ምክንያት፤ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጉዳዮች እስካሁን ድረስ በኢትዮጵያ የፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ተስተናግዶ አለማወቁ ነው፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው፤ በዳሰሳ ጥናቱ ሊሳተፉ የሚችሉ  ሰዎችን ማግኘት አለመቻሉ በራሱ አንድ ግኝት ነው፡፡

## የሕትመቶች ዳሰሳ እና የሕግ ትንታኔ

ርቱዕ ጥሬ መረጃ (primary data) ከመሰብሰቡ አስቀድሞ፤ የምርምር ቡድኖቹ መረጃን ያማከለ ዕውቀት እንዲኖራቸው ለማስቻል፤ የተዛማጅ ድርሳን ዳሰሳ (literature review) ተካሂዷል፡፡ በዚህ እንቅስቃሴ ላይ ለማወቅ የተቻለው፤ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ላይ ያተኮሩ ቀርቶ ርእሱን እንኳ የሚነካኩ የታተሙ ድርሳናት በጣም ጥቂት መሆናቸውን ነው፡፡ የመነመኑ ቢሆንም አግባብነት ያላቸው ሰነዶች ሲገኙ በሪፖርቱ ውስጥ ተጠቅሰዋል፤ ይህም የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል እስካሁን የሃገሪቱ አጀንዳ እንዳልሆነ ተጨማሪ ማረጋገጫ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን በሚመለከቱ ሕጎች፣ ፖሊሲዎች፣ እና የአሠራር ሥርዓቶች ላይ ሁሉን-አቀፍ ትንታኔ የተደረገ ሲሆን፤ ሥራው በሰኔ 2012 ዓ.ም. ተጠናቋል፡፡ ይህንን ተግባር

ስለሚመለከተው የጥናት ዘዴ የበለጠ መረጃ ይህንን ማስፈንጠሪያ

7. ለምሳሌ ወጣት-ተኮር የቅስቀሳ/አውትሪች ሠራተኞች፣ ማኅበራዊ ሠራተኞች፣ ኬዝ ማኔጀሮች፣ የሥነ-ልቦና ባለሙያዎች፣እንዲሁም ከሕፃናት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ በቀጥታ የሚሳተፉ አንዳንድ የጤና እና የሕግ ባለሙያዎች
8. በኢትዮጵያ ውስጥ ካለው የመስክ ቡድን ጋር የተደረገ የግል ግንኙነት

# የዲስረፕቲንግ ሀርም የጥናት ዘዴ

በመጨረሻ የሚገኝ ሲሆን፤ ሙሉው የሕግ ትንታኔ ደግሞ በዚህኛው ማስፈንጠሪያ ይገኛል።

### ከበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ተጎጂዎች ጋር የተደረጉ ውይይቶች

*ዲስረፕቲንግ ሀርም* ከሸፈናቸው ሃገራት ውስጥ በአምስቱ ሃገራት ካሉ 33 የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ተጎጂ ከሆኑ ታዳጊዎች (ማለትም ከኬንያ ዘጠኝ ልጃገረዶች፤ ከካምቦዲያ አምስት ወንድ ልጆች እና ሰባት ልጃገረዶች፣ ከናሚቢያ ሰባት ልጃገረዶች፤ ከማሌዢያ አራት ልጃገረዶች፣ እንዲሁም ከደቡብ አፍሪካ አንድ ወንድ ልጅ) ጋር

ያልተዋቀረ (unstructured) እና የአንድ-ለአንድ ውይይት የተካሄደ ሲሆን፤ ውይይቱም ሰቆቃን በማከም በተካኑ ባለሙያዎች (trauma-informed expert practitioners) የሚመራ ነበር። የተሳታፊዎቹ ዕድሜ ከ16 እስከ 24 ሲሆን፤ ሁሉም በሕፃንነታቸው ወቅት የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ተጎጂ የነበሩ ናቸው። ምንም እንኳ በሁሉም ሃገራት ባይካሄድም፤ የእነዚህ ውይይቶች ዓላማ በመላው የ13ቱ የ*ዲስረፕቲንግ ሀርም* ሃገራት ውስጥ ያሉትን ተመሳሳይ ጭብጦችን እና ጉዳዮችን አጉልቶ ለማሳየት ነው። ይህንን ተግባር ስለሚመለከተው የጥናት ዘዴ የበለጠ መረጃ ይህንን ማስፈንጠሪያ በመጫን ማግኘት ይቻላል። ከ33ቱ ተጠቂዎች ጋር የነበረውን ውይይት ተንተርሶ የተካሄደውን ትንታኔ የያዘ ሪፖርት በተናጠል ወደፊት ይወጣል። ከእነዚህ ምላሽ ሰጪዎች የተሰጡ ጥሬ መረጃዎችን ለይተው የሚጠቅሱ ዋቢዎች በመላው ሪፖርት ውስጥ የተዘረዘሩ ሲሆን፤ እነዚህም የተራ ቁጥሩ መነሻቸው RA5 ሲሆን፤ ለየብቻ ባሉ ሳጥኖች ውስጥ እንዲቀመጡ ተደርጓል።

## ኢንተርፖል በኢትዮጵያ ውስጥ ስለተጠቀማቸው ዘዴዎች በአጭሩ

### የአኃዛዊ (quantitative) ጥሬ መረጃ ትንታኔ

ኢንተርፖል አዲስ አበባ ውስጥ በከፈተው የሃገር-አቀፍ ማእከላዊ ቢሮው (National Central Bureau) አማካኝነት በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል-ነክ ነገረ-ጉዳዮችን የሚመለከት ጥሬ መረጃን ከሕግ አስከባሪ ሹማምንት መረጃ ተጠይቋል። ተቀማጭነታቸው አሜሪካ የሆኑ የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች ለጠ/ብ/የ/ሕ/ብ/ማእከል ከላኳቸው ሕጋዊ ሪፖርቶች፤ እንዲሁም ከሌሎች በርካታ የውጭ ሃገራት ሕግ አስከባሪ መሥሪያ ቤቶችም ጥሬ መረጃዎች የተገኙ ሲሆን፤ ይህም በኢትዮጵያ የተፈጸሙ ተዛማጅነት ስላላቸው ድርጊቶች፣ ስለ በዳዮቹ እና ተጎጂዎቹ ጠባይ፣ እንዲሁም ስለ ወንጀሉ አስቻይ እና አጋላጭ ጎኖች በተመለከተ የጠለቀ ግንዛቤ ለመፍጠር ነው። የወንጀል ድርጊቶችን የተመለከተው ጥሬ መረጃ ላይ ትንታኔ የተደረገው እ.ኤ.አ. ከ2017 እስከ 2019 ድረስ ለሦስት ዓመታት በነበሩት መረጃዎች ላይ ነው። ይህንን ተግባር ስለሚመለከተው የጥናት ዘዴ የበለጠ መረጃ ይህንን ማስፈንጠሪያ በመጫን ማግኘት ይቻላል።

### አቅምን የተመለከቱ ገለጻዊ (qualitative) ግምገማዎች

ከበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የተያያዙ ጥሬ መረጃዎችን ከመጠየቅ ባሻገር፤ ኢንተርፖል ሃገር-አቀፍ የሕግ ማስከበር ዘርፍ ኃላፊዎች ለዚህ መሰል የወንጀል ነገረ-ጉዳዮች ምላሽ የመስጠት አቅማቸውን የተመለከተ ጥሬ መረጃን ለማግኘት ጥያቄ ያቀረበ ሲሆን፤ ሥራ ላይ ላሉ መኮንኖችንም ቃለ-መጠይቅ አድርጓል። ስለ ሰው ኃይል፣ለሥራው በተለይ የሚያስፈልጉ ዓይነተኛ መሣሪያዎች እና ሥልጠና ስለመኖሩ፣ በምርመራ አሠራሮች፣ ዓለም-አቀፍ ትብብርን ለማግኘት ጥቅም ላይ ስለዋሉት ስልቶች፣ እንዲሁም በስኬቶች እና በተግዳሮቶች ላይ የተለየ ትኩረት ተደርጓል። ከእነዚህ ምላሽ ሰጪዎች የተሰጡ ጥሬ መረጃዎችን ለይተው የሚጠቅሱ ዋቢዎች በመላው ሪፖርት ውስጥ የተዘረዘሩ ሲሆን፤ እነዚህም የተራ ቁጥሩ መነሻ RA8 ከሚለው ጀምሮ ለእያንዳንዳቸው የተለየ መለያ አኃዝ ተሰጥቷቸዋል።ይህንን ተግባር ስለሚመለከተው የጥናት ዘዴ የበለጠ መረጃ ይህንን ማስፈንጠሪያ በመጫን ማግኘት ይቻላል።

## በኢትዮጵያ የዩኒሴፍ የምርምር ጽሕፈት ቤት-ኢኖሰንቲ ስለተጠቀማቸው ዘዴዎች በአጭሩ

የሕፃናትን የበይነ-መረብ አጠቃቀም፣ በበይነ-መረብ ስለሚያጋጥሟቸው ስጋቶች እና መልካም አጋጣሚዎች፣ እንዲሁም የተለዩ/ዓይነተኛ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ተሞክሯቸውን ለመረዳት እንዲቻል፤ ናሙና አወሳሰዱ ሃገር-አቀፍ ስብጥርን ያንጸባረቀ የአባወራ/የቤተሰብ የዳሰሳ ጥናት ተካሂዷል። የዳሰሳው የተጠኚዎች ምልአተ-ስብስብ (target population)፤ ባለፉት ሦስት ወራት ውስጥ በይነ-መረብን የተጠቀሙ ዕድሜያቸው ከ12 እስከ 17  ድረስ ያሉ ሕፃናት ነበሩ፡ ፡ በተጨማሪ፤ ለእያንዳንዱ ሕፃን አንድ ተንከባካቢ ቃለ-መጠይቅ ተደርጓል። በሪፖርቱ ውስጥ ሁሉ ‹የአባወራ/የቤተሰብ የዳሰሳ ጥናት› (በእንግሊዝኛው household survey) በሚል የተጠቀሰው ሐረግ፤ በተለይ ከዚህ ዓይነቱ የምርምር ሥራ የወጡ ግኝቶችን የሚያመለክት ቃል ነው። የዳሰሳ ጥናቱ ናሙና 361 ልጃገረዶችን (36 በመቶ) እና 638 ወንድ ልጆችን (64 በመቶ) ያካተተ ነው። በየዕድሜ አርከናቸው ያላቸው ድርሻ እንደሚከተለው ነው፦ 124 (12 በመቶ) የሚሆኑት የ12–13 ዓመት ዕድሜ፣ 267 (27 በመቶ) የሚሆኑት የ14–15 ዓመት ዕድሜ፣ እና 610 (61%) የ16–17 ዓመት ዕድሜ  ያላቸው በዳሰሰው ተጠቃለዋል።.

ናሙናው ሃገር-አቀፍ ስብጥርን ወይም ውክልናን እንዲያረጋግጥ፤ የአባወራ/የቤተሰብ የዳሰሳ ጥናቱ ሃገር-አቀፍ ሽፋን በጠበቀ መልኩ ‹ግምት-ሰጥ የነሲብ ናሙና አመራረጥ› (random probability sampling) ዘዴን ተጠቅሟል። በኢትዮጵያ፤ የመስክ ሥራው አፈጻጸም 82 በመቶ ሲሆን፤ ይህም አንዳንድ አካባቢዎች ለመረጃ ሰብሳቢዎቹ ተደራሽ ባለመሆናቸው ነው። የ‹ሽፋን› ትርጓሜ፤ ከጠቅላላው የሕዝብ ቁጥር ውስጥ በዳሰሳ ጥናቱ የናሙና ምልአተ-ስብስብ (survey sample) ውስጥ የመካተት ዕድል የገጠማቸው ሰዎች ድርሻ በመቶኛ ሲሰላ ሲሆን፤ ይህም በናሙናነት የሚመረጡት ሰዎች የሚኖሩባቸውን እና የመስክ ሥራው የሚያካልላቸውን አካባቢዎችን የሚያጣቅስ ነው።  ለአጥኚ ቡድኑ ተደራሽ ባለመሆናቸው የትግራይ ክልል ሙሉ በሙሉ እንዲሁም የተመረጡ ዞኖች ማለትም በአፋር፣ አማራ፣ ድሬዳዋ፣ ኦሮሚያ እና ሶማሌ ክልል ውስጥ ከተካተቱት የመጀመሪያ ደረጃ ናሙናዎች ዝርዝር ውስጥ እንዲሰረዝ ተደርጓል።

የናሙና አወሳሰዱ በሦስት እርከኖች የተከፈለ፤ እና የነሲባዊ ግምት-ሰጥ ጥምር የናሙና አመራረጥ (random probability clustered sample) ዘዴን ያማከለ ነበር። በአንደኛው እርከን፤ ከኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አጀንሲ ከተሰጠው ዝርዝር ውስጥ፤ 100 የመጀመሪያ ዙር የናሙና አሃዶች (primary sampling units) ተመርጠዋል። በሁለተኛው እርከን፤ ቃለ-ጠያቂዎቹ ከዝርዝሩ ውስጥ ካሉት አድራሻዎች ውስጥ በነሲብ እግራቸው እንደመራቸው (random walk procedures) አድራሻዎችን ከመረጡ በኋላ፤ ከተመረጡት አድራሻዎች ጋር ግንኙነት ለመመሥረት እና አስቀድሞ ባዘጋጁት የመመርጫ ጥያቄ መሠረት ለመመልመል ጥረት አድርገዋል። በሦስተኛው እርከን ላይ ደግሞ የነሲብ (random) ዘዴን በመጠቀም መስፈርቱን የሚያሟሉ አባወራዎች/ቤተሰቦች የተመረጡ ሲሆን፤ በመቀጠልም በእያንዳንዱ አባወራ/ቤሰተብ ውስጥ ያሉ ግለሰቦች (ሕፃናት እና ተንከባካቢዎች) እንዲመረጡ ተደርጓል።

# የዲስረፕቲንግ ሀርም የጥናት ዘዴ

በተሳካ ሁኔታ 10 አባወራዎችን/ቤተሰቦችን ቃለ-መጠይቅ ለማድረግ እንዲቻል፤ ቃለ-ጠያቂዎቹ በእያንዳንዱ የመጀመሪያ-ዙር የናሙና አሃዶች ውስጥ ካሉት አድራሻዎች (ብዛታቸው በሚፈለገው መጠን) ጋር ግንኙነት መሥርተዋል። በእያንዳንዱ የቃለ-ተጠያቂ አባወራ/ቤተሰብ፤ በነሲብ (randomly) ከሚመረጥ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ካለው በይነ-መረብ ተጠቃሚ ጋር አንድ ቃለ-መጠይቅን፤ እንዲሁም ከታዳጊው/ዋ ተንከባካቢ ጋር ሁለተኛ ቃለ-መጠይቅ የማድረግ ሥራ የተካተተ ሲሆን፤ የናሙናዎቹ ጠቅላላ ድምር 1 ሺህ ሕፃናት እና 1 ሺህ ተንከባካቢዎች ነው። ጉብኝት በተካሄደባቸው (ብዛት = 5 ሺህ 928) በእያንዳንዱ አባወራ/ቤተሰብ ላይ፤ በቤተሰቡ ውስጥ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ልጆች ብዛትን፣ ጾታቸውን፣ እንዲሁም ባለፉት ሦስት ወራት በይነ-መረብን ተጠቅመው እንደሆነ ጥሬ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ጥረት የተደረገ ሲሆን፤ ይህም በመላው ኢትዮጵያ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ካላቸው ሕፃናት ውስጥ ምን ያህሉ የበይነ-መረብ ተደራሽ እንደሆኑ ግምት ለማውጣት አስችሏል።

የመስክ ሥራው ከታኅሣሥ 12 ቀን 2013 እስከ ጥር 11 ቀን 2014 ዓ.ም. ድረስ ተካሂዷል። ጥሬ መረጃን የመሰብሰብ ሥራው በ‹ትሪቦንድ ሪሰርች ኤንድ ኮንሰልቲንግ ፒ/ኤል/ሲ› የተከናወነ ሲሆን፤ ማስተባበሩ ደግሞ የዩኒሴፍ የምርምር ጽሕፈት ቤት-ኢኖሰንቲን በወከለው ኢፕሶስ ሞሪ ተካሂዷል። በአባወራ/የቤተሰብ የዳሰሳ ጥናቱ የተገኙትን ጥሬ መረጃዎች ለመተንተን ጥቅም ላይ ስለዋለው ሥነ-ዘዴያዊ አሠራር እና በተለይ ስለ አንዳንዱ ስልቶች ይህንን ማስፈንጠሪያ በመጫን የበለጠ ዝርዝር ማብራሪያ ማግኘት ይቻላል።


### ለሥነ-ምግባር ብቁነት የተሰጠ ይሁንታ

የዩኒሴፍ የምርምር ፕሮቶኮል፤ በኢትዮጵያ የሶሾሎጂስቶች፣ የማኅበራዊ ሠራተኞች፣ እና አንትሮፖሎጂስቶች ማኅበር ተገምግሞ ጸድቋል። የኢ/ሲ/ፒ/ኤ/ቲ/ የምርምር ፕሮቶኮል ደግሞ፤ በሳይንስ እና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ውስጥ ባለው ‹ብሔራዊ የምርምር ሥነ-ምግባር ገምጋሚ ኮሚቴ› አማካኝነት ተገምግሞ ጸድቋል። በተጨማሪም፤ ሁለቱም ፕሮቶኮሎች በ‹ኤች/ኤም/ኤል/ ተቋማዊ የግምገማ ቦርድ›/ አማካኝነት ተገምግመው ጸድቀዋል። የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል አስጊነትን፤ እንዲሁም የሕግ አስከባሪ ባለሥልጣኖች ለስጋቱ ምላሽ የመስጠት አቅማቸውን ኢንተርፖል ገምግሟል። ሁለቱም ግምገማዎች፤ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን የማስተናገድ ኃላፊነት ካለባቸው ከሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ውስጥ ካሉ ሕግ አስከባሪ መኮንኖች ጋር የተደረጉ ቃለ-መጠይቆችን ያጠቃልላሉ። የቃለ-ጠያቂዎቹ ቡድን በበይነ-መረብ የተሰጠውን (በእንግሊዝኛው Responsible Conduct of Research from the Collaborative Institutional training Initiative) ኮርስ፤ እንዲሁም ‹የኢንተርፖል የሥነ-ምግባር ደንብ›ን ተከታትለዋል።

### ሃገር-አቀፍ ምክክር

መስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም. ላይ ሃገር-አቀፍ የምክክር ስብሰባ ተካሂዶ ነበር። የዚህ ሪፖርት ዋና ዋና ግኝቶችን አስመልክቶ፤ ለመንግሥት፣ ለሕግ አስከባሪዎች፣ እና መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ገለጻ የተደረገ ሲሆን፤ *ዲስረፕቲንግ ሀርም* በለገሳቸው ምክረ-ሐሳቦች ላይ ያላቸውን አስተያየት እንዲሰነዝሩ ተጋብዘው ነበር። ዓላማውም ምክረ-ሐሳቦቹ ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተዛማጅ እና አዋጭ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ነበር።

**ምስል 1፡ የዲስረፕቲንግ ሀርም ስልቶች በኢትዮጵያ**



# ስለ የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል

**‹በሕፃናት ላይ የሚፈጸም ወሲባዊ በደል › የሚለው ሐረግ፤ ሕፃናት (ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ሰዎች) የሚፈጸምባቸው ነገር የተለመደ ወይም ቅቡል ጉዳይ አለመሆኑን ተገንዝበውም ሆነ ሳያውቁት በሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ልዩ ልዩ የወሲብ ድርጊቶችን የሚገለጽ አጠራር ነው፡፡ ድርጊቱ በአዋቂዎች ወይም በአቻዎቻቸው (peers) አማካኝነት ሊፈጸም የሚችል ሲሆን፤ ይህም አዘውትሮ እንደሚስተዋለው የአቅም ሚዛን መበላለጥን ያላግባብ በሚጠቀም ግለሰብ ወይም ቡድን አማካኝነት የሚፈጸም ነው፡፡ ጉልበትን መጠቀም ሳያስፈልግ ሊፈጸም የሚችልና፤ አጥፊዎች ባብዛኛው ሥልጣናቸውን፣ ተደማጭነታቸውን፣ ስልታዊ ጥመዘዛን፣ ወይም ማታለልን ተጠቅመው የሚፈጽሙት ነው[9]፡፡**

‹*በሕፃናት ላይ የሚፈጸም ወሲባዊ ብዝበዛ*› ተመሳሳይ ጉዳት አዘል ድርጊቶችን ያካተተ ነው፡፡ ሆኖም፤ እንደ ማስፈራሪያ ወይም እንደ እንካ-በእንካ ያለ ልውጫ (ለምሳሌ ገንዘብ፣ መጠለያ፣ ቁሳቁስ፣ ወይም ጥበቃ እና ወዳጅነትን የመሳሰሉ ኢ-ቁሳዊ ነገሮች) የታከለበት ነገርን፤ አሊያም የተጠቀሱትን ለመስጠት እንዲሁ ቃል መግባትን የመሳሰለ ተጨማሪ ተግባርን ሊያካትት ይገባል[10]፡፡

**የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል** ማለት፤ የዲጂታል፣ የበይነ-መረብ፣ እና የተግባቦት ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም፤ የብዝበዛ ወይም የበደል ድርጊቱ እየተካሄደ በቀጠለበት የጊዜ ፍሰት ወስጥ በአንዱ ነጥብ ላይ ያለውን ሁናቴ የሚያመለክት ነው፡፡ በአጥፊዎቹ እና በሕፃናቱ መካከል የሚደረገው ግንኙነት፤ ሙሉ በሙሉ በበይነ-መረብ ብቻ፤ አሊያም ሁለቱንም ማለትም በይነ-መረብን እና የአካል/የፊትለፊት ግንኙነትን ባጣመረ መልኩ ሊሆን ይችላል፡፡


*የዲስረፕቲንግ ሀርም* ትኩረት፤ ቴክኖሎጂ እንዴት የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን ለማሳለጥ ያላግባብ ጥቅም ላይ እየዋለ ስላለበት ሁኔታ ነው፡፡ ጥናቱ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የሚለውን ቃል ሲጠቀም፤ ሙሉ በሙሉ ከበይነ-መረብ ውጪ የሚፈጸመውን በደል ወይም ብዝበዛ የማይጨምር ከመሆኑም በላይ፤ *ዲስረፕቲንግ ሀርም* በበይነ-መረብ እና በተቃራኒው ከበይነ-መረብ ውጪ በሚካሄዱት የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ድርጊቶች መካከል ሰው-ሠራሽ ድንበር የመፍጠር ዓላማ የለውም፡ ፡ ሕፃናት በዲጂታል ከባቢ ውስጥ ጊዜያቸውን በሚያሳልፉበት ወቀት በደል እና ብዝበዛ ሊደርስባቸው ይችላል፤ ሆኖም ልክ እንደዚሁ፤ አጥፊዎች ድርጊታቸውን ለማሳለጥ ዲጂታል ቴክኖሎጂን ሊጠቀሙ ይችላል፤ ለምሳሌ በአካል/በፊትለፊት በመገናኘት የሚፈጽሙትን በደል እና ብዝበዛ ለመቅረጽ እና ምስሎቹንም ለሌሎች ለማጋራት፤ ወይም ሕፃናቱ በአካል/በፊትለፊት እንዲያገኟቸው ለማሸኮርመም፡፡ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ምንነትን የሚበይን ማናቸውም አገላለጽ፤ በባሕርያቸው እና በድርጊታቸው ረገድ በበይነ-መረብ ውጪ እና በበይነ-መረብ መካከል ያለው ድንበር በየጊዜው እየደበዘዘ መምጣቱን[11] የግድ ሊያገናዝብ የሚገባው እና፤ የሚሰጡ ምላሾችም የዲጂታል ቴክኖሎጂዎች ምናልባት ሊኖራቸው ስለሚችለው ሚና ለማወቅ፤ በተሟላ ዕይታ ዙሪያ-መለሱን የመቃኘትን አስፈላጊነት ከግንዛቤ ውስጥ ሊያስገቡ ይገባል፡፡ ሕፃናት የበይነ-መረብ እና ከበይነ-መረብ ውጪ ያሉት ሁለቱ ዓለሞቻቸው በየጊዜው ይበልጥ እየተጠላለፉ እና ተመሳሳይነታቸውም እየጨመረ ነው የሚል አረዳድ ያላቸው ስለሆነ፤ ይህን መሰሉ የሕፃናቱ አረዳድ በእሳቤ ውስጥ መግባቱን ለማረጋገጥ ይሄ ዓይነቱ ብያኔ የላቀ ሚና አለው[12]፡፡

*በዲስረፕቲንግ ሀርም* ውስጥ፤ ለበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የተሰጠው ብያኔ፤ በተለይ ከታች የተዘረዘሩትን በሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደሎችን እንዲያጠቃልል በሚያደርግ አኳኋን ነው፡-

- **የሕፃናት ወሲባዊ በደል-አዘል ቁሳቁስ (ሕ/ወ/በ/ቁሳቁስ)**ን (በእንግሊዝኛው Child Sexual Abuse Material (CSAM)) ማዘጋጀት፣ ይዞ መገኘት፣ እና ለሌሎች ማጋራት ሲሆን፤ እነዚህም በዋናነት የወሲብ ዓላማ ያላቸው  ፎቶዎች፣ ቪዲዮዎች፣ ድምጾች፣ ወይም ሌሎች ቀረጻዎች፤ አሊያም በእውን ሲካሄድ ተቀረጸም ሆነ በዲጂታል እገዛ የተዘጋጀ በሕፃናት ላይ ወሲባዊ በደል ሲካሄድ ወይም የሕፃናትን ኃፍረተ-ሥጋዎች የሚያሳይ ማናቸውም ዓይነት አቀራረቦች[13]፤
- **የሕፃናት ወሲባዊ በደልን በቀጥታ-ሥርጭት ማስተላለፍ**፡ በሕፃናት ላይ የሚፈጸመው ወሲባዊ በደል እየተካሄደ እያለ፤ ጎን ለጎንም በመገናኛ ዘዴዎች፣ በቪዲዎ ኮንፈረንስ መሣሪዎች፣ እና/ወይም በፍጡን መልእክት መላላኪያ (chat) መተግበሪያዎች (applications) አማካኝነት አሁን-በአሁን (real-time) ወይም በቀጥታ የሚታይበት አድራጎት ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ እንደሚያጋጥመው ድርጊቱ እንዲካሄድ የሚፈልግ ግለሰብ ገንዘብ ወይም ሌሎች ዓይነት ጥቅማጥቅሞችን የሚሰጥ ወይም የሚከፍል ሲሆን፤ ወንጀለኛው ግለሰብ ግን በአካል፤ ሕፃናቱ እና የበደሉ ፈጻሚዎች ካሉበት ቦታ ውጪ ርቆ በሌላ ሥፍራ ሆኖ የሚታዘብ ነው፡፡
- **ለወሲብ ዓላማ ሕፃናትን በበይነ-መረብ ማሸኮርመም**፡ በሕፃናት ላይ ወሲባዊ በደልን እና ብዝበዛን ለመፈጸም በማለም፤ በቴክኖሎጂ አማካኝነት ከሕፃናት ጋር የሚደረግ መስተጋብር ነው፡፡ ማሸኮርመምን (grooming) እንደ ወንጀል

9. Interagency Working Group on Sexual Exploitation of Children. (2016). Terminology Guidelines for the Protection of Children from Sexual Exploitation and Sexual Abuse. Bangkok: ECPAT International. 18.
10. Interagency Working Group on Sexual Exploitation of Children. (2016). Terminology Guidelines for the Protection of Children from Sexual Exploitation and Sexual Abuse. Bangkok: ECPAT International. 24.
11. May-Chahal, C., & Palmer, C. (2018). Rapid Evidence Assessment: Characteristics and vulnerabilities of victims of online-facilitated child sexual abuse and exploitation. Independent Inquiry into Child Sexual Abuse. UK: Lancaster University.
12. Stoilova, M., Livingstone, S., Khazbak, R. (2021). Investigating Risks and Opportunities for Children in a Digital World: A rapid review of the evidence on children's internet use and outcomes. Innocenti Discussion Papers no. 2021-01, Florence: UNICEF Office of Research – Innocenti.
13. Interagency Working Group on Sexual Exploitation of Children. (2016). Terminology Guidelines for the Protection of Children from Sexual Exploitation and Sexual Abuse. Bangkok: ECPAT International. 40.

### ምስል 2፡ በዲስረፕቲንግ ሀርም የተገኙ ዋና ዋና የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ዓይነቶች በየመልካቸው ሲቀመጡ




አድራጎት የሚደነግጉ ዓለም-አቀፍ የሕግ ሰነዶች[14]፤ ድርጊቱ እንደ ወንጀል የሚታየው ሕፃኑን በአካል/በፊትለፊት የማግኘት ዓላማ ከነበረው ብቻ እንደሆነ ቢደነግጉም፤ በአንጻሩ ግን በሕፃናት ላይ ወሲባዊ በደልን ለመፈጸም የሚፈልጉ ወንጀለኞች፤ የግዴታ ሕፃናቱን በአካል አግኝተው በደሉን መፈጸም ሳያስፈልጋቸው፤ ለምሳሌ ሕፃናቱ ራሳቸውን በራሳቸው አንሥተው/ቀርጸው በዲጂታል ቴክኖሎጂዎች አማካኝነት እነዚህን የሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶችን እንዲልኩላቸው ወንጀለኞቹ በስልት ሊጠምዝዟቸው/ሊያሳምኗቸው የሚችሉ ሲሆን፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ ወንጀለኞቹ በመደበኛ ሁኔታ የሚጠቀሙበት ስልት ሁኗል።

የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል እንዲከሠት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን እና ማኅበራዊ-ወባህላዊ ምኅዳሮችን ለመገንዘብ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ሌሎች ጉዳዮችም በ*ዲስረፕቲንግ ሀርም ሪፖ*ርቶች ውስጥ ተዳስሰዋል።

- **ሕፃናት-ቀመስ ግለ-ቀረጽ (self-generated) ወሲባዊ ይዘቶችን ለሌሎች የማካፈል ድርጊት**[15]፤ ምንም እንኳ መጀመሪያ ላይ ይዘቱ የተዘጋጀው እና በአቻዎች/በእኩያሞች መካከል የተሠራጨው በፈቃደኝነት ላይ የነበረ ቢሆንም፤ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል እንዲፈጸም ምክንያት ሊሆን ወይም ለድርጊቱ መፈጸም አስተዋጽኦ ሊያበረክት ይችላል፤ ምክንያቱም ይዘቱ ያለ ባለቤቱ ይሁንታ ለሌሎች ሊተላለፍ፤ አሊያም በማታለል ወይም በማስገደድ ሊወሰድ ስለሚችል ነው።

- **ለወሲብ ሕፃናትን በማስገደድ-መጠቀም**[16] (sexual extortion) ድርጊት ማለት፤ መያዣን (blackmail) ወይም ማስፈራሪያን በመጠቀም፤ ከአንድ ሕፃን ወሲባዊ ይዘቶችን ወይም ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን (ለምሳሌ ገንዘብን) ለማግኘት የሚፈጸም አድራጎት ሲሆን፤ አብዛኛውን ጊዜ ወንጀለኛው እንደ መያዣ የሚጠቀመው ከዚህ ቀደም እጁ ያስገባውን ሕፃኑን የሚመለከት ወሲባዊ ይዘትን ነው።

- የሕፃናት **ወሲባዊ ትንኮሳ**[17] እና **ያለፍላጎታቸው ሕፃናትን ለወሲባዊ ይዘቶች የማጋፈጥ**[18] ድርጊቶች፤እንደ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ሊወሰዱ ወይም በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ ደግሞ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን ለመፈጸም አስቻይ ሁኔታዎችን ሊፈጥሩ የሚችሉ ተጨማሪ አብነቶች ናቸው። ለምሳሌ ያህል፤ አጥፊዎች ከማሽኮርመም ስልታቸው ጋር በተገናኘ ሕፃናቱ ስለ ወሲብ ያላቸውን አቋም ወይም የኀፍረት ስሜት ለማለዘብ ሆን ብለው ወሲባዊ ይዘቶችን እንዲመለከቱ ሊያደርጓቸው ይችላሉ። ሆኖም፤ ማስረጃን የተንተራሰ ፖሊሲን እና ፕሮግራምን ለመቅረጽ ሲባል፤ ሕፃናት በምርጫቸው በሚመለከቷቸው ወሲባዊ ይዘቶች እና ያለምርጫቸው ወይም ተጋፍጠው በሚመለከቷቸው መካከል ያለውን ልዩነት መገንዘብ ያስፈልጋል። በምርጫቸው የሚመለከቱበት ዓይነት ድርጊቶች፤ የ*ዲስረፕቲንግ ሀርም* ጥናት በተጠቀመበት የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ብያኔ ወይም ትርጓሜ ውስጥ አልተካተቱም።

---

14. ለወሲብ ዓላማ ሕፃናትን የማሽኮርመም ድርጊትን በወንጀል አድራጎት እንዲታይ የሚያስገድዱት እና በሥራ ላይ የዋሉት ሁለቱ ብቸኛ ዓለም-አቀፍ የሕግ ድንጋጌ ሰነዶች የእንግሊዝኛ ቅጂዎች ቀጥሎ ተዘርዝረዋል፡- Council of Europe. (2007). Convention on the Protection of Children against Sexual Exploitation and Sexual Abuse. Council of Europe Treaty Series – No. 201. Section 23; and European Parliament and Council. (2011). Directive 2011/92/EU on combating the sexual abuse and sexual exploitation of children and child pornography, and replacing Council Framework Decision 2004/68/JHA. Section 6.
15. Cooper, K., Quayle, E., Jonsson, L. & Svedin, C.G. (2016). Adolescents and self-taken sexual images: A review of the literature. Computers in Human Behavior, vol. 55, 706–716.
16. Interagency Working Group on Sexual Exploitation of Children. (2016). Terminology Guidelines for the Protection of Children from Sexual Exploitation and Sexual Abuse. Bangkok: ECPAT International. 52.
17. Interagency Working Group on Sexual Exploitation of Children. (2016). Terminology Guidelines for the Protection of Children from Sexual Exploitation and Sexual Abuse. Bangkok: ECPAT International. 21.
18. Interagency Working Group on Sexual Exploitation of Children. (2016). Terminology Guidelines for the Protection of Children from Sexual Exploitation and Sexual Abuse. Bangkok: ECPAT International. 44.

# የሥነ-ሕዝብ እና የበይነ-መረብ አጠቃቀም በኢትዮጵያ

በዓለም ዙሪያ የበይነ-መረብ ተደራሽነት እየጨመረ ያለ ቢሆንም፤ የበይነ-መረብ አጠቃቀምን የሚመለከት መደበኛ የስታትስቲክስ መረጃን በየወቅቱ የሚያደራጁ፤ ወይም መረጃውን በሃገራቸው ካሉት ሕፃናት አንጻር ቃኝተው የሚያቀርቡ ሃገራት ጥቂቶች ናቸው። ይህ ሁኔታ፤ በተለይም ዝቅተኛ እና አነስተኛ ገቢ ባላቸው ሃገራት ውስጥ በሚኖሩት ታዳጊዎች ሕይወት ላይ የበይነ-መረብ ቴክኖሎጂዎች ያስከተሉትን ተጽእኖ የማወቅ ተግባርን ፈታኝ አድርጎታል። ከታች የቀረበው ምስል በኢትዮጵያ ያለውን የበይነ-መረብ ተደራሽነት እና የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀምን የተመለከተ የቅርብ ጊዜውን መረጃ ጨምቆ የሚያሳይ ሲሆን፤ አንዳንዶቹ መረጃዎች የተሰበሰቡት ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ባላቸው በይነ-መረብ ተጠቃሚዎች ላይ በተካሄደው እና ሃገር-አቀፍ ስብጥር ባለው የ*ዲስረፕቲንግ ሀርም* የአባወራ/የቤተሰብ የዳሰሳ ጥናት  አማካኝነት ነው።

ከታች የቀረበው ጥሬ መረጃ፤ የሕፃናት የበይነ-መረብ አጠቃቀም ልዩ ልዩ ገጽታዎችን ለመገንዘብ የሚያስችል ጠቃሚ ዳራ ነው። ሆኖም፤ በጥናቱ ሥነ-ዘዴያዊ ውሱንነቶች የተነሣ፤ ከጥቂት ኢርቱዕ ምንጮች (secondary sources) በሚገኘው ጥሬ መረጃ ጥራት ላይ ተጽእኖ ሊኖረው እንደሚችል ታሳቢ ማድረግ ያሻል። ጥናቱ በዓላሚ (purposive) እና በሌሎች የግምት-አልቦ (non-probability) የናሙና አመራረጥ ዘዴዎች ላይ የተመረኮዘ እንደመሆኑ፤ ጥሬ መረጃው የተጠቀሰውን የናሙና ምልአተ-ስብስብ ይወክላል ተብሎ ሊታሰብ አይችልም። አንዳንዴ ደግሞ፤ በጥሬ መረጃ አሰባሰብ ስልቶች ላይ እንዲሁም ለ‹በይነ-መረብ ተጠቃሚ› በሚሰጡ ብያኔዎች ላይ ወጥነት ካለመኖሩ የተነሣ፤ የሃገራትን የእርስ በእርስ ንጽጽሮሽ ፈታኝ ያደርገዋል።

## ጠቅላላ የሕዝብ ቁጥር 2019

የተመድ ጥሬመረጃ

**112,079,000**[19]

(2018: 109,224,000)[20]

## ሴት 2019

የተመድ ጥሬመረጃ

**56,010,000**[21]

(2018: 54,589,000)[22]

## ወንድ 2019

የተመድ ጥሬመረጃ

**56,069,000**[23]


(2018: 54,635,000)[24]

**ኢትዮጵያ በሕዝብ ቁጥር ከፍተኛነት ከዓለም 14ኛ ደረጃ የያዘች ሲሆን፤[25] ከአፍሪካ አህጉር ደግሞ ከናይጄሪያ ተከትላ ሁለተኛውን ሥፍራ ይዛለች**

## ከ18 ዓመት ዕድሜ በታች ያለው ሕዝብ (ብዛቱ እና ድርሻው በመቶኛ)


የተመድ ጥሬመረጃ

**52,244**[26]




## ከጠቅላላው ሕዝብ የከተማ ነዋሪዎች ድርሻ በመቶኛ 2018: 20.8%

እ.ኤ.አ. የ2030 ትንበያ፡ 26.9 በመቶ[27]




## መካከለኛ (MEDIAN) ዕድሜ 2020

**19.5**[28]



19. United Nations Population Division. (2019). World Population Prospects 2019.
20. United Nations Population Division. (2019). World Population Prospects 2019.
21. World Population Review. (2019). Ethiopia Country Profile.
22. United Nations Population Division. (2019). World Population Prospects 2019.
23. United Nations Population Division. (2019). World Population Prospects 2019.
24. United Nations Population Division. (2019). World Population Prospects 2019.
25. United Nations Population Division. (2019). World Population Prospects 2019.
26. UNICEF. (2019). The State of the World's Children 2019. Children, Food and Nutrition: Growing well in a changing world. UNICEF, New York.
27. United Nations Population Division. (2018). World Population Prospects 2019 File 1: Population of Urban and Rural Areas at Mid-Year (thousands) and Percentage Urban, 2018.
28. United Nations Population Division. (2019). World Population Prospects 2019 File POP/5: Median age by region, subregion and country, 1950-2100 (years).


# የሥነ-ሕዝብ እና የበይነ-መረብ አጠቃቀም በኢትዮጵያ

## የነፍስ-ወከፍ ጥቅል ሃገር-አቀፍ ምርት (GDP) በአሜሪካ ዶላር ($) 2019 (US$)

ኢትዮጵያው በቀጣናው ካሉት ድኻ ሃገራት አንዷ ብትሆንም፤ በፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት የቀጣናው መሪ ነች30:: [30]

## የድኽነት መጣኔ

2015: 23.5%[31]





## ቋንቋዎች

**ዐማርኛ**
**እንግሊዝኛ**

ዐማርኛ የኢትዮጵያ የሥራ ቋንቋ ነው[32]:: ሁለቱም ቋንቋዎች ማለትም እንግሊዝኛ እና ዐማርኛ በመላው ሃገሪቱ ባሉ ትምህርት ቤቶች እንደ ትምህርት ይሰጣሉ::[33]


## የበይነ-መረብ ተደራሽነት መጣኔ

2017: 18.6%[34]




ምንጭ የዲስረፕቲንግ ሀርም ጥሬ መረጃ

## እ.ኤ.አ. በ2020 ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ባላቸው ዘንድ የነበረው የበይነ-መረብ ተደራሽነት መጣኔ




ብዛት = 5 ሺህ 928፤ በኢትዮጵያ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው

ምንጭ የዲስረፕቲንግ ሀርም ጥሬ መረጃ

## የበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናቱ ተንከባካቢዎች ዘንድ ያለው የበይነ-መረብ አጠቃቀም

**16%**

ብዛት = 1 ሺህ የበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት ተንከባካቢዎች

ምንጭ የዲስረፕቲንግ ሀርም ጥሬ መረጃ

## ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ባላቸው ዘንድ በይነ-መረብ ለመጠቀም የሚመርጡት መገልገያ*




ብዛት = 1 ሺህ የበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት


*የምርጫ ጥያቄ

29. The World Bank. (n.d.).GDP per capita (current US$) - Ethiopia.
30. World Bank. (2019). Ethiopia Country Profile.
31. The World Bank. (n.d.). Poverty headcount ratio at national poverty lines (% of population) - Ethiopia.
32. Federal Democratic Republic of Ethiopia. (1994) Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.
33. UNICEF. (2016). Ethiopia. The impact of language policy and practice on children's learning: Evidence from Eastern and Southern Africa.
34. ዓለም-አቀፍ የቴሌኮሚዩኒኬሽኖች ኅብረት (ቀን የለውም). የስታትስቲክስ መረጃ፤

# የሥነ-ሕዝብ እና የበይነ-መረብ አጠቃቀም በኢትዮጵያ

## ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ባላቸው ዘንድ በይነ-መረብን የሚጠቀሙበት ተመራጩ ቦታ*

ምንጭ የዲስረፕቲንግ ሀርም ጥሬ መረጃ





ብዛት = 1 ሺህ የበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

*የምርጫ ጥያቄ

## የሕፃናት የበይነ-መረብ አጠቃቀም ድግግሞሽ


ምንጭ የዲስረፕቲንግ ሀርም ጥሬ መረጃ




መደብ፡ በኢትዮጵያ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት፤ ብዛት = 1 ሺህ ሕፃናት

## በበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት ተንከባካቢዎች ዘንድ ያለው የበይነ-መረብ አጠቃቀም ድግግሞሽ


ምንጭ የዲስረፕቲንግ ሀርም ጥሬ መረጃ




ብዛት = 1 ሺህ የበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት ተንከባካቢዎች

# የሥነ-ሕዝብ እና የበይነ-መረብ አጠቃቀም በኢትዮጵያ

## የበይነ-መረብ አገልግሎት ሰጪዎች የገበያ ድርሻ




**‹‹[…] ኢትዮጵያ የቴሌኮም መረብን እና አገልግሎቶችን በመንግሥት ባለቤትነት በሚተዳደር አገልግሎት ሰጪ (ኢትዮ ቴሌኮም) ብቻ እንዲከናወን እስካሁን የሞኖፖል አሠራርን ጠብቀው ከቆዩ የመጨረሻዎቹ ሃገራት አንዷ ነች፡፡››[35]**

**መጋቢት 24 ቀን 2013 ዓ.ም. ላይ የኢትዮጵያ የፋይናንስ ሚኒስቴር፤ ለአዲስ አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ ለመስጠት ባወጣው ጫረታ ሁለት ተጫራቾች እንደተሳተፉ አሳውቆ ነበር፡፡[36]**

**በሚያዝያ 24 ቀን 2013 ዓ.ም. የኢትዮጵያ መንግሥት የቴሌኮም አገልግሎት መስጫ ፈቃድን፤ የቴሌኮም ኩባንያዎች በጣምራ ለመሠረቱት ግሎባል ፓርትነርሺፕ ፎር ኢትዮጵያ ለሚባል ድርጅት ሰጥቷል፡፡ የሃገሪቱ የሚኒስትሮች ምክር ቤትም በኢትዮጵያ የኮሚዩኒኬሽን ባለሥልጣን አማካኝነት ሁለተኛውን የቴሌኮም ፈቃድ ለመስጠት የሚያስችሉ ተግባራት በተቀላጠፈ አኳኋን እንዲካሄዱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡**

ምንጭ የዲስረፕቲንግ ሀርም ጥሬ መረጃ


## ማኅበራዊ ሚዲያን በየሳምንቱ የሚጠቀሙ በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት




ብዛት = 1 ሺህ የበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

ምንጭ የዲስረፕቲንግ ሀርም ጥሬ መረጃ


## ፍጡን የመልእክት መላላኪያን (INSTANT MESSAGING) በየሳምንቱ የሚጠቀሙ በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት




ብዛት = 1 ሺህ የበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት


## የመረጃ እና ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ የልማት ደረጃ

(ICT DEVELOPMENT INDEX RANKING)[38]




## በዓለም የሳይበር ደኅንነት ደረጃ

(GLOBAL CYBERSECURITY INDEX RANKING 2018)[39]




35. Dione, O. (2021, March 21). Why Ethiopia Needs to Open its Telecom Market. World Bank Blogs.
36. Reuters. (2021, April 27). Ethiopia Receives Two Bids for Two Telecoms Operating Licences. Reuters.
37. Getachew, A.. (2021, May 22). Global Consortium Wins Ethiopia's Telecom License for $850M. Anadolu Agency.
38. የመረጃ እና የኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማት መለኪያ (በእንግሊዝኛው ICT Development Index)፤ 11 አመላካቾችን በማጣመር ወጥ በሆነ አንድ ዓይነት ማነጻጸሪያ ለመለካት የሚያስችል መስፈርት ነው፡፡ መስፈርቱ በየተወሰነ የጊዜ ርቀት በሃገራት መካከል በዘርፉ የሚታዩትን ለውጦች ለመከታተል እና ለማነጻጸር ያገለግላል፡፡
39. የዓለም የሳይበር ደኅንነት መለኪያ (Global Cybersecurity Index (GCI)) ሃገራት ለሳይበር ደኅንነት ያላቸው ቁርጠኝነት በዓለም-አቀፍ ደረጃ የሚለካበት አመኔታን ያተረፈ መስፈርት ነው፡፡ የዚህም ዓላማ ስለ ጉዳዩ ፋይዳ እና ልዩ ልዩ ገጽታዎቹ ያለውን ግንዛቤን ለማሳደግ እንዲቻል ነው፡፡ የሳይበር ደኅንነት በበርካታ ኢንደስትሪዎች እና የተለያዩ ዘርፎች ውስጥ በሁለ-ገብነት በስፋት ግልጋሎት ላይ የሚውል እንደመሆኑ፤ የእያንዳንዱ ሃገር የዕድገት ወይም የአጠቃቀም ደረጃ በአምስት ዐበይት ፈርጆች ይገመገማል፡- (ሀ) ሕጋዊ እርምጃዎች፤ (ለ) ቴክኒካዊ እርምጃዎች፤ (ሐ) ድርጅታዊ እርምጃዎች፤ (መ) አቅምን ማጎልበት፤ (ሠ) ትብብር የሚሉት ሲሆን፤ የእነዚህ ውጤት ሲዳመር አጠቃላይ ውጤቱን ይሰጣል፡፡

# የሕግ ማእቀፍ እና የፖሊሲ ዳሰሳ

## የሕግ ማእቀፍ እና የፖሊሲ ዳሰሳ

የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል-ነክ ወንጀሎችን ጨምሮ፤ በጥቅሉ የወሲብ ጥቃቶችን የሚመለከቱ አሁን ላይ ተግባራዊ እየተደረጉ ካሉት የኢትዮጵያ ሕጎች ውስጥ እጅግ ተዛማጅ የሚባሉት፤ የወንጀል ሕጉ (1997 ዓ.ም.)[40] ፤ እና የኮምፒዩተር ወንጀልን ለመደንገግ የወጣው አዋጅ (2008 ዓ.ም.) [41] ናቸው።

የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ (1997)፤ ‹‹ጸያፍ ወይም ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ››[42] ከሚያሰኙ ቁሳቁሶች ጋር የተያያዙ አድራጎቶችን እንደ ወንጀል የሚደነግጉ ሁለት አንቀጾችን አካትቷል። ይህ ያልተብራራ ብያኔ አሻሚ ትርጉም ስላለው፤ በሕፃናት ላይ ወንጀሎችን የፈጸሙ ጥፋተኞች ከተጠያቂነት እንዲያመልጡ ሊያደርጋቸው ይችላል፡ ፡ ከዚህም ባሻገር፤ ለዚህ ወንጀል የተጣለው ቅጣት እስከ ሦስት ዓመታት የሚደርስ ቀላል እሥራት ነው። በ1997 ዓ.ም. በወጣው የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ መሠረት፤ ይህ ዓይነቱ ቅጣት ‹‹ከባድነቱ መካከለኛ የሆነ ወንጀልን ባደረገና ጥፋተኛውም ለኅብረተሰቡ እጅግ አደገኛ መስሎ ባልታየ ጊዜ››[43] የሚጣል እንደሆነ ይደነግጋል። ይህ አካሄድ፤ የሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶች ጋር የተገናኙ ወንጀሎችን አውዳሚ ባሕርይ ከግምት የማያስገባ ነው። በመጨረሻም፤ የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ (1997)፤ ጸያፍ ይዘቶችን በደምሳሰው ከመወንጀል በስተቀር በሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶች ላይ ተፈጻሚነት የሌለው፤ ግን ደግሞ አዋቂዎች በሚተውኑበት የብልግና ቁሳቁሶች (pornographic material) ላይ እጅግ የሰፋ ተፈጻሚነት ያለው ነው።

የኮምፒዩተር ወንጀልን ለመደንገግ የወጣው አዋጅ (2008 ዓ.ም.)፤ ለአካለ-መጠን ያልደረሱ (ወይም ሲታዩ ለአካለ-መጠን ያልደረሱ እንዲመስሉ የተደረጉ ሰዎች) ግልጽ በሆነ አኳኋን ወሲብን ሲፈጽሙ የሚያሳዩ ትዕይንታዊ ቁሳቁሶች (visual materials) ጋር የሚገናኙ ልዩ ልዩ አድራጎቶችን በወንጀልነት ይደነግጋል[44]። አዋጁ በበይነ-መረብ ማሸኮርመምን በከፊል ይወነጅላል፤ የድርጊቱን ትርጉምም ወሲባዊ ይዘት ያላቸውን ስዕሎችን፣ የጽሑፍ መልእክቶችን፣ ወይም ቪዲዮዎችን በኮምፒዩተር ሥርዓት አማካኝነት በመላክ ለአካለ-መጠን ያልደረሰ ልጅን ለወሲባዊ ድርጊት ማነሣሣት ወይም መመልመል እንደሆነ የሚገልጽ[45]ሲሆን፤ ድርጊቱም ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እንደሚያስቀጣ ይደነግጋል[46]። ይህ አንቀጽ ግልጽ በሆነ የወሲባዊ መልእክት ግንኙነት/ልውውጥ የሚካሄድን ማሸኮርመም፤ ምናልባትም ግፋ ቢል የበይነ-መረብ ወሲባዊ ትንኮሳን (sexual harassment) የሚሸፍን ቢሆንም፤ በበይነ-መረብ የሚከናወን ወሲባዊ በደልን ወይም ለወሲብ ተግባር ቀጠሮ ማመቻቸትን ባላመ መልኩ፤ ከሕፃኑ ጋር ግንኙነት ለመመሥረት በበይነ-መረብ የሚደረግ የማሸኮርመም ድርጊትን ግን ድንጋጌው አይሸፍንም።

ይብሱንም፤ የወንጀል ሕጉም (1997) ሆነ የኮምፒዩተር ወንጀልን ለመደንገግ የወጣው አዋጅ (2008)፤ በበይነ-መረብ የሚካሄድን ለወሲብ ዓላማ በማስገደድ-መጠቀምን (sexual extortion)፣ በበይነ-መረብ የሚደረግ ወሲባዊ ትንኮሳን፣ ወይንም በሕፃናት ላይ የሚፈጸመውን ወሲባዊ በደል በቀጥታ ሥርጭት ማስተላለፍን በወንጀል ድርጊትነት አልደነገጉም። የወንጀል ሕጉ ‹‹ጸያፍ ወይም ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆኑ ነገሮችን በትያትር፣ በሲኒማ፣ በተንቀሳቃሽ ፊልሞች፣ በራዲዮ፣ በቪዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ››[47]እንዲተላለፍ የማደራጀት ተግባርን የሚወነጅል ድንጋጌ የያዘ ቢሆንም፤ ጸያፍ ወይም ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሚያሰኙ ነገሮች ምን እንደሆኑ የሚያመለክት ትርጉም ግን አልቀረበም።

ከበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን የሚመለከቱ አዲስ ሕጎችን ለማውጣት ወይም ማሻሻያ ለማካሄድ አሁን ላይ ምንም ዓይነት ዕቅድ ባይኖርም፤ በሕፃናት እና በሴቶች ላይ የሚፈጸመውን ጥቃት ከመቅረፍ አኳያ በሕግ ክፍተቶች እና ተግዳሮቶች ላይ ግምገማ ለማካሄድ ውጥን ያለ ስለመሆኑ በፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ-ሕግ ጽሕፈት ቤት ያለ አንድ ምላሽ ሰጪ መረጃውን አካፍለዋል። የተጠቀሰው ግምገማ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን ለመቅረፍ የሚያግዙ የሕግ ክፍተቶችን ለይቶ እንደሚያስቀምጥ፤ በሂደትም አዲስ ሕግ ወደ ማውጣት ወይም ያሉትን ሕጎች ወደ ማሻሻል እንደሚያመራ ተስፋ ይደረጋል። በፈደራል ጠቅላይ ዐቃቤ-ሕግ ሕግ ጽሕፈት ቤት ያለው ምላሽ ሰጪ (RA1-ET-05-A) እንዳለው፤ ግምገማው በ2014 ዓ.ም. የሚካሄድ ይሆናል። የ*ዲስረፕቲንግ ሀርም* ትንታኔ፤ ለግምገማው እና ወደፊት በኢትዮጵያ ሕጎች ላይ ለሚደረጉት ማሻሻያዎች ጠቃሚ አቅጣጫን በማመላከት ያግዛል።

ኃላፊነት-ከተጣለባቸው አካላት ጋር ቃለ-መጠይቅ ለማድረግ በርካታ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተለዩ ሲሆን፤ እነዚህም ከበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጋር የሚዛመድ ኃላፊነት ያላቸው በሚል መለኪያ ነበር፤ ሆኖም የአንዳቸውም የሥራ ድርሻ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን በግልጽ ያጠቃሰ ወይም ያካተተ ሆኖ አልተገኘም። አግባብነት ያላቸው መሥሪያ ቤቶች የተባሉት፤ የሴቶች፣ ሕፃናት፣ እና ወጣቶች ሚኒስቴር፤ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ-ሕግ ጽሕፈት ቤት፣ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሕፃናት ፍትሕ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት፣ የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት ኤጀንሲ፣ የኢኖቬሽን እና የቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ እንዲሁም የትምህርት ሚኒስቴርን ያጠቃልላል።

በአሁኑ ወቅት፤ የኢትዮጵያ የፌደራል መንግሥት በጀት የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን ለመቅረፍ በሚል ለዚሁ ጉዳይ ብቻ የመደበው ገንዘብ የለም። ከሴቶች፣ ሕፃናት፣ እና ወጣቶች ሚኒስቴር የመጣ አንድ ምላሽ ሰጪ እንደገለጹት፤ በጥቅሉ ለሕፃናት በደል እና ብዝበዛ ጉዳዮች በሚል መንግሥት በጀት መድቦ የነበረ ቢሆንም፤ በጀቱ በቂ ያልሆነ፤ ብሎም በፌደራል እና በክልል

40. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (1997)፤ የወንጀል ሕግ፤
41. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (2008)፤ የኮምፒዩተር ወንጀልን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 958/2008፤
42. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (1997)፤ የወንጀል ሕግ፤ አንቀጽ 640 እና 641
43. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (1997)፤ የወንጀል ሕግ፤ አንቀጽ 106
44. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (2008)፤ የኮምፒዩተር ወንጀልን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 958/2008፤ አንቀጽ 12
45. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (2008)፤ የኮምፒዩተር ወንጀልን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 958/2008፤ አንቀጽ 12 (2)
46. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (2008)፤ የኮምፒዩተር ወንጀልን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 958/2008፤ አንቀጽ 12 (2)
47. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (1997)፤ የወንጀል ሕግ፤ አንቀጽ 641፤

ባሉ እርከኖች በሚካሄዱ ገቢ ማሰባሰቦች ሊደጎም የሚገባ መሆኑን ከዚሁ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት የመጡ ምላሽ ሰጪ አመልክተዋል፡[48] (RA1-ET-01-A)

ምንም እንኳ በተለይ ከበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጋር የተገናኙ ሥራ ላይ የዋሉ ሃገር-አቀፍ ፖሊሲዎች እና ዕቅዶች ባይኖሩም፤ መንግሥት ዘርፈ-ብዙ ባለድርሻዎችን ያካተተ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ላይ ያተኮረ ግብረ-ኃይል እያቋቋመ መሆኑ ይነገራል። የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ላይ እርምጃ የመውሰድ አስፈላጊነትን በተመለከተ፤ የዚህ ግብረ-ኃይል መቋቋም ኢትዮጵያ ለጉዳዩ ዕውቅና መስጠቷን ማሳያ እንደሆነ በሴቶች፣ ሕፃናት፣ እና ወጣቶች ሚኒስቴር የሕፃናት መብቶች አድቮኬሲ ዳይሬክተር (RA1-ET-01-A) ገልጸዋል። ለበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ምላሽ የመስጠት ሥራ የብዙ መሥሪያ ቤቶችን ቅንጅታዊ አሠራር እንደሚሻ መንግሥት የተገነዘበ መሆኑን እና ይህም ጉዳዩ በመንግሥት ዕውቅና ማግኘቱን የሚመሰክር ሌላ ማሳያ ነው። በጉዳዩ ላይ ከሚሠሩ መሥሪያ ቤቶች መካከል በሦስቱ፤ ማለትም በሴቶች፣ ሕፃናት፣ እና ወጣቶች ሚኒስቴር፤ በፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ-ሕግ ጽሕፈት ቤት፣ እንዲሁም በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፤ ውስጥ ጉዳዩን በባለቤትነት የሚከታተሉ ባለሙያዎች የተመደቡ መሆኑ፤ እነዚህ መሥሪያ ቤቶች የሚጠበቅባቸውን ሚና ባግባቡ ለመጫወት ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት ያላቸው መሆኑን አብሮ ያሳያል።

እንደነዚህ ዓይነት ጅምር እንቅስቃሴዎች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል በመንግሥት አጀንዳ ውስጥ የያዘው ሥፍራ ገና በእንጭጭ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑ ይታያል። በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ካሉት ኃላፊነት-የተጣለባቸው አካላት ጋር የተደረጉት ቃለ-መጠይቆች እንደሚያመለክቱት፤ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ርእሰ-ጉዳይ ስለ ሕፃናት ጥበቃ መንግሥት በሚያካሂዳቸው ውይይቶች ላይ እስካሁን ጎልቶ አልወጣም፤ ለምሳሌ በፌደራል ጠቅላይ አቃቤ-ሕግ ጽሕፈት ቤት ሥር ባለው ‹ሃገር-አቀፍ አስተባባሪ አካል› (በእንግሊዝኛው National Coordination Body) አማካኝነት በሚካሄዱ መድረኮች እና በሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች ላይ ባተኮሩ መሰል የማስተባበሪያ መድረኮች ላይም ጎልቶ አልወጣም። የጽሕፈት ቤቱ አንድ ተወካይ እንዳሉት፤ ‹የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የአስተባባሪው አካል አጀንዳነት ፈጽሞ ተካቶ አያውቅም። ስትራቴጂ እና የትግበራ ዕቅድ አለን። አስከማወቀው ድረስ የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛን የተመለከቱ ጉዳዮችን ግን አያካትትም›።

ይህንን ችግር ለመቅረፍ ተገቢውን ዝግጅት ለማድረግ፤ በመንግሥት ውስጥ ያሉ ኃላፊነት-የተጣለባቸው አካላትን አቅም መገንባት ያሻል፡፡ በሴቶች፣ ሕፃናት፣ እና ወጣቶች ሚኒስቴር አማካኝነት ለቁልፍ የመንግሥት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ተሰጥቶ ከነበረው ግንዛቤ ማስጨበጥ መድረክ[49]፤ እንዲሁም እ.ኤ.አ. በ2019 በአፍሪካ ኅብረት ሰብሳቢነት ስለ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ከተካሄዱት ተከታታይ ቀጣናዊ/ክፍለ-አህጉራዊ ስብሰባዎች ውጪ፤ በምላሽ ሰጪነት ከተካተቱት ኃላፊነት-የተጣለባቸው የመንግሥት አካላት መካከል በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን መለየት እና እርምጃ መመውሰድ ላይ ያተኮረ ለፖሊሲ አውጪዎች የሚሆን ሥልጠና ስለመኖሩ አንዳቸውም አያውቁም።

በመንግሥት ደረጃ ሲታይ፤ በየአስተዳደር እርከኖቹ (ፌደራል፣ ክልል፣ ዞን፣ እና ወረዳ[50]) ላይ የሕፃናት አጠባበቅ ግብረ-ኃይሎች አሉ። በቀበሌ[51] ደረጃ፤ የሕፃናት ጥበቃ ሙያተኞች እጥረት ያለ ሰሆን፤ ይህም የሕፃናት ጥበቃ ሥራዎችን አፈጻጸም አጓትቷል። ከዩኒሴፍ ኢትዮጵያ የመጡ አንድ ቃለ-ተጠያቂ አንዳሉት፤ ‹ቅርጽ ያለው የሕፃናት አጠባበቅ ሥርዓትን ለመፍጠር እንዲቻል ዩኒሴፍ መንግሥትን እያገዘው ይገኛል። እ.ኤ.አ. በ2019 በቅርቡ የጸደቀ ለሕፃናት አጠባበቅ ሥራ የሚውል አዲስ የነገረ-ጉዳይ ወይም የኬዝ አያያዝ ማእቀፍ አለ። ነገር ግን ማነው ይህንን ማእቀፍ ሥራ ላይ የሚያውለው? መሬት ላይ ያለ የሰው ኃይል የለንም› (RA1-ET-02-A)

ይህ ክፍተት በመጠኑም ቢሆን በወረዳ ደረጃ ባሉት የሕፃናት ጥበቃ ሙያተኞች የተሸፈነ ሲሆን፤ እነዚህ ሙያተኞች ሥራዎችን ለማከናወን ከማኅበረሰብ-አቀፍ አደረጃጀቶች እና ማኅበራት ጋር በመተባበር ይሠራሉ። በጥቅሉ በአንድ ወረዳ ላይ ከሁለት እስከ አምስት የሕፃናት ጥበቃ ሙያተኞች አሉ።

> **“ከበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን የሚመለከቱ አዲስ ሕጎችን ለማውጣት ወይም ማሻሻያ ለማካሄድ አሁን ላይ ምንም ዓይነት ዕቅድ ባይኖርም፤ በሕፃናት እና በሴቶች ላይ የሚፈጸመውን ጥቃት ከመቅረፍ አኳያ በሕግ ክፍተቶች እና ተግዳሮቶች ላይ ግምገማ ለማካሄድ ውጥን ያለ ስለመሆነ በፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ-ሕግ ጽሕፈት ቤት ያለ አንድ ምላሽ ሰጪ መረጃው ንአካፍለዋል፡”**

48. ከሴቶች፣ ሕፃናት፣ እና ወጣቶች ሚኒስቴር የመጡ አንድ ምላሽ ሰጪ እንዳብራሩት፤ የማኅበረሰብ ክብካቤ ጥምረት (Community Care Coalition) የሚባሉ የሐብት ማሰባሰብ ሥራን የሚያከናውኑ አደረጃጀቶችን መንግሥት ያዋቀረ ሲሆን፤ የእነዚህ መዋቅሮች ዋና ዓላማ በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚኖሩ ተጋላጭ ሕፃናትን ለመርዳት የሚውል የገንዘብም ሆነ የዓይነት ድጋፎችን ከማኅበረሰቡ ማሰባሰብ ነው። በሃገር-አቀፍ ደረጃ፤ ከተ/መ/ድ/ መሥሪያ ቤቶች እና ከዓለም-አቀፍ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የሚሰጡ  የገንዘብ ልገሳዎች ጋር ተዳምሮ በመንግሥት የሚመደበውን በጀት እንደሚደጉመው ምላሽ ሰጪው አብራርተዋል።
49. ይሄ፤ ‹በገርልስ አድቮኬስ አሊያንስ› ፕሮጀክት ሥር በ‹ቴሬ ዴዝሆም› አዘጋጅነት በተካሄደ  ወርክሾፕ ላይ የነበረ አጭር ቆይታ ወይም ውይይት ነው። ስለዚህ በበ/መ/ሕ/ወ/ብ/በደል ላይ ያተኮረ ራሱን የቻለ ዎርክሾፕ አልነበረም ።
50. ወረዳ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ከክልላዊ መንግሥት እና ከዞን ቀጥሎ በሦስተኛ ደረጃ ያለ የአስተዳደር እርከን ነው።
51. ቀበሌ፤ የኢትዮጵያ የመጨረሻው ዝቅተኛ የአስተዳደር እርከን ነው።

## ስለ በይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ያለው ግንዛቤ

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ያለው የሕግ እና የፖሊሲ ማእቀፍ፣ በመላ ሃገሪቱ ስለ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ያለው የግንዛቤ ደረጃ ውሱን መሆኑን ያሳያል። የግንዛቤ ደረጃው አነስተኝነት በ*ዲስረፕቲንግ ሀርም* የጥናት ላይ ሂደት ላይ በተካሄዱት በርካታ ተግባራት በግልጽ የታየ ሲሆን፤ ይህም ግንባር ቀደም አገልግሎት ሰጪዎች ላይ ዳሰሳ ጥናቱ ሲካሄድ፤ ሙሉ ለሙሉ ለማለት በሚቻልበት ሁኔታ ምላሽ ሰጪዎቹ (97 በመቶ፤ ብዛት = 32) በተንከባካቢዎች እንዲሁም በምልአተ-ሕዝቡ ዘንድ ያለውን የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ግንዛቤ ‹ደካማ› በማለት የገለጹበትንም ይጨምራል።

በምልአተ-ሕዝቡ ብቻ ሳይሆን፤ በኢትዮጵያ ፖሊሲ አውጪዎች እና በግንባር ቀደም ሠራተኞች ዘንድ ስለ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ያለው ግንዛቤ እጅግ አነስተኛ መሆኑን፤ በ*ዲስረፕቲንግ ሀርም* ቃለ-መጠይቅ የተደረገላቸው ዘጠኝ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች በሙሉ ይስማሙበታል፡ ፡ ‹ስለ በበይነ-መረብ ወሲባዊ ብዝበዛ ምንም ግንዛቤ የለም፤ ማንም አያውቀውም› ሲሉ አንዱ ኃላፊነት-የተጣለባቸው ኃላፊ፤ ማለትም በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሴቶች፣ ሕፃናት፣ እና ወጣቶች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ገልጸዋል (RA1-ET-03-A)። ቴክኒካዊ ሥራውን የሚያከናውኑ ፖሊሲ አውጪዎች እና ፈጻሚዎች ስለ በይነ-መረብ በደል ዓይነቶች እና የወቅቱን አካሄዶች እንደማያውቁ ከፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ-ሕግ ጽሕፈት ቤት የተወከሉ አንድ ምላሽ ሰጪ የተናገሩ ሲሆን፤ በዚህ የተነሣም የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጉዳይ በየሚመለከታቸው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ውስጥ እንደ አንድ የሥራ ድርሻቸው/ተልእኳቸው እንዲሁም በፕሮግራሞቻቸው ውስጥ አይንጸባርቀም። በሴቶች፣ ሕፃናት፣ እና ወጣቶች ሚኒስቴር የሕፃናት መብቶች አድቮኬሲ ዳይሬክተር (RA1-ET-01-A)፤ ‹አናውቀውም፤ ሌላው ቀርቶ የሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችም ስለዚህ ጉዳይ አያውቁም። የበ/መ.ሕ/ወ/ብ/በደል ገና በእንጭጭ ደረጃ ያለ መሆኑን መናገር እችላለሁ፤ ምክንያቱም ለእኛ በቅርቡ ብቅ ያለ አጀንዳ ነው›› ሲሉ አብራርተዋል።

ስለ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የምልአተ-ሕዝቡን ግንዛቤ ለማሳደግ በመንግሥት አነሣሽነት አሁን ላይ እየተካሄደ ያለው ብቸኛ ፕሮግራም፤ የሕፃናት የበይነ-መረብ ደኅንነትን በሚመለከት በትምህርት ሚኒስቴር እየተካሄደ ያለው ተጠቃሚ-ተኮር/አውትሪች ፕሮግራም ነው። ቃለ-መጠይቅ ከተደረገላቸው ከዘጠኙ የመንግሥት ኃላፊዎች ውስጥ ሁለቱ ብቻ፤ ከሁለት ዓመታት ገደማ በፊት ስለተጀመረው ስለዚህ ተጠቃሚ-ተኮር/አውትሪች ፕሮግራም አያውቁም። አንድ የትምህርት ሚኒስቴር ተወካይ እንዳሉት፤ ይህ ተጠቃሚ-ተኮር/አውትሪች ፕሮግራም በከተሞች አካባቢ ብቻ ያሉትን ሕፃናት እና ወጣቶች ዒላማ ያደረገ ሲሆን፤ የዚህም ምክንያት ከፍተኛ የበይነ-መረብ አጠቃቀም ያለው በሃገሪቱ ባሉ ከተሞች ስለሆነ እና ይህም ለበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ይበልጥ ተጋላጭ እንደሚያደርጋቸው ስለሚታሰብ ነው።

በ*ዲስረፕቲንግ ሀርም* የአባወራ/የቤተሰብ የዳሰሳ ጥናት ላይ፤ 37 በመቶ የሚሆኑት ሕፃናት ደኅንነታቸውን አስጠብቀው እንዴት በይነ-መረብን መጠቀም እንደሚችሉ (ለምሳሌ በበይነ-መረብ አማካኝነት አንድ ሰው ቢያውካቸው/ቢረብሻቸው ማድረግ ስላለባቸው ነገር)፣ በበይነ-መረብ ለሌሎች ማጋራት የሌለባቸው ይዘቶች ምን ዓይነት እንደሆኑ፣ እንዲሁም የራሳቸውን የግላዊነት መቼቶችን (privacy settings) እንዴት ማስተካከል እንደሚችሉ የሚመለከቱ መረጃዎችን *እስካሁን ጨርሶ* አግኝተው እንደማያውቁ ገልጸዋል። በከተማ ካሉት ምላሽ ሰጪዎች ጋር ሲነጻጸር በገጠር ያሉት ሕፃናት ይህንን መሰል መረጃ የማግኘት ዕድላቸው ያነሰ (በገጠር 32 በመቶ፤ በከተማ 47 በመቶ) ነበር። በመላው ኢትዮጵያ የበይነ-መረብ ትስስር እያደገ በሄደ መጠን[52]፤


ለመላው ሕፃናት የሚዳረስ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን የመከላከል ተጠቃሚ-ተኮር ሥራ አጣዳፊ እየሆነ መጥቷል። አንድ የመንግሥት ኃላፊ (RA1-ET-09-A) እንዳጤኑት፤ ‹ወደፊት የኢንተርኔት ተደራሽነት ሲስፋፋ፤ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ችግር አድጎ ሊወጣ ይችላል›።

በበይነ-መረብም ላይም ሆነ ከዚያ ውጪ የሕፃናት ደኅንነት እንዲጠበቅ ተንከባካቢዎች ጠቃሚ ሚና መጫወት ይችላሉ፤ ነገር ግን ስለ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ያላቸው ግንዛቤ እና ዕውቀት በቅድሚያ ሳይገነባ፤ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን ለመከላከል በሚደረጉ ጥረቶች ላይ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ መጠበቅ ያስቸግራል። የበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናቱ ተንከባካቢዎች ውስጥ 22 በመቶዎቹ፤ የልጃቸውን የበይነ-መረብ አጠቃቀም መርዳት እና ማገዝ ስለሚቻልበት ዘዴ የሚያስረዳ፤ አሊያም የልጆቻቸው የበይነ-መረብ ቆይታ ደኅንነትን ማስጠበቅ በሚችሉበት ስልት ላይ ያተኮረ አንድም መረጃ ወይም ምክር ጨርሶ አግኝተው አለማወቃቸውን ተናግረዋል። ሕፃናት፤ ብሎም ተንከባካቢዎቻቸው፤ የበይነ-መረብን ጥቅም ለመቋደስ የሚያስችሏቸውን ክህሎቶች የታጠቁ፤ እንዲሁም የበይነ-መረብ ስጋቶችን በብቃት መቆጣጠር የሚችሉ መሆኑን ለማረጋገጥ፤ በዲጂታል ደኅንነት ላይ ያተኮረ በማስረጃ ላይ የተመረኮዘ ትምህርት ሊኖር ይገባል።

በአባወራ/ቤተሰብ የዳሰሳ ጥናቱ የተሳተፉ ተንከባካቢዎች፤ የሕፃናቶቻቸውን የበይነ-መረብ ቆይታ እንዴት ደኅንነቱን ለማስጠበቅ እንደሚችሉ ለማወቅ ስለ ሚመርጡት የመረጃ ምንጭ የተጠየቁ ሲሆን፤ 41 በመቶዎቹ ተንከባካቢዎች ትምህርት ቤቶች ስለ በይነ-መረብ ደኅንነት ማስገንዘቢያ ሊሰጡ እንደሚገባ፤ እንዲሁም 32 በመቶዎቹ ይህን መሰሉን መረጃ ከቴሌቪዥን ለማግኘት ፈልገው እንደነበር ገልጸዋል (ምስል 3ን ይመለከቷል)። በእነዚህ ግኝቶች መሠረት፤ በበይነ-መረብ ላይ ለሕፃናት መደረግ ያለበት ጥበቃ በኢትዮጵያ ሥርዓተ-ትምህርት እንደ አንድ ምሰሶ ወይም ዐብይ ጭብጥ እንዲካተት ማድረግን ጨምሮ፤ መንግሥት የሚያካሂዳቸው የግንዛቤ ፈጠራ እንቅስቃሴዎች በእነዚህ ዓይነቱ መገናኛ ዘዴዎች ላይ የሚያተኩሩበትን ሁኔታ ታሳቢ ሊያደረግ ይገባል። ከትምህርት ሚኒስቴር ጀነራል ዳይሬክቶሬት የመጡት ቃለ-ተጠያቂ (RA1-ET-04-A)፤ ‹በሕፃናቱ የኑሮ ብልኀቶችን በሚማሩበት እና፤ ደኅንነታቸውን አስጠብቀው በይነ-መረብን መጠቀም በሚችሉበት አኳኋን ... ላይ መሥራት ይገባናል። በሥርዓተ-ትምህርቱ ወስጥ ያለው ይዘት ይህንን ጉዳይ እንዲያካትት መከለስ ግድ ይላል› በማለት ገልጸዋል።

52. Dione, O. (2021, March 21). Why Ethiopia Needs to Open its Telecom Market. World Bank Blogs.

**ምሰል 3. ተንከባካቢዎች ስለ በይነ-መረብ መረጃ ለማግኘት የሚመርጧቸው የመረጃ ምንጮች**




መደብ፡ በኢትዮጵያ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው የበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት ተንከባካቢዎች፤ ብዛት = 1 ሺህ ተንከባካቢዎች

ከመንግሥት ኃላፊዎች መካከል አንዱ ኃላፊ በኢትዮጵያ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ዙሪያ የሰፈነው የግንዛቤ እጦት የተፈጠረበትን መንሥኤ ሲያስረዱ፤ ‹በይነ-መረብ በሁሉም ቦታ እና ወደ እያንዳንዱ ቤተሰብ ያልተዳረሰ ስለሆነ፤ የበ/መ.ሕ/ወ/ብ/በደል እንደ ትልቅ ችግር አይታይም› ብለዋል (RA1-ET-03-A)፡፡ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሕፃናት ፍትሕ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ የሆኑት ሌላኛው ምላሽ ሰጪ (RA1-ET-06-A)፤ ‹የሚበዙት ሕፃናት በገጠር አካባቢዎች ስላሉ፤ በይነ-መረብ ቀርቶ ስልክ እንኳ የላቸውም› ብለዋል፡፡ ለበይነ-መረብ ተደራሽ በመሆን እና በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል መካከል ግልጽ ቁርኝት ያለ ቢሆንም፤ በዲጂታል፣ በበይነ-መረብ፣ ወይም በተግባቦት ቴክኖሎጂዎች አማካኝነት ለሚካሄድ የወሲብ ብዝበዛ እና በደል ተጋላጭ ለመሆን ግን አንድ ሕፃን የግድ በይነ-መረብን መጠቀም ላያስፈልገው እንደሚችል ማጤን ይገባል፡፡ ለምሳሌ፤ በአንድ ሕፃን ላይ የሚፈጸም የወሲብ በደልን በመቅረጽ በበይነ-መረብ ላይ እንዲሠራጭ ማድረግ፤ ልክ በደሉን በቀጥታ ሥርጭት የማስተላለፍ ድርጊት ላይ እንዳለው ሁሉ፤ ይህም በዲጂታል የታገዘ የበደል አድራጎት ተብሎ የሚቆጠር ነው፡፡ ስለዚህ፤ ምንም እንኳ አሁን ባለው ዝቅተኛ የበይነ-መረብ ተደራሽነት የተነሣ፤ *በራሱ* በበይነ-መረብ በኩል ለሚፈጸም (ለምሳሌ በወሲብ ተግባራት እንዲሳተፉ በማኅበራዊ ሚዲያ በኩል የገንዘብ መደለያ ለመስጠት ጥያቄ ማቅረብ የመሳሰለ) በደል፤ ከኢትዮጵያ ሕፃናት ውስጥ ያነሰ ድርሻ ያላቸው ብቻ መጋለጣቸውን ቢያሳየም፤ የበይነ-መረብ ተደራሽነት አለመኖር የበበይነ-መ ረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ሕፃናትን አያሰጋቸውም ማለት ግን አይደለም፡፡

# 1. በይነ-መረብን የሚጠቀሙ ሕፃናት በኢትዮጵያ

ትኩረት፤ ታዳጊ ወጣቶች እና ኃላፊነት-የተጣለባቸው ሰዎች፤ በዲጂታል ቴክኖሎጂዎች እገዛ ወይም አማካኝነት በሕፃናት ላይ ስለሚፈጸመው ብዝበዛ እና በደል ያላቸውን አተያይ ማቅረብ ነው። በኢትዮጵያ ያለውን የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል-ነክ ጥሰቶችን በተሻለ ለመገንዘብ፤ ጥሰቶቹን ሰፋ ያለ አድማስ ባለው በሕፃናት የበይነ-መረብ አጠቃቀም ውስጥ አስገብቶ ማየት ወሳኝነት አለው። በመሆኑም፤ በዚህ በመጀመሪያው የሪፖርቱ ምዕራፍ፤ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ባላቸው ዘንድ ስላለው የሕፃናት የበይነ-መረብ ተደራሽነት እና የበይነ-መረብ እንቅስቃሴ በተመለከተ አጭር ዳሰሳ የቀረበ ሲሆን፤ በመቀጥልም አስጊ የበይነ-መረብ ተግባራት ስለሚከሠቱበት ሁኔታ፤ እንዲሁም ሕፃናት እና ተንከባካቢዎቻቸው እነዚህን ስጋቶች እንዴት እንደሚያዩአቸው ተብራርቷል።

# 1.1 የበይነ-መረብ ተደራሽነት እና መሰናክሎች


እ.ኤ.አ. በ2011 ከነበረበት 1 በመቶ በመነሣት፤ እ.ኤ.አ. በ2019 በግምት 25 በመቶ ኢትዮጵያዊያን በይነ-መረብን ይጠቀሙ እንደነበር የዓለም-አቀፍ ቴሌኮሚዩኒኬሽኖች ኅብረት ያወጣው አኃዝ ያሳያል[53]። የበይነ-መረብ ተደራሽነቱ ላይ እመርታ ተመዝግቦ እያለም፤ በኢትዮጵያ ያለው የበይነ-መረብ ተደራሽነት አሁንም በጣም አነስተኛ እና ሃገሪቱ ከአገልግሎቱ ገና ያልተቋደሰ ዐያሌ የገጠር ሕዝብ የሚኖርባት፤ ብሎም የ3ጂ አገልግሎት በከተሞች ብቻ የሚሰጥ እና ይህ ጥናት በሚደረግበት ጊዜ የ4ጂ አገልግሎት ደግሞ በመዲናዋ ውስጥ የተወሰነ ነው[54]።

የ*ዲስረፕቲንግ ሀርም* የአባወራ/የቤተሰብ ዳሰሳ ጥናት እንደሚያሳየው፤ እ.ኤ.አ. ከ2021 አንሥቶ፤ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ካላቸው የኢትዮጵያ ሕፃናት መካከል 25 በመቶዎቹ የበይነ-መረብ ተጠቃሚ ናቸው፤ ወይም በቀደሙት ሦስት ወራት በይነ-መረብን ተጠቅመዋል ማለት ነው።[55፣56] የ12 እና 13 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ሕፃናት የበይነ-መረብ ተጠቃሚ የመሆን ዕድላቸው ከሁሉም ይባስ ያነሰ  ነበር፤ በዚህ የዕድሜ መደብ ውስጥ ካሉት ሕፃናት 8 በመቶዎቹ ብቻ በቀደሙት ሦስት ወራት የተጠቀሙ ሲሆን፤ በንጽጽር ሲታይ የ14 እና የ15 ዓመት ዕድሜ ካላቸው ውስጥ 19 በመቶዎቹ እንዲሁም የ16 እና የ17 ዓመት ዕድሜ ካላቸው መካከል ደግሞ 46 በመቶዎቹ የበይነ-መረብ ተጠቃሚዎች ናቸው። በጾታዎች መካከል ትልቅ ልዩነት የለም፤ ከወንድ ልጆች 28 በመቶዎቹ በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሲሆኑ፤ በአንጻሩ ልጃገረዶች የ21 በመቶ ድርሻ አላቸው። ጥሬ መረጃው በገጠር እና መካከል የማያሻማ ልዩነት እንዳለ ያሳያል፤ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ካላቸው የገጠር ሕፃናት ውስጥ 21 በመቶዎቹ ብቻ በይነ-መረብን የተጠቀሙ ሲሆን፤ ተመሳሳይ ዕድሜ ካላቸው የከተማ ሕፃናት መካከል ግን 45 በመቶዎቹ በይነ-መረብን ተገልግለዋል።

በዚህ ሪፖርት ላይ የቀረበው የተቀረው የዳሰሳ ጥናቱ ጥሬ መረጃ የተገኘው ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ካላቸው የበይነ-መረብ ተጠቃሚዎች መካከል በናሙናነት ከተመረጡት ሕፃናት ዘንድ ነው። 40 በመቶዎቹ በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት አዘውትረው የማይጠቀሙ፤ ማለትም በወር ከአንድ ጊዜ በታች የሚጠቀሙ ናቸው። ልክ በሌሎች ሃገራት እንዳለው፤[57] በዕድሜ የገፉት ሕፃናት፤ ማለትም 16 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው፤ ይበልጥ በመደጋገም የሚጠቀሙ እና፤ ከታናናሽ ሕፃናት ጋር ሲነጻጸር በየቀኑ ከበይነ-መረብ ጋር የሚገናኙበት ዕድል ይበልጥ የላቀ ነበር[58]። ምናልባት እንደሚጠበቀው፤ በገጠር ካሉ (26 በመቶ) እኩዮቻቸው ጋር ሲነጻጸር በከተሞች ያሉ በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት *በየቀኑ* (42 በመቶዎቹ) ከበይነ-መረብ ጋር ግንኙነት የሚያደርጉበት የላቀ ዕድል አላቸው።

በአባወራ/ቤተሰብ የዳሰሳ ጥናቱ ከተሳተፉት ተንከባካቢዎች ከ80 በመቶዎቹ በላይ በይነ-መረብን ጨርሶ ተጠቅመው አያውቁም፡፡ ዕድሜያቸው 29 ዓመት ወይም በታች የሆኑት ተንከባካቢዎች በዕድሜ ከሚበልጧቸው መሰሎቻቸው ጋር ሲነጻጸሩ፤ በይነ-መረብን በየቀኑ የመጠቀም የላቀ ዝንባሌ ነበራቸው (እንደ ቅደም ተከተላቸው 32 በመቶ እና 3 በመቶ)። ልክ በሕፃናት የበይነ-መረብ አጠቃቀም ላይ እንዳለው ሁሉ፤ በተንከባካቢዎች ዘንድም በጾታዎች መካከል ያለው የአጠቃቀም ድግግሞሽ ላይ እምብዛም የጎነነ መበላለጥ የለም። በትውልዶች/የዕድሜ መደቦች መካከል የዲጂታል ዕውቀት መበላለጥ መኖሩን የበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናቱ የታዘቡ ሲሆን፤ 73 በመቶዎቹ ከተንከባካቢዎቻቸው በተሻለ ስለ በይነ-መረብ እንደሚያውቁ ተናግረዋል (ምስል 4ን ይመለከቷል)። ምናልባት እንደሚጠበቀው፣ ከታናናሾቹ ይልቅ


**ምስል 4. ከተንከባካቢዎቻቸው በተሻለ ስለ በይነ-መረብ እንደሚያውቁ የተናገሩ ሕፃናት በዕድሜ እና በጾታ**




መደብ፡ በኢትዮጵያ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት፤ ብዛት = 1 ሺህ ሕፃናት

53. የዓለም-አቀፍ ቴሌኮሚዩኒኬሽኖች ኅብረት (ቀን አልተጠቀሰም) ስታትስቲክስ፤
54. Bekele, D. (2020, March 4). The First Ethiopia Internet Development Conference: Meeting challenge and opportunity head on.*Internet Society.*
55. በዋናው ዳሰሳ ላይ የሚሳተፉትን ተገቢውን ሕፃናት ለመለየት በነሲብ እግር እንደጣለ (random walk) ዘዴ የናሙና አመራረጥ የተካሄደ ሲሆን፤ ጉብኝት ከተካሄደበት ከእያንዳንዱ አባወራ/ቤተሰብ ውስጥ፤ በቤቱ የሚኖሩ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ሕፃናት ብዛትን፣ ጾታቸውን፣ ዕድሜያቸውን፣ እና በባለፉት ሦስት ወራት በይነ-መረብን ተጠቅመው እንደሆነ ጥሬ መረጃ ተሰብስቧል። ይህም ዕድሜቸው ከ12 እስከ 17 ዓመት በሆኑት በመላው የኢትዮጵያ  ሕፃናት ዘንድ ያለውን የበይነ-መረብ ተደራሽነት መጣኔ ለመገመት ያስችላል። ብዛት = 5 ሺህ 938 አባወራዎች/ቤተሰቦች
56. ዕድሜው/ዋ ከ12 እስከ 17 ዓመት ውስጥ ያለ/ች፤ በይነ-መረብ ተጠቃሚ መሆኑ/ኗን ለማወቅ የቀረበው ጥያቄ፤ በባለፉት ሦስት ወራት ውስጥ በይነ-መረብን ተጠቅመህ/ሽ ታውቃለህ/ቂያለሽ? ይህም፤ የተንቀሳቃሽ ስልክ ቀፎን፣ ታብሌትን፣ ወይም ኮምፒዩተርን በመጠቀም መልእክቶችን መላክ ወይም መቀበል፤ እንደ ፌስቡክ፣ ዋትስአፕ፣ እና ኢንስታግራም ያሉ መተግበሪያዎችን (applications) መጠቀም፤ ኢሜይሎችን መላክ፣ ከጓደኞች እና ከቤሰተሰብ ጋር አጭር መልእክቶችን መላላክ፣ ፋይሎችን መጫን እና ማውረድ፣ ወይም አዘውትረህ/ሽ በይነ-መረብ ላይ የምትሠራው/ሪው ሌላ ነገር የሚሉትን ሊጨምር ይችላል።
57. Global Kids Online. (n.d.). Global Kids Online.
58. Global Kids Online. (n.d.). Global Kids Online.

**ምስል 5፡ ከሕፃናቶቻቸው በተሻለ ስለ በይነ-መረብ እንደሚያውቁ የተናገሩ ተንከባካቢዎች በዕድሜ እና በጾታ**




መደብ፡ በኢትዮጵያ ዕድሜያቸው ከ12 እስከ 17 ዓመት የሆኑ የበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት ተንከባካቢዎች፤ ብዛት = 156 ተንከባካቢዎች

ዕድሜያቸው የገፉት ሕፃናት ይህንን ዓይነት ምላሽ የሚሰጡበት አጋጣሚ የላቀ ነበር። በተቃራኒው፤ 41 በመቶዎቹ ተንከባካቢዎች ከሕፃናቶቻቸው በተሻለ ስለ በይነ-መረብ እንደሚያውቁ ተናግረዋል፡ ፡ በዕድሜ ከሚበልጡት መሰሎቻቸው ይልቅ በወጣትነት ዕድሜ ያሉት ተንከባካቢዎች ይህንን ምላሽ የሚሰጡበት አጋጣሚ በጣም ከፍ ያለ ነበር (ምስል 5ን ይመለከቷል)። በዕድሜ የገፉ ተንከባካቢዎች በዲጂታል ከባቢ ውስጥ የሚያደርጉት መስተጋብር ውሱን ከመሆኑ አንጻር፤ የሕፃናቶቻቸውን የበይነ-መረብ አጠቃቀም ለማረቅ እና ስጋቶችን ለማርገብ እንዲቻል፤ ከትምህርት ቤቶች እና ከሌሎች ባለድርሻዎች የሚበረከተውን ጨምሮ ምን ዓይነት ድጋፍ እንደሚያሻቸው እሳቤ ውስጥ ማስገባት ያሻል።

በ*ዲስረፕቲንግ ሀርም* አባወራ/ቤተሰብ የዳሰሳ ጥናት አማካኝት የተሰበሰበው ጥሬ መረጃ እንደሚያሳየው፤ ልክ በብዙዎች ሌሎች ሃገራት እንዳለው በኢትዮጵያም፤ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ባላቸው በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት (98 በመቶዎቹ) ዘንድ እጅግ የሚመረጠው መገልገያ የስማርት ስልክ ቀፎ ሲሆን፤ ምክንያቱ ደግሞ በአንጻራዊነት ዋጋቸው ስለሚረክስ እና ለአያያዝ ስለሚቀልጥፉ ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታል[59]። እንደ ኮምፒዩተር (5 በመቶ) እና ታብሌት (2 በመቶ) ያሉ ሌሎች ዓይነት መገልገያዎች ያላቸው ድርሻ እጅግ ያነሰ ነው። በሦስቱም ዓይነት መገልገያዎች ላይ በዕድሜ ወይም በጾታ ዘርፎች ላይ የሚታይ እምብዛም የጎላ ልዩነት የለም። ከኢትዮጵያ በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት መካከል በርካቶቹ በይነ-መረብ የሚጠቀሙበትን መገልገያ/ቀፎ ከሌሎች ጋር በጋራ ወይም በደባልነት የሚጠቀሙ ሳይሆን መገልገያውን በባለቤትነት የያዙ ናቸው። የስማርት ተንቀሳቃሽ ስልክ ቀፎ ባለቤት ከሆኑት ሕፃናት መካከል 40 በመቶዎቹ፤ ስማርት ቀፎውን ሌላ ሰው በደባልነት እንዲጠቀምበት አጋርተዋል። በዕድሜ ከገፉት (16-17 ዓመት) እና ከወንድ ልጆች ጋር ሲነጻጸር፤ በዕድሜ ያነሱት ሕፃናት (12-13 ዓመት) እና ልጃገረዶች ስማርት ቀፏቸውን ለሌላ ሰው የማጋራት ዝንባሌያቸው ያመዝን ነበር። በኢትዮጵያ መገልገያን የመጋራት መጣኔ በቀጣናው/ክፍለ-አህጉሩ ውስጥ ባሉ ሌሎች ሃገራት ላይ ከተመዘገበው አኃዝ ያነሰ ነው። የዚህ አንዱ ምክንያት

የኢትዮጵያ የበይነ-መረብ ተደራሽነት በአንጻራዊነት ዝቅተኛ መሆኑ፤ እንዲሁም ከፍተኛ የተደራሽነት መበላለጥ መኖሩ፤ ምናልባትም በናሙናነት የተመረጡት በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት ከፍ ያለ ገቢ ካላቸው ቤተሰቦች የመጡትን ስለሚወክል ሊሆንም ይችላል።

ከጠቅላላው ሕዝብ ውስጥ የተንቀሳቃሽ ስልክ ካርድ ያላቸው ኢትዮጵያዊያን ድርሻ እ.ኤ.አ. በ2008 ከነበረበት 2 በመቶ ተነሥቶ እ.ኤ.አ. በ2017 ላይ 37 በመቶ[60] የደረሰ ቢሆንም፤ በኢትዮጵያ የሕፃናትን የበይነ-መረብ አጠቃቀም አሁንም ውሱን እንዲሆን የሚያድጉ እንቅፋቶች አሉ። 40 በመቶዎቹ የበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት፤ በፈለጉበት ጊዜ ወይም ሲያሻቸው በይነ-መረብን እንዳይጠቀሙ የሚያግዳቸው እንደ ቀርፋፋ መስመር ወይም ደካማ ሞገድ የመሳሰሉ የመሠረተ-ልማት ማነቆዎች መሆኑን ጠቅሰዋል፡ ፡ ከዚህኛው በቅርብ ርቀት ተከትሎ ያለው ማነቆ ደግሞ የዋጋ ውድነት ነው። ምንም እንኳ ኢትዮ ቴሌኮም እ.ኤ.አ. በ2019 ላይ ተከታታይ የዋጋ ቅናሽን አድርጎ የነበረ ቢሆንም፤ በ‹ኢንተርኔት ሶሳይቲ› ሪፖርት ላይ የተገለጹ ግኝቶች ግን የበይነ-መረብ ዋጋ ከአብዛኞቹ ኢትዮጵያዊያን የመግዛት አቅም በላይ መሆኑን ሪፖርቱ ጠቁሟል[61]።

በዕድሜ ካነሱት ሕፃናት ጋር ሲነጻጸር፤ 16 እና 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው በበይነ-መረብ አጠቃቀም ከተደቀኑት መሰናክሎች ውስጥ የሚበዙትን የመጋፈጥ ዕድላቸው የሰፋ ነበር፤ በተለይም ቀርፋፋ መስመር እና የዳታ (የተንቀሳቃሽ ስልክ የበይነ-መረብ አገልግሎት) ውድነት። የዚህ መንሥኤ ምናልባት በዕድሜ ካነሱት ይልቅ ታላላቆቹ ሕፃናት በይነ-መረብን በተደጋጋሚ የመጠቀም ወይም በበይነ-መረብ ላይ ሰፋ ያሉ እንቅስቃሴዎችን የማድረግ ፍላጎት ስላላቸው፤ ይህም የዳታ ፍጆታቸውን ስለሚጨምረው ነው።

በተቃራኒው፤ በዕድሜ ያነሱት ሕፃናት በተንከባካቢዎቻቸው እና በመምህሮቻቸው አማካኝነት አብዛኛውን ጊዜ በበይነ-መረብ አጠቃቀማቸው ላይ ገደብ ይደረግባቸዋል። በተንከባካቢዎች አማካኝነት ስለሚደረግባቸው ገደብ በተመለከተ፤ ከወንድ ልጆች (10 በመቶ) ይልቅ ስለ ገደቡ በተደጋጋሚ በልጃገረዶች (22 በመቶ)

59. Livingstone, S., Kardefelt Winther, D., & Saeed, M. (2019). Global Kids Online Comparative Report. Innocenti Research Report. UNICEF Office of Research - Innocenti, Florence.
60. International Telecommunications Union. (n.d.). Country ICT data until 2018 - Mobile Cellular Subscriptions.
61. Bekele, D. (2020, March 4). The First Ethiopia Internet Development Conference: Meeting challenge and opportunity head on.*Internet Society.*

የተጠቀሰ፤ እና በመምህራን የሚደረገው ዕቀባም ተመሳሳይ ቅኝትን የተከተለ ነበር (ወንድ ልጆች 5 በመቶ፤ ልጃገረዶች 15 በመቶ)። ይህ የሚያሳየው፤ ልጃገረዶች ከጅምሩ በይነ-መረብን የመጠቀም ዕድላቸው መጥበቡን ብቻ ሳይሆን፤ እየተጠቀሙ ያሉትም እንኳ በአግባቡ እንዳይጠቀሙ እላፊ ገደቦች ይገጥሟቸው እንደነበረ ነው።

### የሕፃናትን የበይነ-መረብ ተደራሽነትን መገደብ መፍትሔ ይሆናል?

በርካታ ተንከባካቢዎች ሕፃናቶቻቸውን ከበይነ-መረብ ስጋቶች ለመጠበቅ ሲሉ የበይነ-መረብ አጠቃቀማቸው ላይ ዕቀባ ይጥላሉ። በኢትዮጵያ ይህን መሰል *ገዳቢ አሠራሮችን* (restrictive practices) መጠቀም በጣም የተለመደው አካሄድ ሆኖ ይታያል። በዳሰሳ ጥናቱ ከተሳተፉት በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት መካከል 32 በመቶዎቹ ማኅበራዊ ሚዲያን መጠቀም፤ 37 በመቶዎቹ ደግሞ በበይነ-መረብ ቪዲዮዎችን መመልከት እንደማይፈቀድላቸው የገለጹ ሲሆን፤ 15 በመቶዎቹ ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ ተንከባካቢዎቻቸው የበይነ-መረብ ቆይታቸው ላይ የጊዜ ወሰን እንደሚጥሉባቸው ተናግረዋል። ከተንከባካቢዎች መካከል፤ 16 በመቶዎቹ ልጃቸው በበይነ-መረብ ላይ ባየው ነገር ከተረበሸ በልጃቸው የበይነ-መረብ አጠቃቀም ላይ ገደብ እንደሚያደርጉ፤ 20 በመቶዎቹ ደግሞ ልጃቸውን እንደሚቀጡ ተናግረዋል።

ገዳቢ አሠራሩ ሕፃናት ለበይነ-መረብ ስጋቶች የሚጋለጡበትን ቅርበት ሊቀንስ ይችላል፤ ሆኖም የዲጂታል ክህሎታቸውን እና ከበይነ-መረብ ከባቢ ጋር የሚኖራቸውን ተላምዶ ግን አብሮ እንዲያሽቆለቁል ያደርገዋል። በሌላ በኩል፤ በበይነ-መረብ ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ አዋቂዎች ለሕፃናት የሚያደርጉት *አጋዥ መስተጋብር* (supportive engagement)፤ በሌሎች ሃገራት ባሉ ሕፃናት ላይ አዎንታዊ የክህሎት ዕድገትን የመፍጠር ሚናው አብሮ ይነሣል[62]a ፡

አጋዥ መስተጋብር (ከሕፃናቶቻቸው ባነሰ በይነ-መረብን በሚጠቀሙ ተንከባካቢዎችም ጭምር ሊተገበር ይችላል) የሚባለው፤ በበይነ-መረብ የሚካሄዱ ነገሮችን ከሕፃናቱ ጋር አብሮ ማድረግ፣ ስለ በይነ-መረብ አጠቃቀማቸው ሕፃናቱን ማዋራት፣ እንዲሁም በበይነ-መረብ ላይ ስላሉት ስጋቶች እና መመከቻ ዘዴዎች ማስተማር የመሳሰሉትን ሊጨምር ይችላል። በእነዚህ መንገዶች አማካኝነት የበይነ-መረብ ስጋቶችን ተረማምደው ጉዳት ሳያገኛቸው እንዲቀጥሉ አቅጣጫ እና ድጋፍ በመስጠት፤ በይነ-መረብ ከሚለግሳቸው በርካታ አዎንታዊ ነገሮች ሕፃናት እንዲቋደሱ ማድረግ እንችላለን።

62. Livingstone, S., Kardefelt Winther, D., & Saeed, M. (2019). Global Kids Online Comparative Report. Innocenti Research Report. Florence: UNICEF Office of Research - Innocenti.

# 1.2 የሕፃናት እንቅስቃሴ በበይነ-መረብ

**ስለ ዲጂታል ተሞክሮዎቻቸው ወይም ገጠመኞቻቸው ይበልጥ ማወቅ እንዲቻል፤ ሕፃናቱ ማድረግ ስለሚወዷቸው ነገሮች ተጠይቀው ነበር (ምስል 6ን ይመለከቷል)፡፡ ማኅበራዊ ሚዲያን መጠቀም፣ ፍጡን መልእክት መላላኪያን መጠቀም (instant messaging)፣ እንዲሁም ከቤሰተብ እና ከጓደኞች ጋር ማውራት የመሳሰሉ ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች በኢትዮጵያ በይነ-መረብን በሚጠቀሙ ሕፃናት ዘንድ እጅግ የሚዘወተሩ ተግራት ናቸው፡፡ ከላይ የቀረበው አባባል፤ እነዚህ በየፈርጁ ተከፋፍለው የቀረቡ ተግባራት አንዱ ከአንዱ የማይቀላቀሉ እና በተናጠል የሚታዩ ብቻ ተደርጎ ሊታይ እንደማይገባ ማጤን ያስፈልጋል፤ ለምሳሌ አንድ ሕፃን በትምህርት ቤቱ የታዘዘች/ውን ለመሥራት እንዲያግዘው/ዛት በበይነ-መረብ አማካኝነት ቪዲዮ ሊ/ትመለከት ይችላል፡፡ ለማንኛውም፤ በኢትዮጵያ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ልጆች በይነ-መረብን ስለሚጠቀሙበት ሁኔታ እና ስለሚያዝናኗቸው ተግበራት ይበልጥ ለመረዳት በሚያስችል አገላለጽ ከታች የቀረበውን ምስል 6ን ይመልከቱ፡፡ በንጽጽር ሲታይ በበይነ-መረብ የሚደረግ የጨዋታ ግጥሚያ (online gaming) ኢምንት ነው[63]፡፡ የተለመዱት የበይነ-መረብ አጠቃቀም ማነቆዎች (ለምሳሌ የዳታ አገልግሎት ክፍያ ከፍተኝነት እና ቀርፋፋ መስመር) ሕፃናቱ ከባድ ሞገድ (bandwidth) በሚጠይቀው በዚህ ዓይነቱ የጨዋታ ግጥሚያ ላይ ያልተሠማሩበት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡**

ሌላኛው ምክንያት ሊሆን የሚችለው፤ 50 በመቶዎቹ ሕፃናት ከሌሎች ሰዎች ጋር በበይነ-መረብ ለመጫወት/ለመጋጠም ተንከባካቢዎቻቸው እንደማይፈቅዱላቸው የገለጹት ጉዳይ ነው፡፡

ከማኅበራዊ ሚዲያ እና ከፍጡን መልእክት መላላኪያዎች (ይበልጡኑ በዕድሜ በገፉት ሕፃናት የሚወደድ) ላይ ከሚታየው ልዩነት ውጪ፤ በሁሉም የዕድሜ መደቦች ላይ ያሉ ሕፃናት በሚያደርጓቸው የበይነ-መረብ ተግባራት ዓይነቶች ላይ እምብዛም ልዩነት የለም፡፡ ይሄ ግኝት አሁንም እንደገና፤ በሌሎች ሃገራት ከተገኘው ውጤት ጋር የተራራቀ ነው፡፡ በሌሎች ሃገራት ያለው ግኝት፤ ከታናናሾቹ ጋር ሲነጻጸር በዕድሜ የገፉት ሕፃናት ሰፋ ባሉ የበይነ-መረብ ተግባራት ላይ የሚሠማሩበት አጋጣሚ የላቀ ነበር፡፡

**ምስል 6. በይነ-መረብን በሳምንት ቢያንስ አንዴ የሚጠቀሙ ሕፃናት የሚያደርጉት ተግባራት**

| የበይነ-መረብ ተግባራት | ድምር | 12–13 | 14–15 | 16–17 | ወንድ ልጆች | ልጃገረዶች |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማኅበራዊ ሚዲያ የተጠቀሙ | 44% | 24% | 35% | 53% | 47% | 40% |
| ፍጡን የመልእክት መላላኪያን የተጠቀሙ | 34% | 26% | 29% | 38% | 34% | 35% |
| በሩቅ ቦታ ከሚኖሩ ቤተሰቦች እና ጓደኞች ጋር የተነጋገሩ | 27% | 25% | 21% | 30% | 25% | 30% |
| ቪዲዮዎችን የተመለከቱ | 26% | 33% | 21% | 26% | 28% | 22% |
| አዳዲስ መረጃዎችን ለማፈላለግ የተጠቀሙበት | 24% | 11% | 20% | 28% | 25% | 21% |
| የትምህርት ቤት ሥራ | 20% | 10% | 18% | 24% | 21% | 19% |
| ዜና ለማግኘት የተጠቀሙበት | 20% | 19% | 13% | 23% | 23% | 14% |
| ሰዎች አስተያየቶቻቸውን በሚያጋሩበት ድረ-ገጽ ላይ የተሳተፉ | 20% | 13% | 15% | 23% | 21% | 18% |
| ዝነኛ እና ስመ-ጥር ሰዎችን በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ የተከተሉ | 18% | 15% | 18% | 19% | 20% | 15% |
| የጤና መረጃዎችን ለማፈላለግ የተጠቀሙበት | 16% | 13% | 17% | 17% | 17% | 14% |
| የሥራ እና የትምህርት ዕድሎችን የተመለከቱ መረጃዎችን ለማፈላለግ የተጠቀሙበት | 15% | 9% | 13% | 17% | 15% | 14% |
| በሰፈራቸው አካባቢ ስለሚካሄዱ ኩነቶች/ዝግጅቶች ወይም መረጃዎችን ለማፈላለግ የተጠቀሙበት | 14% | 7% | 14% | 15% | 17% | 9% |
| ስሜታቸውን የሚያጽናና ነገር ለማግኘት የተጠቀሙበት | 13% | 11% | 12% | 15% | 14% | 12% |
| ቀጥታ ሥርጭቶችን የተመለከቱበት | 13% | 7% | 12% | 14% | 13% | 12% |
| በበይነ-መረብ ግጥሚያዎችን የተጫወቱ | 10% | 16% | 12% | 9% | 11% | 8% |
| ፖለቲካዊ እና ማኅበራዊ ችግሮችን የተወያዩ | 8% | 6% | 7% | 10% | 9% | 8% |
| ጦማር ወይም ድረ-ገጽ የከፈቱ | 6% | 4% | 5% | 6% | 6% | 4% |
| የራሳቸውን ቪዲዮ ወይም ሙዚቃ ያስተላለፉ | 5% | 5% | 6% | 5% | 5% | 4% |

መደብ፡ በኢትዮጵያ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት፤ ብዛት = 1 ሺህ ሕፃናት

63. Livingstone, S., Kardefelt Winther, D., & Saeed, M. (2019). Growing up in a Connected World. Innocenti Research Report. Florence: UNICEF Office of Research - Innocenti.

# 1.3 አስጊ የበይነ-መረብ ተግባራትን የተመለከቱ አተያዮች እና ተሞክሮዎች

**ስለ በይነ-መረብ ስጋቶች የሚደረጉ ውይይቶች አብዛኛውን ጊዜ ከአዋቂዎች እሳቤ ወይም አተያይ (perception) አንጻር የተቃኙ ናቸው። የሕፃናቱንም አተያይ  መረዳታችንን ለማረጋገጥ፤ ሕፃናት እና ተንከባካቢዎቻቸው በተለያዩ አደጋ-አማጪ የበይነ-መረብ ተግባራት ላይ ስለነበራቸው ተሳትፎ እና በሂደቱም የታዘቡትን እንዲያካፍሉ ተጠይቀው ነበር።**

## 1.3.1 በበይነ-መረብ እና በአካል ከባይተዋሮች ጋር ግንኙነት መመሥረት


በሚበዙት የበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት እና በተንከባካቢዎቻቸው በጋራ የተገለጸው ስጋት፤ የማይታወቁ ሰዎች ሕፃናትን በበይነ-መረብ በኩል ሊያገኟቸው የሚችሉበትን ተጋላጭነት ነው። ከተለያዩ የበይነ-መረብ አጠቃቀም ተግባራት/ጠባያት መካከል አስጊ የሚሉትን በደረጃ እንዲያስቀምጡ ለቀረበላቸው ጥያቄ፤ 52 በመቶዎቹ ተንከባካቢዎች እና 26 በመቶዎቹ ሕፃናት አስቀድሞ በፍጹም በአካል አግኝተው ከማያውቁት ሰው ጋር በበይነ-መረብ መነጋገር ለሕፃናት ‹እጅግ አደገኛ› የሆነ ጉዳይ መሆኑን አስቀምጠዋል። በተገላቢጦሹ፤ 34 በመቶዎቹ ሕፃናት ድርጊቱ ጨርሶ አስጊ እንዳልሆነ የገለጹ ሲሆን፤ 16 በመቶዎቹ ደግሞ ይሄን ማድረግ አደገኛ አካሄድ ስለመሆኑ ወይም አለመሆኑ እርግጠኛ አይደሉም።

በተመሳሳይ፤ የግል መረጃዎቻቸውን (ለምሳሌ ሙሉ ስም፣ አድራሻ፣ ወይም ስልክ ቁጥርን) ከዚህ በፊት ፈጽሞ በአካል አግኝተውት ለማያውቁት ሰው የላኩ ሕፃናት ‹እጅግ አደገኛ› የሚያሰኝ ድርጊት እንደፈጸሙ የሚቆጠር ስለመሆኑ 69 በመቶዎቹ ተንከባካቢዎች እና 39 በመቶዎቹ በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት በጋራ የሚስማሙበት ጉዳይ ሲሆን፤ ነገር ግን 25 በመቶዎቹ ሕፃናት ይህንን ማድረግ ጨርሶ እንደማያሰጋ፤ 12 በመቶዎቹ ደግሞ ድርጊቱ አስጊ ስለመሆኑ ወይም አለመሆኑ እርግጠኛ እንዳልሆኑ ተናግረዋል። በዕድሜ ከገፋት ይልቅ በዕድሜ ያነሱት ሕፃናት፤ ይህ ድርጊት እንደማያሰጋ የሚገልጹበት አጋጣሚ ከፍ ያለ ነበር። ከማያውቁት እና ለመጀመሪያ ጊዜ በበይነ-መረብ ከተዋወቁት ሰው ጋር በአካል/በፊትለፊት የሚደረግ ግንኙነት ‹እጅግ አደገኛ› ስለመሆኑ፤ በ57 በመቶዎቹ ተንከባካቢዎች እና በ30 በመቶዎቹ በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት ዘንድ ይታመናል። ሆኖም ሌሎቹ 28 በመቶ ሕፃናት ድርጊቱ ‹ምንም አያሰጋም› የሚል ዕይታ ነበራቸው። እነዚህ ድርጊቶች መጥፎ ጠባሳ አስከትለው የሚያልፉበትን አጋጣሚ ለመቀነስ እንዲቻል፤ ስለእነዚህ አደጋ-ጋባዥ ጠባያት የሰዎችን ግንዛቤ የማሳደግ ሥራ ማስፈለጉን ከተጠቀሱት አኃዞች መገንዘብ ይቻላል።

የሕፃናቱ አተያይ/አረዳድ ከአጠቃቀም ጠባያቸው ጋር እንዴት ይመሳሰላል? በባለፈው ዓመት፤ 42 በመቶ ሕፃናት ከዚህ በፊት በፍጹም አግኝተዋቸው የማያውቋቸውን ሰዎች ወደ አድራሻ ቋታቸው ውስጥ ያስገቡ ሲሆን፤ በተጨማሪም 25 በመቶ ሕፃናት ከዚህ በፊት ጨርሶ ገጽ-ለገጽ ተገናኝተው ለማያውቁት ሰው የግል መረጃዎቻቸውን አጋርተዋል።

ከዚህ ባለፈ፤ ‹‹በባለፈው ባለው ጊዜ ውስጥ፤ አስቀድሞ በበይነ-መረብ የተዋወቅከ/ሽው ሰው ጋር ገጽ-ለገጽ ተገናኝተህ/ሽ ታውቃለህ/ቂያለሽ ወይ?››[64]የሚል ጥያቄ ለበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት ቀርቦላቸው ነበር። 18 በመቶዎቹ (ብዛት = 183) አዎ ሲሉ በጥያቄው የተጠቀሰውን ማድረጋቸውን አረጋግጠዋል።

**ምስል 7፤ ከማያውቋቸው ሰዎች ጋር መነጋገር ስላለው አደጋ የሕፃናቱ አረዳድ እና፤ በባለፈው ዓመት ባይተዋሮችን በአድራሻ ቋታቸው በመዘገቡ ሕፃናት መካከል ያለው ቁርኝት**




መደብ፡ በኢትዮጵያ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት፤ ብዛት = 1 ሺህ

ቁጥራቸው 193 ከሚሆኑት ከእነዚህ ሕፃናት መካከል፤ እጅግ

64. Livingstone, S., Kardefelt Winther, D., & Saeed, M. (2019). Growing up in a Connected World. Innocenti Research Report. Florence: UNICEF Office of Research - Innocenti.


### ምስል 8፡ የግል መረጃቸውን ለማይታወቁ ሰዎች ማጋራት ስላለው አደጋ የሕፃናቱ አረዳድ እና፤ በባለፈው ዓመት በዚህ መሰል ጠባይ የተሠማሩ ሕፃናት መካከል ያለው ቁርኝት

**የግል መረጃዎችን (ለምሳሌ ሙሉ ስማቸውን፣ አድራሻቸውን፣ ወይም ስልክ ቁጥራቸውን) ከዚህ ቀደም ፈጽሞ ገጽ-ለገጽ አግኝተው ለማያውቁት ሰው መላክ**




**%** ይህ ድርጊት በእነርሱ ዕድሜ ላሉ ሕፃናት ‹በጣም አደገኛ› መሆኑን የገለጹ ሕፃናት - 39 በመቶ

**የግል መረጃዎቼን (ለምሳሌ ሙሉ ስሜን፣ አድራሻዬን፣ ወይም ስልክ ቁጥሬን) ከዚህ ቀደም ፈጽሞ ገጽ-ለገጽ አግኝቼው ለማላውቅ ሰው ልኬያለሁ**




**%** በባለፈው ዓመት ይህንን ያደረጉ ሕፃናት - 25 በመቶ

መደብ፡ በኢትዮጵያ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት፤ ብዛት = 1 ሺህ

### ምስል 9፡ አስቀድሞ በበይነ-መረብ የተዋወቁትን ሰው በአካል ማግኘት ስላለው አደጋ የሕፃናቱ አረዳድ እና፤ በባለፈው ዓመት በዚህ መሰል ጠባይ የተሠማሩ ሕፃናት መካከል ያለው ቁርኝት

**አስቀድሞ በበይነ-መረብ ከተዋወቁት ሰው ጋር በአካል ወይም ገጽ-ለገጽ መገናኘት፤**




% ይህ ድርጊት በእነርሱ ዕድሜ ላሉ ሕፃናት ‹በጣም አደገኛ› መሆኑን የገለጹ ሕፃናት - 30 በመቶ


**በባለፈው ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ፤ አስቀድሞ በበይነ-መረብ ከተዋወቅከ/ሽው ሰው ጋር ገጽ-ለገጽ ተገናኝተህ/ሽ ታውቃለህ/ቂያለሽ?**




**%** በባለፈው ዓመት ይህ ድርጊት የፈጸሙ ሕፃናት - 18 በመቶ

መደብ፡ በኢትዮጵያ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት፤ ብዛት = 1 ሺህ

**አስቀድሞ በበይነ-መረብ ከተዋወቁት ሰው ጋር ገጽ-ለገጽ ከተገናኙበት አጋጣሚዎች ውስጥ የቅርቡ ወይም የመጨረሻው አጋጣሚን በተመለከተ የሕፃናቱ ስሜት**




መደብ፡ በባለፈው ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ፤ አስቀድሞ በበይነ-መረብ ከተዋወቁት ሰው ጋር ገጽ-ለገጽ የተገናኙ በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት፤ ብዛት = 183 ሕፃናት

ብዙኃኑ፤ ድርጊታቸውን በአዎንታዊ እንደሚመለከቱት እና፤ አስቀድሞ ከማያውቁት ሰው ጋር መገናኘት ጉዳት የማስከተል ዕድሉ በአንጻራዊነት ዝቅተኛ መሆኑን አመልክተዋል። እጅግ ብዙዎቹ (ከ80 በመቶ የሚልቁት ወይም በቁጥር 146) ያደረጉት ግንኙነት የደስታ ስሜት እንዳሳደረባቸው፤ 14 በመቶዎቹን ደግሞ እንዳስፈነጠዛቸው ገልጸዋል (ምስል 10ን ይመለከቷል)። ከወንድ ልጆች ይልቅ ልጃገረዶች መሰል ድርጊቶችን የመፈጸም ዝንባሌያቸው አናሳ ነበር። በዓለም ዙሪያ ባሉ ከ30 በሚበልጡ ሃገራት ላይ የተካሄደው ጥናት፤ ከዚህ ጋር የሚመሳሰሉ ግኝቶችን ያንጸባርቃሉ።[65],[66]ሆኖም በእነዚህ ሁኔታዎች አማካኝት አደጋ ቢከሰት፤ ጉዳቱ እጅግ አስከፊ ይሆናል፡ ፡ እንደነዚህ የመሰሉ ትውውቆች ዓይነታቸው የተለያየ እና በርካታ ናቸው፤ ለምሳሌ ወደ ማኅበረሰቡ ከመጣ/ች አዲስ ሕፃን ጋር የሚመሠረት ግንኙነት ወይም ሕፃናት ተንከባካቢዎቻቸውን ተከትለው ሰዎች በተሰበሰቡበት ዝግጅት/ኩነት ላይ ሲታደሙ። ሆኖም እነዚህ ግንኙነቶች ወይም ትውውቆች ክፉ ሐሳብ ካላቸው አጥፊዎች ጋርም ሊሆን ይችላል። ሕፃናትን እና ተንከባካቢዎቻቸውን ስለ እነዚህ አደጋዎች ማስተማር ወሳኝ ነው።

## 1.3.2 በበይነ-መረብ ወሲባዊ ይዘቶችን መመልከት

የአባወራ/ቤተሰብ የዳሰሳ ጥናቱ ሲካሄድ፤ በበይነ-መረብ አማካኝነት ወሲባዊ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን መመልከት ለሕፃናት በጣም አደገኛ መሆኑን፤ በ58 በመቶዎቹ ሕፃናት እና በ81 በመቶዎቹ ተንከባካቢዎች ተገልጿል። በተመሳሳይ፤ በኢትዮጵያ ያሉ ግንባር ቀደም ሠራተኞች ለበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የሚያጋልጡ የስጋት መንሥኤዎችን እንዲዘረዝሩ ወይም እንዲመርጡ በተጠየቁ ጊዜ፤ ሁሉም 33 ምላሽ ሰጪዎች የብልግና ቁሳቁሶች ሥርጭት እና ከቁሳቁሶቹ ጋር የመገጣጠም ዕድል መኖሩ፤ የሕፃናትን የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ተጋላጭነት ጨምሮታል።

የአባወራ/ቤተሰብ የዳሰሳ ጥናቱ እንደሚያመለክተው፤ በኢትዮጵያ ካሉ ሕፃናት አንድ-ሦስተኛው በባለፈው ዓመት ውስጥ ቢያንስ አንዴ ወሲባዊ ይዘቶችን በበይነ-መረብ ተመልከተዋል። ከአምስቱ ሕፃናት አንዳቸው ያለማንም ጎትጓች በራሳቸው ተነሣሽነት ወሲባዊ ምስሎችን እና ቪዲዮዎችን በበይነ-መረብ ሲያፈላልጉ ወይም ትዕዛዝ-ፍለጋ (internet search) ሲያካሂዱ እንደነበር፤ 27 በመቶዎቹ ደግሞ ይህን መሰል ይዘት በበይነ-መረብ ላይ በድንገት አጋጥሟቸው መመልከታቸውን ገልጸዋል። በድንገተኛ ግጥምጥም ወሲባዊ ይዘቶችን ከተመለከቱ ሕፃናት መካከል፤ ከአንድ-ሦስተኛው የሚበልጡት ይህን መሰሉ ይዘት የገጠማቸው በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ መሆኑን (35 በመቶ)፣ 17 በመቶዎቹ በቀጥታ መልእክት (ላኪው እና ተቀባዩ ብቻ በሚያዩት መላላኪያ) አማካኝነት እንደተላከላቸው፣ 18 በመቶዎቹ በበይነ-መረብ ላይ ባሉ ማስታወቂያዎች የተነሣ እንዳዩ፣ እንዲሁም 13 በመቶዎቹ በበይነ-መረብ ላይ ፍለጋዎችን ሲያካሂዱ እንደተገጣጠሙ አስታውቀዋል። በዕድሜ ከሚያንሱት ይልቅ በዕድሜ የገፉት ሕፃናት በማስታወቂያዎች አማካኝነት ወሲባዊ ይዘቶችን የመመልከት አጋጣሚያቸው ከፍ ያለ ነበር። ከወንድ ልጆች ይልቅ በቁጥር የሚልቁ ልጃገረዶች በበይነ-መረብ ላይ ወሲባዊ ይዘቶችን በድንገት ስለማየታቸው ገልጸዋል (29 በመቶ ልጃገረዶች፤ 23 በመቶ ወንድ ልጆች)።

## 1.3.3 ግለ-ቀረጽ ወሲባዊ ይዘቶችን ማዘጋጀት እና ለሌሎች ማጋራት


በዳሰሳ ጥናቱ የተሳተፉት አብዛኞቹ ሕፃናት እና ተንከባካቢዎች፤ ‹‹አንድ ሰው ዕርቃኑን ሆኖ የሚያሳዩ ፎቶዎችን ወይም ቪዲዮዎችን በገዛ ራሱ ማንሣት ወይም መቅረጽ የተሳሳተ ተግባር ነው›› ብለው

65. ይህ ጥያቄ ዘርፈ-ብዙ ሁኔታዎችን ያቀፈ ነው፤ ሕፃኑ ከበይነ-መረብ ውጪ ከተዋወቃቸው የሩቅ ዘመድ-አዝማዶች ወይም መጀመሪያ በበይነ-መረብ ከተገናኛቸው የጓደኛ ጓደኞች አንሥቶ፤ የማሽኮርመም ሂደቱ አንድ አካል በሆነ ሁኔታ ከአዋቂ ጋር በአካል የተደረገውን ግንኙነት ያጠቃልላል።

66. Livingstone, S., Kardefelt Winther, D., & Saeed, M. (2019). Global Kids Online Comparative Report. Innocenti Research Report. Florence: UNICEF Office of Research - Innocenti.

## 1.3 አስጊ የበይነ-መረብ ተግባራትን የተመለከቱ አተያዮች እና ተሞክሮዎች

**ምስል 11. በበይነ-መረብ ወሲባዊ ይዘቶችን ስለመመልከት የሕፃናቱ የአደጋ ምዘና እና፤ በባለፈው ዓመት ውስጥ በራሳቸው አነሣሽነት ይህን መሰል ይዘት ሲያፈላልጉ ከነበሩ ሕፃናት ጋር ሲነጻጸር**





መደብ፡ በኢትዮጵያ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት፤ ብዛት = 1 ሺህ

ያምናሉ፡፡ በተጨማሪ፤ 81 በመቶዎቹ ተንከባካቢዎች እና 60 በመቶዎቹ ሕፃናት፤ ወሲባዊ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን በበይነ-መረብ በኩል ለሌላ ሰው የማጋራት ድርጊት፤ ለሕፃናት ‹በጣም አደገኛ› መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በምስል 12 ላይ እንደተመለከተው፤ የአንድ ሰውን ዕርቃን የሚያሳዩ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን ለሌሎች የማጋራት ድርጊት፤ በሕግ ሊከለከል እንደሚገባ የሚያምኑ መሆኑን አብዛኞቹ ተናግረዋል፡፡ እንዲሁም የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ ማናቸውንም ዓይነት ጸያፍ ቅሰቀሳዎችን ማሠራጨት እና ማዘዋወር በወንጀልነት መደንገጉ እርግጥ ሲሆን፤ ይህም ዳኝነቱ እንደሚሰጠው አተረጓጎም ማንኛውንም ዓይነት ወሲባዊ ምስሎችን ሊያጠቃልል ይችላል፡፡

በኢትዮጵያ ካሉ በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት ውስጥ ወደ 8 በመቶ ገደማ ያክሉ፤ በባለፈው ዓመት ውስጥ የገዛ ዕርቃናቸው የሚያሳዩ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን ራሳቸውን በራሳቸው አንሥተው እንደነበር ገልጸዋል፡፡ ምናልባትም መጠቋቆሚያ (stigma) እንዳይሆኑ በመፍራት፤ ወይም በተለምዶ ስለ ወሲብ እና ወሲባዊ ይዘቶችን ስለማዘጋጀት ማውራት ምቾት የማይሰጥ ጉዳይ በመሆኑ፤ የተጠቀሰው አኃዝ አሳንሶ የተገለጸ ሊሆን ይችላል፡፡ በባለፈው ዓመት ውስጥ፤ ከልጃገረዶች እና በዕድሜ ከገፉት ሕፃናት ይልቅ ወንድ ልጆች እና በዕድሜ ያነሱት ሕፃናት የገዛ ራሳቸውን ዕርቃን የሚያሳዩ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን ያነሡበት ወይም የቀረጹበት አጋጣሚ በጥቂቱ ከፍ ያለ ነበር፡ ፡ ከዚሁ ጋር በተገናኘ፤ 6 በመቶ ሕፃናት በባለፈው ዓመት ውስጥ ራቁታቸውን ሆነው ሌላ ሰው በምስል ወይም በቪዲዮ እንዲቀርጻቸው መፍቀዳቸውን አሳውቀዋል፡፡ ይህ ጉዳይ አሳሳቢ እና ምናልባትም የበደል ወይም የብዝበዛ ድርጊትን ጠቋሚ ቢሆንም፤ እነዚህ ክሥተቶች በሚተማመኑ አቻዎች/ባልእንጀሮች መካከል ሊፈጸምም ይችላል፤ (በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥም ቢሆን ለሌሎች  ሳያጋሩ መቅረታቸውን ማረጋገጥ የማይቻልበት ስጋት መኖሩ እንደተጠበቀ ነው)፡፡

የጥናቱ ጥሬ መረጃ በተጨማሪ የሚያሳየው አሳሳቢ ነገር፤ በባለፈው ዓመት ውስጥ 11 በመቶዎቹ ሕፃናት ወሲባዊ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን እንዲልኩላቸው የዕድሜ አኩዮቻቸውን ሲጎተጉቱ ነበር፡፡ ይህም ሕፃናትን ስለ ይሁንታ ወይም ፈቃደኝነት በአስቸኳይ የማስተማርን አስፈላጊነት ይጠቁማል፡፡ በዳሰሳ ጥናቱ ከተሳተፉት ሕፃናት መካከል 48

**ምስል 12፡ ዕርቃንን የሚያሳዩ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን ማንሣት እና ለሌሎች ማጋራትን በተመለከተ ሕፃናት እና ተንከባካቢዎች ያላቸው አተያይ**




መደብ፡ በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት | የበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት ተንከባካቢዎች፤ ብዛት = 1 ሺህ ሕፃናት | ብዛት = 1 ሺህ ተንከባካቢዎች

**ምስል 13. ወሲባዊ ይዘቶችን በበይነ-መረብ ለሌሎች ማጋራት ስላለው አደጋ የሕፃናቱ ግምገማ እና፤ በባለፈው ዓመት ውስጥ በዚህ መሰል ጠባይ ከተሠማሩ ሕፃናት ጋር ሲነጻጸር**

**ለሰው ወሲባዊ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን በበይነ-መረብ መላክ**




**%** በመቶዎቹ ሕፃናት ይህ ድርጊት ለሕፃናት ‹በጣም አደገኛ› መሆኑን ከገለጹት ውስጥ ናቸው።

**በባለፈው ዓመት ውስጥ፤ የገዛ ዕርቃንህ/ሽን የሚያሳዩ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን በበይነ-መረብ ስንት ጊዜ ለሰዎች ልከሀ/ሻል?**




**%** በባለፈው ዓመት ውስጥ ይህንን ያደረጉት ሕፃናት 8 በመቶዎቹ ናቸው።

መደብ፡ በኢትዮጵያ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት፤ ብዛት = 1 ሺህ

በመቶዎቹ፤ የሥርዓተ-ጾታ ትምህርት እንዳገኙ ገልጸዋል። ምናልባት እንደሚጠበቀው፤ በዕድሜ ከሁሉም የሚተልቁት ሕፃናት ይህንን ትምህርት አግኝተው የመሆን ዕድላቸው የላቀ ነበር። መብታቸውን ከማስከበር እንዳያፈገፍጉ እና በወሲባዊ ተግባራት መሳተፍን ካልፈለጉ ‹አይሆንም› ማለት እንዳለባቸው ሕፃናትን ከማስተማር ባሻገር፤ እነዚህ የሥርዓተ-ጾታ ትምህርቶች በወሲብ ስለሚተላለፉ በሽታዎች፣ ስለ ግብረ-ገብነት (ከሕፃኑ አኳያ ከወሲብ ጋር በተገናኘ ትክክል ወይም ስህተት የሆኑትን)፣ እና ስለ ወሊድ መከላከያ የመሳሰሉ ጉዳዮችን ሳያካትቱ አንዳልቀረ ይገመታል።

በዚህ ንዑስ-ናሙና ውስጥ ካሉት 75 ሕፃናት መካከል፤ የገዛ ራሳቸውን የሚያሳዩ ወሲባዊ ምስሎችን ለመላክ ከገፋፏቸው ምክንያቶች ውስጥ፤ በፍቅር መያዝ (ብዛት = 18)፣ የመቃበጥ (flirting) እና  የመቃለድ ስሜት (ብዛት = 18)፣ ወይም ሌላኛውን ሰው ማመን (ብዛት =11) የሚሉት ይጠቀሳሉ። ሆኖም፤ ጥቂት ሕፃናት ለምን ይህን መሰል ይዘት አንዳጋሩ የሰጡት ምክንያት አሳሳቢ ነገር መኖሩን አሳይቷል። ለአብነት ያህል፤ አምስት ሕፃናት ይህንን ያደረጉት ማስፈራሪያ ስለደረሰባቸው፤ ሦስት ሕፃናት ደግሞ ጓደኞቻቸው ስለጎተጎቷቸው ነበር።

75 ሕፃናትን ከያዘው ንዑስ-ናሙና ውስጥ፤ 30 ሕፃናት (40 በመቶዎቹ) የገዛ ዕርቃናቸውን የሚያሳዩ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን ለአሁን ወይም ለቀድሞ የፍቅር አጋራቸው ልከዋል። 15 ሕፃናት (20 በመቶዎቹ) መጀመሪያ በበይነ-መረብ ለተዋወቁት ግን ከሕይወታቸው ጋር በሌላ መንገድ ለተቆራኘ (ለምሳሌ በቤተሰብ አባላቸው ወይም በጓደኛቸው የሚታወቅ) ሰው አጋርተዋል። 15 በመቶዎቹ ወይም በቁጥር 11 ሕፃናት ግለ-ቀረጽ ወሲባዊ ምስሎችን ለጓደኛቸው ወይም በአካል ለሚያውቁት ሰው ያጋሩ ሲሆን፤ ሦስት ሕፃናት (4 በመቶ የሚሆኑት) ደግሞ የገዛ ዕርቃናቸውን የሚያሳዩ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን ለማይታወቅ እና በሕይወታቸው ውስጥ ምንም ቁርኝት ለሌለው ሰው አጋርተዋል።


## የሕፃናት-ቀመስ ግለ-ቀረጽ ወሲባዊ ይዘቶች መናር

የቴክኖሎጂ አጠቃቀም በየጊዜው እየጨመረ በመምጣቱ የተነሣ፤ በአንዳንድ የዓለም ክፍሎች ውስጥ ባሉ ሕፃናት፤ በተለይም በታዳጊዎች፤ ዘንድ ግላዊነትን (privacy) እና አማላይነትን (sexuality) የሚገነዘቡበት ዕይታ ላይ ለውጦች ይታያሉ። ወጣቶች እንደ ተገቢ ወይም የተለመደ ነገር አድርገው በየጊዜው እየተቀበሏቸው ያሉት አንዳንድ ጠባዮች፤ በሌላ ዘመን ተወልደው ያደጉ ጎልማሶችን ግራ ሊያጋቡ ይችላሉ። ለአብነት ያህል፤ ትናንሽም ሆነ በርካታ አባላት ባሏቸው ቡድኖች፤ በዝግ (private) ሆነ ስም-የለሽ (anonymous) ታዳሚዎች በሚሳተፉባቸው ለሕዝብ ክፍት በሆኑ መድረኮች ላይ፤ የጽሑፍ መልእክትን መጻጻፍ ወይም ቪዲዮዎችን እየቀረጹ በቀጥታ ማስተላለፍ የተለመደ ነገር ሆኗል፡ ፡ ምንም እንኳ አብዛኛው መሰል ተግባር ጎጂ ባይሆንም፤ በእነዚህ መገልገያዎች አማካኝነት ግለ-ቀረጽ ወሲባዊ ይዘቶችን ማዘጋጀት እና ለሌሎች የማጋራት ድርጊትም እንዲሁ እየጨመረ እና የማይናቅ ስጋቶችን እያስከተለ ነው።[67]

በሕፃናት አማካኝነት ግለ-ቀረጽ ወሲባዊ ይዘቶችን ለሌሎች የማጋራት ተግባር ውስብስብ እና የተለያዩ ዘርፈ-ብዙ ሁኔታዎችን፣ ስጋቶችን፣ እና ጉዳቶችን የያዘ ጉዳይ ነው። የዲስረፕቲንግ ሀርም ጥሬ መረጃ እንደሚያሳየው፤ አንዳንድ ግለ-ቀረጽ ይዘቶች ለሌሎች እንዲጋሩ የሚደረግበት ምክንያት፤ ሕፃናት ፍቅር ስለያዛቸው ወይም ለመቀላለድ በሚል ነበር። መሰል መላላኮች ከታዳጊዎች የወሲብ አደራረግ ውስጥ እንደ አንዱ ተግባር እየሆነ የመጣበት ሂደት ጨምሯል። ሆኖም፤ ጥሬ መረጃው ግለ-ቀረጽ ወሲባዊ ይዘቶችን የማዘጋጀት እና ለሌሎች የማጋራት ድርጊት፤ በማስፈራሪያ እና በአቻዎች ግፊት አማካኝነት በሚደረግ ጫና ወይም ማስገደድም ጭምር ሊፈጸም ይችላል። (ምዕራፍ 2.2 ን ይመለከቷል)

የማስገደድ ድርጊት፤ ወንጀል እና በቀጥታ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑ በግልጽ ሊታይ የሚችል ቢሆንም፤ ማናቸውንም ወሲባዊ ይዘቶችን የማጋራት ድርጊት (ግዳጅ በሌለበት ሁኔታ እንኳ) በሕፃናት ላይ ዐሉታዊ ጠንቆችን ሊያስከትል ይችላል። በፍቃደኝነት የተጋራ ቁሳቁስ መጀመሪያ ላይ ጉዳት ላያስከትል ይችላል፤ ቢሆንም ኋላ ላይ ቆይቶ ካዘጋጀው ሰው ቁጥጥር ውጪ ወጥቶ ለሌሎች የሚጋራበት ስጋት ግን እንደተጠበቀ ነው። ቁሳቁሱ እስካለ ድረስ፤ በማታለል ወይም በማስገደድ ሊወሰድ እና በወንጀለኞች አማካኝነት ማለቂያ በሌለው ቅብብሎሽ ሊሠራጭ ይችላል (ምስል 14ን ይመለከቷል)።[68፣69]

## ምስል 14፡ የሕፃናት-ቀመስ ግለ-ቀረጽ ወሲባዊ ይዘቶችን ለሌሎች መጋራት የሚያስከትለው ጠንቆች ሲዳሰሱ




67. Thorn & Benson Strategy Group. (2020). Self-Generated Child Sexual Abuse Material: Attitudes and experiences.U.S.: Thorn.
68. EUROPOL. (2019). Internet Organized Crime Threat Assessment 2019. Netherlands: EUROPOL.
69. Bracket Foundation. (2019). Artificial Intelligence: Combating Online Sexual Abuse of Children. 10.

# 2. የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል በኢትዮጵያ

የበፊቱ ክፍል በመቀጠል፤ በዚህ ምዕራፍ በኢትዮጵያ የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ስላጠላው ስጋት ይዳሰሳል። ይህ ምዕራፍ፤ ከሕግ አስከባሪው የተገኘውን ጥሬ መረጃ፣ ተቀማጭነታቸው አሜሪካ ከሆኑ የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች ወደ የጠ/ብ/የ/ሕ/ብ/ማእከል የተላኩ ኢትዮጵያን የተመለከቱ ይፋዊ ሪፖርቶችን፣ በግንባር ቀደም ሠራተኞች ላይ የተካሄዱ ዳሰሳዎችን እና ከራሳቸው ከሕፃናቱ ጋር የተደረጉ ውይይቶችን፣ እንዲሁም የአባወራ/ቤተሰብ የዳሰሳ ጥናቱን ጨምሮ ከተለያዩ ምንጮች የተውጣጣ ይዘት ያለው ሲሆን፤ ይህም በሕፃናት ላይ ስለሚፈጸሙት ስለእነዚህ ወንጀሎች ባሕርይ ዙሪያ-መለስ ዕይታን ለማስቃኘት እንዲቻል ነው።

## 2. የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል በኢትዮጵያ

**በዚህ ምዕራፍ፤ ከበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጋር የተያያዙ ሃገር-አቀፍ የሕግ ማስከበር ዘርፉን የሚመለከት ጥሬ መረጃ (ምዕራፍ 2.1) የሚቀርብ ሲሆን፤ በመቀጠልም በራሳቸው በሕፃናቱ በተገለጹ ገጠመኞች መነሻነት የተወሰኑ የበ/መ/ሕ/ወ/ብ/በደሎችን አፈጻጸም ወይም ክሥተት የሚመለከቱ ትንበያዊ-ግምቶች (estimates/estimations) ቀርበዋል (ምዕራፍ 2.2. እና 2.3)። የእነዚህ ትንበያዊ-ግምቶች ዓላማ፤ ስለ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የሥርጭት አድማስ ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ መረጃ ሆኖ እንዲታይ አይደለም። ለዚህም በርካታ ምክንያቶች አሉ፡ ፡ የመጀመሪያው፤ አሁን ያሉት አስተዳደር-ነክ ጥሬ መረጃዎች (ለምሳሌ በሕግ አስከባሪ ባለሥልጣናት የተመዘገቡት) ውስጥ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጉዳዮች ለብቻ ተለይተው ወይም በተናጠል ተመድበው የተቀመጡበት አሠራር ኢምንት ነው። ሁለተኛ፤ የአባወራ/ቤተሰብ የዳሰሳ ጥናቱን በተመለከተ፤ ከግላዊነት ስጋቶች ወይም ገመናን ለመደበቅ ከመሻት፣ ስለ ወሲብ እና ወሲባዊነት/አማላይነት በግልጽ ለመናገር ከማቅማማት፣ እንዲሁም አንዳንዶቹ ድርጊቶች የሚያስከስሱ በመሆኑ ራሳቸውን በሕግ እንዳያስወነጅሉ ከመፍራት የተነሣ፤ በተወሰነ ደረጃ አሳንሶ ምላሽ መስጠት ሊኖር እንደሚችል በማንም ሰው ይጠበቃል። በተጨማሪም፤ የወሲብ በደል በሚፈጸምበት ቤተሰብ ውስጥ፤ ሕፃናት ለዚህ ዓይነቱ የዳሰሳ ጥናት ምላሽ እንዲሰጡ ፈቃድ የሚያገኙበት ዕድል ያነሰ ነው። በመጨረሻም፤ ብዙዎቹ ትንበያዊ-ግምቶች በአባወራ/ቤተሰብ የዳሰሳ ጥናቱ ውስጥ ከንዑስ-ናሙናዎች በተገኙት ጥሬ መረጃዎች ላይ የተካሄደውን ትንታኔ መሠረት በማድረግ የተሠሩ ሲሆን፤ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል እስካሁንም ደረስ ሪፖርት የማይደረግ ክሥተት በመሆኑ ንዑስ ናሙናዎቹ አናሳ ናቸው። የእነዚህ ንዑስ ናሙናዎች አነስተኛ መሆን፤ የስህተት ሕዳጉ (margin of error) እንዲሰፋ አድርጎታል።**

ምንም እንኳ የ*ዲስረፕቲንግ ሀርም* ቡድን በጥሬ መረጃው እና በተወሰደው ናሙና ጥራት ላይ የሚተማመን ቢሆንም፤ በእነዚህ ዓይነተኛ እና ስሱ (sensitive) ጉዳዮች ላይ ያውም ሕፃናትን ያካተተ ምርምር ለማካሄድ ተግዳሮት ከነበር፤ የማጠቃለያ ትንበያዊ-ግምቱ እንከን አልባ እንዳይሆን ያደርገዋል ማለት ነው። በእነዚህ ምክንያቶች የተነሣ፤ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ያሉትን ግኝቶች የሚያነብ አንባቢ፤ በኢትዮጵያ ከበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጋር የተያያዙ በሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ አንዳንድ የወንጀል ድርጊቶችን ስብጥር፤ ብሎም በኢትዮጵያ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት ለበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የተጋለጡበትን ደረጃ እንደሚያመላክት ለእውነት የቀረበ ጥሩ ግምት አድርጎ መውሰድ ይችላል።

> **የኢትዮጵያ ሕግ አስከባሪ አካላት እንደገለጹት፤ እ.ኤ.አ. በ2017፣ በ2018፣ እና 2019 ከበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጋር የተያያዘ አንድ እንኳ ነገረ-ጉዳይን አልመዘገቡም**

# 2.1 የሕግ አስከባሪ ዘርፉ ጥሬ መረጃ

**በዚህ ምዕራፍ ያለው ትንታኔ፤ ከሕግ አስከባሪ ባለሥልጣናት እና ከበርካታ አጋር ድርጅቶች የተገኙ አኃዛዊ እና ገለጻዊ (qualitative and quantitative) ጥሬ መረጃዎችን የተንተራሰ ሲሆን፤ ይህም ተያያዥነት ስላላቸው የጥፋት ድርጊቶች፣ ስለ አጥፊዎቹ እና ስለ ተጎጂዎቹ ባሕርያት፣ ስለ የወንጀሉ አስቻይ ሁኔታዎች፣ እና ስለ ደካማ ጎኖች ግንዛቤ ለመጨበጥ እንዲቻል ነው።**

### 2.1.1. የተመዘገቡ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል-ነክ ጥፋቶች

የኢትዮጵያ ሕግ አስከባሪ አካላት እንደገለጹት፤ እ.ኤ.አ. በ2017፣ በ2018፣ እና 2019 ከበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጋር የተያያዘ አንድ እንኳ ነገረ-ጉዳይን አልመዘገቡም። ስለዚህ በዚህ ምዕራፍ የቀረበው ትንታኔ የተመረኮዘው፤ የ‹ሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል (ሕ/ወ/ብ/በደል)› በሚል ጥቅል ምድብ ሥር ያለውን የሕግ ማስከበር ስታትስቲክስን ጨምሮ፤ በሌሎች ደጓሚ ጥሬ መረጃዎች ላይ ነው። እ.ኤ.አ. ከ2017 እስከ 2019 ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል (ሕ/ወ/ብ/በደል) የ283 በመቶ ዕድገት አሳይቷል። በሕግ አስከባሪ አካላት የተሰጠው ጥሬ መረጃ፤ የሕ/ወ/ብ/በደሎችን እንደየ ዓይነታቸው በተናጠል ለያይቶ አላስቀመጠም።

### 2.1.2 ዓለም-አቀፍ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ድርጊቶችን ተከታትሎ ማወቅ እና ለሚመለከተው መምራት

የኢትዮጵያ ሕግ አስከባሪ ዘርፉን በመወከል፤ ከጠ/ብ/የ/ሕ/ብ/ማእከል ለዲስረፕቲንግ ሀርም ጥሬ መረጃ እንዲሰጥ ጥያቄ ተልኮ የነበረ ሲሆን፤ ይህም በኢትዮጵያ እንደተፈጸሙ የሚጠረጠሩ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ ድርጊቶችን የተመለከቱ የሳይበር ጥቆማዎችን ለማግኘት ነበር።[70]

ለኢትዮጵያ የሚላከው የሳይበር ጥቆማ መጠን የየዓመታቱ ጭማሪ እ.ኤ.አ. በ2018 ላይ የ234 በመቶ ዕድገት ካስመዘገበ በኋላ፤ እ.ኤ.አ. በ2019 በ54 በመቶ አሽቆልቁሏል። የአንዱ ዓመት ብቻ ሲሰላ እ.ኤ.አ. በ2018 በኢትዮጵያ የታየው የ53 በመቶ ዕድገት፤ በመላው ዓለም ከታየው የ66 በመቶ የሳይበር ጥቆማ ዕድገት ጋር ተመሳሳይነት የሌለው ከመሆኑም በላይ፤ እ.ኤ.አ. በ2019 ላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የታየው ትልቅ ቅናሽ በዓለም ከቀነሰበት አማካይ (8 በመቶ) ቁጥር ጋር ሲነጻጸር ልዩነቱ ጉልህ ነው።[71] እ.ኤ.አ. የ2020 የወል (public) መረጃ ተካቶበት ሲታይ፤ እ.ኤ.አ. የ2018ቱ አኃዝ ያፈነገጠ ሊሆን ይችላል። ከመላው ዓለም የሳይበር ጥቆማዎች ብዛት ጠቅላላ ድምር ጋር ሲነጻጸር የኢትዮጵያ ድርሻ በተከታታይ ዝቅተኛ (በአማካይ 0.12 በመቶ) መጠን የሚመዘገብበት ሲሆን፤ ኢትዮጵያ ከዓለም ጠቅላላ የሕዝብ ቁጥር የ1.45 በመቶ ድርሻ፤ እንዲሁም እንደ ዓለም-አቀፍ የቴሌኮሚዩኒኬሽኖች ኅብረት ግምት[72] ከጠቅላላው የዓለም የበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕዝብ ውስጥ የ0.53 በመቶ ሽፋን ያላት ከመሆኑ አንጻር ሲታይ፤ አኃዙ ምናልባትም ይጠበቅ ከነበረው በታች ሊሆን ይችላል።

**ምሰል 15፡ በኢትዮጵያ የሕግ ማስከበር ዘርፍ የተመዘገቡ የሕ/ወ/ብ/በደል ወይም የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጉዳዮች ብዛት**

| Department of Special Investigations (DSI) | እ.ኤ.አ. 2017 | እ.ኤ.አ. 2018 | እ.ኤ.አ. 2019 |
|---|---|---|---|
| የሕ/ወ/ብ/በደል ነገረ-ጉዳዮች ብዛት | 147 | 186 | 563 |
| የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ነገረ-ጉዳዮች ብዛት | 0 | 0 | 0 |

መደብ፡ ኢንተርፖል አዲስ አበባ ከከፈተው ‹ሃገር-አቀፍ ማእከላዊ ቢሮ› (National Central Bureau) የተገኘ ጥሬ መረጃ

**ምስል 16፡ በኢትዮጵያ እንደተፈጸሙ የሚጠረጠሩ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ ድርጊቶችን የተመለከቱ የሳይበር ጥቆማዎች**

| | እ.ኤ.አ. 2017 | እ.ኤ.አ. 2018 | እ.ኤ.አ. 2019 | እ.ኤ.አ. 2020 | ከ2017 ወደ 2018 ለውጥ በመቶኛ | ከ2018 ወደ 2019 ለውጥ በመቶኛ | ከ2017 ወደ 2019 ለውጥ በመቶኛ | ከ2019 ወደ 2020 ለውጥ በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ኢትዮጵያ | 9,838 | 32,824 | 15,054 | 17,451 | 234% | −54% | 53% | 16% |
| የዓለም በጠቅላላ | 10,214,753 | 18,462,424 | 16,987,361 | 21,751,085 | 81% | −8% | 66% | 28% |
| ከዓለም የኢትዮጵያ ድርሻ በመቶኛ | 0.10% | 0.18% | 0.09% | 0.08% | | | | |

መደብ፡ በጠ/ብ/የ/ሕ/ብ/ማእከል የቀረበ የሳይበር ጥቆማ ጥሬ መረጃ

70. ተቀማጭነታቸው በአሜሪካ የሆኑ የኤሌክትሮኒክ አገልግሎት ሰጪዎች፤ አጠራጣሪ የሕፃናት ብዝበዛ ድርጊቶችን ለጠ/ብ/የ/ሕ/ብ/ማእከል የሳይበር-ጥቆማ-መስመር (CyberTipline) ሪፖርት እንዲያደርጉ በአሜሪካ የፌደራል ሕግ ግዴታ ተጥሎባቸዋል። ተቀማጭነታቸውን አሜሪካ ያላደረጉ አገልግሎት ሰጪዎች፤ ሪፖርት የሚያደርጉት በፈቃደኝነት ነው። የሚያጠራጥሩ የሕፃናት የወሲብ ብዝበዛ ጉዳዮችን ሁሉም ወይም መላው አገልግሎት ሲጪዎች ወይም ፕላትፎርሞች ሪፖርት ላያደርጉ ይችላሉ። ስለዚህ ጥናቱ ባተኮረባቸው ሃገራት ውስጥ ብዙኃኑ በሚጠቀሙባቸው በርካታ ፕላትፎርሞች ላይ ስላለው የበ/መ/ሕ/ወ/ብ/በደል በተመለከተ የመረጃ ክፍተት አለ ማለት ነው።
71. እ.ኤ.አ. በ2019 በብዙ ሃገራት የተስተዋለው የሪፖርቶች መቀነስ ዋነኛው ምክንያት፤ በአንድ ሪፖርት ላይ በርካታ ፋይሎችን አባሪ ለማድረግ መቻሉን ጨምሮ፤ የኤሌክትሮኒክ አገልግሎት ሰጪዎቹ የሪፖርት አደራረግ ሥርዓታቸው ላይ ባሳዩት መሻሻሎች የተነሣ ነው።
72. ዓለም-አቀፍ የቴሌኮሚዩኒኬሽኖች ኅብረት፤ (ቀን አልተጠቀሰም)፤ ስታትስቲክስ፤

ኢንተርፖል አዲስ አበባ በከፈተው ‹ሃገር-አቀፍ ማእከላዊ ቢሮ› በኩል የኢትዮጵያ ሕግ አስከባሪው አካል የሳይበር ጥቆማዎችን ተቀብሏል። በአንድ በኩል ከላይ የቀረበው አኃዝ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ሕግ ማስከበር ዘርፉ አንድም የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ነገረ-ጉዳይ ያለመመዝገቡ የማይታበል ተቃርኖ መኖሩን የሚያሳይ ሲሆን፤ ይህም ከጠ/ብ/የ/ሕ/ብ/ማእከል የሚላኩ የሳይበር ጥቆማዎች በኢትዮጵያ ስለሚከወኑበት ሂደት ጥያቄ ሊያስነሣ ይችላል።

በሳይበር ጥቆማዎቹ የተጠቀሱትን ጉዳዮች በየዘርፋቸው ለመለየት የተካሄደው ትንታኔ እንደሚያመለክተው፤ በተጠቀሰው የሪፖርት ዘመን ውስጥ ለኢትዮጵያ ከተላኩት የሳይበር ጥቆማዎች ውስጥ ለሙሉ በሙሉ በሚጠጋ መጠን የተላከው የጥቆማ ዓይነት፤ የሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶችን (በአሜሪካ ሕግ ‹ሕፃናትን የሚያሳዩ የብልግና ቁሳቁሶች› "child pornography" ተብሎ የተጠቀሰው)ን ማዘጋጀት እና ማሠራጨት ሥር የሚመደበው የወንጀል ዓይነት ነው፡
፡

### ምስል 17፡ በኢትዮጵያ አጠራጣሪ የሕፃናት ወሲባዊ በደሎችን የተመለከቱ የሳይበር ጥቆማዎች በየድርጊቶቹ ዓይነት

| የድርጊቱ ዓይነት | እ.ኤ.አ. 2017 | እ.ኤ.አ. 2018 | እ.ኤ.አ. 2019 |
|---|---|---|---|
| የሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶች፤ ይህም ይዞ መገኘትን፣ ማዘጋጀትን፣ እና ማከፋፈልን ጨምሮ (የጠ/ብ/የ/ሕ/ብ/ማእከል ‹ሕፃናትን የሚያሳዩ የብልግና ቁሳቁሶች›/child pornography በሚል የሰየማቸው)[73,74] | 9,838 | 32,821 | 15,052 |
| ከሕፃናት ጋር ወሲብ ለመፈጸም የሚደረግ ጉዞ (የጠ/ብ/የ/ሕ/ብ/ማእከል የሕፃናት ወሲብ ቱሪዝም/child sex tourism በሚል የሰየመው)[75] | 0 | 0 | 2 |
| የሕፃናት ወሲባዊ ዳበሳ (sexual molestation) | 0 | 1 | 0 |
| በበይነ-መረብ ላይ ያሉ አሳሳች ቃሎች ወይም የዲጂታል ምስሎች | 0 | 2 | 0 |
| **የኢትዮጵያ ድምር** | **9,838** | **32,824** | **15,054** |

መደብ፡ ከጠ/ብ/የ/ሕ/ብ/ማእከል የተሰጠ የሳይበር ጥቆማ ጥሬ መረጃ

### ምስል 18፡ በኢትዮጵያ አጠራጣሪ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛን የሚመለከቱ የሳይበር ጥቆማዎች፤ በሪፖርት አድራጊ የኤሌክትሮኒክ አገልግሎት ሰጪዎች አንጻር ሲታይ

| ሪፖርት አድራጊው የኤሌክትሮኒክ አገልግሎት ሰጪ | እ.ኤ.አ. 2017 | እ.ኤ.አ. 2018 | 2እ.ኤ.አ. 019 | እ.ኤ.አ. ከ2019 ድምር ያለው ድርሻ በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| Facebook | 9,817 | 32,756 | 14,829 | 98.51% |
| Google | 8 | 32 | 133 | 0.88% |
| Instagram, Inc. | 8 | 30 | 79 | 0.52% |
| WhatsApp Inc. | — | 2 | 4 | |
| SmugMug-Flickr | — | — | 3 | |
| Hacker Factor | — | — | 2 | |
| Tagged.com | — | — | 2 | |
| Tumblr | — | — | 2 | |
| 4chan community support LLC | — | 1 | — | |
| Chatstep | 2 | — | — | |
| Yahoo! Inc. | 3 | — | — | |

መደብ፡ ከጠ/ብ/የ/ሕ/ብ/ማእከል የተሰጠው የሳይበር ጥቆማ መረጃ፤ (እ.ኤ.አ. በ2019 በተደረገው ቆጠራ እንደየዓይነቱ ተከፋፍሎ፤ ብቁ ያልሆኑት ውጤቶች ተወግደዋል)

73. በዚህ ረድፍ ላይ የሰፈረው ቃል፤ ከአሜሪካ ሕግ ጋር በተጣጣመ መልኩ፤ የጠ/ብ/የ/ሕ/ብ/ማእከልን ብያኔ ወይም ምደባ የሚያንጸባርቅ ነው። ዲስረፐቲንግ ሀርም "child sexual abuse material" (በግርድፍ የዐማርኛ ትርጉሙ ‹የሕፃናት ወሲባዊ በደል-አዘል ቁሳቁሶች›) የሚለውን ሐረግ መጠቀምን የሚያበረታታ ሲሆን፤ ይህም በእንግሊዝኛ ከታተመው ከ Luxembourg Guidelines ጋር የተጣጣመ ነው።
74. በዚህ ምድብ ውስጥ ያሉት የሳይበር ጥቆማዎች የሚያመለክቱት፤ የሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶችን ለሚመለከት ለአንድ ጥቆማ/ሪፖርት ብዙ ፋይሎች ሊኖሩ እንደሚችል ነው። ለምሳሌ ያህል አንዳንዶቹ ሪፖርት አቅራቢ የኤሌክትሮኒክ አገልግሎት ሰጪዎች ፤ ለእያንዳንዱ ምስል አንድ ፋይል እንዲሁም ለአንዱ ተጠርጣሪ በርካታ ፋይሎችን ይከፈቱ የነበረበትን የበፊቱን አሠራር በማሻሻል፤ በአንድ ሪፖርት ውስጥ ብዙ ፋይሎች እንዲካተቱ የሚደረግበትን አሠራር ያመለክታል።
በዚህ ረድፍ ላይ የሰፈረው ቃል፤ ከአሜሪካ ሕግ ጋር በተጣጣመ መልኩ፤ የጠ/ብ/የ/ሕ/ብ/ማእከልን ብያኔ ወይም ምደባ የሚያንጸባርቅ ነው። ዲስረፐቲንግ ሀርም "travelling child sex offences" (በግርድፍ የዐማርኛ ትርጉሙ ‹ከሕፃናት ጋር ወሲብ ለመፈጸም የሚደረግ ጉዞ›) የሚለውን ሐረግ መጠቀምን የሚያበረታታ ሲሆን፤ ይህም በእንግሊዝኛ ከታተመው ከ Luxembourg Guidelines ጋር የተጣጣመ ነው።
75. The terminology used in this column reflects classification by NCMEC in line with U.S. legislation. Disrupting Harm advocates use of the term travelling child sex offences, in line with the Luxembourg Guidelines.

## 2.1 የሕግ አስከባሪ ዘርፉ ጥሬ መረጃ

ከሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶች ጋር የሚገናኙ በሚል በዚሁ ሥር የተመደቡት የሳይበር ጥቆማዎች ብዛት እ.ኤ.አ. በ2018 ጨምሯል፤ እ.ኤ.አ. በ2019 ላይ ግን ቀንሷል። እ.ኤ.አ. ከ2017 እስከ 2019 ድረስ የነበረው አጠቃላይ ዕድገት 53 በመቶ ነበር። ሊሰጣቸው በሚገባ ትኩረት/የተቀዳሚነት ደረጃ አንጻር ሲታይ፤ የጠ/ብ/የ/ሕ/ብ/ማእከል ለኢትዮጵያ ከላካቸው ሪፖርቶች ውስጥ ደረጃ 1 (Priority 1) የሚለውን ከፍተኛውን መለያ የሰጠው ምንም ሪፖርት የለም፡ ፡ ደረጃ 1 የሚለው መለያ ሕፃኑ/ኗ አይቀሬ አደጋ ውስጥ መሆኑ/ኗን የሚያመለክት ምድብ ነው።

እ.ኤ.አ. ከ2017 እስከ 2019 ባለው ጊዜ ውስጥ ለኢትዮጵያ ከተሰጡ ሳይበር ጥቆማዎች ውስጥ ከሦስቱ በስተቀር ቀሪዎቹ በሙሉ፤ ከኤሌክትሮኒክ አገልግሎት ሰጪዎች የተላኩ ናቸው። ብዛታቸው በድምሩ 11 የሆኑ ኤሌክትሮኒክ አገልግሎት ሰጪዎች፤ በተጠቀሰው የሪፖርት ዘመን ውስጥ ቢያንስ አንድ አጠራጣሪ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛን የሚመለከት የሳይበር ጥቆማ ልከዋል፡ ፡ በዲስረፕቲንግ ሀርም ከታቀፉት ሃገራት ከአንዳንዶቹ ጋር ሲነጻጸር (ምናልባትም ከበይነ-መረብ ተጠቃሚው ሕዝብ ብዛት ጭምርም ጋር ሲተያይ)፤ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ፈጻሚዎች ሕገ-ወጥ ድርጊታቸውን የሚፈጽሙባቸው ፕላትፎርሞች ወይም አማራጮች ውሱን መሆናቸውን ከላይ የቀረበው መረጃ ያመለክታል። [76]

እ.ኤ.አ. በ2019 ብቻ ሳይሆን በመላው የሪፖርት ዘመንም ጭምር ለኢትዮጵያ ከተላኩት የሳይበር ጥቆማዎች ውስጥ 99 በመቶውን ድርሻ የያዘው ፌስቡክ ሆኖ ሳለ፤ እ.ኤ.አ. በ2019 ፌስቡክ የላካቸው የሳይበር ጥቆማዎች ብዛት ግን በበፊተኛው ዓመት ከተላከው ግማሹን እንኳ አያክልምነበር። ከጉግል እና ከኢንስታግራም የሚላኩት የሳይበር ጥቆማዎች መጠን፤ ጥቂት በጥቂት ግን ያለማቋረጥ እያደገ መሆኑ ይታያል። ከ Tagged.com የተገኙት ሁለት የሳይበር ጥቆማዎች፤ ፍቅረኛ ፈላጊዎችን የሚያገናኙ ድረ-ገጾች (adult dating sites)፤ አጠራጣሪ የሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶችን ለማሠራጨት ያላግባብ ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው ፍንጭ ይሰጣል። ተጠቃሚዎች ማንነታቸውን ሳይገለጹ በስም-የለሽ (anonymously) የተለያዩ ምስሎችን እንደ ማስታወቂያ ሰሌዳ የሚለጥፉበትን አገልግሎት ከሚሰጠው ከ‹ፎርቻን› (4chan) ድረገጽ፤ እንዲሁም የዲጂታል ፎረንሲክ የምርምር ኩባንያ ከሆነው ከ ‹ሀከር ፋክተር› (Hacker Factor) የተገኙት መረጃዎች እንደሚያሳዩት፤ ምንም እንኳ ከማኅበራዊ ሚዲያዎች እና ከበይነ-መረብ ትዕዛዘ-ፍለጋ አገልግሎት ሰጪዎች (search providers) ከተገኘው ጋር ሲነጻጸር በእነዚህ አካላት የተሰጡት የሳይበር ጥቆማዎች ብዛት አነስተኛ ቢሆንም፤ በኢትዮጵያ ውስጥ የረቀቀ ቴክኒክን የሚጠቀሙ እና የሚፈልጉትን በውል የለዩ እና በአትኩሮት የሚሠሩ የተወሰኑ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ፈጻሚዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ይገኛሉ።

### ቴሌግራም

በሁሉቱም ዘዴዎች፤ ማለትም ከመንግሥት ኃላፊዎች ጋር በተደረጉት ቃለ-መጠይቆችም ሆነ ከአባወራ/ቤተሰብ የዳሰሳ ጥናቱ የተገኘው ጥሬ መረጃ፤ እንደ ዋትስአፕ ካሉ ሌሎች የመልእክት መላላኪያ መተግበሪያዎች ጋር ሲወዳደር በኢትዮጵያ ውስጥ ቴሌግራም የብዙኃኑ ምርጫ ሲሆን፤ የተመራጭነቱ ደረጃም በሌሎች የአፍሪካ ሃገራት ውስጥ ካለው ይበልጣል። በምዕራፍ 2.2.1 እንደተብራራው፤ በንጽጽር ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው የኢትዮጵያ ሕፃናት ስለ ወሲብ እንዲያወሩ ወይም ወሲባዊ ይዘቶችን እንዲልኩ የሚጠይቁ ግብዣዎችን በቴሌግራም በኩል መቀበላቸውን ተናግረዋል። *ዲስረፕቲንግ ሀርም* ባተኮረባቸው ሌሎች ሀገራት ውስጥ ግን ይሄን መሰል ጉዳይ አልተከሠተም።

እዚህ ላይ ሊጤን የሚገባው፤ ቴሌግራም ለጠ/ብ/የ/ሕ/ብ/ማእከል ሪፖርት የማያቀርብ መሆኑን ነው፤ ምክንያቱም ተቀማጭነቱ በአሜሪካ ያልሆነ የኤሌክትሮኒክ አገልግሎት ሰጪ በመሆኑ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ የለበትም።

ቴሌግራም የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል በደረሰባቸው የኢትዮጵያ ሕፃናት ዘንድ ስሙ ገንኖ የሚነሣ መሆኑ ሲታይ፤ መተግበሪያው በኢትዮጵያ ውስጥ ተወዳጅነት ያተረፈበትን ምክንያት ሳይጠቁም አይቀርም፡ ፡ ነገር ግን ከሕግ አስከባሪ አካላት እና ከግንባር ቀደም ሠራተኞች ተጨማሪ መረጃዎችን ማግኘት ያሻል።

አጠራጣሪ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛዎችን ለማካሄድ ጥቅም ላይ ስለዋሉት የብቸኛ የበይነ-መረብ ፕሮቶኮል/አይፒ (unique Internet Protocol - IP) መለዮዎችን በሚመለከተው ግርድፍ ስታትስቲክስ ላይ ትንታኔ ለማካሄድ፤ ለኢትዮጵያ የተላኩት የሳይበር ጥቆማዎች አመቺ አጋጣሚ ፈጥረዋል።

**ምስል 19: በኢትዮጵያ አጠራጣሪ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ ጉዳዮችን የተመለከቱ የሳይበር ጥቆማዎች፤ ብቸኛ የአፕሎድ አይፒ መለዮዎች ብዛት በየዓመታቱ[76]**

| | እ.ኤ.አ. 2017 | እ.ኤ.አ. 2018 | እ.ኤ.አ. 2019 | እ.ኤ.አ. ከ2017 እስከ 2019 የታየው ለውጥ በመቶኛ | እ.ኤ.አ. ከ2018 እስከ 2019 የታየው ለውጥ በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| ብቸኛ የአፕሎድ አይፒ መለዮዎች በኢትዮጵያ | 1,815 | 3,664 | 3,527 | 94% | -4% |
| የኢትዮጵያ ሪፖርቶች በድምሩ | 9,838 | 32,824 | 15,054 | 53% | -54% |
| በእያንዳንዱ ብቸኛ የአይፒ መለዮ ላይ የቀረቡ ሪፖርቶች | 5.42 | 8.96 | 4.27 | -21% | -52% |

ከጠ/ብ/የ/ሕ/ብ/ማእከል የተሰጠው የሳይበር ጥቆማ ጥሬ መረጃ

76. ተመሳሳዩ ወይም ያው አንዱ የአይፒ መለዮ ብቅ ያለበት መጠን የሚቆጠር ሲሆን፤ ቆጠራው የተካሄደበት ዘመን ከአንድ ዓመት በላይ ያለውን ጊዜ ሊጨምርና፤ አንድ ሪፖርትም ከአንድ በላይ ብቸኛ የአይፒ መለዮን ሊይዝም ይችላል። የዳይናሚክ የአይፒ መለዮዎች አሰጣጥ፤ ብሎም ቨርዥን ቁጥር 4 የአይፒ መለዮዎችን ለብዙ መገልገያ መሣሪያዎች የማከፋፈል ስልትን ጨምሮ፤ በኤሌክትሮኒክ አገልግሎት ሰጪዎች የሚተገበሩ ሌሎች ቴክኒካዊ አሠራሮች፤ ከመረጃ መረቡ ጋር ግንኙነት የጀመሩ እና ብቸኛ መታወቂያ ያላቸው የአይፒ መለዮዎች ብዛት በትክክል እንዳይታወቅ አሠራሮቹ ተጽእኖ ሊያደርጉ ይችላሉ።

እያንዳንዱ መገልገያ መሣሪያ ለብቻው ተለይቶ በሚታወቅ ጊዜ እና በተለየ መረብ ላይ በተናጠል የሚጠቀምበት የአይፒ መለዮ ይሰጠዋል። በአንድ የአይፒ መለዮ ላይ በርካታ ሪፖርቶች የሚቀርቡ ከሆነ፤ ተጠርጣሪዎች (ወይም ቢያንስ መገልገያ መሣሪያዎቻቸው) በተመሳሳዩ ወይም በዚያው በአንዱ የበይነ-መረብ ቆይታቸው (the same online session) ላይ እንዳሉ ከሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶች ጋር የተያያዙ በርካታ የወንጀል ድርጊቶችን በአንዴ እየፈጸሙ መሆኑን ሊያመለክት ይችላል። በንጽጽር ሲታይ በኢትዮጵያ በእያንዳንዱ ሪፖርት ላይ የሚመዘገቡት አማካይ የአይፒ መለዮዎች ብዛት ከፍ ያለ ሲሆን፤ ይህም ማወቅ በተቻለው በአንዱ ቆይታ (a detected session) በርካታ የሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶችን የመጫን (አፕሎድ) ዝንባሌን አጥፊዎች እንደሚከተሉ፤ ብሎም በደንብ የታቀደበት የወንጀል አፈጻጸም ስልት መኖሩን ያመለክታል።

በመጨረሻም፤ እ.ኤ.አ. ከ2017 እስከ 2019 ባለው ጊዜ ውስጥ ከበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ ድርጊቶች ጋር የተያያዙ ሁለት ምሪቶችን (referrals) ወደ ኢትዮጵያ እንደላከ አንድ የውጭ ሃገር ሕግ አስከባሪ መሥሪያ ቤት አሳውቋል።[77] የውጭ ሃገራት የሕግ አስከባሪ መሥሪያ ቤቶች አብዛኛውን ጊዜ ምሪቶችን የሚልኩት፤ በወቅቱ የተጀመረ ምርመራ ካለና ምርመራውም በሁለተኛ ሃገር ውስጥ ያለ አጥፊን ወይም ተጎጂን ያነካካ ሲሆን፤ አሊያም በዚያው ሃገር የሚንቀሳቀስ አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ለሃገሪቱ ሕግ አስከባሪ ባለሥልጣን ሪፖርት ሲያደርግ ነው፤ ይህም በሁለተኛው ሃገር ውስጥ የሚካሄድ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል መኖሩን ያመለክታል። የዚህ ፕሮጀክት የጥሬ መረጃ ፍላጎት፤ ከኢትዮጵያ ውጪ ካሉ ከሁሉም ሕግ አስከባሪ መሥሪያ ቤቶች የተላኩ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል-ነክ ምሪቶችን የሚመለከት ጥሬ መረጃን በሥርዓት ማሰባሰብን ስለማይጨምር፤ በሪፖርት ዘመኑ ውስጥ ከሌሎች የውጭ ሃገራት ሕግ አስከባሪ መሥሪያ ቤቶች የተላኩ ተጨማሪ ዓለም-አቀፍ ምሪቶች ሊኖሩ የሚችሉበት ሁኔታ አለ።

## 2.1.3 ስለ የሕ/ወ/በ/ቁሳቁስ ከሌሎች ምንጮች የተገኘ ማስረጃ

ሆስቲንግ፡ ለአይ/ሲ/ሲ/ኤ/ኤም/ (በእንግሊዝኛው ምሕፃረ-ቃል ICCAM) ፕላትፎርም የመረጃ ግብአት በሚሰጡት የኢንሆፕ (IN-HOPE) አባል ሆትላይኖች (አደጋ-ማሳወቂያ-መስመሮች) በሕገ-ወጥነት የሚፈረጁቻውን ዓይነት ምስሎችን እና ቪዲዮዎችን፤ ሆስት ከሚያደርጉ ሃገራት ውስጥ ኢትዮጵያ እንደሌለችበት ታውቋል፡ :[78] በተጨማሪም፤ በእንግሊዝኛ ስያሜው ‹ኢንተርኔት ዋች ፋውንዴሽን› የሚሰኘው ድርጅት፤ እ.ኤ.አ. በ2017፣ በ2018፣ እና በ2019 ዓመታት ውስጥ በኢትዮጵያ ሆስት የተደረጉ የተረጋገጡ የሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶች መኖሩን የሚጠቁም ምንም ሪፖርት አላወጣም። ከአይ/ሲ/ሲ/ኤ/ኤም/ ፕሮጀክት የተገኘው ጥሬ መረጃ፤ የኢንሆፕ (INHOPE) አባል አደጋ-ማሳወቂያ-መስመሮች ለአይ/ሲ/ሲ/ኤ/ኤም/ በሚልኩለት ላይ የተመረኮዘ በመሆኑ፤ እንደገናም የእንግሊዝን የሕ/ወ/በ/ቁሳቁስ አደጋ-ማሳወቂያ-መስመርን (CSAM hotline) በዋናነት የሚከውነው የ‹ኢንተርኔት ዋች ፋውንዴሽን› በመሆኑ፤ ከላይ የቀረበው አባባል ግን በኢትዮጵያ ውስጥ የሕ/ወ/በ/ቁሳቁስ ሆስቲንግ ስላለመኖሩ እንደ ማረጋገጫ ሊወሰድ አይገባም።

**በአቻ-ለአቻ መረቦች (peer-to-peer networks) በኩል የሚደረግ ሥርጭት፡** በእንግሊዝኛው ‹ቻይልድ ሬስኪው ኮአሊሽን› ተብሎ የሚጠራው አካል፤ በአቻ-ለአቻ የሰነድ መቀባበያ መረቦች (peer-to-peer file sharing networks) አማካኝነት የሚካሄደውን የሕ/ወ/በ/ቁሳቁስ ሥርጭትን ተከታትሎ ለማወቅ እንዲቻል፤ ‹የሕፃናት ጥበቃ ሥርዓት›ን (Child Protection System) እየከወነ ይገኛል። ከሰኔ 2 ቀን 2011 ዓ.ም. እስከ ሰኔ 1 ቀን 2012 ዓ.ም. ያለውን ጊዜ ያካተተ ጥሬ መረጃ የተላከ ሲሆን፤ ሰባት የኢትዮጵያ የአይፒ መለዮዎች ለአቻ-ለአቻ ሥርጭት ወይም ለዳወንሎዲንግ (ሰነዶችን ለማውረድ) ጥቅም ላይ መዋላቸውን የተላከው መረጃ ያጋልጣል (ምስል 20ን ይመለከቷል)። ‹የሕፃናት ጥበቃ ሥርዓቱ› በሁሉም የሰነድ መቀባበያ መረቦች ላይ ክትትል ስለማያደርግ፤ በበፊቱ ዓረፍተ-ነገር የተገለጸው አባባል በመሰል ፕላትፎርሞች ላይ የሚፈጸሙ የሕ/ወ/በ/ቁሳቁስ-ነክ ጥፋቶች በሙሉ ሲደመሩ ያለውን አኃዝ ወይም ሙሉውን ብዛት የሚወክል እንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል። ኢትዮጵያን፤ ጎን ለጎንም በ*ዲስረፕቲንግ ሀርም* ጥናት የታቀፉ የሌሎች ሃገራትን የሚያንጻባርቅ ጥሬ መረጃ እርስ በርስ ለማነጻጸር ያግዛል።

**ምስል 20፡ ዲስረፕቲንግ ሀርም ባተኮረባቸው ሃገራት የሕ/ወ/በ/ቁሳቁስ ሥርጭትን እና ዳወንሎዲንግ ሂደትን፤ ‹ቻይልድ ሬስኪው ፋወንዴሽን› በአቻ-ለአቻ የሰነድ መቀባበያ መረቦች ላይ እንደታዘበው**

| | የአይፒ መለዮዎች | ብቸኛ ዓለም-አቀፋዊ መታወቂያዎች |
|---|---|---|
| ኢትዮጵያ | 7 | 4 |
| ኬንያ | 76 | 24 |
| ሞዛምቢክ | 6 | 10 |
| ናሚቢያ | 94 | 117 |
| ደቡብ አፍሪካ | 2,413 | 842 |
| ታንዛንያ | 47 | 5 |
| ዩጋንዳ | 4 | 4 |

መደብ፡ ከሰኔ 2 ቀን 2011 ዓ.ም. እስከ ሰኔ 1 ቀን 2012 ዓ.ም. ያለውን ወቅት የሚመለከት በ‹ቻይልድ ሬስኪው ፋውንዴሽን› የቀረበው ጥሬ መረጃ

በ*ዲስረፕቲንግ ሀርም* ጥናት ከታቀፉት ሌሎች ሃገራት ጋር ሲነጻጸር፤ በተጠቀሱት የአቻ-ለአቻ መረቦች አማካኝነት የሚካሄደው የሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶች ሥርጭት፤ በኢትዮጵያ ባሉ ተተቃሚዎች ዘንድ ያለው ተመራጭነት በጣም አነስተኛ ሆኖ ይታያል። ከጠ/ብ/የ/ሕ/ብ/ማእከል የተላከው መረጃ እ.ኤ.አ. በ2017፣ በ2018፣ እና በ2019 ላይ ባሉት ጊዜያት ውስጥ በኢትዮጵያ የሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶችን ይዞ ከመገኘት፣ ከማዘጋጀት፣ እና ከማከፋፈል ጋር እንደሚገናኙ የሚጠረጠሩ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ጉዳዮችን ያካተተ ግዙፍ መረጃ እንደነበር ሲታይ፤ ምናልባትም በኢትዮጵያ ያሉ የሕ/ወ/በ/ቁሳቁስ-ነክ ወንጀል ፈጻሚዎች የአቻ-ለአቻ የሰነድ መቀባበያ መረቦችን ለመጠቀም ተቀማጭነታቸው በአሜሪካ ያደረጉትን የዓለም ዝነኛ ፕላትፎርሞችን ምርጫቸው አድርገው ሊሆን ይችላል።

77. ጥናቱ ባተኮረባቸው ሃገራት ላይ ያነጣጠሩ የደኅንነት መረጃዎችን (intelligence) ወይም ተጠቃሚ-ተኮር (outreach) እንቅስቃሴዎችን ያካተተ ጥሬ መረጃን እና ገለጻዊ (qualitative) ማብራሪያዎችን ለማግኘት፤ ኢንተርፖል ለበርካታ የውጭ ሃገራት ሕግ አስከባሪ መሥሪያ ቤቶች ጥያቄ አቅርቦ ነበር። የደኅንነት መረጃ የአያያዝ ሥርዓቶች እና የመረጃ አጠባበቅ ደንቦች ያስቀመጡትን ድንጋጌዎች ለማክበር ሲባል፤ ከእነዚህ የመረጃ ምንጮች ውስጥ የአንዳንዶቹ ትክክለኛ ማንነት አይገለጽም።
78. ስለ አይ/ሲ/ሲ/ኤ/ኤም/ICCAM ፕሮጀክት የበለጠ መረጃ ለማግኘት፡ በእንግሊዝኛ የቀረበውን ማብራሪያ የያዘውን ማስፈንጠሪያ ይጫኑ፤ International Association of Internet Hotlines: What is ICCAM and Why is it Important?.

**የሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶችን ለማግኘት በድረ-ገጽ የሚደረግ ትዕዛዘ-ፍለጋ፡** በኢትዮጵያ የሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶች ምን ያህል ፈላጊ እንዳላቸው ለማወቅ እንዲቻል፤ በ‹ጉግል ትሬንድስ›/ Google Trends[79] ላይ ጥናት ተካሂዷል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ፤ የኢንተርፖል ‹በሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች› የሥራ ክፍል አባላት በሕ/ወ/በ/ቁሳቁስ ላይ የተለየ አትኩሮት ያላቸው ሰዎች በበይነ-መረብ ትዕዛዘ-ፍለጋ (online search) ሲያካሂዱ እንደሚጠቀሟቸው የሚገመቱ ቃላትን እና ሐረጎችን የያዙ ብዛታቸው 20 ዝርዝሮችን አዘጋጁ፡፡ ከታሕሣሥ 23 ቀን 2009 ዓ.ም. እስከ ታሕሣሥ 22 ቀን 2011 ዓ.ም. ድረስ ባለው ወቅት ውስጥ፤ በእነዚህ በተመረጡት 20 ቃላት ላይ በኢትዮጵያ ውስጥ ተደርጎ የነበረ ትዕዛዘ-ፍለጋ ስለመኖሩ በተደረገው አሰሳ የተገኘው ውጤት፤ ‹በቂ መረጃ የለም› የሚል መልስ ነበር፡፡

‹በቂ መረጃ የለም› የሚለው መልስ የሚያመለክተው፤ ቃለቶቹ በተጠቃሚዎች ዘንድ ያላቸው አንጻራዊ ተመራጭነት ወይም የተዘውታሪነት ደረጃ ባዶ ወይም ዜሮ እንደነበር ሲሆን፤ ይህም ማለት በተቀመጠው የመልክአ-ምድር (ቦታ) እና የጊዜ (ከ-እስከ) መቼቶች ውስጥ ያሉ ተጠቃሚዎች ለቃላቱ ያላቸው ፍላጎት በአንጻራዊነት አነስተኛ መሆኑን እንጂ በቃላቱ ፈጽሞ ትዕዛዘ-ፍለጋ አልተደረገም ወይም በፍጹምነት ሲታይ ውጤቱ ባዶ/0 ነው ማለት አይደለም፡፡ በተመሳሳዩ ጊዜ እና ቃላት በዓለም ዙሪያ እና በሌሎች ሃገራት ውስጥ ከተካሄዱት ትዕዛዘ-ፍለጋዎች ጋር ሲነጻጸር፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ዓይነተኛ የሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶች ፍላጎት ያላቸው ሰዎች የሚጠቀሟቸው የትዕዛዘ-ፍለጋ ቃላት መጠን ከአንዳንድ ሌሎች ሃገራት ጋር ሲወዳደር አነስተኛ መሆኑን ነው፡፡ የሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶችን ከሚያፈላልጉት ውስጥ ይበልጥ የተራቀቁት ወንጀለኞች፤ ትዕዛዘ-ፍለጋዎችን በነቂስ ድረ-ገጾች (open web) ላይ የማካሄድ ዝንባሌያቸው ዝቅተኛ ነው የሚል መከራከሪያ ሊኖር ቢችልም፤ በሌሎቹ ሃገራት አንዳንዶቹ የኢንተርፖል ናሙና ቃላት በአንጻራዊነት የሚዘወተሩ መሆኑ ሲታይ፤ የሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶች ለማግኘት የሚካሄዱ ትዕዛዘ-ፍለጋዎች እስካሁን ድረስም በነቂስ ድረ-ገጾች አማካኝነት እንደሚደረግ ጠቋሚ ነው፡፡

በኢትዮጵያ በሪፖርቱ ዘመን ውስጥ፤ ዓይነተኛ ፍላጎት ካላቸው ወይም ሙያተኛ ወንጀለኛ ከሚባሉት ዝቅ ባሉት እና፤ በ‹ጀማሪ ደረጃ› ባሉ ሰዎች ከሕ/ወ/ብ/በደል ጋር የተያያዙ ትዕዛዘ-ፍለጋዎችን ማድረግ የተንሰራፋ ተግባር ሲሆን፤ ይህም በታዳጊዎች መካከል ወይም ከታዳጊዎች ጋር፣ ከሕፃናት ጋር፣ እና ከጨቅላዎች ጋር የሚደረጉ ወሲባዊ ተግባራትን የሚያሳዩ ምስሎችን እና ቪዲዮዎችን ለማግኘት በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚደረጉ ትዕዛዘ-ፍለጋዎችንም ይጨምራል፡፡ የፍለጋ አድማሱን በማጥበብ የሚደረጉ ለምሳሌ በእንግሊዝኛው 'high-definition video' (በቪዲዮዎቹ የጥራት ደረጃ)፣ 'amateur'/አማተር የሚሉትን ቃላት በመጠቀም፣ እንዲሁም በቤተሰብ መካከል የተፈጸሙ በደሎችን የሚያሳዩ ቅጂዎችን ለማግኘት የሚደረጉ ተጓዳኝ ትዕዛዘ-ፍለጋዎች ያሉ መሆኑ ሲታይ፤ በኢትዮጵያ ያሉ የድረ-ገጽ ትዕዛዘ-ፍለጋዎችን የሚያካሂዱ አንዳንድ ሰዎች በዓይነታቸው የተለዩ ፍላጎቶች ያሏቸው መሆኑን፤ ብሎም የሕ/ወ/በ/ቁሳቁስን ወይም የብልግና ትዕይንቶችን ለመጀመሪያ ጊዜ የሚመለከት ሰው እንደሚገጥመው ዓይነት ግርምት ሳይሆን፤ ከዚያ ያለፈ እጅግ ሥር የሰደደ እና የነቃ ፍላጎት ሳያዳብሩ እንዳልቀረ ያሳያል፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ የሕ/ወ/በ/ቁሳቁስን ለማግኘት የሚሹ ሰዎች ትዕዛዘ-ፍለጋዎችን ከእንግሊዝኛ ውጪ ባሉ ቋንቋዎች ሊያካሂዱ የሚችሉ በመሆኑ፤ ይህ ሁኔታ በቀበሊኛ እና በአራዳ ቋንቋዎች የሚደረጉ ትዕዛዘ-ፍለጋዎች ላይ ወሳኝ የዕውቀት ክፍተት እንዲፈጠር አድርጓል፡፡ የሕግ አስከባሪ አካላት ጥፋት ፈጻሚዎች የሚጠቀሙባቸውን ተጨማሪ ቃላትን እና የትዕዛዘ-ፍለጋ አጻጻፎችን ለመለየት በሚያስችላቸው መልኩ፤ በኢትዮጵያ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ላይ የሚካሄዱ ምርመራዎች ሂደትን ለመከለስ ወይም ለመፈተሽ የተጠቀሰው የዕውቀት ክፍተት እንደ ጥሩ አጋጣሚ ሊወሰድ ይችላል፡፡ የሆነ ሆኖ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶች ፍላጎት መኖሩን እና እነዚህንም ለማግኘት ሰዎች የነቂስ (open) ድረ-ገጾችን የሚጠቀሙ መሆኑን ከላይ የቀረቡት ግኝቶች ያሳያሉ፡፡

## 2.1.4 ከጉዞ እና ከቱሪዝም ጋር ያለው ቁርኝት

ከሕፃናት ጋር ወሲብ ለመፈጸም ጉዞ የሚያደርጉ ወንጀለኞችን የተመለከተው ጥሬ መረጃ፤ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል መኖሩን ፍንጮ ይሰጣል፤ ምክንያቱም እነዚህ ወንጀለኞች በሕፃናት ላይ የሚፈጽሙትን ወሲባዊ በደል ወይም ብዝበዛ አብዛኛውን ጊዜ የመቀረጽ ልማድ ስላላቸው እና የቀረጹትንም ለራሳቸው ብቻ ከመጠቀም አልፎ ስለሚያሠራጩትም ነው፡፡ ተጓዥ ወንጀለኞች በበይነ-መረብ የታገዘ የሕ/ወ/ብ/በደልን ስለመፈጸማቸው መታዘብ የሚቻል ሲሆን፤ ይህም የተግባቦት ቴክኖሎጂን በመጠቀም ከበይነ-መረብ ውጭ በሕፃናት ላይ በደል ለመፈጸም በሚያመቻች መልኩ የማሽኮርመም ወይም የምልመላ ድርጊት፤ አሊያም ቀድሞውኑ ከበይነ-መረብ ውጪ በደል ከፈጸሙባቸው ሕፃናት ጋር ግንኙነታቸውን በበይነ-መረብ የመቀጠል ድርጊት ተስተውሏል፡፡

በብዙ ሃገራት በወሲብ ወንጀሎች የተቀጡ ሰዎች ወደ ውጭ ሃገራት ስለሚያደርጉት ጉዞ ለሃገሪቱ ማእከላዊ ባለሥልጣን አስቀድሞ የማሳወቅ ግዴታ ተጥሎባቸዋል፡፡ አንድ የውጭ ሃገር ሕግ አስከባሪ መሥሪያ ቤት በሰጠው ጥሬ መረጃ ላይ የተካሄደው ትንታኔ እንደሚያመለክተው፤ እ.ኤ.አ. ከ2015 እስከ 2020 ባሉት ዓመታት ውስጥ፤ ወደ ኢትዮጵያ የሚደረጉ ጉዞዎችን የተመለከቱ ዘጠኝ ማስጠንቀቂያዎች/ማንቂያወች በተለያዩ ሃገራት ላሉ ‹ለሃገር-አቀፍ የወሲብ ወንጀለኞች ባሕር-መዝገብ› (national sex offender registries) መላኩን፤ ይህም በተጠቀሰው ዘመን ውስጥ የወጡት ማስጠንቀቂያዎች ሁሉ ሲደመሩ ካለው ጠቅላላ ብዛት የ0.13 በመቶ ድርሻ እንዳለው፤ በተጨማሪም የ*ዲስረፐቲንግ ሀርም* ጥናት ባተኮረባቸው በሌሎች የአፍሪካ ሃገራት ውስጥ ካሉት ማስጠንቀቂያዎች ደግሞ የ14 በመቶ ድርሻ አለው፡ ፡[80] ከመጀመሪያው በመቀጠል ሌላ መሥሪያ ቤት እንዳሳወቀው፤ በወሲብ-ወንጀል የተፈረደባቸው ሰዎች እ.ኤ.አ. ከግንቦት 2017 እስከ ሰኔ 2020 ባለው ጊዜ ውስጥ ስለሚያደርጉት ጉዞ ከወጡት 283 ማስጠንቀቂያዎች ውስጥ፤ የ0.5 በመቶዎቹ መዳረሻ ኢትዮጵያ ነበር፡፡

79. ‹ጉግል ትሬንድስ›/Google Trends፤ የትዕዛዘ-ፍለጋ ቃላትን እና ዝርዋንን/ strings (ከቃላቱ የሚወጡ ዕርባታዎች እና ተያያዥ ትእምርቶች/ምልክቶች) ከሌሎች መሰሎቻቸው ጋር በማነጻጸር ምን ያህል በተጠቃሚዎች እንደሚዘወተሩ ለማወቅ የሚያስችል የወል የበይነ- መረብ መገልገያ ሲሆን፤ ይህም ተጠቃሚዎች ባስቀመጧቸው የፍለጋ አድማስ መቼቶች መሠረት ውጤቱን ይገልጻል፡፡ የተደረጉትን ሁሉንም ትዕዛዘ-ፍለጋዎችን በጠቅላላው ከማሳየት ይልቅ፤ በተቀመጡት የመልክአ-ምድር እና የጊዜ መቼቶች መሠረት በተመረጡት ቃላት ወይም ዝርዋን ብቻ የተደረጉ ፍለጋዎችን ብዛት፤ በሁሉም ቃላት/ዝርዋን ከተደረጉት የትዕዛዘ-ፍለጋዎች ብዛት ጠቅላላ ድምር ጋር በማካፈል የሚገኘውን ድርሻ ወይም አኃዝ መሠረት በማድረግ፤ ቃላቱ/ዝርዋኑ ያላቸውን አንጻራዊ ተዘውታሪነትን ለማስላት እና ውጤት (ከ 1 እስከ 100 ድረስ) ለመስጠት የሚያስችል መገልገያ ነው፡፡ ስለ ጥሬ መረጃዎች እና ውጤት አሰጣጥ የበለጠ ለመረዳት፤ በማስፈንጠሪያው ‹‹FAQ about Google Trends data›› ውስጥ ያለውን ማብራሪያ ይመለከቷል፡፡

80. ጥናቱ ባተኮረባቸው ሃገራት ላይ ያነጣጠሩ የደኅንነት መረጃዎችን (intelligence) ወይም ተጠቃሚ-ተኮር (outreach) እንቅስቃሴዎችን ያካተተ ጥሬ መረጃን እና ገለጻዊ (qualitative) ማብራሪያዎችን ለማግኘት፤ ኢንተርፖል ለበርካታ የውጭ ሃገራት ሕግ አስከባሪ መሥሪያ ቤቶች ጥያቄ አቅርቦ ነበር፡፡ የደኅንነት መረጃ የአያያዝ ሥርዓቶች እና የመረጃ አጠባበቅ ደንቦች ያስቀመጡትን ድንጋጌዎች ለማክበር ሲባል፤ ከእነዚህ የመረጃ ምንጮች ውስጥ የአንዳንዶቹ ትክክለኛ ማንነት አይገለጽም፡፡

## 2.1 የሕግ አስከባሪ ዘርፉ ጥሬ መረጃ

በአሜሪካ የሆም ላንድ ሰኪዩሪቲ መሥሪያ ቤት ሥር ያለው ‹ኤንጅል ዋች ሴንተር›፤ በሕፃናት ወሲባዊ ወንጀሎች የተፈረደባቸው አሜሪካዊያንን የተረጋገጠ የጉዞ ዕቅዳቸውን በመዳረሻ ሃገራት ላሉ ባለሥልጣኖች ጥቆማ ይልካል። መንገደኛው በመዳረሻው ሃገር እንዲገባ ያልተፈቀደለት መሆኑ ሲረጋገጥ ግለሰቡ ‹የተከለከሉ›/ denials ከሚለው ውስጥ ይመደባል። እ.ኤ.አ. ከ2017 እስከ 2020 ባሉት የበጀት ዓመታት ውስጥ፤ ወደ ኢትዮጵያ የሚሄዱ ተጓዦችን የተመለከቱ አምስት ጥቆማዎችን የላከ ሲሆን፤ በእነዚህ በተጠቀሱት ዓመታት ውስጥ *ዲስረፕቲንግ ሀርም* ላተኮረባቸው ለሌሎቹ የአፍሪካ ሃገራት ከተላኩት ጠቅላላ ጥቆማዎች ውስጥ የ4 በመቶ ድርሻን ይይዛል። ይሁንና፤ መሥሪያ ቤቱ ከእነዚህ ግለሰቦች መካከል አንዳቸው አንኳ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገቡ ስለመከልከላቸው የሚገለጽ ማረጋገጫ  አላገኘም።

# 2.2 በኢትዮጵያ ስላለው የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የሕፃናቱ ተሞክሮዎች

**በዲስረፕቲንግ ሀርም ፕሮጀክት ውስጥ ለበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የተሰጠው ብያኔ፤ በተለይ ለወሲብ ዓላማ በበይነ-መረብ ሕፃናትን የማሸኮርመም ድርጊትን፣ የሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶችን፣ እና ሕፃናት ወሲባዊ በደል ሲፈጸምባቸው በቀጥታ ሥርጭት ማስተላለፍን በሚያጠቃልል መልኩ ነው። የምርምር ግኝቶችን በየመልካቸው ለማደራጀት እና ለማቅረብ እነዚህ ጽንሰ-ሐሳቦች በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ጥቅም ላይ ውለዋል። ጎን ለጎንም፤ ሕፃናት ለበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የሚጋለጡባቸው መንገዶች ከሚታሰበው በላይ በጣም ውስብስብ እና ቁልጭ ያለ ገጽታ የሌላቸው መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ያሻል። አብዛኛውን ጊዜ ገጠመኞቹ እና ጥቃቶች የሚከሠቱት ሁለቱም በአንድ ጊዜ ወይም በቅደም ተከተል ነው። በተጨማሪም፤ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል በዲጂታል ከባቢ ውስጥ ብቻ የሚከሠት አይደለም፤ ዲጂታል ቴክኖሎጂ በአካል/በፊትለፊት የሚደረግ ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን የሚያሣልጥ ወይም ቀርጾ የሚያስቀር መሣሪያ ሆኖ ሊያገለግልም ይችላል።**

## 2.2.1 በበይነ-መረብ ማሸኮርመም

*ዲስረፕቲንግ ሀርም* ለበይነ-መረብ ማሸኮርመም የሚሰጠው ብያኔ፤ ሕፃኑ/ኗ ላይ ወሲባዊ በደል ወይም ብዝበዛ ማድረስን ታላሚ ባደረገ መልኩ በቴክኖሎጂ አማካኝነት ከሕፃኑ/ኗ ጋር የሚደረግ መስተጋብር ነው። ይህም ሙሉ በሙሉ በበይነ-መረብ አሊያም በይነ-መረብን እና የአካል ግንኙነቶችን አጣምሮ ሊካሄድ ይችላል።

በበይነ-መረብ የሚካሄድ ማሸኮርመም፤ አብዛኛውን ጊዜ የማይጨበጥ ባሕርይ ያለውና እና ተከታትሎ ለማወቅ የሚያስቸግር ሲሆን፤ ይልቁንም በወንጀል ፈጻሚው እና በሕፃኑ መካከል የነበረው የአመኔታ ግንባታ ሂደት በእርጋታ እና በተራዘመ ጊዜ የተካሄደበት ሁኔታ ሲኖር፤ ሂደቱ ውስብስብ ይሆናል። አብዛኛውን ጊዜ እንደሚደረገው፤ ሕፃኑ ለወሲብ በደል ‹ዝግጁ እንዲሆን› ከተደረገ በኋላ፤ ማጭበርበርን፣ ጫናን፣ ወይም ዛቻን በመጠቀም በበይነ-መረብ ወይም በአካል በሚፈጸሙ ወሲባዊ ድርጊቶች ላይ እንዲሳተፍ ይደረጋል። ሆኖም በበይነ-መረብ ማሸኮርመም ሳይታቀድ በድንገት ሊደረግ ወይም ያልታሰበበት መስሎ ሊታይ ይችላል፤ ይህም በማስገደድ-መጠቀምን/ extortion ጨምሮ፤ ጥፋት ፈጻሚው ሕፃናቱን የገዛ ራሳቸውን የሚያንጸባርቁ ወሲባዊ ይዘቶችን አንዲልኩለት ድንገተኛ ጥያቄ ሊያቀርብላቸው ወይም ጫና ሊያሳድርባቸው ይችላል።

ቀጣዩ ንዑስ-ምዕራፍ በዋናነት የሚያተኩረው፤ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት ለአባወራ/ቤተሰብ የዳሰሳ ጥናቱ የሰጡትን መረጃ መነሻ በማድረግ፤ በተለያዩ የበይነ-መረባዊ ማሸኮርመም ገጽታዎች ላይ ሕፃናት ስላሏቸው ተሞክሮዎች ነው። በሕፃናት ላይ የሚደረጉ የወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ድርጊቶች በተለያዩ በርካታ መንገዶች እና ስፍራዎች ሊፈጸሙ የሚችሉ መሆኑን ከግንዛቤ በማስገባት፤ ከታች የቀረቡት የሚበዙት የጥሬ መረጃዎቹ ነጥቦች፤ በርካታ ምላሾችን ሊያካትቱ እና ድምራቸውም በመቶኛ ሲሰላ ከ100 ሊያልፍ ይችላል።

### ማሸኮርመምን ስለሚመለከተው ሕግ

የኮምፒዩተር ወንጀልን ለመደንገግ ኢትዮጵያ ያወጣችው አዋጅ፤ ወሲባዊ ይዘት ያላቸውን ንግግሮችን፣ ስዕሎችን፣ የጽሑፍ መልእክቶችን፣ ወይም ቪዲዮዎችን በኮምፒዩተር ሥርዓት አማካኝነት በመላክ ለአካለ-መጠን ያልደረሰ ልጅን ለወሲባዊ ድርጊት የማነሣሣት ወይም የመመልመል ተግባርን በወንጀልነት የሚደነግግ እና፤ ድርጊቱም ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እንደሚያስቀጣ ይደነግጋል።[81,82]ይህ አዋጅ የሚሸፍነው፤ የወሲብ በደልን ታላሚ ባደረገ ሁኔታ በበይነ-መረብ ከአንድ ሕፃን ጋር የሚደረግን ‹‹ግልጽ ወሲባዊ ተግባቦት››ን/sexually explicit communication ነው።

### አጠራጣሪ የማሸኮርመም ድርጊቶች - ስለ ወሲብ እንዲያወሩ የተጠየቁ ሕፃናት

በባለፈው ዓመት ውስጥ ብቻ፤ በኢትዮጵያ በአባወራ/ቤተሰብ የዳሰሳ ጥናቱ ከተሳተፉት በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት ውስጥ 12 በመቶዎቹ፤ ፍላጎቱ ከእነሱ ሳይመጣ ስለ ወሲብ ወይም ወሲባዊ ድርጊቶች እንዲያወሩ ጥያቄ ያቀረበላቸው ሰው ገጥሟቸዋል። ከምላሽ ሰጪ ሕፃናቱ መካከል ይሄ ነው የሚባል የዕድሜ እና የጾታ ልዩነት አልታየም። እንደነገሩ ሁኔታ ቢለያይም፤ እነዚህ ገጠመኞች በሕፃናት ላይ ደረጃው የሚለያይ ጉዳት መድረሱን ያመለክታል፡ ፡ ለምሳሌ ያህል፤ በወንድ ወይም በሴት የፍቅር ጓደኛ ስለ ወሲብ እንዲያወራት/እንድታወራ የተጠየቀ/ች ግን በወቅት ድርጊቱን ያልፈጸመ/ች አንድ ሕፃን፤ በክሥተቱ የተነሣ ብርቱ ጉዳት ላያገኘው/ኛት ይችል ይሆናል። በሌላ ጎን ሲታይ ግን፤ እነዚህ ክሥተቶች ከክፋት የመነጨ የማሸኮርመም ሙከራ ሊኖር እንደሚችል የሚያስጠረጥር ምልክት ሊሆን ይችላል፤ ለዚህም ነው ‹የተረጋገጠ› ከማለት ይልቅ አጠራጣሪ የማሸኮርመም ድርጊት ምልክቶች በሚል የተገለጸው።

**በበይነ-መረብ ወይስ ከበይነ-መረብ ውጪ?** በአባወራ/ቤተሰብ የዳሰሳ ጥናቱ ከተሳተፉት እና በባለፈው ዓመት ውስጥ ከፍላጎታቸው ውጪ ስለ ወሲብ እንዲያወሩ ጥያቄ ከቀረበላቸው ከ120 ሕፃናት ውስጥ 59ኙ እንዳሉት፤ ድርጊቱ የተፈጸመው በበይነ-መረብ ነው፡ ፡ ድርጊቱ በበይነ-መረብ (በማኅበራዊ ሚዲያ ወይም በበይነ-መረብ በቀጥታ በሚደረግ የጨዋታ ግጥሚያ) እንደተፈጸመ የገለጹት 59ኙ ሕፃናት ብቻ በቀጣዩ ትንተና ላይ ተካተዋል፤ ምክንያቱም እነዚህ ድርጊቶች እንደ አጠራጣሪ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ነገረ-ጉዳይ የሚታዩ በመሆኑ ነው።

ከፍላጎታቸው ውጪ ስለ ወሲብ ወሬ በማኅበራዊ ሚዲያ ጥያቄ ከተቀበሉት (ብዛት = 59) ውስጥ፤ ጥያቄው የተሰነዘረው በፌስቡክ ወይም በፌስቡክ ሜሴንጀር እና በቴሌኮም በኩል የመሆን አጋጣሚው እጅግ ያመዝን ነበር።

**ሕፃናቱ ምን ተሰማቸው**፡ ያለፍላጎታቸው ስለ ወሲብ ወይም የወሲብ ድርጊቶች በበይነ-መረብ አውታሮች በኩል እንዲያወሩ ጥያቄ ከደረሳቸው ሕፃናት መካከል 71 በመቶዎቹ፤ ድርጊቱ ዐሉታዊ ስሜት እንዳሳደረባቸው ተናግረዋል። በተነጻጻሪ፤ 28 በመቶዎቹ ሕፃናት ምንንም እንዳልተሰማቸው ገልጸዋል። በዕድሜ ከገፉት (16-17 ዓመት 27 በመቶ) ጋር ሲነጻጸር በዕድሜ ያነሱት ሕፃናት (12-13 ዓመት 67 በመቶ) በመሰል ገጠመኞች የመናወጥ ዝንባሌያቸው እጅጉን ያነሰ ነበር።

**የሕፃናቱ አጸፋ**፡ በናሙናው ውስጥ ከታቀፉት እና ያለፍላጎታቸው ስለ ወሲብ እንዲያወሩ በበይነ-መረብ ከተጠየቁት 59 ሕፃናት መካከል፤ ከግማሽ የሚልቁት ጥያቄውን አልተቀበሉም። በአብዛኞቹ ከተሰጡት ተመሳሳይ ምላሾች መካከል የአንዳንዶቹ አጸፋ ፈጣን

81. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (2008)፤ የኮምፒዩተር ወንጀልን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 958/2008፤ ንዑስ-ክፍል 3፤ አንቀጽ 12 (2)
82. በኢትዮጵያ ውስጥ ሁለት ዓይነት እስራት አለ፤ ቀላል እና ጽኑ። ጽኑ እስራት ተፈጻሚ የሚሆነው፤ እጅግ ከባድ የሆኑ ወንጀሎችን በፈጸሙ እና በተለይም ለኅብረተሰቡ አደገኛ እንደሆኑ በሚገመቱ ጥፋተኞች ላይ ነው። ወንጀለኛውን ከመቅጣት እና ከማረም በተጨማሪ፤ የጽኑ እስራት ቅጣት አንጻራዊ የመንቀሳቀስ ነጻነት ላይ ጥብቅ ገደቦችንም ያካትታል።

መደብ፡ በኢትዮጵያ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት፤
ብዛት = 1 ሺህ ሕፃናት

# በባለፈው
# ዓመት ውስጥ ያለፍላጎቱ ስለ ወሲብ እንዳወራ ተጠይቄ ነበር

**አዎ 12%**

## ይህ ጉዳይ በበይነ-መረብ የተከሠተበት የቅርቡ ገጠመኝ ...

### ምን አደረግህ/ሽ?

- እምቢ አልኩ 53%
- ጓቄ ተውኩት 15%
- ግለሰቡ እንዲተወኝ ጥረት አደረግኩኝ 10%
- ግለሰቡን አገድኩት 10%

### ምን ተሰማህ/ሽ?

- ምንም አልተሰማኝም 28%
- ንዴት 17%
- መከፋት 14%
- ጸጸት 14%

### ይህንን ያደረገው ማን ነው?

- የፍቅር ጓደኛ (ወይም የበፊት) 25%
- ጓደኛ/የማውቀው (18+ ዓመት ዕድሜ) 22%
- የቤተሰብ አባል 8%
- ጓደኛ/የማውቀው(ከ18 ዓመት ዕድሜ በታች) 7%
- ባልገልጸው እመርጣለሁ 7%
- በሕፃኑ/ኗ የማይታወቅ 38%

ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ ያለፍላጎታቸው ስለ ወሲብ እንዲያወሩ በበይነ-መረብ የተጠየቁ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 59 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

### የት ነው ተከሠተው?

- በማኅበራዊ ሚዲያ 41%
- በአካል 33%
- በበይነ-መረብ የጨዋታ ግጥሚያ 9%
- በሌላ ዓይነት መንገድ 12%

ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ ያለፍላጎታቸው ስለ ወሲብ እንዲያወሩ በበይነ-መረብ የተጠየቁ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 120 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

### ጉዳዩ የተከሠተው በየትኛው ፕላትፎርም በኩል ነው?

- ፌስቡክ ወይም ፌስቡክ ሜሴንጀር 59%
- ቴሌግራም 41%
- ትዊተር 6%
- ኢሞ 6%

ብዛት = ያለፍላጎታቸው ስለ ወሲብ እንዲያወሩ በማኅበራዊ ሚዲያ በኩል በጣም በቅርቡ ጥያቄ የቀረበላቸው ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 49 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

እነዚህ አኃዞች በልጆች የተመረጡትን እና በጣም የተለመዱ ምላሾችን ይወክላሉ
እነዚህ አሃዞች በልጆች የተመረጡትን በጣም የተለመዱ እና በጣም ያልተለመዱ ምላሾችን ይወክላሉ
የምርጫ ጥያቄ

### ለማን ነገርህ/ሽ?

የመጀመሪያ 3

- ለጓደኛ 42%
- ለማንም 22%
- Sibling 17%

የመጨረሻ 3

- ለዕርዳታ መጠየቂያ መስመር/Helpline 3%
- ለሴት ተንከባካቢ 3%
- ለማኅበራዊ ሠራተኛ 2%
- ለፖሊስ 2%
- ሌላ የማምነው አዋቂ ሰው፤ 0%

ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ ያለፍላጎታቸው ስለ ወሲብ እንዲያወሩ በበይነ-መረብ የተጠየቁ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 59 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

### ለሰው ያልነገርክ/ሽበት ምክንያት ምንድን ነው?

- ለማን መንገር እንዳለብኝ አላውቅም ነበር 31%
- የኃፍረት ስሜት አደረብኝ 25%
- ጉዳዩ በሚሥጥር ላይጠበቅ ይችላል ብዬ ስለሰጋሁ 25%
- ድርጊቱን የፈጸመውን ሰው ለችግር መዳረግ ስላልፈለግኩ 15%

ብዛት = ያለፍላጎታቸው ስለ ወሲብ እንዲያወሩ በበይነ-መረብ ስለተጠየቁበት የቅርቡ ገጠመኝ ለማንም ያልተናገሩ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 13 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

ምንጭ የዲስረፕቲንግ ሀርም ጥሬ መረጃ

እና ቁርጠኛ ነበር፤ ለምሳሌ ግለሰቡን ማገድ ወይም ከሌሎች ተሳታፊዎች ውስጥ እነሱን ነጥሎ እንዲተዋቸው ሌላኛውን ግለሰብ መጠየቅ የሚሉት ይጠቀሳሉ። ሌሎች በተመሳሳይነት የተሰጡ አጸፋዎች ደግሞ ሽሽትን ያማከሉ ናቸው፤ ለምሳሌ ችግሩን እንዳላየ ማለፍ እና በራሱ ጊዜ እስኪወገድ በተስፋ መጠበቅ፣ ለተወሰነ ጊዜ በይነ-መረብን አለመጠቀም (7 በመቶዎቹ)፣ እና ከሌላኛው ግለሰብ የተላኩ መልእክቶችን በሙሉ መደምሰስ (2 በመቶዎቹ)። ይሁንና፤ ጥቂት ሕፃናት (9 በመቶዎቹ)፤ ምንም እንኳ ፍላጎቱ የመነጨው ከእነሱ ባይሆንም የተጠየቁትን ፈጽመዋል።

**ጥያቄዎቹን ያቀረበው ማን ነው**፡ ያለፍላጎታቸው ስለ ወሲብ በበይነ-መረብ እንዲያወሩ ለሕፃናት ጥያቄ የሚያቀርብላቸው ሰው ባብዛኛው ቀድሞውኑ የሚያውቁት ሰው ነው፤ ከእነዚህም ውስጥ እጅግ የሚበዛውን ድርሻ የሚይዘው  የበፊት ወይም የአሁን የፍቅር አጋር/ጓደኛ ሲሆን፤ በመቀጠል 18 ዓመት እና በላይ ዕድሜ ያላቸው ጓደኞች እና የቀደመ ትውውቅ ያላቸው ግለሰቦች ናቸው። 38 በመቶ ገደማ የሚሆኑ ሕፃናት፤ ጥያቄው የደረሳቸው ከማያውቁት ግለሰብ እንደሆነ ሲገልጹ፤[83]  በመቶዎቹ ደግሞ ለጥያቄው ምላሽ ነፍገዋል።

በመቶዎቹ ደግሞ ለጥያቄው ምላሽ ነፍገዋል።**ስለጉዳዩ ሕፃናት ለማን እንደነገሩ (ካለ)**፡ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል እንዴት እንደሚቀረፍ እና ምላሽ እንደሚሰጥ ሲታሰብ፤ መደበኛ የአቤቱታ ማቅረቢያ አሠራሮች (በዚህ ሪፖርት ምዕራፍ 3 ላይ ተዘርዝረዋል) መኖር ወሳኝ ጉዳይ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ በተካሄደው የዲስረፕቲንግ ሀርም ጥናት የተሰበሰበው ጥሬ መረጃ እንደሚያመለክተው፤ ከሙሉው የበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት ናሙና ውስጥ 57 በመቶዎቹ፤ በእነርሱ በራሳቸውም ሆነ በጓደኛቸው ላይ ወሲባዊ ጉንተላ (sexual assault) ወይም ወሲባዊ ትንኮሳ (sexual harassment) ቢፈጸም፤ ከየት ቦታ ዕርዳታ ማግኘት እንደሚችሉ አያውቁም። በእርግጥም፤ በባለፈው ዓመት ለወሲባዊ ጥቃት የተጋለጡ ሕፃናት ተሞክሮ እንደሚያሳየው፤ የደረሰባቸውን ለመደበኛ አካላት ወይም አሠራሮች የሚያመለክቱበት ሁኔታ ኢምነት መሆኑን ነው።

በባለፈው ዓመት ውስጥ ያለፍላጎታቸው ስለ ወሲብ እንዲያወሩ በበይነ-መረብ ጥያቄ የደረሳቸው ሕፃናት ከተካተቱበት ንዑስ-ናሙና ውስጥ፤ አንድ ሕፃን ብቻ በበይነ-መረብ አቤቱታ የሚቀርብበትን አሠራር በመጠቀም የደረሰበትን ጉዳይ ያመለከተ ሲሆን፤ ሁለት ሕፃናት ለአደጋ ማሳወቂያ መስመር (hotline) እንዲሁም አንድ ሕፃን ለፖሊስ አሳውቀዋል። በዚህ ንዑስ-ናሙና ከታቀፉ ሕፃናት ውስጥ 22 በመቶዎቹ ስለተፈጠረው ነገር ለማንም አልተናገሩም፡ ፡ የቅርብ ጊዜውን ክሥተት ለማንም ያልተናገሩ 31 ሕፃናት ሲሆኑ፤ ዋነኛ ምክንያታቸውም ለማን መንገር እንዳለባቸው አለማወቃቸው፤ እንዲሁም የመሸማቀቅ ወይም የኃፍረት ስሜት ስላደረባቸው ነው። ከእነዚህ ሕፃናት ውስጥ አምስቱ፤ ክሥተቱ እስከማመልከት የሚያደርስ ብርቱ ጉዳይ አንዳልሆነ አድርገው የተመለከቱት ሲሆን፤ አምስት የሚሆኑት ደግሞ ጉዳያቸው በሚሥጥር ላይጠበቅ ይችላል የሚል ስጋት ነበራቸው።

ያለፍላጎታቸው ስለ ወሲብ እንዲያወሩ በበይነ-መረብ ከሰው ጥያቄ እንደደረሳቸው ያሳወቁ ሕፃናት፤ እጅግ የሚያመዝኑት ለጓደኞቻቸው ወይም ለወንድም/እኅቶቻው እንጂ ለአዋቂዎች አልነበረም (ገጽ xx ን ይመለከቷል)። ለአዋቂዎች የተናገሩበት አጋጣሚ ካለ፤ የሚሥጥራቸው ተካፋይ የሚያደርጓቸው ወንድ ተንከባካቢዎችን (14 በመቶ) ሲሆን፤ በመቀጠልም መምህራንን (12 በመቶ) ነበር፡ ፡ በናሙናው ውስጥ ያሉት ወንድ ልጆች እና ልጃገረዶች ሁለቱም እኩል በሚባል ደረጃ ስለ ወሲብ እንዲያወሩ የተጠየቁበት ሁኔታ ቢኖርም፤ ሕፃናት (ወንድ ልጆችም ሆኑ ልጃገረዶች) ስለደረሰባቸው ነገር ለእናቶች እና ለሴት ተንከባካቢዎች (3 በመቶ) ከመንገር ይልቅ ለአባታቸው ወይም ለወንድ ተንከባካቢያቸው ነገሩን ማዋየት ይበልጥ ይቀናቸው ነበር።

በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ያለ ጎጂ ይዘት ሲያጋጥማቸው አቤቱታ ስለሚቀርብበት መንገድ ማወቃቸውን በእርግጠኝነት የተናገሩት 36 በመቶዎቹ ሕፃናት ብቻ ናቸው። ብዙዎቹ የበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት ማኅበራዊ ሚዲያን (44 በመቶዎቹ) ወይም የፍጡን መልእክት መላላኪያ መተግበሪያዎችን (34 በመቶዎቹ) ቢያንስ በየሳምንቱ የሚጠቀሙ እና ከእነዚህ አስጊ ገጠመኞች ጋር የሚገጣጠሙ መሆኑ ሲታሰብ፤ በዚህ ግኝት ላይ በሁሉም የዕድሜ እና የጾታ መደቦች ላይ ከፍተኛ ወጥነት መንጸባረቁ ይህን ግኝት አሳሳቢ እንዲሆን አድርጎታል።

### አጠራጣሪ የማሸኮርመም ድርጊት - ወሲባዊ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን እንዲያጋሩ የተጠየቁ ሕፃናት

አንዳንድ ጥፋት ፈጻሚዎች፤ ሕፃናትን በአካል የማግኘት ዕቅድ ከመነሻው ጭምር ኖሯቸውም ሆነ ሳይኖራቸው፤ ሕፃናት የቀረጿቸውን የገዛ ራሳቸውን የሚያሳዩ ወሲባዊ ምስሎችን እና ቪዲዮዎችን በዲጂታል ቴክኖሎጂዎች አማካኝነት እንዲልኩላቸው ሕፃናትን በስልት የመጠምዘዝ ሐሳብ አላቸው። ሕፃናት የገዛ ራሳቸውን የሚያሳዩ ወሲባዊ ምስሎችን እና ቪዲዮዎችን እንዲልኩላቸው ለማድረግ ብቻ ታልሞ (ለማግኘት ሳይሆን) የሚካሄደውን ሕፃናትን በበይነ-መረብ የማሸኮርመም ቸግርን ለመፍታት፤ ዓለም እያደረገው ያለው እርምጃ አዝጋሚ ነው።[84]የጉዳዩ አሳሳቢነት ቀጥሎ ባላበት ሁኔታ እ.ኤ.አ. በ2015 ላይ የአውሮፓ ምክር-ቤት ያወጣውን ‹ሕፃናትን ከወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ለመጠበቅ የወጣ ኮንቬንሽን›ን (Convention on the Protection of Children against Sexual Exploitation and Abuse) ትግበራ በበላይነት እንዲቆጣጠር ኃላፊነት የተሰጠው ኮሚቴ (የ‹ላንዛሬት ኮሚቴ›ም በሚል ይታወቃል) ስለ ጉዳዩ አስተያዩትን ይፋ አድርጎ ነበር። ለወሲብ ዓላማ በበይነ-መረብ የሚፈጸመው የማሸኮርመም ወንጀልን፤ ‹‹የወሲባዊ በደሉ የደረሰው የአካል ግንኙነት በመደረጉ የተነሣ ሳይሆን በበይነ-መረብ አማካኝነት የተፈጸመበት ሁኔታዎች››ን[85] ጭምር ያካትታል በሚል መንግሥታት አስፍተው እንዲተረጉሙት ኮሚቴው ያቀረበው ምክረ-ሐሳብ ያትታል።

በአባወራ/ቤተሰብ የዳሰሳ ጥናቱ የተሳተፉ ሕፃናት፤ በባለፈው ዓመት ‹‹ያለፍላጎታቸው የገዛ ኃፍረተ-ሥጋቸውን የሚያሳይ ፎቶ ወይም ቪዲዮን›› የተመለከተ ጥያቄ ደርሷቸው የነበረ ስለመሆኑ ተጠይቀው ነበር። ምንም እንኳ የተጠየቁት መረጃ፤ ከአቻዎቻቸው ጋር የተላላኩትን በአንጻራዊነት የማይጎዱ መሰል ይዘቶችን ሊያካትት ቢችልም፤ ግን ደግሞ ሕፃናት የቀረጿቸውን የገዛ ራሳቸውን የሚያሳዩ ወሲባዊ ምስሎችን እና ቪዲዮዎችን በዲጂታል ቴክኖሎጂዎች አማካኝነት እንዲልኩላቸው የታሰበ ሕፃናትን በስልት የመጠምዘዝ ሙከራ መኖሩን አብሮ ሊጠቁምም ይችላል። በባለፈው ዓመት፤ በኢትዮጵያ በዳሰሳው ከተሳተፉት 84 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት ውስጥ 8 በመቶዎቹ፤ እነርሱ ፍላጎት ባላሳዩበት ሁኔታ የገዛ ኃፍረተ-ሥጋቸውን የሚያሳይ ፎቶ ወይም ቪዲዮን የተመለከተ ጥያቄ

83. ይህ አኃዝ ሁለት እርስበርሳቸው የሚጻረሩ የምረጥ መልሶችን አንድ ምላሽ ሰጪ በመምረጡ፤ አኃዙ የሁለቱን ድብልቅ ይወክላል፡ ‹‹ይህ ጉዳይ ከተፈጸመበት ጊዜ በፊት ትውውቅ የሌለኝ ወይም የማላውቀው ግለሰብ›› የሚለው እና ‹‹ግለሰቡ ማን እንደነበር አላውቅም›› የሚለውን፤
84. Interagency Working Group on Sexual Exploitation of Children. (2016). Terminology Guidelines for the Protection of Children from Sexual Exploitation and Sexual Abuse. Bangkok: ECPAT International. 50.
85. Council of Europe’s Lanzarote Committee. (2015). Opinion on Article 23 of the Lanzarote Convention and its explanatory note. Para 20.

ደርሷቸው ነበር።

**ሕፃናቱ ምን እንደተሰማቸው**፡ ስለ ወሲብ *እንዲያወሩ* እንደተጠየቁት ሕፃናት በተመሳሳዩ፤ ያለ ፍላጎታቸው ወሲባዊ ምስሎችን የተጠየቁት ሕፃናት፤ ሁኔታው የኃፍረት ስሜት ያሳደረባቸው አሊያም በተቃራኒው ጨርሶ ያልተናወጡ የመሆን አጋጣሚው ከፍ ያለለ ነበር። ወሲባዊ ምስሎች የተጠየቁበትን ቀድሞ የተጠቀሰውን ገጠመኛቸውን አብሮ ታሳቢ በማድረግ፤ ሕፃናቱ የንዴት (11 በመቶ)፣ የጸጸት (10 በመቶ)፣ እና የመጨናነቅ (10) ስሜት እንዳሳደረባቸው በማከል ገልጸዋል።

**የሕፃናቱ አጸፋ**፡ ያለፍላጎታቸው ወሲባዊ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን ከተጠየቁ 84 ሕፃናት መካከል፤ 45 በመቶዎቹ እምቢ ብለዋል፤ 10 በመቶዎቹ ችግሩን ንቀው ትተውታል፣ 10 በመቶዎቹ ሌላኛው ግለሰብ እንዲተዋቸው ለማሳመን ጥረት አድርገዋል፤ እንዲሁም 7 በመቶዎቹ ለተወሰነ ጊዜ በይነ-መረብን መጠቀም አቁመዋል። ይህ ሁኔታ ያለ ፍላጎታቸው ስለ ወሲብ እንዲያወሩ ሲጠየቁ ከሰጡት ምላሽ ጋር ይመሳሰላል። ምላሾቹ የተመሳሰሉበት ምክንያት፤ ምናልባት ሕፃናት ስለ ወሲብ እንዲያወሩ ከተጠየቁ በኋላ *ወዲያውኑ በማስከተል* ወሲባዊ ምስሎችን እንዲልኩ በዚያው ቆይታ ስለተጠየቁ ሊሆን ይችላል። እነዚህ መሰል ጥያቄዎች ከደረሳቸው ሕፃናት ውስጥ 14 በመቶዎቹ (ብዛት = 12) የተጠየቁትን ፈጽመዋል።

*ዲስረፕቲንግ ሀርም* ባተኮረባቸው በሌሎች ሃገራት ካሉ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ተጎጂዎች ጋር የተደረጉ ቃለ-መጠይቆች እንደሚጠቁሙት፤ ያለፍላጎት በበይነ-መረብ የሚላክ ጥያቄ፤ አብዛኛውን ጊዜ መደናገርን ያስከትላል። በካምቦዲያ ያለ አንድ ተጎጂ፤ የተጠየቀው ነገር ተቀባይነት ያለው ጉዳይ ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ ማወቅ ተስኖት እንደነበር ያስታውሳል፤ ‹‹አብረን እናወራ ነበር። ሰውየው ለምን እንደዚያ ዓይነት ፎቶዎችን እንዳነሣ ማውራት ጀመርን። ግን ምክንያቱን አላወቅንም ወይም አልተረዳንም፡ ፡ ለምን ፎቶ ማንሣት እንዳስፈለገው ሊገባን አልቻለም። አንዳንዴ ጓደኛዬ ‹ግማሽ አካሌ ወደ ላይ ተቀስሮ እያለ ፎቶ አነሣኝ› የሚል እና ተመሳሳይ ነገሮችን ይነግረኝ ነበር፤ እናም የምር ምንም ግድ አልሰጠንም ነበር፤ እና ሌላው ነገር ደግሞ፤ እንደዚያ ሁኖ ፎቶ መነሣት ... ያደርገን እንደነበር ... ያደርገን እንደነበር አላወቅንም ነበር፤ እንዳንዴ ነገሩ ስህተት ነው ወይስ ትክክል የሚለው ጥያቄ በጣም ያብሰለስለን ነበር››፡ ፡ (RA5-CA-02) አንድ ሌላ ተጎጂ፤ ሲፈጸምበት የነበረው ነገር ትክክል አለመሆኑ ቆይቶ ገብቶታል፤ ‹‹በተለይ የሚያደርግብኝ ነገር ትክክል አለመሆኑን ከነቃሁ በኋላ፤ ሰውየው እንዴት ስብእናዬን ያደቅቀው እንደነበር መላልሼ አስበዋለሁ››። (RA5-NA-02-A)

**ጥያቄዎቹን የሚያቀርበው ማን ነው**፡ አብዛኛውን ጊዜ እንደሚያጋጥመው፤ ሕፃናትን ያለፍላጎታቸው የገዛ ራሳቸውን የሚመለከት ወሲባዊ ይዘቶችን እንዲልኩላቸው ጥያቄውን የሚያቀርቡት፤ በዋናነት የፍቅር ጓደኞች፣ በመቀጠል የቤተሰብ አባላት፣ ጓደኞች፣ ወይም 18 ዓመት እና በላይ ዕድሜ ያለው/ላት ቀድሞ የሚያውቁት ግለሰብ፣ እንዲሁም ከ18 ዓመት በታች ያሉ ጓደኞች (12 በመቶ) ናቸው። 18 በመቶዎቹ ሕፃናት እንዳሉት፤ ጠያቂውን አስቀድሞ የማያውቁት ሲሆን፤ 14 በመቶዎቹ ደግሞ ለዚህ የዳሰሳ ጥናት ጥያቄ መልስ መስጠት አልፈለጉም። በጥቅሉ ሲታይ ሕፃናት ከማያውቁት ባይተዋር ይልቅ አስቀድሞ በሚያውቁት ሰው፤ የገዛ ራሳቸውን የሚመለከቱ ወሲባዊ  ምስሎችን ወይም ስለ ወሲብ እናውራ የሚሉ ጥያቄዎች ያለፍላጎታቸው ሊቀርብላቸው የሚችልበት ዕድል ከፍ ያለ ነበር።

**በበይነ-መረብ ወይስ ከበይነ-መረብ ውጪ?**፡ *ወሲባዊ ይዘቶችን እንዲልኩ የተጠየቁ* ሕፃናት፤ መሰል ጥያቄዎችን በአካል/በፊትለፊት ከሚጠየቁበት አጋጣሚ ይልቅ በበይነ-መረብ (በማኅበራዊ ሚዲያ እና/ወይም በበይነ-መረብ የጨዋታ ግጥሚያዎች በኩል) ዒላማ የተደረጉበት አጋጣሚ ከፍ ያለ ነበር። የወሲባዊ ምስል እና ቪዲዮ ጥያዌዎቹን ለማቅረብ በጣም በዋናነት ጥቅም ከዋሉት ማኅበራዊ ሚዲያዎች መካከል፤ ፌስቡክ አሊያም የፌስቡክ ሜሴንጀር እና ቴሌግራም ትልቁን ድርሻ ሲይዙ፤ በሕፃናቱ የተጠቀሱት ሌሎች ፕላትፎርሞች ደግሞ ትዊተር (12 በመቶ)፣ ኢሞ (12 በመቶ)፣ እና ዩቲዩብን (12 በመቶ) ያጠቃልላሉ።

**ስለጉዳዩ ሕፃናት ለማን እንደነገሩ (ካለ)**፡ ከሦስት ሕፃናት አንዳቸው፤ የወሲባዊ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን ተጠይቀው ስለነበረበት የቅርቡ አጋጣሚ ለጓደኛቸው የነገሩ ሲሆን፤ እጅግ ጥቂቶቹ ብቻ የደረሰባቸውን ነገር ለአዋቂ ሰው አካፍለዋል። 27 በመቶዎቹ (ብዛት = 23) ገጠመኛቸውን ለማንም አላዋዩም። ይህ ጥሬ መረጃ የሚያሳየው አሳሳቢ አዝማሚያ አለ፤ ይህም ሕፃናት ችግሩን በራሳቸው እየተቋቋሙ መሆኑን፤ ወይም እንዴት መራመድ እንዳለባቸው እና መሰል ጥያቄዎችን መቀበል የሚያስከትሉትን መዘዞች እንዴት እንደሚቋቋሙት በልጅ አእምሯቸው እያሰላሰሉ እንደሆነ ነው። *ያለፍላጎታቸው ወሲባዊ ምስሎችን እንዲልኩ የተጠየቁትን እና ጥያቄውንም ለማንም ያልተናገሩትን* 23 ሕፃናት በተመለከተ፤ ላለመናገራቸው ዋናው ምክንያት የት መሄድ እንዳለባቸው እና ለማን እንደሚነግሩ አለመገንዘባቸው ሲሆን፤ አንዳንዶቹ ደግሞ አንዳች ዓይነት ጥፋት እንደፈጸሙ ስለተሰማቸው ነገሩን ራሳቸው ውጠው አልፈውታል።

ሕፃናቱ ከሰጧቸው እማኝነቶች በመነሣት ሲገመገም፤ ያለፍላጎት የሚቀርቡ ጥያቄዎች በኢትዮጵያ ያሉ የተወሰኑ በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናትን የሚፈታተን ነባራዊ ችግር መሆኑ ግልጽ ነው፡ ፡ ሪፖርት ካለመደረጉ ጋር ተዳምሮ ሲታይ፤ ሕፃናት አንዳንድ አስጊ ሁኔታዎችን ለመለየት እና ጉዳት ቢደርስባቸው ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለማወቅ የሚያስችላቸውን ግንዛቤ በበቂ ሁኔታ አለመጨበጣቸውን ይህ ግኝት ይጠቁማል።

በሕፃናት ዘንድ ግንዛቤ የመፍጠር፤ ብሎም ከመሰል ሁኔታዎች ለመራቅ ወይም ለማምለጥ በሚያስችላቸው ዕውቀት እና ክህሎት ሕፃናትን የማስታጠቅ ተግባር፤ የዘርፈ-ብዙ አካላት ሥራ እና የጋራ ኃላፊነት ነው። ምናልባት ይህንን ችግር ለመቅረፍ ከሚቻልባቸው መንገዶች አንዱ፤ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን እና መገለጫ ባሕርያቱን   በካተተ መልኩ፤ ብሎም የዲጂታል ክህሎቶችን፣ እንዲሁም ሰዎችን/ላኪዎችን ማገድ ወይም ያልተገቡ የበይነ-መረብ ድርጊቶችን ሪፖርት ማድረግን የመሳሰሉ የአጸፋ እርምጃዎችን ያጠናቀረ ሥርዓተ-ትምህርትን በማዘጋጀት ነው።

በበይነ-መረብ ላይ ስላሉት የተለያዩ ዓይነት ስጋቶች ሕፃናትን ስናስተምር፤ የፍቃደኝነት/የይሁንታ መኖር አስፈላጊ ስለመሆኑ፤ በዚህ የተነሣ ደግሞ አብረው ሊከሠቱ ስለሚችሉ (በተለይም የገዛ ራሳቸውንም ሆነ የሌሎችን ወሲባዊ ምስሎችን መላክ) ስጋቶች በትምህርቱ ውስጥ አጽንኦት መስጠት ወሳኝ ጉዳይ ነው፡ ፡ በተጨማሪም፤ ብዙዎቹ እኒህ ጥያቄዎች የሚላኩት በማኅበራዊ ሚዲያ ፕላትፎርም በኩል እንደመሆኑ፤ ሕፃናት በበይነ-መረብ ለሚፈጸም ማናቸውም ዓይነት ጉዳት ወይም ወሲባዊ በደል ቢዳረጉ ሕፃናቱ ማድረግ ስላለባቸው ነገሮች (ለምሳሌ ለሚያምኑት አዋቂ ሰው ሪፖርት ማድረግ ወይም ማሳወቅ ስለሚችሉበት አግባብ) የሚጠቁሙ ምክሮችን (ሕፃናት በሚገነዘቧቸው ቃላት) በፕላትፎርሞቹ ላይ ሊቀርብ የሚገባ አስፈላጊ ጉዳይ መሆኑ ግልጽ ነው። እነዚህ ፕላትፎርሞች አጠራጣሪ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ

## በባለፈው


# ዓመት ውስጥ ያለፍላጎቴ ኃፍረተ-ሥጋዬን የሚያሳይ ፎቶ ወይም ቪዲዮ እንዳጋራ ተጠይቄ ነበር

መደብ፡ በኢትዮጵያ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት፤
ብዛት = 1 ሺህ ሕፃናት

**አዎ 8%**




## ይህ የሆነበት የቅርቡ ጊዜ ገጠመኝ ...












ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ ያለፍላጎታቸው ወሲባዊ ምስሎችን እንዲልኩ የተጠየቁ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 84 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት




ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ ያለፍላጎታቸው ወሲባዊ ምስሎችን እንዲልኩ የተጠየቁ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 84 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት




ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ ያለፍላጎታቸው ወሲባዊ ምስሎችን በማኅበራዊ ሚዲያ በኩል እንዲልኩ በጣም በቅርቡ ጥያቄ የቀረበላቸው ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 26 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት


* እነዚህ አኃዞች በልጆች የተመረጡትን እና በጣም የተለመዱ ምላሾችን ይወክላሉ

** እነዚህ አሃዞች በልጆች የተመረጡትን በጣም የተለመዱ እና በጣም ያልተለመዱ ምላሾችን ይወክላሉ

† የምርጫ ጥያቄ




ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ ያለፍላጎታቸው ወሲባዊ ምስሎችን እንዲልኩ የተጠየቁ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 84 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት




ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ ያለፍላጎታቸው ወሲባዊ ምስሎችን እንዲልኩ ስለተጠየቁበት የቅርቡ ጊዜ አጋጣሚ ለማንም ያልነገሩ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 23 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

ምንጭ የዲስረፕቲንግ ሀርም ጥሬ መረጃ

# 2.2 በኢትዮጵያ ስላለው የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የሕፃናቱ ተሞክሮዎች

እና በደልን የተመለከቱ ጉዳዮች ሪፖርት ሲደርሳቸው፤ ለሪፖርቶቹ ፈጣን ምላሽ የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው፤ ምናልባትም ግዴታው በሕግም ሊደነገግ ይገባል።

> አዋቂዎች እና ሕፃናት ስለ ወሲብ-ነክ ገጠመኞች ይበልጥ ግለጽ የሆነ ውይይት ማድረግ እንዳለባቸው አንድ የማሌዥያ ተሳኚ በአጽንኦት ተናግሯል፤ ‹‹ሰዎች ስለ ጉዳዩ ይበልጥ መወያየት እንዳለባቸው ይሰማኛል፤ ተንከባካቢዎችም ልጆቻቸው ገና ዕድሜያቸው ሳይጠና ጀምሮ እነዚህን ዓይነት ውይይቶች ከልጆቻቸው ጋር ማድረግ አለባቸው፤ ለምሳሌ ‹አንድ ሰው እንዲህ ማድረግ ከጀመረ፤ እንዲህ ዓይነት ነገር ካደረገ፤ ያንን ያደረጉት ለእናንተ አስበውላችሁ ሳይሆን እናንተን ሊጠቀሙባችሁ ስለሚፈልጉ ነው› [ብሎ መንገር]፤ እና እንደዚያ ዓይነት ነገሮችን … ቀጣዩ [የወላጆች] ትውልድ በተሻለ ሁኔታ ልጆችን እንደሚያሳድግ እና ከእነርሱ ጋርም እኒህን ዓይነት ውይይቶች ያደርጋል ብዬ አስባለሁ››። (RA5-MY-01-A)

### ወሲባዊ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን ለማግኘት ሕፃናትን በገንዘብ ወይም በስጦታ መደለል

ወሲባዊ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን ለማግኘት ሕፃናትን በገንዘብ ወይም በስጦታ የመደለል ድርጊት፤ የሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶችን ለማግኘት ታስቦ የሚደረግ የማሸከረመም ተግባር መኖሩን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሆኖ ይወሰዳል። 74 ሕፃናት (በዳሰሳው ከተሳተፉት ከኢትዮጵያ በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት ውስጥ 7 በመቶዎቹ)፤ በባለፈው ዓመት ውስጥ የገዛ ራሳቸውን የሚያሳዩ ወሲባዊ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን ቢልኩ በምትኩ ገንዘብ ወይም ስጦታ እንሰጣችኋለን የሚል ጥያቄ ገጥሟቸዋል። እነዚህ ሕፃናት ባሉባት በዚህ ቡድን አባላት መካከል ይህ ነው የሚባል ጉልህ የዕድሜ ወይም የጾታ ልዩነቶች አልተስተዋለም።

**መደለያውን ለመስጠት ቃል የገባው ማን ነው**፡ በባለፈው ዓመት ለዚህ ነገር የተዳረጉ ሕፃናት እንዳሉት ከሆነ፤ እነዚህ መደለያዎች በዙሪያቸው ካሉ ቅርብ ሰዎች የሚሰነዘርበት ሁኔታ እጅግ ያመዘነ ነበር፤ ምክንያቱም ለ25 በመቶዎቹ ሕፃናት በገንዘብ ወሲባዊ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን ለማግኘት ጥያቄ የቀረበው ከቤተሰብ አባላቸው ሲሆን፤ በቅርብ አኃዝ የሚከተሉት ደግሞ የፍቅር ጓደኞች፣ ጓደኞች ወይም 18 ዓመት እና በላይ ዕድሜ ያላቸው ቀድሞ የሚያውቋቸው ሰዎች፣ እንዲሁም ጓደኞች ወይም ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ቀድሞ የሚያውቋቸው ሰዎች ናቸው። በገንዘብ ወይም በስጦታ በመደለል ወሲባዊ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን ለማግኘት ከማይታወቁ ሰዎች ጥያቄ የቀረበላቸው ሕፃናት 22 በመቶ ያህል የሚሆኑት ናቸው።

**በበይነ-መረብ ወይስ ከበይነ-መረብ ውጪ?** በዚህ ምዕራፍ እንደገለጹት እንደሌሎቹ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ዓይነቶች ባለ መልኩ፤ ያልተፈለጉ ጥያቄዎች ለሕፃናት የሚላኩት በዋናነት በበይነ-መረብ አውታሮች በኩል ነው። ሆኖም 22 በመቶ ሕፃናት ድርጊቱ የደረሰባቸው በአካል/ ፊትለፊት ግንኙነት መሆኑን እና 16 በመቶዎቹ ደግሞ ጥያቄው በሌላ መንገድ እንደደረሳቸው ገልጸዋል። ርእሰ-ጉዳዩ ስሱ መሆኑ ሲታሰብ፤ ለዚህ የዳሰሳ ጥያቄ በርካታ (27 በመቶ) ምላሽ ሰጪዎች መልስ መንፈጋቸው አስገራሚ አይሆንም። የገንዘብ ወይም የስጦታ መደለያ በመስጠት በምትኩ ወሲባዊ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን እንዲልኩላቸው በማኅበራዊ ሚዲያ በኩል ጥያቄ በመቀበል ረገድ በጣም የቅርብ ጊዜ ገጠመኝ ያላቸው 15 ሕፃናት እንዳሉት፤ እነዚህ ክሥተቶች የተፈጠሩት በፌስቡክ ወይም በፌስቡክ ሜሴንጀር፣ በቴሌግራም፣ በትዊተር፣ በኢሞ፣ እና በላይን (7 በመቶዎቹ) ነው።

**ስለጉዳዩ ሕፃናት ለማን እንደነገሩ (ካለ)**፡ ከ74ቱ ሕፃናት 33 በመቶዎቹ እጅግ የቅርቡን ገጠመኛቸውን ለጓደኛቸው የነገሩ ሲሆን፤ 6 በመቶዎቹ ደግሞ ለወንድም/እኅታቸው ነግረዋል። በአንጻሩ፤ 16 በመቶዎቹ ለወላጆቻቸው ወይም ለተንከባካቢያቸው (11 በመቶዎቹ ለአባታቸው፤ 5 በመቶዎቹ ለእናታቸው) ጉዳዩን የነገሩ ሲሆን፤ 9 በመቶዎቹ ደግሞ ዕርዳታ ፍለጋ ወደ መምህራቸው አምርተዋል። ወሲባዊ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን ቢልኩ የገንዘብ ወይም የስጦታ መደለያ እንደሚሰጣቸው ቃል ከተገባላቸው ወይም ጥያቄው ከቀረበላቸው ሕፃናት ውስጥ 25 በመቶ የሚጠጉት፤ ለማንም አልነገሩም። ላለመንገራቸው ዋና ምክንያት አድርገው እነዚህ 17 ሕፃናት ያነሷቸው ችግሮች፤ የት መሄድ እንዳለባቸው እና ለማን እንደሚነግሩ አለማወቃቸው፤ ብሎም የኃፍረት ስሜት ማሳደር የሚሉት ናቸው። በቁጥር ኢምንት የሆኑ ሕፃናት ብቻ ጉዳዩን ለዕርዳታ መጠየቂያ መስመሮች (ብዛት = 1)፣ ለማኅበራዊ ሠራተኞች (ብዛት = 1)፣ ወይም ለፖሊስ (ብዛት = 1) አሳውቀዋል፡
፡ አቤቱታ/ሪፖርት በማድረግ ረገድ በሌሎቹ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ዓይነቶች ላይ እንዳለው ሁሉ፤ በገንዘብ መደለያ ወሲባዊ ይዘቶችን የተጠየቁ ሕፃናትም ኢትዮጵያ ውስጥ በሥራ ላይ ያሉትን መደበኛ የአቤቱታ/ሪፖርት ማቅረቢያ አሠራሮችን የተጠቀሙበት ሁኔታ እጅግ ያነሰ ሲሆን፤ እጅግ ለከፋ እና ምናልባትም ሰቆቃ ለሚያስከትል ገጠመኝ በሚዳረጉበት ወቅት ከአዋቂዎች ይልቅ በእጅጉ በዕድሜ አቻዎቻቸው ላይ መመርኮዝ ይቀናቸዋል። ይህ ሁኔታ፤ ምክር የተጠየቁት ታዳጊዎች አቅጣጫ እንዲያሳዩ እና ለእነዚህ መሰል ዱብ እዳ ለሆኑ ጥያቄዎች የተሻለ ምላሽ እንዲሰጡ የሚሻ ከባድ ሸክም እንዲወድቅባቸው ያደርጋል፡
፡ ሕፃናትን ጨምሮ በምልአተ-ሕዝቡ ዘንድ በኢትዮጵያ ውስጥ ስለ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ያለው ግንዛቤ አነስተኛ ከመሆኑ አንጻር፤ ይህ አዝማሚያ በተለይ የሚያሳስብ ጉዳይ ነው። (ገጽ xx ን ይመለከቷል)።

### በአካል በመቅረብ ለሚፈጸሙ ወሲባዊ ድርጊቶች ለሕፃናት የገንዘብ እና የስጦታ መደለያ ማቅረብ

በኢትዮጵያ ውስጥ አባወራ/ቤተሰብ የዳሰሳ ጥናቱ ከተሳተፉት ሕፃናት 7 በመቶዎቹ፤ በባለፈው ዓመት ውስጥ በአካል/በፊትለፊት በመገናኘት አንዳች ዓይነት ወሲባዊ ነገርን እንዲያከናውኑ የገንዘብ ወይም የስጦታ መደለያ ቀርቦላቸው እንደነበር ገልጸዋል፡
፡ እንደብዙዎቹ እነዚህን መሰል ጉዳዮች፤ ሕፃናት የደረሰባቸውን የብዝበዛ እና የበደል ገጠመኞችን ለማሳወቅ ምቾት ወይም የሚያስተማምን ደኅንነት ላይሰማቸው ስለሚችል እነዚህ አኃዞች ከትክክለኛው መጠን በታች ሊሆኑ እንደሚችሉ መገመት ይቻላል።

**በበይነ-መረብ ወይስ ከመበይነ-መረብ ውጪ?**፡ በአካል/ በፊትለፊት በመገናኘት ለሚከናወኑ ወሲባዊ ድርጊቶች ለሕፃናት የገንዘብ እና የስጦታ መደለያ የማቅረብ ተግባር፤ ቴክኖሎጂን መጠቀም ሳያስፈልግ ሙሉ በሙሉ ‹ከበይነ-መረብ ውጪ› ሊደረግ ይችላል። ሕፃናት ስለ ወሲብ እንዲያወሩ የተጠየቁበት እጅግ የቅርቡ ገጠመኛቸውን በተመለከተ ጥያቄው የደረሳቸው በማኅበራዊ ሚዲያ፣ በበይነ-መረብ ላይ ባደረጉት የጨዋታ ግጥሚያ፣ ወይስ በሌላ መንገድ እንደሆነ ለሕፃናቱ መጠይቅ ተደርጎላቸው ነበር፡
፡ በባለፈው ዓመት ውስጥ በአካል ቀርበው ለሚያከናውኗቸው ወሲባዊ ድርጊቶች የገንዘብ እና የስጦታ መደለያ ቀርቦላቸው ነበር ካሉት 58 ሕፃናት መካከል 18 በመቶዎቹ፤ መሰል ጥያቄዎችን የተቀበሉት በአካል/በፊትለፊት በተደረገ ግንኙነት/ቆይታ አማካኝነት ነበር። እነዚህ መሰል ጥያቄዎች ምላሽ ሰጪዎቹ በበይነ-መረብ አውታሮች በኩል የመቀበል አጋጣሚያቸው ያመዝናል፤ ምክንያቱም 21 በመቶዎቹ በማኅበራዊ ሚዲያ፤ እንዲሁም 18 በመቶዎቹ

በበይነ-መረብ የጨዋታ ግጥሚያ በኩል የደረሳቸው በመሆኑ ነው፡ ፡ 10 ያህል ሕፃናት ጥያቄው የደረሳቸው በሌላ መንገድ እንደሆነ ሲገልጹ፤ 25 በመቶዎቹ ደግሞ ምናልባት ስለ ክሥተቱ ዝርዝር ነገሮችን ቢናገሩ ሌላ ሚሥጥር እንዳይሾልክባቸው ከማቅማማት የተነሣ ለዚህ መጠይቅ መልስ አልሰጡም። ይህን መሰሉ ገጠመኝ በማኅበራዊ ሚዲያ በኩል ከደረሰባቸው ሕፃናት መካከል፤ የብዙዎቹ የቅርቡ ገጠመኝ በፌስቡክ ወይም በፌስቡክ ሜሴንጀር፣ በቴሌግራም፣ እና በኢሞ ላይ የተከሠተ ነበር።

**መደለያዎቹን ያቀረበው ማነው?** በሕጻኑ/ኗ ከማይታወቁ ከባይተዋር ሰዎች ይልቅ፤ ከሕፃኑ/ኗ ጋር የቀደመ ትውውቅ ያላቸው ግለሰቦች እነዚህን መሰል ድርጊቶች የፈጸሙበት አጋጣሚ እጅግ የላቀ ነበር። ሕፃናቱ የሰጡት መልሶች እንደሚያመለክቱት፤ ወሲባዊ ድርጊቶችን በአካል ተገናኝቶ ለማከናወን የገንዘብ እና የስጦታ መደለያዎችን በበይነ-መረብ ለሕፃናት በማቅረብ ረገድ የአሁን ወይም የበፊት የፍቅር ጓደኞች እና የቤተሰብ አባላት አመዛኙን ድርሻ ይዘዋል። በሕፃኑ/ኗ በማይታወቅ ግለሰብ የተፈጸሙት ድርጊቶች አምስት ብቻ ናቸው።

**ስለጉዳዩ ሕፃናት ለማን እንደነገሩ (ካለ)፡** አሁንም በድጋሚ፤ ሕፃናት መደበኛ የአቤቱታ ማቅረቢያ መስመሮችን የተጠቀሙበት አጋጣሚ እጅግ ያነሰ እና፤ ይልቁንስ ለግል ወዳጆቻቸው ማካፈል ይቀናቸዋል (በገጽ xx ላይ የቀረበውን ገላጭ ምስል ይመለከቷል)። በተመሳሳይም ሕፃናት ለጓደኛቸው ወይም ለወንድ ተንከባካቢያቸው የመንገር ዝንባሌ ነበራቸው። በአካል/በፊትለፊት በመገናኘት ወሲባዊ ድርጊቶችን እንዲያከናውኑ የገንዘብ እና የስጦታ መደለያ ከቀረበላቸው 20 ሕፃናት ውስጥ አራቱ ለማንም ያልነገሩ ሲሆን፤ ምክንያታቸው ደግሞ  የት መሄድ እንዳለባቸው ወይም ለማን እንደሚነግሩ አለመገንዘባቸው፣ የመሸማቀቅ እና የኃፍረት ስሜት ያደረባቸው መሆኑ፣ እንዲሁም ጉዳዩ በሚሥጥር ተጠብቆ ላይቆይ ይችላል የሚሉት ናቸው።

### ለወሲብ በማስገደድ-መጠቀም

ለወሲብ አስገድዶ-መጠቀም/sexual extortion ድርጊት አንዳንዴ በማሽኮርመም ሂደት ላይ ጥቅም ላይ ይውላል። አብዛኛውን ጊዜ እንደሚሰተዋለው፤ ጥፋት ፈጻሚዎቹ ቀድሞውኑ የሕፃናቱን ወሲባዊ ምስሎችን በእጃቸው ካስገቡ በኋላ፤ ሕፃናት ተጨማሪ ምስሎችን እንዲልኩላቸው ወይም በሌሎች ዓይነት ወሲባዊ ተግባራት እንዲሳተፉ ለማስገደድ በሚያስችላቸው አኳኋን በእጃቸው ያለውን ምስል በይፋ ለሕዝብ እንደሚናኙት አሊያም ለጓደኞቻው እና ለቤተሰባቸው አባላት እንደሚልኩላቸው በመንገር ሕፃናትን ያስፈራሩበታል። አስገድዶ ገንዘብ ለመውሰድም መሰል ማስፈራሪያ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል። በበይነ-መረብ አውታሮች በኩል በሕፃናት ላይ ዛቻ እና በመያዣ የማስፈራራት ድርጊት ስለመኖሩ የሚያሳይ ማስረጃ ቢኖርም፤ በአንጻሩ ግን በበይነ-መረብ አማካኝነት የሚፈጸም ለወሲብ አስገድዶ-መጠቀም/sexual extortion ድርጊትን በወንጀልነት የሚደነግግ ሕግ በኢትዮጵያ ውስጥ የለም።

በኢትዮጵያ በተካሄደው የ*ዲስረፕቲንግ ሀርም* የአባወራ/ቤተሰብ የዳሰሳ ጥናት መሠረት፤ 5 በመቶዎቹ በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት(ብዛት = 55)፤ በባለፈው ዓመት ውስጥ ቢያንስ አንዴ በወሲባዊ ተግባራት እንዲሳተፉ ዛቻ ወይም የመያዣ-ማስፈራሪያ እንደደረሳቸው ገልጸዋል። በዚህ ንዑስ-ምዕራፍ ላይ በከፍተኛ መጠን መልስ የተነፈጋቸው አንዳንድ ጥያቄዎች መኖራቸው እንደታየው ሁሉ፤ ሕፃናት ለዚህኛውም ጥያቄ መልስ መስጠት እምብዛም ምቾት ላይሰጣቸው ስለሚችል፤ አኃዙን በማሳነስ ወይም በማጉደል የተገለጸ ሊሆን ይችላል።

*ዲስረፕቲንግ ሀርም* በተካሄደባቸው ሌሎች ሃገራት ውስጥ ለወሲብ አስገድዶ-መጠቀም/sexual extortion ተጠቂዎች ጋር በተደረጉ ቃለ-መጠይቆች ላይ አስገድዶ-መጠቀም ስለተፈጸመበት ሂደት ተብራርቷል፤ ‹‹የእኔን ፎቶ እንደሚፈልግ ነገረኝ፤ ምንም ነገር እንደማልልክለት ነገርኩት፤ አይሆንም፤ በምንም ዓይነት አይሆንም። ከዚያ በኋላ ማስፈራራት ጀመረ፡ ፡ የሁሉንም ጓደኞቼን ስም ዝርዝር ከእኔ ስክሪን ላይ ፎቶ አንሥቶ ወሰደ። ከዚያም ፎቶዎችን የማልልክለት ከሆነ፤ከዚህ በፊት ደርሶት የነበሩትን ሁሉንም ፎቶዎች በዝርዝሩ ውስጥ ላሉት ጓደኞቼ በሙሉ እንደሚልክላቸው ነገረኝ።›› (RA5-CA-07-A) ተጎጂዎቹ በሰጧቸው እማኝነቶች ላይ ሁሉ ምስሎችን የማሠራጨት ማስፈራሪያ በተደጋጋሚ ተጠቅሷል። ‹‹ ‹ያልኩሽን ካላደረግሽ፤ ዕርቃንሽን ተነሥተሽ የላክሺልኝን ፎቶዎች ይፋ አወጣቸዋለሁ፤ ሁሉንም በኢንታግራም እና በፌስቡክ እና በቲክቶክ ላይ እለጥፋቸዋለሁ፤ እንዲሁም በዋትአፕ ላይም አሠራጨቸዋለሁ› እያለ ያስፈራራኝ ጀመር። ‹እባክህ እንደዚያ አንኳ አታድርግብኝ፤ እንዳታደርገው፤ ፎቶዎቼን ማኅበራዊ ሚዲያ ላይ እንዳታወጣቸው› እያልኩ ለመንኩት። ያሳየኝ ‹አይሆንም፤ ያበቃ ነገር ነው› ዓይነት ጸባይ ነበር።

መሰል ዛቻዎች በአካል/በፊት ለፊት ሊሰነዘርባቸው እንደሚችለው ሁሉ፤ በተመሳሳዩ በበይነ-መረብ (በማኅበራዊ ሚዲያ እና በበይነ-መረብ የጨዋታ ግጥሚያ) ላይም ለወሲብ አስገድዶ-የመጠቀም ድርጊት ሊዳረጉ ይችላሉ። ይህ ክሥተት፤ ማለትም በበይነ-መረብም ሆነ ከበይነ-መረብ ውጪ  የበደል ድርጊቱ ሊፈጸም የሚችልበት አጋጣሚ እኩል ወይም ተመሳሳይ የመሆኑ ጉዳይ፤ የአባወራ/ቤተሰብ የዳሰሳ ጥናቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኘው የተለየ የበደል አፈጻጸም ጠባይ ነው። የዚህ ምክንያት ምናልባት ብዙዎቹ አጥፊዎች ለሕፃኑ/ኗ ቅርብ ከሚባሉት ሰዎች ውስጥ የሚመደቡ ከመሆናቸው ጋር የተቆራኘ እና፤ በዚህ የተነሣም ለሕፃኑ/ኗ ተደራሽነት ያላቸው እና ገጽ-ለገጽ በመገናኘት መሰል ዛቻዎችን ለመሰንዘር ስለሚችሉ ነው። በማኅበራዊ ሚዲያ ወይም በበይነ-መረብ የጨዋታ ግጥሚያ አማካኝነት እጅግ በቅርቡ ድርጊቱ እንደተፈጸመባቸው የገለጹት ሕፃናት ብቻ (ብዛት = 20) በቀጣዩ ትንታኔ ውስጥ እንዲካተቱ ተደርገዋል።

በበይነ-መረብ ለተፈጸመ ለወሲብ አስገድዶ-የመጠቀም ተግባር ስለተዳረጉት 20 ሕፃናት በተመለከተ፤ እጅግ የሚያመዝኑት አጥፊዎች የአሁን ወይም የቀድሞ የፍቅር ጓደኞች ሲሆኑ፤ በቅርብ ርቀት የሚከተሉት ደግሞ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ጓደኞች ወይም የቀደመ ትውውቅ ያላቸው ናቸው፡ ፡ አጥፊዎቹ የማይታወቁ ባይተዋሮች የሆኑባቸው አጋጣሚዎች አሉ። ምንም እንኳ ከ‹ባይተዋር አደጋ› ለመዳን የሚተገበሩ የመከላከል እርምጃዎች አስፈላጊ ቢሆኑም፤ በበይነ-መረብ በኩል በሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች ዙሪያ የሚካሄዱ ተዋስኦዎች/ውይይቶች ላይ፤ በሕፃናት ሕይወት ውስጥ ጠልቀው የገቡትን ሰዎች ትቶ በባይተዋሮች ላይ ከልክ ያለፈ ትኩረት የመስጠት ዝንባሌ፤ ጥሬ መረጃዎቹ በግልጽ ከሚያሳዩት ሂደት ጋር የሚቃረን እና ከውጤታማነትም ሊያሰናክል ይችላል። በምላሽ አሠጣጥ ሥርዓቶች ሊካተት የሚገባው ሌላኛው ታሳቢ ጉዳይ፤ ተጠቂዎቹ የአጥፊዎቹ የስሜት እና/ወይም የኢኮኖሚ ጥገኛ ከሆኑ ከእነዚያው ከሚያውቋቸው አጥፊዎች ዕርዳታ ለመጠየቅ ለተጠቂዎቹ እጅግ በጣም ሊከብዳቸው እንደሚችል ነው።

በበይነ-መረብ ለተፈጸመ ወሲባዊ አስገድዶ-መጠቀም የተዳረጉ ሕፃናት፤ ስለ ሁኔታው ለጓደኛቸው ወይም ለወንድማቸው/

መደብ፡ በኢትዮጵያ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት፤
ብዛት = 1 ሺህ ሕፃናት

OCSEA

# በባለፈው ዓመት ውስጥ በገንዘብ ወይም በስጦታ መደለያ ወሲባዊ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን እንድልክ ተጠይቄ ነበር

አዎ 7%

## ይህ የሆነበት የቅርቡ ጊዜ ገጠመኝ ...

ብዛት = ወሲባዊ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን ለማግኘት የገንዘብ ወይም የስጦታ መደለያ የቀረበላቸው ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 74 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

### ይህንን ያደረገው ማን ነው?

- 27% — የቤተሰብ አባል
- 25% — የፍቅር ጓደኛ (ወይም የበፊት)
- 16% — ጓደኛ/ቀደሞ የማውቀው (ከ18 ዓመት ዕድሜ በላይ)
- 14% — ጓደኛ/ቀደሞ የማውቀው (ከ18 ዓመት ዕድሜ በታች)
- 7% — ባልናገር እመርጣለሁ
- 22% — በሕፃኑ/ኗ የማይታወቅ ሰው

### የት ነው የተከሠተው?

- 20% — በማኅበራዊ ሚዲያ
- 20% — በአካል
- 18% — በበይነ-መረብ የጨዋታ ግጥሚያ
- 16% — በሌላ መንገድ

ብዛት = ወሲባዊ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን ለማግኘት የገንዘብ ወይም የስጦታ መደለያ የቀረበላቸው ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 74 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

### ጉዳዩ የተከሠተው በየትኛው ፕላትፎርም ላይ ነው?

- በፌስቡክ ወይም በፌስቡክ ሜሴንጀር — 47%
- በቴሌግራም — 33%
- በትዊተር — 27%

ብዛት = ወሲባዊ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን ለማግኘት በጣም በቅርብ ጊዜ የገንዘብ ወይም የስጦታ መደለያ በማኅበራዊ ሚዲያ የቀረበላቸው ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 15 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

### ለማን ነገርህ/ሽ?

የመጀመሪያ 3

- ለጓደኛዬ — 34%
- ለማንም አልተናገርኩም — 23%
- ለወንድሜ ወይም ለእኅቴ — 15%

የመጨረሻ 3

- 1% — ለማኅበራዊ ሠራተኛ
- 1% — ለዕርዳታ መጠየቂያ መስመር
- 1% — ለፖሊስ

ብዛት = ወሲባዊ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን ለማግኘት የገንዘብ ወይም የስጦታ መደለያ የቀረበላቸው ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 74 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

### ለምን ለሰው አልነገርክ/ሽም?

- ለማን መንገር እንደነበረብኝ ስላላወቅኩኝ — 35%
- አላውቅም — 33%
- የኃፍረት ስሜት ስለተሰማኝ — 24%

ብዛት = ወሲባዊ ምስሎችን ወይም ቪዲዮዎችን ለማግኘት በቅርብ ጊዜ የገንዘብ ወይም የስጦታ መደለያ የቀረበላቸው እና ለማንም ያልነገሩ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 74 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

* እነዚህ አኃዞች በልጆች የተመረጡትን እና በጣም የተለመዱ ምላሾችን ይወክላሉ
** እነዚህ አሃዞች በልጆች የተመረጡትን በጣም የተለመዱ እና በጣም ያልተለመዱ ምላሾችን ይወክላሉ
† የምርጫ ጥያቄ

ምንጭ የዲስረፕቲንግ ሀርም ጥሬ መረጃ

OCSEA

በባለፈው

# ዓመት ውስጥ በአካል/በፊትለፊት ተገኝቼ ወሲባዊ ድርጊቶችን እንዳከናውን የገንዘብ ወይም የስጦታ መደለያ ቀርቦልኝ ነበር

መደብ፡ በኢትዮጵያ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት፤
ብዛት = 1 ሺህ ሕፃናት

አዎ 7%

## ይህ ጉዳይ በበይነ-መረብ የተፈጸመበት የቅርቡ ጊዜ ገጠመኝ ...

ይህንን ያደረገው ማን ነው?

| ማን | % |
|---|---|
| የፍቅር ጓደኛ (ወይም የበፊት) | 31% |
| የቤተሰብ አባል | 28% |
| ጓደኛ/ቀደሞ የማውቀው (ከ18 ዓመት ዕድሜ በላይ) | 23% |
| ጓደኛ/ቀደሞ የማውቀው (ከ18 ዓመት ዕድሜ በታች) | 12% |
| በሕፃኑ/ኗ የማይታወቅ ሰው | 20% |

ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ በአካል/በፊትለፊት በመገኘት ወሲባዊ ድርጊቶችን እንዲያከናውኑ የገንዘብ ወይም የስጦታ መደለያ በበይነ-መረብ በኩል የቀረበላቸው ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 25 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

### የት ነው የተከሠተው?

| የት | % |
|---|---|
| በማኅበራዊ ሚዲያ | 21% |
| በአካል | 19% |
| በበይነ-መረብ የጨዋታ ግጥሚያ | 18% |
| በሌላ መንገድ | 16% |

ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ በአካል/በፊትለፊት በመገኘት ወሲባዊ ድርጊቶችን እንዲያከናውኑ የገንዘብ ወይም የስጦታ መደለያ የቀረበላቸው ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 68 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

### ጉዳዩ የተከሠተው በየትኛው ፕላትፎርም ላይ ነው?

| ፕላትፎርም | % |
|---|---|
| በፌስቡክ ወይም በፌስቡክ ሜሴንጀር | 85% |
| በቴሌግራም | 23% |
| በኢሞ | 23% |
| በዩቲዩብ | 8% |

ብዛት = በአካል/በፊትለፊት በመገኘት ወሲባዊ ድርጊቶችን እንዲያከናውኑ በጣም በቅርቡ የገንዘብ ወይም የስጦታ መደለያ በማኅበራዊ ሚዲያ በኩል የቀረበላቸው ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 14 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

* እነዚህ አኃዞች በልጆች የተመረጡትን እና በጣም የተለመዱ ምላሾችን ይወክላሉ
** እነዚህ አሃዞች በልጆች የተመረጡትን በጣም የተለመዱ እና በጣም ያልተለመዱ ምላሾችን ይወክላሉ
† የምርጫ ጥያቄ

### ለማን ነገርህ/ሽ?

የመጀመሪያ 3

- ለወንድ ተንከባካቢ 24%
- ለጓደኛዬ 24%
- ለማንም አልተናገርኩም 16%

የመጨረሻ 3

- 4% ለሌላ የማውቀው እና የማምነው አዋቂ ሰው፤
- 4% ለአስተማሪ ወይም ለማእምር/ educator
- 4% ለማኅበራዊ ሠራተኛ
- 4% ለዕርዳታ መጠየቂያ መስመር
- 4% ለፖሊስ

ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ በአካል/በፊትለፊት በመገኘት ወሲባዊ ድርጊቶችን እንዲያከናውኑ የገንዘብ ወይም የስጦታ መደለያ በበይነ-መረብ በኩል የቀረበላቸው ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 25 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

### ለምን ለሰው አልነገርክ/ሽም?

| ምክንያት | % |
|---|---|
| የኃፍረት ስሜት ስለተሰማኝ | 50% |
| ጉዳዩ በሚሥጥር አይጠበቅም ብዬ ስለሰጋሁ | 25% |
| ለማን መንገር እንደነበረብኝ ስላላወቅኩኝ | 25% |

ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ በአካል/በፊትለፊት በመገኘት ወሲባዊ ድርጊቶችን እንዲያከናውኑ የገንዘብ ወይም የስጦታ መደለያ በበይነ-መረብ በኩል ለቀረበላቸው የመጨረሻው ጥያቄ ለማንም ያልነገሩ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 4 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

ምንጭ የዲስረፕቲንግ ሀርም ጥሬ መረጃ

እኅታቸው የሚነግሩበት አጋጣሚ ያመዘነ ነበር። አንድ ሕፃን ብቻ ለፖሊስ አሳወቁል/ቃለች፤ ሁለት ያህሉ ለዕርዳታ መጠየቂያ መስመር ያመለከቱ ሲሆን፤ ቁጥራቸው 20 ከሚሆኑት ከእነዚህ ሕፃናት መካከል አራቱ ለማንም አልነገሩም።

## 2.2.2 የሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶች እና የሕፃናት ወሲባዊ በደልን በቀጥታ ሥርጭት ማስተላለፍ

የኢትዮጵያ ሕግ የሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶችን በሁለንተናዊ መልኩ ብያኔ አይሰጠውም፤ በወንጀልነትም አይደነግገውም። ከዚህ ጋር የሚዛመዱት ብቸኛ ድንጋጌዎች፤ በወንጀል ሕጉ የተካተተው ‹‹ጸያፍ እና ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ››[86] ነገሮችን ከማሠራጨት ጋር የተያያዙ ድርጊቶችን በሕገ-ወጥነት የሚደነግገው (ሕጉ የጥፋቱን ምንነት የተመለከተ ብያኔ ስላላስቀመጠ ለአተረጓጎም ያሻማል) እና፤ የኮምፒዩተር ወንጀልን ለመደንገግ የወጣው አዋጅ፤ ለአካለ-መጠን ያልደረሱ (ወይም ሲታዩ ለአካለ-መጠን ያልደረሱ እንዲመስሉ የተደረጉ ሰዎች) ግልጽ በሆነ አኳኋን ወሲብን ሲፈጽሙ የሚያሳዩ ትዕይንታዊ ቁሳቁሶች (visual materials) ጋር የሚገናኙ ልዩ ልዩ አድራጎቶችን በወንጀልነት ይደነግጋል[87]። ይህ አንቀጽ ለወሲባዊ ዓላማ የአንድን ሕፃን ወሲብ ቀስቃሽ ብልቶችን ማሳየትን፤ ኢ-ትእይንታዊ (non-visual) ቁሳቁሶችን፤ ብሎም በምናብ የተፈጠሩ ሕፃናትን እውን የሚመስል ገጽታ በማላበስ የተሰናዱትን ጨምሮ በዲጂታል ቴክኖሎጂ የተፈበረኩ የሕፃናት ወሲባዊ በደል ቁሳቁሶችን አይሸፍንም። በተጨማሪም፤ የሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶችን ሆን ብሎ ወይም በማወቅ የመቀበል ድርጊትን እንደ ወንጀል አድራጎት አይደነግግም።

የሕፃናት ወሲባዊ በደልን በቀጥታ-ሥርጭት የማስተላለፍ ድርጊት በኢትዮጵያ ሕግ ውስጥ እንደ ወንጀል አድራጎት አልተደነገገም፡ ፡ ሆኖም የወንጀል ሕጉ ‹‹ጸያፍ ወይም ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆኑ ነገሮችን በትያትር፣ በሲኒማ፣ በተንቀሳቃሽ ፊልሞች፣ በራዲዮ፣ በቪዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ››[88] እንዲተላለፍ የማደራጀት ተግባርን የሚወነጅል ድንጋጌ ይዟል፡ ፡ ይሁንና፤ ጸያፍ ወይም ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሚያሰኙ ነገሮች ምን እንደሆኑ የሚያመለክት ትርጓሜ ግን አልቀረበም፡ ፡ በተጨማሪም፤ በኢትዮጵያ ሕግ ውስጥ፤ አንድን ሕፃን በብልግና ተውኔቶች (pornographic performances) ወስጥ እንዲሳተፍ መመልመል፣ መንሥኤ መሆን፣ ወይም የማስገደድ ተግባር፤ ብሎም ሕፃናትን የሚያሳይ የብልግና ተውኔት መሆኑን እያወቀ በእነዚህ ተውኔቶች ላይ የመታደም ተግባራት እንደ ወንጀል አድራጎት አልተደነገገም።

በአሁኑ ወቅት፤ የሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶች እንዲሁም የሕፃናት ወሲባዊ በደልን በቀጥታ-ሥርጭት የማስተላለፍ ርእሰ-ጉዳዮች ራሳቸውን እንደቻሉ የሕግ ጽንሰ-ሐሳቦች እየታዩ ቢሆንም፤ እውነታው ግን በሕፃናት ላይ የሚፈጸም ወሲባዊ በደልን በቀጥታ-ሥርጭት የማስተላለፍ ተግባር፤ የሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶች የሚዘጋጁበት፣

የሚሠራጩበት፣ እና ለዕይታ የሚበቁበት አንዱ ስልት እንደመሆኑ፤ በሁለቱ መካከል አለ ተብሎ የሚገለጸው ልዩነት ሀቁን አያንጸባርቅም፡ ፡

### ያለ ይሁንታ ወሲባዊ ምስሎችን በማጋራት ረገድ የሕፃናት ተሞክሮዎች

የሕ/ወ/በ/ቁሳቁስ በኢትዮጵያ ሕፃናት ደኅንነት እና ጤናማነት ላይ የተጋረጠ እውነተኛ እና ነባራዊ ስጋት ስለመሆኑ፤ በምዕራፍ 2.1 ስለ ሳይበር ጥቆማ የቀረበው ጥሬ መረጃ አሳይቶ ነበር። ሙሉ ለሙሉ ለማለት በሚያስደፍር መጠን እ.ኤ.አ. ከ2017 እስከ 2019 ለኢትዮጵያ የተላኩት የሳይበር ጥቆማዎች፤ የሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶችን ይዞ መገኘት፣ ማዘጋጀት፣ እና የማከፋፈል ድርጊቶችን የሚመለከቱ ነበሩ። ይበልጡንም፤ የዲስረፕቲንግ ሀርም የአባወራ/ቤተሰብ የዳሰሳ ጥናት እንዳረጋገጠው፤ በኢትዮጵያ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ካላቸው በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት  መካከል 5 በመቶዎቹ (ብዛት = 50) የገዛ ራሳቸውን የሚያሳዩ ወሲባዊ ምስሎቻቸውን ግለሰቦች ያለይሁንታቸው ለሌሎች አንዳጋሩባቸው ገልጸዋል። እነዚህ ገጠመኞች የሚያስከትሉት ጠንቅ ሲታሰብ አኃዙ አስደንጋጭ ነው። ከ16 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸውን ካቀፈው ናሙና ውስጥ ያሉት ሕፃናት (ከ50ዎቹ ሕፃናት 34ቱ)፤ ያለይሁንታቸው ምስሎቻቸው የተጋራበት አጋጣሚ የላቀ ነበር፡ ፡ ከልጃገረዶች ይልቅ ወንድ ልጆች በባለፈው ዓመት ውስጥ ይህን መሰል ጉዳት ያስተናገዱበት አጋጣሚ ከፍ ያለ ነበር (የወንድ ልጆች ብዛት = 37፤ የልጃገረዶች ብዛት = 13)።

የሕፃናት ወሲባዊ ምስሎች፤ በተለይም በበይነ-መረብ ላይ የተሠራጩት፤ በስፋት ሊዳረሱ እና በዓለም ዙሪያ በተደጋጋሚ ሊታዩ የሚችሉ ሲሆን፤ ይህም ተጎጂዎቹ ዘወትር በኃፍረት እና በመጋለጥ የፍርሀት ስሜት እንዲኖሩ ያስገድዳቸዋል። ከእንደነዚህ ዓይነት ምስሎች ወይም ቪዲዮዎች ውስጥም የከፋ የወሲብ በደልን የሚያንጸባርቁ ሲኖሩ ደግሞ፤ የይዘቱ መሠራጨት ተጎጂዎቹ በአካል/በፊትለፊት ያሳለፉትን መጥፎ ትውስታ በየጊዜው በተደጋጋሚ እንዲቀሰቀስ ሊያደርግባቸው ይችላል። ሆኖም *ዲስረፕቲንግ ሀርም* የከፋ የወሲብ በደልን በተለይ የተመለከተ ጥሬ መረጃ ከሕፃናት ለመሰብሰብ ጥረት አላደረገም፤ የዚህ ዋነኛው ምክንያት ደግሞ፤ የተከተልነው የሥነ-ምግባር እና የጥናት ሥነ-ዘዴ ሕፃናት በራሳቸው አባባል የሚገልጹትን ጉዳዮች ብቻ መዝግበን እንድንይዝ እንጂ፤ የተለያየ ቅርጽ ያላቸው የበደል ዓይነቶችን ፈልፍሎ ለማውጣት እና ጠልቆ ለመመርመር ስለማይፈቅድልን ነበር። ይሁንና የመሰል ድርጊት ተጎጂዎች በናሙናዎቻችን ውስጥ አልተካተቱም ለማለት ሳይሆን፤ ጉዳዩ ያልተገለጸ ስለነበር ነው።

በኢትዮጵያ በዳሰሳው ከተሳተፉት ሕፃናት አብዛኞቹ (73 በመቶዎቹ) እንዳሉት፤ አንድ ግለሰብ ዕርቃናቸውን እያሉ ፎቶ ወይም ቪዲዮ ቢቀርጻቸው እና ቀረጻዎቹ ለሌሎች ሰዎች ቢዳረስ ጥፋቱ የራሳቸው ሆኖ እንደሚቆጠር የገለጹ ሲሆን፤ 84 በመቶዎቹ ተንከባካቢዎቻቸም ተመሳሳይ አቋም አላቸው። ይህን መሰሉ ተበዳዩን የመውቀስ ሁኔታ፤ ለበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ተዳርገው በነበሩ ሕፃናት በተሰጡት ጥሬ መረጃዎች ላይ ሁሉ መንጸባረቁ ሲታይ፤ ተጎጂዎች የሚያደርጉት ሪፖርት ዝቅተኛ የሆነበት መንሥኤ ምናልባት ከዚሁ ጋር ሊያያዝ እንደሚችል ይጠቁማል። በምሳሌ ለማሳየት፤ የወሲባዊ ምስሎቻቸው ያለይሁንታቸው ለሌሎች ከተሠራጩባቸው 50 ሕፃናት መካከል፤ አንድ-አምስተኛ (10 ሕፃናት) ያህሉ ለማንም ሳይነግሩ ቀርተዋል፡ ፡ ሕፃናቱ ለሰው ቢነግሩ ኖሮ እንኳ የሚነግሩት፤ በዋናነት ለጓደኛቸው፣ ቀጥሎ ለተንከባካቢዎቻቸው እና ለወንድ/እኅታቸው የመሆን አጋጣሚው የላቀ ነበር። እጅግ ጥቂት ሕፃናት ለአስተማሪ ወይም ለወንድም/እኅት የነገሩ ሲሆን፤ አራት ብቻ ሕፃናት ግን ለዕርዳታ መጠየቂያ መስመር ወይም ለፖሊስ አመልክተዋል (በገጽ xx ላይ የቀረበውን አስረጂ ምስል ይመለከቷል)።

86. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (1997)፤ የወንጀል ሕግ፤ አንቀጽ 640
87. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (2008)፤ የኮምፒዩተር ወንጀልን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 958/2008፤ አንቀጽ 12
88. ECPAT International. (2020). Summary Paper on Sexual Exploitation of Children in Prostitution. Bangkok: ECPAT International.

መደብ፡ በኢትዮጵያ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት፤
ብዛት = 1 ሺህ ሕፃናት

OCSEA


# በባለፈው ዓመት ውስጥ በወሲባዊ ተግባራት እንድሳተፍ ዛቻ ወይም በመያዣ-ማስፈራሪያ የሰነዘረብኝ ሰው ነበር

**አዎ 5%**



## ይህ ጉዳይ በበይነ-መረብ የተፈጸመበት የቅርቡ ጊዜ ገጠመኝ …

Who did it?*†




ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ በወሲባዊ ድርጊቶች እንዲሳተፉ በበይነ-መረብ በኩል ዛቻ ወይም የመያዣ-ማስፈራሪያ የተሰነዘረባቸው ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 20 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

### የት ነው የተከሠተው?

- በማኅበራዊ ሚዲያ 24%
- በአካል 35%
- በበይነ-መረብ የጨዋታ ግጥሚያ 13%
- በሌላ ዓይነት መገናኛ 18%

ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ በወሲባዊ ድርጊቶች እንዲሳተፉ ዛቻ ወይም የመያዣ-ማስፈራሪያ የተሰነዘረባቸው ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 55 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

### ጉዳዩ የተከሠተው በየትኛው ፕላትፎርም ላይ ነው?

- በፌስቡክ ወይም በፌስቡክ ሜሴንጀር 69%
- ኢንስታግራም 15%
- ትዊተር 8%
- ዋትስአፕ 15%
- ስናፕቻት 8%

ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ በወሲባዊ ድርጊቶች እንዲሳተፉ እጅግ በቅርቡ ዛቻ ወይም የመያዣ-ማስፈራሪያ በማኅበራዊ ሚዲያ በኩል የተላከባቸው ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 13 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

* እነዚህ አኃዞች በልጆች የተመረጡትን እና በጣም የተለመዱ ምላሾችን ይወክላሉ
** እነዚህ አሃዞች በልጆች የተመረጡትን በጣም የተለመዱ እና በጣም ያልተለመዱ ምላሾችን ይወክላሉ
† የምርጫ ጥያቄ

### ለማን ነገርህ/ሽ?

ለማንም አልነገርኩም 20%

የመጀመሪያ 3
- ለጓደኛ 20%
- ወንድም/እኅት 20%

የመጨረሻ 3
- 15% ለሴት ተንከባካቢ
- 15% ለወንድ ተንከባካቢ
- 10% ለሌላ የማውቀው እና የማምነው አዋቂ ሰው፤

ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ በወሲባዊ ድርጊቶች እንዲሳተፉ በበይነ-መረብ በኩል ዛቻ ወይም የመያዣ-ማስፈራሪያ የተሰነዘረባቸው ከ 12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 20 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

### ለምን ለሰው አልነገርክ/ሽም?

- ጉዳዩ በሚሥጥር አይጠበቅም ብዬ ስለሰጋሁ 50%
- ለማን መንገር እንደነበረብኝ ስላላወቅኩኝ 25%
- የኃፍረት ስሜት ስለተሰማኝ 25%

ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ በወሲባዊ ድርጊቶች እንዲሳተፉ በበይነ-መረብ በኩል ዛቻ ወይም የመያዣ-ማስፈራሪያ ስለተሰነዘረባቸው የቅርቡ ጊዜ ገጠመኝ ለማንም ያልነገሩ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 4 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

ምንጭ የዲስረፕቲንግ ሀርም ጥሬ መረጃ

### ያለ ይሁንታ ወሲባዊ ምስሎችን በማጋራት ረገድ የሕፃናት ተሞክሮዎች

የሕ/ወ/በ/ቁሳቁስ በኢትዮጵያ ሕፃናት ደኅንነት እና ጤናማነት ላይ የተጋረጠ እውነተኛ እና ነባራዊ ስጋት ስለመሆኑ፤ በምዕራፍ 2.1 ስለ ሳይበር ጥቆማ የቀረበው ጥሬ መረጃ አሳይቶ ነበር። ሙሉ ለሙሉ ለማለት በሚያስደፍር መጠን እ.ኤ.አ. ከ2017 እስከ 2019 ለኢትዮጵያ የተላኩት የሳይበር ጥቆማዎች፤ የሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶችን ይዞ መገኘት፣ ማዘጋጀት፣ እና የማከፋፈል ድርጊቶችን የሚመለከቱ ነበሩ። ይበልጡንም፤ የዲስረፕቲንግ ሀርም የአባወራ/ቤተሰብ የዳሰሳ ጥናት እንዳረጋገጠው፤ በኢትዮጵያ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ካላቸው በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት መካከል 5 በመቶዎቹ (ብዛት = 50) የገዛ ራሳቸውን የሚያሳዩ ወሲባዊ ምስሎቻቸውን ግለሰቦች ያለይሁንታቸው ለሌሎች አንዳጋሩባቸው ገልጸዋል። እነዚህ ገጠመኞች የሚያስከትሉት ጠንቅ ሲታሰብ አኃዙ አስደንጋጭ ነው። ከ16 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸውን ካቀፈው ናሙና ውስጥ ያሉት ሕፃናት (ከ50ዎቹ ሕፃናት 34ቱ)፤ ያለይሁንታቸው ምስሎቻቸው የተጋራበት አጋጣሚ የላቀ ነበር። ከልጃገረዶች ይልቅ ወንድ ልጆች በባለፈው ዓመት ውስጥ ይህን መሰል ጉዳት ያስተናገዱበት አጋጣሚ ከፍ ያለ ነበር (የወንድ ልጆች ብዛት = 37፤ የልጃገረዶች ብዛት = 13)።

የሕፃናት ወሲባዊ ምስሎች፤ በተለይም በበይነ-መረብ ላይ የተሠራጩት፤ በስፋት ሊዳረሱ እና በዓለም ዙሪያ በተደጋጋሚ ሊታዩ የሚችሉ ሲሆን፤ ይህም ተጎጂዎቹ ዘወትር በኃፍረት እና በመጋለጥ የፍርሀት ስሜት እንዲኖሩ ያስገድዳቸዋል። ከእንደነዚህ ዓይነት ምስሎች ወይም ቪዲዮዎች ውስጥም የከፋ የወሲብ በደልን የሚያንጸባርቁ ሲኖር ደግሞ፤ የይዘቱ መሠራጨት ተጎጂዎቹ በአካል/በፊትለፊት ያሳለፉትን መጥፎ ትውስታ በየጊዜው በተደጋጋሚ እንዲቀሰቀስ ሊያደርግባቸው ይችላል። ሆኖም ዲስረፕቲንግ ሀርም የከፋ የወሲብ በደልን በተለይ የተመለከተ ጥሬ መረጃ ከሕፃናት ለመሰብሰብ ጥረት አላደረገም፤ የዚህ ዋነኛው ምክንያት ደግሞ፤ የተከተልነው የሥነ-ምግባር እና የጥናት ሥነ-ዘዴ ሕፃናት በራሳቸው አባባል የሚገልጹትን ጉዳዮች ብቻ መዝግበን እንድንይዝ እንጂ፤ የተለያየ ቅርጽ ያላቸው የበደል ዓይነቶችን ፈልፍሎ ለማውጣት እና ጠልቆ ለመመርመር ስለማይፈቅድልን ነበር። ይሁንና የመሰል ድርጊት ተጎጂዎች በናሙናዎቻችን ውስጥ አልተካተቱም ለማለት ሳይሆን፤ ጉዳዩ ያልተገለጸ ስለነበር ነው።

በኢትዮጵያ በዳሰሳው ከተሳተፉት ሕፃናት አብዛኞቹ (73 በመቶዎቹ) እንዳሉት፤ አንድ ግለሰብ ዕርቃናቸውን እያሉ ፎቶ ወይም ቪዲዮ ቢቀርጻቸው እና ቀረጻዎቹ ለሌሎች ሰዎች ቢዳረስ ጥፋቱ የራሳቸው ሆኖ እንደሚቆጠር የገለጹ ሲሆን፤ 84 በመቶዎቹ ተንከባካቢዎችም ተመሳሳይ አቋም አላቸው። ይህን መሰሉ ተበዳዩን የመውቀስ ሁኔታ፤ ለበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ተዳርገው በነበሩ ሕፃናት በተሰጡት ጥሬ መረጃዎች ላይ ሁሉ መንጸባረቁ ሲታይ፤ ተጎጂዎች የሚያደርጉት ሪፖርት ዝቅተኛ የሆነበት መንሥኤ ምናልባት ከዚሁ ጋር ሊያያዝ እንደሚችል ይጠቁማል። በምሳሌ ለማሳየት፤ የወሲባዊ ምስሎቻቸው ያለይሁንታቸው ለሌሎች ከተሠራጨባቸው 50 ሕፃናት መካከል፤ አንድ-አምስተኛ (10 ሕፃናት) ያህሉ ለማንም ሳይነግሩ ቀርተዋል። ሕፃናቱ ለሰው ቢነግሩ ኖሮ እንኳ የሚነግሩት፤ በዋናነት ለጓደኞቻቸው፣ ቀጥሎ ለተንከባካቢዎቻቸው እና ለወንድ/እኅታቸው የመሆን አጋጣሚው የላቀ ነበር። እጅግ ጥቂት ሕፃናት ለአስተማሪ ወይም ለወንድም/እኅት የነገሩ ሲሆን፤ አራት ብቻ ሕፃናት ግን ለዕርዳታ መጠየቂያ መስመር ወይም ለፖሊስ አመልክተዋል (በገጽ xx ላይ የቀረበውን አስረጂ ምስል ይመለከቷል)።

**ምስሎቹን ያጋሩት እነማን ናቸው፡** የቤተሰብ አባላት፣ በአዋቂ ዕድሜ ያሉ ጓደኞች/ወዳጆች እና የቀደመ ትውውቅ ያላቸው እና በጥቅሉ በሕፃኑ/ኗ የሚታወቁ ግለሰቦች ትልቁን ድርሻ የያዙበት ሁኔታ ነበር (እንደ ቅደም-ተከተላቸው ብዛት = 11 እና 12)። በአስረጂ ምስሉ ላይ እንደሚታየው፤ በሁለተኛ ደረጃ ያሉት የድርጊቱ ፈጻሚዎች ከ18 ዓመት ዕድሜ በታች ያሉ ጓደኞች/ወዳጆች እና የቀደመ ትውውቅ ያላቸው፣ እንዲሁም የፍቅር አጋሮች ናቸው። ከዚህ ወጣ ያለው ጉዳይ፤ ዘጠኝ ሕፃናት ምስሎቻቸው በማያውቁት ሰው እንደተጋራባቸው የገለጹት ሲሆን፤ ይህም ሕፃናቱ ዕርቃን ምስላቸውን ምናልባት በማጭበርበር ወይም በማስፈራሪያ ልከው፤ አሊያም ተሰርቆባቸው ሊሆን እንደሚችል ይጠቁማል። ምናልባት በገለጻዊ (qualitative) ስልትም ቢሆን የተበጣጠሰ ይዘት ያላቸውን ጉዳዮች ይበልጥ በማጠናቀር፤ የእነዚህ መሰል ጉዳዮችን ድባብ በደንብ ለመረዳት የሚያስችል በቀጣይ ራሱን የቻለ ምርምር ማካሄድ ያስፈልጋል።

**በበይነ-መረብ ወይስ ከበይነ-መረብ-ውጪ፡** በባለፈው ዓመት ውስጥ ምስሎቻቸው ያለይሁንታቸው ከተጋሩባቸው 50 ሕፃናት መካከል፤ 13ቱ በማኅበራዊ ሚዲያ፤ 10ሩ ደግሞ በበይነ-መረብ የጨዋታ ግጥሚያ ላይ ድርጊቱ እንደተፈጸመባቸው ተናግረዋል፡ ፡ ምስሎቻቸው በማኅበራዊ ሚዲያ የተጋራባቸው ሕፃናትን በተመለከተ፤ ድርጊቱ የደረሰባቸው እጅግ በቅርቡ የነበረ እና በፌስቡክ፣ በትዊተር፣ በዋትስአፕ፣ እና/ወይም በቴሌግራም ላይ የመሆኑ አጋጣሚ የላቀ ነበር። ድርጊቱ በአካል/በፊትለፊት እንደተፈጸመባቸው 12 ሕፃናት የገለጹ ሲሆን፤ ይህም የድርጊቱ ፈጻሚ ምስሉን ያጋራው ከሕፃኑ/ኗ ጋር አብሮ እያለ፤ አሊያም ያለሕፃኑ/ኗ ይሁንታ የሕፃኑ/ኗ ምስል አንሥቶ ነበር ማለት ነው፡ ፡ ስድስት ሕፃናት ያለ እሺታቸው ምስሎቻቸው በሌላ መንገድ እንደተጋሩባቸው ገልጸዋል።

### ለወሲባዊ ምስሎች ወይም ቪዲዮዎች የገንዘብ ወይም የስጦታ መደለያዎችን መቀበል

ሕፃናት አንዳች ነገር ለመቀበል በሚል ወሲባዊ ይዘቶችን የሚያዘጋጁ ከሆነ፤ ድርጊቱን የፈጸሙት በውዴታም ይሁን በግዴታ፤ ሁኔታው እንደ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ ይቆጠራል[89]። የሂደቱ መነሻ ምንም ሆነ ምን ለወሲባዊ ይዘቶች የገንዘብ ወይም የስጦታ መደለያ ስለተሰጡበት ሁኔታ በዚህ ንዑስ-ምዕራፍ ውስጥ ይዳስሳል።

ምንም እንኳ ለወሲባዊ ድርጊቶች ገንዘብ መቀበል ተሰምቶ የማይታወቅ እንግዳ ነገር ባይሆንም[90]፤ በዲጂታል ቴክኖሎጂዎች በኩል የሚደረገው ግን አዲስ አሠራር ነው። ይህ አሠራር የቅብብሎሽ ሥርጭትን ወይም ማጋራትን ስለሚጨምር በተለይ ለሕፃናት አደጋው የጎላ ነው። ከኢንንተርኔት ዋች ፋውንዴሽን እና ከማይክሮሶፍት የተገኘው ጥሬ መረጃ እንደሚያሳየው፤ የሕፃናት-ቀመስ ግለ-ቀረጽ ወሲባዊ ይዘቶች በቅብብሎሽ ለሌሎች የሚጋሩበት ሁኔታ እጅግ የተለመደ ጉዳይ ሁኗል። በኢንንተርኔት ዋች ፋውንዴሽን እና በማይክሮሶፍት ጥናት ዳሰሳ ከተካሄደባቸው ‹ወጣት-ቀረጽ› (‘youth generated’) ወሲባዊ ምስሎች  እና ቪዲዮዎች ውስጥ 90 በመቶዎቹ፤ መጀመሪያ አፕሎድ ከተደረጉበት ቦታ የተቃረሙ (‘harvested’ from the original upload location) እና በሦስተኛ ወገን ድረገጾች[91] ላይ ዳግም የተሠራጩ ነበሩ።

89. ECPAT International. (2020). Summary Paper on Sexual Exploitation of Children in Prostitution. Bangkok: ECPAT International.
90. Peebles, G. (2012, March28). Stolen Childhoods: Child Prostitution And Trafficking In Ethiopia. Eurasia Review.

## 2.2 በኢትዮጵያ ስላለው የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የሕፃናቱ ተሞክሮዎች

ይህ ርእሰ-ጉዳይ በባሕርይው ስሱ እንደመሆኑ፤ ‹የገንዘብ ወይም የስጦታ መደለያ በመቀበል ወሲባዊ ይዘቶችን ሰጥታችኋል ወይ› የሚለው ጥያቄን፤ ከ15 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ለተካተቱበት *የዲስረፕቲንግ ሀርም* የዳሰሳ ጥናት የምላሽ ሰጪዎች ናሙና ብቻ ነበር ጥያቄው የቀረበው። ይህ ጥያቄ ከቀረበላቸው 751 ምላሽ ሰጪዎች ውስጥ፤ አራት በመቶዎቹ (31 ሕፃናት) አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ማንነት በማይገለጽበት የዳሰሳ ጥናት እንኳ፤ ሕፃናት በዚህ መሰል ተግባር ስለመሠማራታቸው ለመግለጽ እንደሚያቅማሙ የሚጠበቅ ጉዳይ ነው።

በዚህ ዓይነቱ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ዙሪያ እስካሁንም ድረስ ያልተደፈኑ ክፍተቶች አሉ። በዚህ መሰል ተግባር ላይ እንዲሳተፉ ሕፃናትን ስለሚገፋፏቸው ነገሮች፣ ስጋቶቹን እንዴት እንደሚገነዘቧቸው፣ እንዲሁም ይህን ልማድ መጀመሪያውኑ እንዴት እንደተማሩት የሚሉ ወሳኝ ጥያቄዎችን የሚያነሣ እና በተጠቀሱት ዙሪያ ያሉትን ውስብስብ ጉዳዮች ለመረዳት የሚያስችል ተጨማሪ ጥናት ማካሄድ ያሻል።


## በባለፈው ዓመት ውስጥ ወሲባዊ ምስሎቼን ያለይሁንታዬ ያጋራብኝ ሰው ነበር

**አዎ 5%**



### ይህ ጉዳይ የተፈጸመበት የቅርቡ ጊዜ ገጠመኝ ...

**ይህንን ያደረገው ማን ነው?**




ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ ወሲባዊ ምስሎቻቸው ያለይሁንታቸው የተጋራባቸው ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 50 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

**የት ነው የተከሠተው?**

- 26% በማኅበራዊ ሚዲያ
- 24% በአካል/በፊትለፊት
- 20% በበይነ-መረብ የጨዋታ ግጥሚያ
- 12% በሌላ መንገድ

ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ ወሲባዊ ምስሎቻቸው ያለይሁንታቸው የተጋራባቸው ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 50 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

**ጉዳዩ የተከሠተው በየትኛው ፕላትፎርም ላይ ነው?**

- በፌስቡክ ወይም በፌስቡክ ሜሴንጀር 75%
- ትዊተር 17%
- ዋትስአፕ 17%
- ቴሌግራም 15%

ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ ወሲባዊ ምስሎቻቸው ያለይሁንታቸው በማኅበራዊ ሚዲያ በኩል እጅግ በቅርቡ የተጋራባቸው ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 13 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

**ለማን ነገርህ/ሽ?**

የመጀመሪያ 3
- ለጓደኛ 26%
- ለሴት ተንከባካቢ 16%
- 8% ለዕርዳታ መጠየቂያ መስመር
- 8% ለፖሊስ

የመጨረሻ 3
- 4% ለአስተማሪ ወይም ለማዕምር/educator
- 4% ለማኅበራዊ ሠራተኛ
- 0% ለሌላ የማውቀው እና የማምነው አዋቂ ሰው፤

ለማንም 20%

ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ ወሲባዊ ምስሎቻቸው ያለይሁንታቸው የተጋራባቸው ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 50 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

**ለምን ለሰው አልነገርክ/ሽም?**

- ለማን መንገር እንደነበረብኝ ስላላወቅኩኝ 40%
- ማንም አያምነኝም ብዬ ስላሰብኩ 20%
- ለሰው ብናገር ችግር ያመጣብኛል ብዬ ስለሰጋሁ 11%
- ምንም ውጤት የሚያስገኝ መስሎ ስላልታየኝ 11%
- አላውቅም 20%
- እንዳች ዓይነት ጥፋት እንደሠራሁ ስለተሰማኝ 11%

ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ ወሲባዊ ምስሎቻቸው ያለይሁንታቸው ስለተጋራበት የቅርቡ ገጠመኛቸው ለማንም ያልነገሩ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 10 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

* እነዚህ አኃዞች በልጆች የተመረጡትን እና በጣም የተለመዱ ምላሾችን ይወክላሉ
** እነዚህ አሃዞች በልጆች የተመረጡትን በጣም የተለመዱ እና በጣም ያልተለመዱ ምላሾችን ይወክላሉ
† የምርጫ ጥያቄ

ምንጭ የዲስረፕቲንግ ሀርም ጥሬ መረጃ

# 2.3 ከበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጋር ምናልባት የሚቆራኙ ሌሎች የሕፃናት ገጠመኞች

**አስቀድሞ ከቀረቡት የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል አብነቶች በተጨማሪ፤ ሕፃናት ሊጎዱ ቸው በሚችሉ ለሌሎች የበይነ-መረብ ገጠመኞች ሊዳረጉ ይችላሉ፤ ለምሳሌ ያህል ወሲባዊ ትንኮሳ ወይም ያለፍላጎታቸው በወሲብ ከተቃኘ ይዘት ጋር እንዲገጣጠሙ ወይም እንዲጋፈጡ መሆን። ከዚህ ባሻገርም፤ ከእነዚህ ገጠመኞች ውስጥ አንዳንዶቹ፤ የሕፃናትን የኃፍረት ስሜት ለማለዘብ እና ብሎም በዚህ አማካኝነትም በወሲባዊ ወሬዎች ወይም በወሲባዊ ድርጊቶች የሚሳተፉበት አዝማሚያ  እንዲጨምር አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፤ ለምሳሌ በማሽኮርመም ሂደት ላይ።**

## 2.3.1 ወሲባዊ ትንኮሳ

በኢትዮጵያ ከአምስት በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት አንዱ ያህሉ (19 በመቶዎቹ)፤ በባለፈው ዓመት ውስጥ ምቾት የማይሰጡ ወሲባዊ አስተያየቶች በበይነ-መረብ በኩል እንደደረሳቸው ከአባወራ/ቤሰተብ የዳሰሳ ጥናት የተገኘው ጥሬ መረጃ ያሳያል፡ ፡ እነዚህ መሰል አስተያየቶች፤ በሕፃኑ/ኗ አካላዊ ቁመና ላይ ያተኮሩ ቀልዶችን፣ ወሬችን ወይም አስተያየቶችን፤ ወይም ወሲባዊ ተግበራትን ይጨምራሉ። በዚህ መልኩ ከተተነኮሱ 191 ሕፃናት መካከል የሚበዙት ድርጊቱ የተፈጸመባቸው በአካል ሳይሆን በበይነ-መረብ ነበር። ድርጊቱ የተካሄደበት እጅግ የተለመዱት ፕላትፎርሞች፤ ፌስቡክ እና የፍጡን መልእክት መተግበሪያዎቹ ቴሌግራም እና ኢሞ ነበሩ።

በሕፃናት ላይ ወሲባዊ ትንኮሳውን የፈጸሙት ባይተዋር ግለሰቦች (26 በመቶ)፣ የፍቅር አጋሮች (21 በመቶ)፣ የቤተሰብ አባላት (19 በመቶ)፣ ከ18 ዓመት ዕድሜ የሚልቅ ጓደኛ (18 በመቶ)፣ እንዲሁም ከ18 ዓመት ዕድሜ ያነሰ ጓደኛ (8 በመቶ) ነበሩ። ይህ የሚየሳየው፤ በበይነ-መረብ ካሉ ባይተዎሮች ይልቅ፤ ሕፃናት አስቀድሞ በሚያውቋቸው ሰዎች ወሲባዊ ትንኮሳ ሊደርስባቸው የሚችልበት አጋጣሚ ይበልጥ ተደጋግሞ የሚታይ መሆኑን ነው።

የከፉ ወሲባዊ ጥቃቶች ላይ እንዳለው ሁሉ በተመሳሳዩም፤ በበይነ-መረብ ስለደረሰባቸው የወሲባዊ ትንኮሳ የቅርቡ ገጠመኛቸው፤ ሕፃናት ወይ ለጓደኛቸው የነገሩበት አሊያ ግን ለማንም ጨርሶ ያልነገሩበት ሁኔታ ከፍ ያለ ነበር። ለተንከባካቢያቸው የነገሩ ሕፃናት 15 በመቶ ብቻ ነበሩ። ሕፃናት ስለገጠመኛቸው ለማንም እንዳይነግሩ ያገዷቸው እጅግ ተደጋግመው የሚጠቀሱት ምክንያቶች፤ ወዴት መሄድ እና ለማን መንገር እንዳለባቸው ያለማወቅ፣ ጉዳዩ እስከማመልከት የሚያደርስ ክብደት አለው ብሎ ያለማሰብ፣ እንዲሁም የኃፍረት ስሜት ማሳደር የሚሉት ይጠቀሳሉ፡ ፡

በአሁኑ ወቅት በሕፃናት ላይ የሚፈጸም የበይነ-መረብ ወሲባዊ ትንኮሳ፤ በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግም ሆነ የኮምፒዩተር ወንጀልን ለመደንገገው በወጣው አዋጅ ላይ እንደ ወንጀል አልተደነገገም። ሆኖም ከላይ እንደተጠቀሰው፤ የኮምፒዩተር ወንጀልን ለመደንገገው የወጣው አዋጅ፤ ወሲባዊ ይዘቶችን በኮምፒዩተር ሥርዓቶች አማካኝነት በመላክ ለአካለ-መጠን ያልደረሱ ልጆችን ለወሲባዊ ድርጊት ማነሣሣትን እና መመልመልን በወንጀልነት የደነገገ ሲሆን[92]፤ ይህም በሕፃናት ላይ የሚፈጸም ወሲባዊ ትንኮሳን ምናልባት ሊሸፍን ይችላል።

## 2.3.2 ያለፍላጎት ወሲባዊ ምስሎችን መቀበል

በናሙናው ውስጥ ያሉ 19 በመቶ ሕፃናት፤ በባለፈው ዓመት ውስጥ ያለፍላጎታቸው ወሲባዊ ምስሎችን የላከላቸው ሰው እንደነበረ ገልጸዋል። እነዚህ ክሥተቶች በአጋጣሚ ወይም ሳይታሰብበት የተፈጠሩ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ግን ደግሞ የማሽኮርመም ሙከራ መኖሩን ሊጠቁሙም ይችላሉ። የቅርቡ ገጠመኝ የሆነበት እጅግ የተለመዱት ፕላትፎርሞች ፌስቡክ፣ ቴሌግራም፣ እና ኢሞ ናቸው፡ ፡ እስካሁን ከተገለጹት ገጠመኞች የተለየ አካሄድ በሚከተል መልኩ፤ አብዛኞቹ ድርጊቶች ሕፃኑ/ኗ በማያውቃቸው ሰዎች የተፈጸሙ (40 በመቶ) መሆኑ ነው።  ከዚህ ተከትለው ያሉት የቤሰተብ አባላት (16 በመቶ)፣ የፍቅር አጋር (15 በመቶ)፣ እና ከ18 ዓመት ዕድሜ በታች የሆኑ ጓደኞች (12 በመቶ) ናቸው።

ያለፍላጎታቸው ወሲባዊ ምስሎች በበይነ-መረብ ከደረሳቸው ሕፃናት ወስጥ፤ 35 በመቶዎቹ ለማንም ያልነገሩ ሲሆን፤ 35 በመቶ የሚሆኑት ሌሎቹ ደግሞ ለጓደኛቸው ነግረዋል። ለተንከባካቢያቸው የነገሩ ሕፃናት 10 በመቶዎቹ ብቻ ሲሆኑ፤ ለመምህር ወይም ለማኅበራዊ ሠራተኛ የነገሩ፤ አሊያም ለፖሊስ ወይም ለዕርዳታ መጠየቂያ መስመር አቤቱታ ያቀረቡ የሉም ለማለት ያስደፍራል፡ ፡ ስለገጠመኛቸው ለማንም ያልነገሩ ሕፃናትን በተመለከተ ዋነኞቹ ምክንያቶች፤ ወዴት መሄድ ወይም ለማን መንገር እንዳለባቸው ያለማወቅ፣ የመሳቀቅ እና ኃፍረት ስሜት ማሳደር፣ እንዲሁም ጉዳዩ እስከማመልከት የሚያደርስ ክብደት አለው ብሎ ያለማሰብ የሚሉት ይጠቀሳሉ።

ለልዩ ልዩ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ዓይነቶች የተጋለጡ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ምላሽ ሰጪዎች ገጠመኛቸውን ካላሳወቁባቸው ምክንያቶች መካከል አንዱ፤ የመሳቀቅ እና የኃፍረት ስሜት ስላደረብን የሚለው፤ በምዕራፍ 2.2 እና 2.3 ላይ ሁሉ በተደጋጋሚ የተነጸባረቀ ምክንያት ነበር።

> **በባለፈው ዓመት ውስጥ ያለፍላጎታቸው ወሲባዊ ምስሎችን የላከላቸው ሰው እንደነበረ ገልጸዋል።**

92. Government of Ethiopia. (2016). Computer Crime Proclamation No. 958/2016, Article 12 (2).

መደብ፡ በኢትዮጵያ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት፤
ብዛት = 1 ሺህ ሕፃናት

# በባለፈው ዓመት ውስጥ ምቾቴን የነኩኝ እኔን የሚመለከቱ ወሲባዊ አስተያየቶችን የሰጠ ሰው ነበር


**አዎ 19%**



## ይህ ጉዳይ የተፈጸመበት የቅርቡ ጊዜ ገጠመኝ ...

### ምን ተሰማህ/ሽ?

ምንም አልተሰማኝም




- ምንም አልተሰማኝም 36%
- መሰቀቅ/ኃፍረት 16%
- ንዴት 10%

### ለማን ነገርህ/ሽ?

| | |
|---|---|
| የፍቅር ጓደኛ (ወይም የበፊት) | 21% |
| የቤተሰብ አባል | 19% |
| ጓደኛ/የማውቀው (18+ ዓመት ዕድሜ) | 18% |
| ባልገልጸው እመርጣለሁ | 13% |
| ጓደኛ/የማውቀው(ከ18 ዓመት ዕድሜ በታች) | 8% |
| ሌላ ሰው | 1% |
| በሕፃኑ/ኗ የማይታወቅ | 26% |

ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ ለወሲባዊ ትንኮሳ የተዳረጉ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 191 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

### የት ነው ተከሠተው?

| | |
|---|---|
| በማኅበራዊ ሚዲያ | 28% |
| በአካል | 33% |
| በበይነ-መረብ የጨዋታ ግጥሚያ | 13% |
| በሌላ ዓይነት መንገድ | 7% |

ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ ለወሲባዊ ትንኮሳ የተዳረጉ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 191 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

### ጉዳዩ የተከሠተው በየትኛው ፕላትፎርም በኩል ነው?

| | |
|---|---|
| ፌስቡክ ወይም ፌስቡክ ሜሴንጀር | 61% |
| ቴሌግራም | 36% |
| ኢሞ | 19% |

ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ፤ በማኅበራዊ ሚዲያ በኩል ወሲባዊ ትንኮሳ እጅግ በቅርቡ የተሰነዘረባቸው ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 54 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

### ለማን ነገርህ/ሽ?

የመጀመሪያ 3

- ለማንም 29%
- ለጓደኛ 30%
- ለወንድም/እኅት 12%

የመጨረሻ 3

- 2% ለማኅበራዊ ሠራተኛ
- 1% ለዕርዳታ መጠየቂያ መስመር/Helpline
- 1% ሌላ የማምነው አዋቂ ሰው፤

ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ ለወሲባዊ ትንኮሳ የተዳረጉ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 191 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

### ለሰው ያልነገርክ/ሽበት ምክንያት ምንድን ነው?

| | |
|---|---|
| ለማን መንገር እንዳለብኝ አላውቅም ነበር | 49% |
| ጉዳዩ ያን ያህል ክብደት አለው ብዬ ስላላሰብኩኝ | 16% |
| የኃፍረት ስሜት አደረብኝ | 13% |

ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ ወሲባዊ ትንኮሳ ስለደረሰባቸው የቅርቡ ገጠመኝ ለማንም ያልነገሩ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 55 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

* እነዚህ አኃዞች በልጆች የተመረጡትን እና በጣም የተለመዱ ምላሾችን ይወክላሉ
** እነዚህ አሃዞች በልጆች የተመረጡትን በጣም የተለመዱ እና በጣም ያልተለመዱ ምላሾችን ይወክላሉ
† የምርጫ ጥያቄ

ምንጭ የዲስረፕቲንግ ሀርም ጥሬ መረጃ

መደብ፡ በኢትዮጵያ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት፤
ብዛት = 1 ሺህ ሕፃናት

በባለፈው

# ዓመት ውስጥ ሳልፈልግ ወሲባዊ ምስሎችን የላከልኝ ሰው ነበር

አዎ 19%



## ይህ ጉዳይ የተፈጸመበት የቅርቡ ጊዜ ገጠመኝ ...

### ምን ተሰማህ/ሽ?

- ምንም ተጽእኖ አላሳደረብኝም: 25%
- መሰቀቅ/ኃፍረት: 16%
- ንዴት: 12%

### Who did it?*†

| | |
|---|---|
| የቤተሰብ አባል | 16% |
| የፍቅር አጋር (ወይም የበፊት-) | 15% |
| ጓደኛ/ቀደሞ የማውቀው (ከ18 ዓመት ዕድሜ በላይ) | 12% |
| ጓደኛ/ቀደሞ የማውቀው (ከ18 ዓመት ዕድሜ በታች) | 11% |
| ባልገልጽ እመርጣለሁ | 11% |
| ሌላ ሰው | 1% |
| በሕፃኑ/ኗ የማይታወቅ ሰው | 40% |

ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ ያለፍላጎታቸው ወሲባዊ ምስሎች የደረሳቸው ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 186 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

### የት ነው የተከሠተው?

- በማኅበራዊ ሚዲያ: 34%
- በአካል: 20%
- በበይነ-መረብ የጨዋታ ግጥሚያ: 14%
- በሌላ መንገድ: 13%

ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ ያለፍላጎታቸው ወሲባዊ ምስሎች የደረሳቸው ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 186 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

### ጉዳዩ የተከሠተው በየትኛው ፕላትፎርም ላይ ነው?

- በፌስቡክ ወይም በፌስቡክ ሜሴንጀር: 65%
- በቴሌግራም: 37%
- በኢሞ: 16%

ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ ያለፍላጎታቸው በማኅበራዊ ሚዲያ በኩል ወሲባዊ ምስሎችእጅግ በቅርቡ የደረሳቸው ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 63 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

### ለማን ነገርህ/ሽ?

የመጀመሪያ 3

- ለጓደኛ: 35%
- ለወንድም/እኅት: 9%
- ለወንድ ተንከባካቢ: 7%

የመጨረሻ 3

- ለዕርዳታ መጠየቂያ መስመር: 1%
- ለማኅበራዊ ሠራተኛ: 1%
- ለፖሊስ: 1%

ለማንም: 35%

ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ ያለፍላጎታቸው ወሲባዊ ምስሎች የደረሳቸው ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 186 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

### ለምን ለሰው አልነገርክ/ሽም?

- ለማን መንገር እንደነበረብኝ ስላላወቅኩኝ: 23%
- የኃፍረት ስሜት ስለተሰማኝ: 17%
- አላውቅም: 15%

ብዛት = በባለፈው ዓመት ውስጥ ያለ ፍላጎታቸው ወሲባዊ ምስሎች እንዲደርሳቸው ስለተደረገበት የቅርቡ ገጠመኛቸው ለማንም ያልነገሩ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸው 65 በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት

* እነዚህ አኃዞች በልጆች የተመረጡትን እና በጣም የተለመዱ ምላሾችን ይወክላሉ
** እነዚህ አሃዞች በልጆች የተመረጡትን በጣም የተለመዱ እና በጣም ያልተለመዱ ምላሾችን ይወክላሉ
† የምርጫ ጥያቄ

ምንጭ የዲስረፕቲንግ ሀርም ጥሬ መረጃ

# 2.4 ከሚታወቁ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል እና የሕ/ወ/ብ/በደል ነገረ-ጉዳዮች መነሻነት ስለ ተጎጂዎች እና ስለ አጥፊዎች የተቀሰሙ ቁምነገሮች

## 2.4.1 ተጎጂዎች

የዲስረፕቲንግ ሀርም የጥናት ቡድን፤ በአባወራ/ቤተሰብ የዳሰሳ ጥናቱ አማካኝነት ለማጠናቀር ከቻለው የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ተጎጂዎች ማንነትን ከሚያመላክተው ጥሬ መረጃ የዘለለ፤ ያገኘው ተጨማሪ ጥሬ መረጃ እጅግ ያነሰ ነበር። አስቀድሞ እንደተገለጸው፤ በኢትዮጵያ ያሉ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ተጎጂዎችን ወይም አጥፊዎችን የሚመለከት ከሕግ አስከባሪ ምንጮች  የተሰጠ ምንም ጥሬ መረጃን የለም።

የዲጂታል፣ የበይነ-መረብ፣ ወይም የተግባቦት ቴክኖሎጂን በማያሻማ መልኩ ያላካተቱ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል (ሕ/ወ/ብ/በደል) ድርጊቶች የዚህ ሪፖርት ትኩረት ባይሆኑም፤ ከበይነ-መረብ ውጪ የሚፈጸሙ ጥሰቶችን የተመለከቱ ጥሬ መረጃዎች ግን እዚህ ውስጥ ተካተዋል፤ ምክንያቱም ድርጊቶቹ ምናልባት በቴክኖሎጂ የታገዙ ግን ያልተመዘገቡ ሊሆኑ ስለሚችሉ ነው። በተጨማሪም፤ ከበይነ-መረብ ውጪ ስላሉት የጥፋት ዓይነቶች ጥሬ መረጃ ቢኖረን፤ የበይነ-መረብ ጥሰቶቹ ወደፊት ስለሚፈጸሙበት ወይም ምናልባትም ከወዲሁ እየተፈጸሙ ስላለበት አግባብ ለመረዳት ሊያግዘን ይችላል።

**ምስል 21፡ በኢትዮጵያ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ተጎጂዎች በዘመን እና ባስመዘገቡት የዕድሜ ምድብ** [93]

| የተጎጂው የዕድሜ ምድብ | እ.ኤ.አ. 2017 | እ.ኤ.አ 2018 | እ.ኤ.አ 2019 | እ.ኤ.አ. ከ2017 እስከ 2019 የታየው ለውጥ በመቶኛ | እ.ኤ.አ. ከ2017 እስከ 2019 ድረስ ያለው ጠቅላላ ድምር | ከጠቅላላው ድምር የመቶኛ ድርሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ከ0 እስከ 3 ዓመት | 14 | 26 | 17 | 21% | 57 | 6.4% |
| ከ4 እስከ 6 ዓመት | 17 | 40 | 52 | 206% | 109 | 12.2% |
| ከ7 እስከ 9 ዓመት | 16 | 29 | 49 | 206% | 94 | 10.5% |
| ከ10 እስከ 12 ዓመት | 29 | 61 | 43 | 48% | 133 | 14.8% |
| ከ13 እስከ 15 ዓመት | 43 | 84 | 83 | 93% | 210 | 23.4% |
| 16 እና 17 ዓመት | 116 | 68 | 49 | -58% | 233 | 26.0% |

መደብ፡ ለዲስረፕቲንግ ሀርም ከሕግ አስከባሪ ምንጮች በመጠይቅ አማካኝነት የተሰጠ ጥሬ መረጃ፤

**ምስል 22፡ በኢትዮጵያ የሕ/ወ/ብ/በደል ተጎጂዎች በዘመን እና በጾታ**

| የተጎጂ ጾታ | እ.ኤ.አ 2017 | እ.ኤ.አ 2018 | እ.ኤ.አ 2019 | እ.ኤ.አ. ከ2017 እስከ 2019 የታየው ለውጥ በመቶኛ | እ.ኤ.አ. ከ2017 እስከ 2019 ድረስ ያለው ጠቅላላ ድምር | ከጠቅላላው ድምር ያለው ድርሻ በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ወንድ | 31 | 25 | 26 | -16% | 82 | 11% |
| ሴት | 204 | 161 | 267 | 31% | 632 | 89% |

መደብ፡ ለዲስረፕቲንግ ሀርም ከሕግ አስከባሪ ምንጮች በመጠይቅ አማካኝነት የተሰጠ ጥሬ መረጃ፤

93. ማስታወሻ፡ እ.ኤ.አ. የ2018 ላይ በሁለቱ ፈርጆች ላይ ባሉት የተጠቂዎች ድምሮች (ማለትም በዕድሜ ምድብ (ብዛት = 308) እና በጾታ (ብዛት = 186))፤ መካከል መጣረስ እንዳለ ተስተውሏል፡ ፡

## 2.4.2 አጥፊ

በኢትዮጵያ ውስጥ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ስለሚፈጸምበት ማእቀፍ ወይም ሁኔታ በተመለከተ አሁኑ ያለውን ዕውቀት ለማዳበር በማሰብ፤

ግንባር ቀደም አገልግሎት ሰጪዎችን ባሳተፈው ዳሰሳ ላይ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ነገረ-ጉዳዮች ላይ እንደሠሩ የገለጹ ሠራተኞችን ዓይነተኛ ትዝብት ለማግኘት ተሞክሯል። ይህም በአጥፊዎቹ እና በተጎጂዎቹ ሕፃናት መካከል ስላለው ግንኙነት የታዘቡትን ጉዳይ ነበር። ልክ የኢትዮጵያ ሕግ አስከባሪ አካላት ከሰጡት ምላሽ ጋር በሚመሳሰል ሁኔታ፤ በዚህኛውም ላይ እጅግ የሚበዙት ምላሽ ሰጪዎች (ከ33ቱ 30ዎቹ) በባለፉት 12 ወራት ውስጥ አንድም የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ነገረ-ጉዳይን ይዘው ወይም አስተዳድረው አያውቁም። ሦስት ምላሽ ሰጪዎች ብቻ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ነገረ-ጉዳዮች ላይ ተሞክሮ እንዳላቸው የገለጹ ሲሆን[94]፤

ከሦስቱ ውስጥ ደግሞ ሁለቱ ስለ አጥፊዎቹ የታዘቡትን ሲገለጹ፤ አንዱ ምላሽ ሰጪ ‹ከ18 ዓመት ዕድሜ በላይ ያለ/ች የማኅበረሰቡ አባል› በሚል፤ ሌላኛው ምላሽ ሰጪ ደግም ‹ከ18 ዓመት ዕድሜ በታች የሆነ ዘመድ› የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። ስለ ‹አመቻችቾች›[95] ለቀረበው ጥያቄ፤ ሁለት ምላሽ ሰጪዎች ብቻ አመቻቾች በተሳተፉበት የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ነገረ-ጉዳዮች ላይ ሠርተው እንደሚያውቁ ገልጸዋል። አንዱ ምላሽ ሰጪ አመቻቾች ስላሉት ግለሰብ ‹ከ18 ዓመት ዕድሜ በላይ ያለ/ች የማኅበረሰቡ አባል› በማለት የገለጹ ሲሆን፤ ሌላኛው ምላሽ ሰጪ ደግሞ ‹ከ18 ዓመት ዕድሜ በታች የሆነ ዘመድ› የሚል ምላሽ አቅርበዋል።[96]

### በኢትዮጵያ የሕ/ወ/ብ/በደል ፈጻሚዎች በዘመን እና በተመዘገቡ የዕድሜ ምድቦች[96]

| የአጥፊዎች የዕድሜ ምድብ | እ.ኤ.አ. 2017 | እ.ኤ.አ. 2018 | እ.ኤ.አ. 2019 | እ.ኤ.አ. ከ2017 እስከ 2019 ድረስ የታየው ለውጥ በመቶኛ | እ.ኤ.አ. ከ2017 እስከ 2019 ድረስ ያለው ጠቅላላ ድምር | ከጠቅላላው ድምር ያለው ድርሻ በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ከ18 ዓመት በታች | 106 | 36 | 69 | -34.9% | 211 | 28.0% |
| 18–29 | 27 | 105 | 204 | 655.6% | 336 | 44.6% |
| 30–39 | 0 | 29 | 88 | - | 117 | 15.5% |
| 40–49 | 5 | 11 | 38 | 660.0% | 54 | 7.2% |
| 50–59 | 7 | 0 | 7 | 0.0% | 14 | 1.9% |
| 60–69 | 0 | 3 | 9 | - | 12 | 1.6% |
| 70–79 | 2 | 2 | 3 | 50.0% | 7 | 0.9% |
| 80 ዓመት እና ከዚያ በላይ | 0 | 0 | 2 | - | 2 | 0.3% |

መደብ፡ ከሕግ አስከባሪ ምንጮች ለዲስረፕቲንግ ሀርም በመጠይቆች አማካኝነት የተሰጠ ጥሬ መረጃ

94. ማስታወሻ፡ እ.ኤ.አ. የ2019 ላይ በሁለቱ ፈርጆች ላይ ባሉት የተጠቂዎች ድምሮች (ማለትም በዕድሜ ምድብ (ብዛት = 420) እና በጾታ (ብዛት = 563))፤ መካከል መጣረስ እንዳለ ተስተውሏል።
95. ግንባር ቀደም ሠራተኞቹ እነዚህን ነገረ-ጉዳዮች እንደ በ/መ/ሕ/ወ/ብ/በደል ነገረ-ጉዳይ ቆጥረው የገለጹ ቢሆንም፤ እምብዛም በመደበኛ የፍትሕ ሥርዓቱ በኩል ያለፉ አይደሉም። ስለዚህ ‹የፍትሕ ተደረዳሽነት›ን በተመለከተ ቃለ-መጠይቅ የሚደረግላቸው አካላትን ለመወሰን የወጣውን መሥፈርት የሚያሟሉ አልሆኑም።
96. ማስታወሻ፡ እ.ኤ.አ. የ2019 ላይ በሁለቱ ፈርጆች ላይ ባሉት የተጠቂዎች ድምሮች (ማለትም በዕድሜ ምድብ (ብዛት = 420) እና በጾታ (ብዛት = 563))፤ መካከል መጣረስ እንዳለ ተስተውሏል።

# 3. የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ምላሽ አሠጣጥ በኢትዮጵያ

በዚህ ምዕራፍ የቀረበው፤ በኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ወቅት ለበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ምላሽ ስለሚሠጥባቸው አሠራሮች የተመለከተ ማስረጃ ነው። ይህም መደበኛ የአቤቱታ/የሪፖርት ማቅረቢያ አማራጮችን፤ እንዲሁም በፖሊስ እና በፍርድ ቤት ሥርዓቱ የተደረጉ ምላሾችን ያጠቃልላል። የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን ለመታገል መንግሥት፣ ሲቪል ማኅረሰቡ፣ እንዲሁም የበይነ-መረብ እና የቴክኖሎጂ ዘርፉ ያበረከቱት አስተዋጽኦ እሳቤ ውስጥ እንዲገባ ተደርጓል። በዚህ ምዕራፍ ያለው አብዛኛው ጥሬ መረጃ የተገኘው ከገለጻዊ (qualitative) ቃለ-መጠይቆች እና ምላሾች እንደመሆኑ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የምላሽ አሠጣጥ አሠራሮችን የተጠቀሙ ሰዎች ያጋጠሟቸውን ዘርፈ-ብዙ ተሞክሮዎችን ጥሬ መረጃው በተሟላ መልኩ ላያንጸባርቅ ይችላል።

# 3.1 መደበኛ የሪፖርት/የአቤቱታ ማቅረቢያ አሠራሮች

**በዚህ ሪፖርት ውስጥ አስቀድሞ እንደተጠቀሰው፤ የበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት ለበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል መዳረግ ከጅመሩ የቆየ ቢሆንም፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ግንዛቤ ግን አሁንም በጣም ዝቅተኛ ነው። የፍትሕ ሥርዓቱን የተጠቀመ ለናሙና እንኳ አንድ ሕፃንን ለማግኘት ዲስረፕቲንግ ሀርም ያደረገው ጥረት እምብዛም ስኬት አላስገኘለትም። ቃለ-መጠይቅ የተደረገላቸው ኃላፊነት-የተጣለባቸው አካላት ደጋግሞ የተጠቀሰውን የግንዛቤ እና የእርምጃ አለመኖርን ያረጋገጡ ሲሆን፤ በአንጻሩ ግን ጉዳዩ ካለበት ደረጃ ላይ በፍጥነት ተከታትለው ለመድረስ እና አብሮ ለመራመድ ያላቸውን ፍላጎት ገልጸዋል።**

## 3.1.1 የአቤቱታ ማቅረቢያ አሠራሮች

በምዕራፍ 2 ላይ እንደተጠቀሰው፤ ሕፃናት ስለደረሰባቸው ወሲባዊ ጥቃት ለመደበኛ የአቤቱታ ማቅረቢያ አሠራሮች ሳያሳውቁ መቅረታቸው እጅግ ጎልቶ የሚታይ እና፤ ይልቁን ግን ለግለሰቦች እና ለኢ-መደበኛ አካላት የገለጹበት አጋጣሚ በእጅጉ ያመዘነ ነበር፡ ፡ የአባወራ/ቤተሰብ የዳሰሳ ጥናቱ እንደሚያሳየው፤ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ክሥተቶችን ለዕርዳታ መጠየቂያ መስመሮች፣ ለማኅበራዊ ሠራተኞች፣ ወይም ለፖሊስ ያሳወቁ ሕፃናት የሉም ለማለት የሚያስደፍር ሲሆን፤ ስለደረሰባቸው አጠራጣሪም ሆነ እውነተኛ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል በርካታ ሕፃናት በፍጹም ለማንም አልነገሩም።

ይህ ግኝት ከመንግሥት አካላት ጋር ከተደረጉት ቃለ-መጠይቆች ከወጡት ግኝቶች ጋር የሚጣጣም ሲሆን፤ ‹የኢትዮጵያ የሕፃናት ጥበቃ ሥርዓት አቅም› ላይ እየተካሄደ በነበረው ግምገማ ሂደት ላይ የታዩ ቀዳሚ ግኝቶችን በማጣቀስ ከዩኒሴፍ ኢትዮጵያ የመጡ አንድ ምላሽ ሰጪ እንዳሉት፤ በሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለሕግ አስከባሪ መሥሪያ ቤቶች የማሳወቅ ወይም የማመልከት ዝንባሌ ዝቅተኛ እንደሆነ ነው (RA1-ET-02-A)። ይህ አገላለጽ፤ በሕፃናት እና በወጣቶች ላይ በሚፈጸሙ ጥቃቶች ላይ በማጠንጠን እ.ኤ.አ. በ2019 ከተካሄደው የገለጻዊ ጥናት ግኝት ጋር የሚዛመድ ሲሆን፤ ይህም በኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ የጥቃት ነገረ-ጉዳዮች ሪፖርት እንደማይደረጉ፤ አሊያም በቤተሰብ፣ በጓደኞች፣ በማኅበረሰቡ እገዛ፣ በኢ-መደበኛ አሠራሮች፣ ወይም በሃይማኖት ተቋማት አማካኝነት እልባት እንደሚሰጣቸው የተጠቀሰው ጥናት አብራርቷል፡ ፡ በተጨማሪም ጥናቱ ተጋላጭነት ያለባቸው ሕፃናት እና ወጣቶች የአስገድዶ መድፈር ወይም የወሲባዊ ጉንተላ (sexual assault) ነገረ-ጉዳዮችን በአቤቱታ የማመልክት ዝንባሌያቸው ይባስ ያነሰ መሆኑን ገልጿል[97]።

ከበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን በኢትዮጵያ ውስጥ ማመልከት የሚቻልባቸው በርካታ መንገዶች አሉ። በዐበይት እና አነስተኛ ከተሞች ውስጥ፤ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ነገረ-ጉዳዮችን የማስተናገድ ኃላፊነት የተጣለው በፖሊስ ጣቢያዎች ውስጥ ተማክለው ለተደራጁ የሕፃናት ጥበቃ የሥራ ክፍሎች ነው። ምንም እንኳ በመርኅ ደረጃ እያንዳንዱ ፖሊስ ጣቢያ የሕፃናት ጥበቃ የሥራ ክፍል ሊኖረው የሚገባ ቢሆንም፤ ብዙውን ጊዜ እውነታው ከዚህ የራቀ ነው። የሥራ ክፍሎቹ ኖረው እንኳ፤ የፖሊስ አባላቱ በሥራ የሚወጠሩበት ሁኔታ እንዳለ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሕፃናት ፍትሕ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ገልጸዋል (RA1-ET-06-A)፡ ፡ የተጠቀሰው የአቅም እጦት፤ በዳሰሳው በተሳተፉት ግንባር ቀደም ሠራተኞች ዘንድም በተመሳሳዩ የተንጸባረቀ እና፤ ሁሉም ምላሽ ሰጪዎች (ብዛት = 33) የሕግ አስከባሪውን የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ግንዛቤ እና የምላሽ አሠጣጥ ደረጃ ደካማ በማለት ግምገማቸውን አስቀምጠዋል።

ለፖሊስ ከማመልከት ባለፈ፤ በተለይም በገጠር፤ እንደ መምህራን ወይም የአንድ-መስኮት ማእከላትን እና የአደጋ ማሳወቂያ መስመሮችን የመሳሰሉ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል አቤቱታዎችን ለማቅረብ የሚያስችሉ የተለያዩ መዋቅሮች ያሉ መሆኑን፤ ኃላፊነት-ከተጣለባቸው አካላት ጋር በተደረገው ቃለ-መጠይቅ የተገኙት ምላሾች ጠቁመዋል[98]። ምንም እንኳ እነዚህ መዋቅሮች በስም የተጠቀሱ ቢሆንም፤ የጥናት ቡድኑ ግን ስለመዋቅሮቹ ምንም ዓይነት መረጃ ለማግኘት ያልቻለ እና፤ በዚህ የተነሣም የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ስጋቶችን በመቅረፍ ረገድ ምን ያህል ውጤታማ እንደሆነ ለመገምገም አልቻለም።

በኢትዮጵያ ካሉት ከ12ቱ ክልሎች በስድስቱ፤ በ919 አጭር ኮድ በስልክ የሚደወልባቸው የአደጋ ማሳወቂያ መስመሮች ሥራ ላይ የዋሉ ሲሆን፤ እነዚህም በክልል የፖሊስ ጽሕፈት ቤቶች ውስጥ የተማከሉ ናቸው። የኢትዮጵያ መንግሥት ከሁለት የተመድ ድርጅቶች (በእንግሊዝኛ ምሕፃረ ቃላቸው የ/ኤን/ኤፍ/ፒ/ኤ/ እና ዩ/ኤን/ ዉሜን) ጋር በፈጠረው አጋርነት የሚደገፉት እነዚህ የአደጋ ማሳወቂያ መስመሮች፤ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን አቤቱታ ለመቀበል ብቻ የተዘጋጁ አይደሉም፤ አንድ ምላሽ ሰጪ እንዳሉት የአደጋ ማሳወቂያ መስመሮች ለበይነ-መረብ ጉዳዮች የተለየ ብቸኛ ምድብ ላይኖራቸው ቢችልም፤ የወሲባዊ ብዝበዛ ነገረ-ጉዳዮችን ግን መመዝገብ ይችላሉ።

ያም ሆነ ይህ፤ የአደጋ ማሳወቂያ መስመሮች በኢትዮጵያ በስፋት የሚታወቁ አይመስልም። እንደዚህ ለማለት የሚያስደፍረው ምክንያት ደግሞ ከ91 በመቶዎቹ የግንባር ቀደም ሠራተኞች የተገኘው የዳሰሳው ጥሬ መረጃ፤ አቤቱታዎች እንዳይቀርቡ ከሚያደርጉ ዋነኛ ማነቆዎች ውስጥ አንዱ ብለው የጠቀሱት በሃገሪቱ ‹የአደጋ ማሳወቂያ መስመር/የዕርዳታ መጠየቂያ መስመር አለመኖር›ን በመሆኑ ነው። ይህንን ጉዳይ ታሳቢ በማድረግ፤ ከአደጋ ማሳወቂያ መስመሮቹ አንዱ (በእንግሊዝኛ ምሕፃረ ቃሉ ኢ/ሲ/ኤፍ/ኤ ኢትዮጵያ)፤ ስለተቀበላቸው የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል-ነክ ጥሪዎች ለ‹ቻይልድ ሄልፕ ኢንተርናሽናል› (Child Helpline International) ባቀረበው ሪፖርት፤ እ.ኤ.አ. በ2017 70 ጥሪዎችን ብቻ እንደተቀበለ፤ እ.ኤ.አ. በ2018 እና በ2019 ግን ምንም እንዳላስተናገደ ገልጾ ነበር። እነዚህ 70 ጥሪዎች፤ የበይነ-መረብ የሕ/ወ/በ/ቁሳቁስ ሥርጭትን እና ማሽኮርመምን ጨምሮ፤ በልጃገረዶች ላይ የተፈጸሙ ጥቃቶችን የሚመለከቱ ነበሩ።

97. Chuta, N., Morrow, V., Pankhurst, A., &Pells, K. (2019, August). Understanding Violence Affecting Children in Ethiopia: a Qualitative Study. Young Lives.

98. የአደጋ ማሳወቂያ መስመሮች (hotlines) ያሉባቸው ቦታዎች የሚከተሉት ናቸው፡ አዲስ አበባ ከተማ፤ ኦሮሚያ ክልል፣ ጋምቤላ ክልል፣ ቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ክልል፣ ሐረሪ ክልል፣ እና ሶማሌ ክልል ናቸው። 12 አስተዳደራዊ ክልሎች ያሉ እና የአደጋ ማሳወቂያ መስመሮቹ ግን የሚሸፍኑት አዲስ አበባን እና አምስት ክልሎችን ብቻ እንደመሆኑ፤ የአደጋ ማሳወቂያ መስመሮቹ መላውን ኢትዮጵያ አይሸፍኑም። የአደጋ ማሳወቂያ መስመሮች በመንግሥት የሚደገፉ እና በክልል የፖሊስ ጽሕፈት ቤቶች ውስጥ የተማከሉ ናቸው። የኢትዮጵያ መንግሥት በፌደራል ደረጃ ያሉ ባለሦስት አኃዝ የስልክ መስመሮች አገልግሎትን እንደሚያስጀምር በሁለተኛው የመንግሥት የዕድገት ዕቅድ ውስጥ የተወጠነ ቢሆንም፤ አንድም ምላሽ ሰጪ እነዚህ መስመሮች ስለመዘጋጀታቸው ያነሣው ነገር የለም።

የሪፖርት ማቅረብ አለመኖር ሌላኛው ማሳያ፤ በናሙና ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ መደበኛ የፍትሕ ሥርዓቱን ተጠቅመው የነበሩ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ተጎጂዎችን ለማግኘት የዲስረፕቲንግ ሀርም የምርምር ቡድን የገጠመው ፈተና ብርቱ ነበር። በሕገወጥ የሰዎች ዝውውር፣ እና በወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ከተጠቁ ተበዳይ ሕፃናት ጋር አብረው የሚሠሩ ከ20 የሚልቁ የሃገር ውስጥ እና ዓለም-አቀፍ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች፣ ከፍትሕ ባለሙያዎች፣ እንዲሁም ከሕግ አስከባሪ መኮንኖች ጋር ግንኙነት ተደርጎ የነበረ ቢሆንም፤ የዲስረፕቲንግ ሀርም የምርምር ቡድን መደበኛ የፍትሕ ሥርዓቱን ተጠቀመ/ቸ ከ15 እስከ 18 ዓመት ዕድሜ ያለው/ላት አንድም የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ተጎጂን ማግኘት አልቻለም።

### 3.1.2 ሕፃናት ሪፖርት ሳያደርጉ የሚቀሩት ለምንድን ነው?

እጅግ የሚያመዝኑት ሕፃናት የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ክሥተትን ለማንም ሳያሳውቁ የመቅረታቸው ነገር አሳሳቢ ነው። በእኩል ደረጃ የሚያሳስበው ጉዳይ ደግሞ፤ ኃላፊነት-ከተጣለባቸው ጋር በተደረጉት ቃለ-መጠይቆች ላይ የተሳተፉት አብዛኞቹ፤ ሪፖርት የማይደረገው በኢትዮጵያ ውስጥ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል እየተከሠተ ስላልሆነ ነው የሚል አስተያየት የሰጡ መሆኑ ነው (RA1-ET-09-A, RA1-ET-03-A, RA1-ET-06-A)። የተጠቀሰው አባባል፤ አጠራጣሪ እና እውነተኛ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጉዳዮችን ለአባወራ/ቤተሰብ የዳሰሳ ጥናቱ የገለጹ ሕፃናት ከሰጡት ማስረጃ ጋር የሚቃረን፤ ብሎም ቀጥሎ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ሪፖርት ላለማድረግ አስተዋጽኦ እንዳላቸው ይጠቁማል፡ - የኃፍረት፣ የመጠቋቆሚያ (stigma) መሆን፣ እና በተበዳዩ የመላከክ ፍራቻ፤ አጠራጣሪ ወይም የተረጋገጡ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ክስተቶችን እንዴት ወይም ለማን ወይም ወዴት ማመልከት እንደሚቻል ያለማወቅ፤ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ድርጊት የሙብት ጥሰት መሆኑን ያለማወቅ፤ እንዲሁም በፖሊስ እና በሌሎች ድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶች ላይ አመኔታ ማጣት።

#### የኃፍረት፣ የመጠቋቆሚያ መሆን፣ እና በተበዳዩ የመላከክ ፍራቻ

ሕፃናት ስለ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ገጠመኛቸው ለሌሎች ለማውራት አብዛኛውን ጊዜ የኃፍረት ስሜት ይሰማቸዋል። የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ተጎጂዎች ሪፖርት እንዳያደርጉ ተጽእኖ የሚያደርጉባቸው ዋነኛ ምክንያት ተብለው በዳሰሳው በተሳተፉ ግንባር ቀደም ሠራተኞች የተገለጹት መንሥኤዎች፤ በማኅበረሰቡ መጠቋቆሚያ መሆን እንዲሁም ስለ ወሲብ ማውራት ምቾት የሚነሣ ጉዳይመሆኑ ነው፡ ፡ ሕፃናት ጉዳዩን ባሳውቅ ችግር ውስጥ እገባለሁ የሚል ጭንቀት፤ ወይም ያለሁኔትን ሁኔታ ማንም አያምነኝም ወይም አይረዳኝም የሚል ስሜት እንደሚያድርባቸው ከሕፃናቱ ጋር ባደረጓቸው ቃለ-መጠይቆች መታዘባቸውን አንድ የሕፃናት ጥበቃ ሙያተኛ የገለጹ ሲሆን፤ አክለውም ‹አንዳንዴ ጉዳዩ ከቤተሰቡ ክብር ጋር የሚገናኝ ነው። ስለዚህ እንደነዚህ ዓይነት ጉዳዮችን አይገለጹም›። (RA1-ET-02-A)

የኢትዮጵያ ሕግ ‹‹ለተፈጥሮ ባሕርይ ተቃራኒ የሆኑ የግብረ-ሥጋ ግንኙነቶች› በሚለው የወንጀል ሕግ ክፍል ሥር በተመሳሳይ ጾታዎች መካከል የሚካሄዱ ወሲባዊ ድርጊቶችን በወንጀልነት ይደነግጋል[99]። በዓለም ዙሪያ ያለው ማስረጃ እንደሚያመለክተው ግን፤ እንደነዚህ ዓይነት ሕጎች መሰል ጾታ ባለው ግለሰብ ወሲባዊ በደል የደረሰባቸው ወንድ ልጆች፤ ምንም እንኳ ተጎጂ ቢሆኑም እነርሱ ራሳቸው እንዳይወነጀሉ በመፍራት ዝምታን እንዲመርጡ ያደርጓቸዋል፡ ፡ ለአካለ-መጠን ባልደረሱ ልጆች ላይ የግብረ-ሰዶም ተግባራትን የሚፈጽሙትን የሚቀጣ ሕግ በኢትዮጵያ ያለ ቢሆንም፤ ይኸው ሕግ በመሰል ጾታ ወሲባዊ ብዝበዛ ወይም በደል የደረሰባቸው ሕፃናት ዕርዳታ ከማፈላለግ እንዲቆጠቡ ሊያደርጋቸው ይችላል[100]።

#### የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን የት ተሂዶ ማመልከት እንደሚቻል አለማወቅ

51 በመቶዎቹ በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት፤ ወሲባዊ ጉንተላ ወይም ትንኮሳ ቢደርስባቸው ከየት ዕርዳታ ማግኘት እንደሚችሉ አያውቁም። በባለፈው ዓመት ለበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የተዳረጉ ሕፃናት እንዳሉት፤ እንዳያሳውቁ ወይም አቤቱታ እንዳያቀርቡ ከሚያደርጓቸው ዋነኛ ማነቆዎች ውስጥ አንዱ የተጠቀሰው ችግር ነው።

#### ሕፃናት ስለ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ትምህርት ስላልተሰጣቸው የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን እንደ ስህተት ላይመለከቱት ይችላሉ


በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሴቶች፣ ሕፃናት፣ እና ወጣቶች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር እንዳሉት፤ ‹ስለ የበይነ-መረብ ሲባዊ በደል ምንም ግንዛቤ የለም፤ እጅግ ብዙዎቹ አያውቁትም፤ ሰዎች ከበይነ-መረብ ውጪ በሕፃናት ላይ ስለሚፈጸመው ወሲባዊ ብዝበዛ የተሻለ ያውቃሉ›። (RA1-ET-03-A)

#### በፖሊስ እና በሌሎች ድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶች ላይ አመኔታ ማጣት

ስለገጠሟቸው ልዩ ልዩ ዓይነት አጠራጣሪ ወይም እውነተኛ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጉዳዮች ለፖሊስ ያመለከቱ እና በአባወራ/ቤተሰብ የዳሰሳ ጥናቱ የተሳተፉ ሕፃናት የሉም ለማለት ያስደፍራል። ግንባር ቀደም አገልግሎት ሰጪዎች በተሳተፉበት ዳሰሳ ላይ 94 በመቶዎቹ ምላሽ ሰጪዎች ሕፃናት የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ነገረ-ጉዳዮችን ሪፖርት የማያደርጉት አገልግሎቶቹ ስለማይታመኑ እንደሆነ፤ እንዲሁም 82 በመቶዎቹ ደግሞ የአገልግሎቶቹ ጥራት ደካማነትን በዋና በመንሥኤነት ገልጸዋል። የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል አቤቱታ ተቀባዮች እምብዛም እርምጃ የማይወስዱ እና ይህም በአቤቱታ ማቅረቢያ አሠራሮች ላይ ያለውን አመኔታ ይበልጥ እንደሚሸረሽረው ኃላፊነት-ከተጣለባቸው ጋር የተካሄዱት ቃለ-መጠይቆችም በተመሳሳዩ ጠቁመዋል (RA1-ET-02-A)። አሁን ያሉት አገልግሎቶች ሚሥጥር የመጠበቅ አቅማቸው አጠራጣሪ መሆኑ ሲታከልበት፤ አስቀድሞ በተጠቀሰው በአቤቱታ ማቅረቢያ ሥርዓቶች ላይ ያለውን የአመኔታ እጦት ይበልጥ ያጎላዋል፡ ፡ (79 በመቶዎቹ የግንባር ቀደም ሠራተኞች የሚሥጥር ጠባቂነት ስጋት አቤቱታ እንዳይቀርብ የሚያሰናክል እንቅፋት መሆኑን ገልጸዋል።)

99. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (1997)፤ የወንጀል ሕግ፤ አንቀጽ 629
100. Josenhans, V., Kavenagh, M., Smith, S., & Wekerle, C. (2020). Gender, rights and responsibilities: The need for a global analysis of the sexual exploitation of boys. *Child Abuse & Neglect, 110* (1), 6.

**ምስል 24፡ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ሪፖርት እንዳይደረግ የሚያሰናክሉ ማኅበራዊ እና ባህላዊ እንቅፋቶች**




መደብ፡ ብዛት = 33

## ስለ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል በግንባር ቀደም ሠራተኞች ዘንድ ያለው ዕውቀት

ግንባር ቀደም አገልግሎት ሰጪዎች የተሳተፉበት የዳሰሳ ጥናት የተከናወነው በአካል (የኢ/ሲ/ፒ/ኤ/ቲ/ አባል አዲስ አበባ ውስጥ ባለው ጽሕፈት ቤት) ነበር፤ የዚህ አንዱ ምክንያት አብዛኞቹ ግንባር ቀደም ሠራተኞች እና ማህበራዊ አገልግሎት ሰጪዎች መደበኛ የበይነ-መረብ ግንኙነት ስላሌላቸው ነው። እንደዚህ ዓይነቱ ከበይነ-መረብ ግንኙነት ውጪ የመሆን ሁኔታ የሚያመለክተው፤ ግንባር ቀደም ሠራተኞች ወጣቶች አዘውትረው ስለሚጠቀሙባቸው ፕላትፎርሞች ለማወቅ እና በፕላትፎርሞቹም ለመሳተፍ ያላቸው ዕድል አነስተኛ መሆኑን ነው። ለበይነ-መረብ እንግዳ መሆን፤ ስለ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል እና ስለ አጋላጭ ጎኖች ግንባር ቀደም ሠራተኞች ያላቸው ግንዛቤ ደካማ እንዲሆን እና ይህም ሕፃናት የደረሰባቸውን እንዳይገለጹ ተጨማሪ መሰናክልን የሚፈጥር ነው።

የግንባር ቀደም ሠራተኞች አንዳንድ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል-ነክ ርእሰ-ጉዳዮችን በደንብ እንደሚገነዘቧቸው እና በሌሎች ርእሰ-ጉዳዮች ላይ ደግሞ ወጥ የሆነ ዕውቀት እንዲኖራቸው ሥልጠና መስጠት አስፈላጊ መሆኑን የዳሰሳው ውጤት ያመለክታል። በዳሰሳ ጥናቱ ላይ፤ ለ33ቱ ግንባር ቀደም ሠራተኞች የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ሊከሠት ስለሚችልባቸው ሦስት ምስለ-ሁኔታዎች (scenarios) ወይም ቢሆኖች ከተገለጸላቸው በኋላ፤ በእንዳንዱ ምስለ-ሁኔታ ላይ አንድ ሕፃን ተጎጂ እንዲሁም አንድ ወንጀለኛ ደግሞ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል-ነክ ጥሰቶችን ፈጻሚ ሊሆኑ የሚችሉበት ምን ያህል ዕድል አለ ወይም የለም የሚል ጥያቄዎችን ተጠይቀው ነበር። እነዚህ ጥያቄዎች የተቀረጹት፤ ልዩ ልዩ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ዓይነቶችን እና ድባቦችን ተሳታፊዎቹ እንዴት እንደሚረዷቸው ለማወቅ የሚያስችሉ ቁምነገሮችን ለመጨበጥ ነበር። ምላሾቹ ተሳታፊዎቹ ስለ ጉዳዩ ባላቸው ዕውቀት ላይ ሊመረኮዙ፤ ብሎም በማኅበራዊ ወግ-ልማዶች እና እምነቶች፤ እንዲሁም እነዚህ ጉዳዮች በሃገር ውስጥ ሕጎች በተበየኑበት (ባልተበየኑበት) ሁኔታዎች ሊቃኙ እንደሚችል ይገመታል። በሦስቱም ምስለ-ሁኔታዎች ላይ ግንባር ቀደም ሠራተኞቹ እጅግ ትክክል በሆነ አኳኋን ሕፃናቱን ተጠቂ፤ አዋቂዎችን ደግሞ አጥፊ በማለት ለይተው አስቀምጠዋል። ይሁንና አንዳንድ የአተያይ ልዩነቶች ነበሩ፤ ለምሳሌ አንድ ግለሰብ የ16 ዓመት ዕድሜ ያላት ሴት ልብሷን ስታወልቅ የሚያሳይ ቪዲዮን በበይነ-መረብ ቢመለከት፤ ግለሰቡ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል-ነክ ወንጀልን እንደፈጸመ ይቆጠራል ወይስ አይቆጠርም የሚለው ጥያቄ ነው።

# 3.2 የሕግ አስከባሪው ምላሽ

### 3.2.1 የተመዘገቡ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል-ነክ ነገረ-ጉዳዮች ውሱንነት

የኢትዮጵያ ሕግ አስከባሪ አካላት እ.ኤ.አ. ከ2017 እስከ 2019 ድረስ ባሉት ጊዜያት ውስጥ አንድም ከበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጋር የተያያዙ ነገረ-ጉዳዮችን አልመዘገቡም። ከሕግ አስከባሪ ኃላፊዎች ጋር የተደረጉ ቃለ-መጠይቆች ይህንን ግኝት ያረጋግጣሉ። አልፎ አልፎ ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጃገረዶችን ከሚጨምሩ እና በሴቶች ላይ ከተፈጸሙ የወሲባዊ አስገድዶ-መጠቀም (sexual extortion) ነገረ-ጉዳዮች በስተቀር፤ እስካሁን ድረስ ወደ ሥራ ክፍላቸው የተመራ ከበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጋር የተያያዘ ምንም ነገረ-ጉዳይ እንደሌለ፤ ሰፊ እና ዘርፈ-ብዙ የበይነ-መረብ ወንጀሎች ላይ በዋናነት አተኩሮ ከሚሠራው ከሳይበር ወንጀሎች የሥራ ክፍል የመጡ አንድ ምላሽ ሰጪ ጠቁመዋል። እነዚህ የተጠቀሱት ድርጊቶች፤ በወሲባዊ አስገድዶ-መጠቀም ሂደቱ በአንድ ነጥብ ላይ በቴክኖሎጂ ታግዘው የነበሩ ከሆነ፤ እንደ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል-ነክ ነገረ-ጉዳይ ሊቆጠሩ ይችላሉ። ከፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ-ሕግ ጽሕፈት ቤት የመጡ አንድ ዐቃቤ-ሕግ እንዳሉት፤ ‹*አንዳንዴ ሕፃናት ለወሲባዊ ቁሳቁስ እንዲጋለጡ የተደረጉበት ጉዳዮች እንዲሁም በተንቀሳቃሽ ስልክ ወሲባዊ ይዘቶችን  መላላክ [sexting]ን የተመለከቱ ጉዳዮች ይገጥመናል እንጂ፤ የበይነ-መረብ ማሽኮርመምን፣ በቀጥታ-ሥርጭት ማስተላለፍን፣ ወይም የሕፃናት ወሲባዊ በደልን የሚያሳዩ ቁሳቁሶችን የተመለከቱ ጉዳዮች አላጋጠመንም*›። (RA1-ET-05-A)

በሕግ አስከባሪው ዘርፍ ከተሰጡት ምላሾች ጋር በሚጣጣም መልኩ፤ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሕፃናት ፍትሕ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ኃላፊም፤ እስከዛሬ ድረስ በተናጠል የተመዘገበ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል-ነክ ነገረ-ጉዳይ እንደሌለ አጢነዋል። ‹*ልናገር የምችለው ተጨባጭ የሆነ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጉዳይ የለም*› (RA1-ET-06-A)። ምንም እንኳ ከአባወራ/ቤተሰብ የዳሰሳ ጥናት የተገኘው ጥሬ መረጃ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል በኢትዮጵያ ውስጥ እየተካሄደ መሆኑን ቢያሳይም፤ እነዚህ ነገረ-ጉዳዮች በኢትዮጵያ የፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ግን አይታዩም። ሁለቱንም ማለትም በይነ-መረብን እና ከበይነ-መረብ ውጪ ያሉትን ስልቶች ያጣመሩ የሕፃናት ወሲባዊ አስገድዶ-መጠቀም እና በደልን የተመለከቱ አንዳንድ ነገረ-ጉዳዮች፤ ምናልባት በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል-ነክ ነገረ-ጉዳይ ሥር ሳይመደቡ እየተስተናገዱም ሊሆን ይችላል።

### 3.2.2  ቴክኒካዊ አቅም እና ሥልጠና

የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል-ነክ ነገረ-ጉዳዮችን በመመርመር፣ ክስ በመመሥረት፣ እና የተሳካ ዳኝነት በመስጠት ረገድ የሕግ አስከባሪ አካላት ያላቸው ግንዛቤ እና የቴክኒክ አቅም ውሱን መሆኑን፤ ቃለ-መጠይቅ የተደረገላቸው ሁሉም ኃላፊዎች በጋራ ይስማማሉ። ለዚሁ ዓላማ የተደራጀ በፖሊስ ሥር የተዋቀረ የሳይበር ወንጀል ክፍል ያለ ቢሆንም፤ የሥራ ክፍሉ በርካታ እና ዘርፈ-ብዙ የበይነ-መረብ ወንጀሎችን ያስተናግዳል። ይህ ሲባል ግን የሳይበር ወንጀል ክፍሉ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን በልዩ ወይም እንደ ዓይነተኛ የሥራ ድርሻው ተቀብሎ ምርመራ ያካሂዳል ማለት አይደለም፤ ምክንያቱም አባላቱ በመሰል ምርመራዎች ላይ ሥልጠና ያላገኙ፤ ብሎም የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል-ነክ ነገረ-ጉዳዮች ምርመራን ለመደገፍ የተመደበ ገንዘብ የሌለ መሆኑን፤ ከሳይበር ወንጀል ክፍል የመጡ አንድ ምላሽ ሰጪ ገልጸዋል።

የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ቴክኒካዊ ክህሎት አለመኖር ጋር ተዳምሮ፤ የሳይበር ወንጀል ክፍሉ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል-ነክ ነገረ-ጉዳዮችን በብቃት ለመመርመር የሚያስፈልጉ ግብአቶች (ሶፍትዌር እና ሀርድዌር) አሁን ላይ እንደሌሉት፤ የሳይበር ወንጀል ክፍል አንድ ተወካይ ገልጸዋል። ክፍሉ አሁን እየተጠቀመበት ያለው ሶፍትዌር ዘመን ያለፈበት ስለሆነ ሊዘምን (update) ይገባዋል በማለት ተወካዩ የገለጹ ሲሆን፤ አክለውም፡- ‹*የእኔ የሥራ ክፍል ከስልኮች፣ ከኮምፒዩተሮች፣ እንዲሁም ከማኅበራዊ ሚዲያ ፕላትፎርሞች ለምሳሌ ፌስቡክ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ላይ ምርመራ ያካሂዳል። ችግሩ ግን ቁሳቁስ፣ ሶፍትዌር፣ ሀርድዌር፣ እና ሥልጠና ነው። ሶፍትዌሩ ዘመን ያለፈበት ነው፤ የአገልግሎት ዕድሜው ለሦስት ወይም ለሁለት ዓመታት ነው። ሊዘምን ይገባል፤ ስለዚህ በጣም አስቸጋሪ ነው*› ብለዋል። (RA1-ET-12-A) በተጨማሪም፤ በሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ ድርጊቶች እና ቁሳቁሶች ላይ እየሠሩ ላሉት የሚደረግ የሥነ-ልቦናዊ የበላይ ክትትል የለም።

ኢትዮጵያ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን ለመመርመር በልዩ የተደራጀ የሥራ ክፍል የላትም። እንደ ሕግ አስከባሪው ዘርፍ አባባል ከሆነ፤ ለሁሉም ዓይነት የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ምርመራዎች በድምሩ 180 አባላት ተመድበው እየሠሩ ሲሆን፤ ሥምሪታቸው የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል-ነክ ነገረ-ጉዳዮችን ምናልባት ሊጨምር ቢችልም፤ ከእነዚህ አባላት ውስጥ አንዳቸውም ስለ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ሥልጠና ላይኖራቸው ይችላል። (RA8-ET) የፖሊስ መኮንንኖች እና የፍርድ ቤት ዳኞች ስለ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ሥልጠና እንዳልተሰጣቸው በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሕፃናት ፍትሕ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ የተናገሩ ሲሆን አክለውም፤ ‹*በመሬት ላይ እየሆነ ያለው ነገር፤ ወሲባዊ ጥቃቶችን ለመመርመር ሥልጠና የወሰዱ የፖሊስ አባላት የሌሉን መሆኑን ነው*›። (RA1-ET-06-A)

የኢትዮጵያ ሕግ አስከባሪው ዘርፍ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል  ላይ ያለው የቴክኒክ ክህሎት ውሱን በመሆኑ የተነሣ፤ የተመድ የአደንዛዥ ዕፅ እና የወንጀል ጽሕፈት ቤት (በእንግሊዝኛው United Nations Office on Drugs and Crime) በፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ውስጥ የተማከለ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን ለመግታት የሚያሻውን ዓይነተኛ አቅም የጨበጠ አደረጃጀትን በመገንባት ላይ አተኩሮ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ለዚሁ ግብ መዳረሻ እንዲሆን፤ የተመድ የአደንዛዥ ዕፅ እና የወንጀል ጽሕፈት ቤት ለከፍተኛ የፖሊስ ኃላፊዎች በናይሮቢ ኬንያ[101] ወዳለው የ‹*ጾረ-የሰዎች ዝውውር እና የሕፃናት ጥበቃ ክፍል*› ትምህርታዊ ጉብኝት አዘጋጅቶ ነበር። (RA1-ET-13-A) በተጨማሪም፤ የተመድ የአደንዛዥ ዕፅ እና የወንጀል ጽሕፈት ቤት በሳይበር ወንጀል ክፍሉ ውስጥ ለሚሠሩ እና የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን ለሚመረምሩ መርማሪዎች የሥራ ላይ ሥልጠና መስጠት የጀመረ ሲሆን፤ በግምት 19 ያህል መርማሪዎች የሥራ ላይ ሥልጠና ወስደዋል። ለ19ኙ አባላት ሥልጠናው የተሠጠው በዎርክሾፕ መልክ ሳይሆን፤ ከተመድ የአደንዛዥ ዕፅ እና የወንጀል ጽሕፈት ቤት የመጣ ባለሙያ በየተወሰነ ክፍለ-ጊዜ ከጥቂት አባላት ጋር አብሮ ተቀምጦ፤ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ምርመራ ላይ ያሉ ውስብስብ

101. ይህ በኬንያ የበ/መ/ሕ/ወ/ብ/በደል ምርመራ ላይ ያተኮረ የሥራ ክፍል ነው።

## 3.2 የሕግ አስከባሪው ምላሽ

ጉዳዮችን አብሮ እየከወነ፤ እንዲሁም ተገቢውን የሕግ ሂደት ተከትሎ ማስረጃ ማግኘት ስለሚቻልበት ብልኀት አብሮ እያሰየ የተከናወነ ነበር።

ተመሳሳዩ የተመድ የአደንዛዥ ዕፅ እና የወንጀል ጽሕፈት ቤት ምላሽ ሰጪ እንዳለው፤ ጽሕፈት ቤቱ የሳይበር ወንጀል ክፍሉ ወደ ሥራ እንዲገባ የሚያስፈልጉትን ሁሉንም ቁሳቁሶች ለመርዳት ፍላጎት ያለው ሲሆን፤ ስለዚሁ ጉዳይ በፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ውስጥ ካሉ ፖሊሲ አውጪዎች ጋር ውይይት ተጀምሯል፤ ‹በኢትዮጵያ ውስጥ የሳይበር ወንጀል ክፍል አለ … በክፍሉ ውስጥ፤ የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ ወንጀሎችን የሚመረምር ማእከል ማቋቋም እንፈልጋለን። በናይሮቢ ያለው በኢትዮጵያም እንዲኖር እንፈልጋለን … በኢንተርፖል በኩል እንዲሁም ከጠፉ እና ለብዝበዛ ከተጋለጡ ሕፃናት ብሔራዊ ማእከል በኩል የሚመጣልንን መረጃ ለማሳለጥ እንፈልጋለን፤ እናም ይህንን መረጃ በመጠቀም ወንጀለኞች የሚያዙበትን ሁኔታ ለመፍጠር እንፈልጋለን። ብዙዎቹ ዕቃዎች ተገዝተዋል፤ የሚቀረው ተከላ ብቻ ነው›። (RA1-ET-13-A)

የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ያጋጠማቸውን ታዳጊዎችን መደገፍ የሚችሉ በማኅበረሰብ እርከን ላይ ያሉ የሠለጠኑ ባለሙያዎች እጥረት በመላው ኢትዮጵያ ይታያል። (RA1-ET-02-A) የግንባር ቀደም ሠራተኞች በተሳተፉበት ዳሰሳ ላይ ይህ ክፍተት መኖሩ ተረጋግጦ ነበር። ስለ ድጋፍ አገልግሎቶች በተመለከተ በነበረው ጥያቄ እና መልስ ላይ፤ በኢትዮጵያ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ለተጠቁ ሕፃናት የሚሰጡ የሕክምና፣ የሥነ-ልቦና፣ የሕግ፣ እና የመልሶ ማቋቋም አገልግሎቶችን አቅርቦት እና ጥራትን በጥቅሉ እንዴት እንዲገመግሟቸው ምላሽ ሰጪዎች ተጠይቀው ነበር። ሁሉም ምላሽ ሰጪዎች ለማለት በሚቻል መልኩ (ከ97 እስከ 100 በመቶ ወይም፤ በቁጥር ከ32 እስከ 33) የአገልግሎቶቹን ደረጃ ደካማ በማለት መድበዋቸዋል። እዚህ ላይ ትኩረትን የሚስበው ነገር፤ በኢትዮጵያ በዳሰሳው ከተሳተፉት ከ33 የግንባር ቀደም ሠራተኞች ውስጥ አንዳቸውም በባለፉት 12 ወራት በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ነገረ-ጉዳይ ላይ ሠርተው የማያውቁ መሆኑ ነው።

# 3.3 የፍትሕ ተደራሽነት እና ማካካሻዎች

**የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ተጎጂዎች ስላገኙት ፍትሕ የተመለከተ ግምገማ አሁን ላይ ለመቅረብ የሚቻል አልሆነም። ከ20 የሚልቁ ድርጅቶችን ምክር መጠየቅን ጨምሮ እ.ኤ.አ. ከሰኔ 2010 እስከ መስከረም 2013 ድረስ ሰፊ ፍለጋ የተካሄደ ቢሆንም፤ በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ያሉ እና የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል-ነክ ነገረ-ጉዳዮች ላይ የሥራ ልምድ ያላቸው የወንጀል ፍትሕ ባለሙያዎችን ዲስረፕቲንግ ሀርም ለማግኘት ተስኖታል፡ ፡ በተመሳሳዩ ፍትሕ ለማግኘት የሞከሩ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ተጎጂዎችንም ለማግኘት የሚቻል አልሆነም።**

ከሕፃኑ/ኗ ወደ ችሎቱ ወይም ከችሎቱ ወደ ሕፃኑ/ኗ ጥያቄዎችን በአቀባባይ አማካኝነት የሚተላለፍበትን አማራጭ ጨምሮ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ከሕፃናት ምሥክርነትን ወይም የእማኝነት ቃሎችን ለመቀበል የሚያስችሉ ለሕፃን-ምቹ አሠራሮችን ተግብሯል[102፡103]። ሆኖም፤ የዲስረፕቲንግ ሀርም የምርምር ቡድን እነዚህ አሠራሮች ምን ያህል በደንብ እንደተተገበሩ ማረጋገጥ አልቻለም። ሌላው መጠቀስ የሚገባው ጉዳይ፤ የሕፃናት ፍትሕ አሠጣጥ መመሪያ (Child Justice Guidelines) ረቂቅ ሰነድ ላይ ለመወያየት እና ለማጽደቅ እ.ኤ.አ. በ2018 በኢትዮጵያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አዘጋጅነት የተካሄደ እና በርካታ የፍትሕ ባለድርሻዎችን ያሳተፈ የምክክር ስብሰባ ተካሂዶ ነበር[104]። በስብሰባው ላይ አራት መመሪያዎች እንዲጸድቁ ቀርበው የነበሩ ሲሆን፤ እነዚህም የተጎጂዎች ፈንድን ከማቋቋም፣ ለሕፃናት ነጻ የሕግ ድጋፍ አገልግሎትን ከማቅረብ፤ ለሕፃናት እና ለተንከባካቢዎቻቸው ጊዜያዊ መጠለያን፣ ምክርን፣ መጓጓዣን፣ ወይም የቤት ኪራይ አበልን በመስጠት ከመደገፍ፤ እንዲሁም በሥነ-ልቦና አገልግሎቶች ከማገዝ ጋር የተያያዙ ነበሩ[105]። ሆኖም ይህ ሪፖርት እስከተጻፈበት ጊዜ ድረስ፤ እነዚህ መመሪያዎች ተሠራጭተው ወይም ተተግብረው ስለመሆኑ በግልጽ የታወቀ ነገር የለም።

## ማካካሻ

የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 101፤ ተበዳይ ሰዎች ‹‹በዳዩ ያደረሰባቸውን ጉዳት እንዲክሳቸው ወይም ያፈረሰውን እንደነበረ እንዲመልስ እንዲሁም ለደረሰባቸው ጉዳት ተመዛዛኝነት ያለው ካሣ በኪሣራ ስም እንዲከፈላቸው እንዲፈረድበት ሊጠይቁ ይችላሉ››[106] ብሎ መብት ያጎናጽፋል። ይህ ማለት ቢያንስ በንድፈ-ሐሳብ ደረጃ፤ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ተጎጂዎች የፍትሐ-ብሔር ክስን ከወንጀል ክስ ጋር አጣምረው[107] ወይም በተናጠል በማቅረብ ካሣ የመጠየቅ ዕድል ያላቸው ሲሆን፤ ይህም የፍትሐ-ብሔር ሕግ አንቀጽ 2028 ባስቀመጠው ጠቅላላ መርኅ መሠረት ነው[108]።

በተጨማሪም የወንጀል ሕጉ፤ ከወንጀለኛው ላይ ከተያዘው ዕቃ ከሚገኘው ገንዘብ ውስጥ ወይም በዋስትና መያዣ ስም ካስያዘው ገንዘብ ውስጥ ወይም ከመቀጮው ውስጥ ወይም በጉልበት ሥራ ተለውጦ ከሚያገኘው የገቢ ሒሳብ ውስጥ ወይም ከተወረሰው ንብረት ሒሳብ ውስጥ ለተበዳይ ወገን ካሣ እንዲከፈል የሚያስችል ድንጋጌ አለው[109]። ሆኖም፤ ይህ ድንጋጌ በሃገር-አቀፍ ደረጃ ከሚተዳደር የገንዘብ ቋት የካሣ ክፍያን ለመጠየቅ የሚያስችል አማራጭን አልያዘም።የካሣ አከፋፈልን ከሚመለከቱት ድንጋጌዎች ውስጥ አንዱም ድንጋጌ ከበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ተጎጂዎች ጋር የሚያያዙ ዓይነተኛ እርምጃዎችን አይጠቅሱም። ካሣ የተቀበሉ ወይም አርኪ ማካካሻዎችን ያገኙ ሕፃናትን በተመለከተ ምንም መረጃ ለማግኘት አልተቻለም።

በመጨረሻም፤ ‹ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከልከል እና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 909/2007›፤ በወሲባዊ ብዝበዛ የተጎዱ ሕፃናትን ጨምሮ፤ በሰዎች ሕገ-ወጥ ዝውውር ጉዳት የደረሰባቸው ተጎጂ ሕፃናት የሚካሡበትን ድንጋጌ ይዟል። አልፎ ተረፎም፤ በአንቀጽ 31 (1) እና (2) ላይ በተደነገገው መሠረት ተጎጂዎች ካሣ ማግኘት ካልቻሉ እና ዜግነታቸው ኢትዮጵያዊ ከሆኑ፤ መንግሥት የማካካሻ ክፍያ እንዲከፍላቸው ለመጠየቅ የሚችሉ ሲሆን፤ ክፍያውም በአዋጅ ቁ 909/2007 አንቀጽ 32 እና 38 መሠረት ከተቋቋመው ፈንድ ላይ ተቀንሶ የሚከፈል ነው። ይህ አንቀጽ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ተጎጂ ሕፃናት ላይ ያለው ተፈጻሚነት ግልጽ አይደለም።

102. UNICEF Ethiopia. (2014, September 4). In Ethiopia, Danish diplomats observe progress in child protection. UNICEF Ethiopia blog. See also: UNICEF Ethiopia & Ministry of Finance. (2019, October). *National Situation Analysis of Children and Women in Ethiopia*.
103. UNICEF Ethiopia & Ministry of Finance. (2019). National Situation Analysis of Women and Children in Ethiopia.
104. Justice for All-Prison Fellowship Ethiopia. (2018, October 8). *Workshop on the validation of Draft Child Justice Guideline*. Justice for All-Prision Fellowship.
105. Justice for All-Fellowship Ethiopia. (2018, October 8). *Workshop on the validation of Draft Child Justice Guideline*. Justice for All-Prision Fellowship.
106. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (1997)፤ የወንጀል ሕግ፤ አንቀጽ 101
107. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (1997)፤ የወንጀል ሕግ፤ አንቀጽ 101
108. የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት (1952)፤ የፍትሐ-ብሔር ሕግ፤ አንቀጽ 2028
109. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (1997)፤ የወንጀል ሕግ፤ አንቀጽ 102 (1)

# 3.4 ቅንጅት እና ትብብር

**የማቀናጀት እና ትብብሩን የመቆጣጠር ሚና የመንግሥት የሆነበት የዘርፈ-ብዙ ባለድርሻዎች አሠራርን መዘርጋት፤ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት  ወሳኝነት አለው። በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ምላሽ አሠጣጥ ረገድ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ በሲቪል ማኅበረሰቡ፣ እንዲሁም በበይነ-መረብ አገልግሎት ሰጪዎች መካከል እየተተገበረ ያለው ቅንጅታዊ አሠራር ገና በእንጭጭ ደረጃ  ላይ ያለ መሆኑን በኢትዮጵያ የተሰበሰበው ጥሬ መረጃ ያሳያል።**

የሕግ ማእቀፍ እና የፖሊሲ ዳሰሳ በሚለው ርእሰ-ክፍል ላይ እንደቀረበው፤ በአሁኑ ወቅት ከበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጋር የሚዛመዱ ምንንም ዓይነት ሃገር-አቀፍ ፖሊሲዎች እና ዕቅዶች የሌሉ ሲሆን፤ ይህም የመንግሥት ምላሽ አሠጣጥ ላይ ጉልህ ክፍተት መኖሩን ያሳያል። ይህ ክፍተት ለተሟላ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ምላሽ አሰጣጥ ተሳትፏቸው ወሳኝ በሆኑ በሌሎቹ ባለድርሻ አካላትም ዘንድ በተመሳሳይ የሚታይ ችግር ነው። ለምሳሌ ያህል፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ወስጥ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ምላሽ አሠጣጥ ተሳትፎ የነበራቸው ጥቂቶቹ ብቻ ሲሆኑ፤ በሌሎች ሃገራት ያሉ የሲቪል ማኅበረሰብ አካላት ግን ነገረ-ጉዳዮች ወደ ፖሊስ እንዲመሩ በማድረግ፣ በፍርድ ቤት ሂደት ላይ ተጎጂዎችን በመደገፍ፣ በትምህርት ቤቶች እና በሕፃናት ዘንድ ግንዛቤን በመፍጠር፣ እንዲሁም ግንባር ቀደም አገልግሎት ሰጪዎችን እና ሌሎች ባለሙያዎችን በማሠልጠን ረገድ ወሳኝ ሚና እየተጫወቱ ይገኛል።

የፍትሕ ኃላፊዎች በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ዙሪያ ስላላቸው ትብብር በተመለከተ፤ ከፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ-ሕግ ጽሕፈት ቤት የመጡ አንድ ምላሽ ሰጪ እንዳሉት፤ በሕፃናት ላይ በሚፈጸሙ ወንጀሎች ላይ ያለው ትብብር በጥቅሉ ጥሩ የሚባል ነው፤ ምክንያቱም በወንጀል ፍትሕ መስክ ውስጥ ያሉ የተለያዩ አካላት (ፖሊስ፣ ዐቃቤ-ሕግ፣ እና ፍርድ ቤቶች) የሕፃናት ነገረ-ጉዳዮችን የማስተናገድ ተልእኮ የተሰጣቸው የሥራ ክፍሎች ያሏቸው በመሆኑ ነው። እነዚህ አካላት ሕፃናትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተቀራርበው ለመሥራት የተቀመጡ አደረጃጀቶች መሆናቸውን ምላሽ ሰጪዋ ያብራሩ ሲሆን፤ አክለውም ‹በፍትሕ ተዋናዮች መካከል ጠንካራ ቅንጅት አለ። እያንዳንዱ ዘርፍ በሕፃናት ጉዳዮች ላይ የሚሠራ የራሱ አደራጃጀት አለው፤ ፖሊስ በሃገር-አቀፍ ደረጃ እና በዝቅተኛ እርከኖች የተዋቀሩ የሕፃናት ጥበቃ የሥራ ክፍሎች አሉት፤ ዐቃቤ-ሕግ በሕፃናት እና በሴቶች ላይ ያተኮረ የተለየ የሥራ ክፍል አለው፤ እነዚህ ሁለት የሥራ ክፍሎች ተቀራርበው በጋራ ይሠራሉ፤ ፍርድ ቤቶች ለሕፃናት ምቹ ችሎቶች አሏቸው። ስለዚህ ሁሉም በጥሩ ሁኔታ አብረው እየሠሩ ነው›። (RA1-ET-05-A)

ይህ በዚህ እንዳለ፤ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ-ሕግ ጽሕፈት ቤት አንድ ተወካይ እንዳሉት፤ የሕፃናት የፍትሕ ጉዳዮች ላይ ለመምከር የሚመለከታቸው ኃላፊዎችን በአንድ ቦታ የሚያሰባስብ ቅንጅታዊ አሠራር ያለ ሲሆን፤ ሆኖም የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ርእሰ-ጉዳይ በአሠራሩ ስትራቴጂ እና የአፈጻጸም ዕቅድ ውስጥ የተካተተ አይደለም (RA1-ET-05-A)። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከሳይበር ወንጀል ክፍል የመጡ አንድ ምላሽ ሰጪ እንዳሉት፤ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን ለመመርመር እና ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ዕቅድ የሚነድፍ እና አሠራሮችን የሚያስቀምጥ ከሁሉም የፍትሕ አካላት እና ከሌሎች የመንግሥት ሚኒስቴሮች ተውጣጥቶ የተዋቀረ ፎረም ስለሌለ፤ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ዙሪያ ያለው ቅንጅት ክፍተት አለበት። ምላሽ ሰጪው አክለው እንዳሉት፤ ምንም እንኳ ፖሊስ የተለያዩ የፖሊስ የሥራ ክፍሎችን በአንድ ላይ የሚያሰባስቡ ፎረሞች ያሉት ቢሆንም፤ ፎረሞቹ ስለ ወንጀሎች በደፈናው ውይይት የሚደረግባቸው በመሆኑ፤ የሚከተለውን ምክረ-ሐሳብ ሰጥተዋል፤ ‹ፖሊስ፣ መንግሥት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ጨምሮ የሚመለከታቸው አካላት በሙሉ በቅንጅት መሥራት አለባቸው፤ እንዲሁም ለበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል አንድ ፎረም ሊኖር ይገባል›። (RA1-ET-12-A)

ወንጀሎችን ለመመርመር፣ ጥፋተኞችን ለማስቀጣት፣ እና የሕ/ወ/በ/ቁሳቁሶችን ሥርጭት ለመግታት፤ በሕግ አስከባሪዎች፣ በፍትሕ ተዋንያን፣ እንዲሁም በበይነ-መረብ አገልግሎት ሰጪዎች እና ፕላትፎርሞች መካከል ያለው ቅንጅት ወሳኝነት አለው። ከዚህ አኳያ ያሉት ሕጋዊ ደንቦች እና ተግባራዊ ሥነ-ሥርዓቶች የሚወሰኑት፤ እነዚህ አንቀሳቃሾች ኢትዮጵያዊ ኩባንያዎች አሊያም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ዓለም-አቀፋዊ የበይነ-መረብ አገልግሎት ሰጪዎች በመሆናቸው ላይ የተመረኮዘ ነው። ሕግ አስከባሪዎች የአጥፊውን ማንነት ለመለየት እና ያለበትን ለማወቅ ሲሹ (የአይፒ መለዮን ወይም በሃገር ውስጥ ኩባንያ የተሰጠ ስልክ ቁጥርን)፤ የደንበኛው መረጃ እንዲሰጣቸው  ለሃገር ውስጥ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቱ ሕጋዊ ጥያቄ ማቅረብ የሚችሉ ሲሆን፤ በመረጃውም ተጠርጣሪውን ለመያዝ፤ ብሎም ለፍርድ ቤት እንደ ማስረጃ ለመጠቀም ይችላሉ።[110]

ይሁንና፤ አብዛኛውን ጊዜ እንደሚያጋጥመው በመረጃ ማሰባሰብ ሂደት ላይ አንድ ተጨማሪ ሥራ ያጋጥማል፤ ይህም ከዓለም-አቀፍ ፕላትፎርሞች ለምሳሌ ከፌስቡክ ማስረጃ ማሰባሰብ የሚያስፈልግበት ሁኔታ ሲፈጠር ነው። በኢትዮጵያ ያሉ ባለሥልጣኖች እ.ኤ.አ. በ2017፣ በ2018፣ እና በ2019 ባሉት ጊዜያት ውስጥ በይዘቶች ላይ ገደብ እንዲጣል ወይም የደንበኞቻቸው መረጃ እንዲሰጣቸው አንድም ጥያቄ ለዐበይት የማኅበራዊ ሚዲያ ፕላትፎርሞች አቅርበው አያውቁም። ይህ የሚያመለክተው፤ ከዓለም-አቀፍ የኤሌክትሮኒክ አገልግሎት ሰጪዎች (በዋናነት ከፌስቡክ) የተሰጡ በሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያን የተመለከቱ አጠራጣሪ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጉዳዮች ላይ ያጠነጠኑ የጠ/ብ/የ/ብ/ሕ/ማእከል የሳይበር ጥቆማዎች እያሉም፤ በሃገሪቱ ያሉ ሕግ አስከባሪ አካላት በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጉዳይ ዙሪያ ከእነዚህ አገልግሎት አቅራቢዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት ዝቅተኛ መሆኑን ነው።

110. ይህ አገላለጽ፤ የበይነ-መረብ አገልግሎት ሰጪዎች ቨርዥን 4 በፍጥነት እየተመናመኑ የሚሄዱ የአይፒ መለዮዎችን በአንድ ጊዜ ለበርካታ ተጠቃሚዎች በሚታደሉበት አሠራር፤ ማለትም (በእንግሊዝኛው carrier grade Network Address Translation) የተነሣ የሚከሠቱ ተግዳሮቶችን የማያካትት ሲሆን፤ በዚህ የተነሣም በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ከአይፒ መለዮው ጀርባ ያለውን መገልገያ መሣሪያ እና ተጠቃሚ ማንነት በማያሻማ አኳኋን ለመለየት እንዳይቻል ያደርገዋል።

# 4. በኢትዮጵያ እንዴት ጉዳትን መግታት እንደሚቻል

የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የሚያደርሰውን ጉዳት ለመግታት፤ የሁሉንም ባለድርሻዎች (ቤተሰቦች፣ ማኅበረሰቦች፣ መንግሥታዊ ኃላፊነት-የተጣለባቸው፣ የሕግ አስከባሪ መሥሪያ ቤቶች፣ የፍትሕ እና የማኅበራዊ ድጋፍ አገልግሎት ባለሙያዎች፣ እንዲሁም የሃገር-አቀፍ እና ዓለም አቀፍ የቴክኖሎጂ እና የተግባቦት ኢንደስትሪውን) ሁለንተናዊ እና ያላሰለሰ ጥረት ይሻል። ምንም እንኳ ሕፃናትም የመፍትሔው አካል ቢሆኑም፤ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የሚያደርሰውን ጉዳት አዋቂዎች ለሕፃናቱ ተገን ሁነው እንዲከላከሉ የግድ ይላል። ሕፃናት ራሳቸውን የመጠበቅ ኃላፊነትን ያለ እገዛ በራሳቸው ብቻ እንዲሸከሙ እንዳናደርግ መጠንቀቅ ይገባናል።

በኢትዮጵያ እንዲተገበሩ የተሰጡ ዝርዝር ምክረ-ሐሳቦች፤ ከዲስረፕቲንግ ሀርም ምርምር የተገኙ አራት ዐበይት ቁምነገሮች በሚሉት አርእስት ሥር ተሸክፈው የቀረቡ ሲሆን፤ በየዘርፉ ባሉ የተለያዩ ባለድርሻዎች የተቃኘ አጭር ማብራሪያንም ይዟል። ይሁንና እነዚህ የትግበራ ምክረ-ሐሳቦች እርስ በእርሳቸው የተቆራኙ ስለሆነ፤ ውጤታማ የሚሆኑት ሁሉም አንድ ላይ ሲተገበሩ ነው።

## ቁምነገር 1.

**በባለፈው ዓመት ብቻ በኢትዮጵያ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ካላቸው በይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት መካከል 10 በመቶዎቹ፤ በዓይነታቸው እጅግ በከፉ የበይነ-መረብ ወሲባዊ ብዝበዛ እና የበደል ድርጊቶች ተጠቅተዋል፡ ፡ ይህም ሕፃናት በወሲባዊ ድርጊቶች እንዲሳተፉ በመያዣ ማስገደድን (blackmailing)፣ የገዛ ወሲባዊ ምስሎቻቸውን ያለይሁንታቸው ለሌሎች ማጋራትን፣ ወይም በገንዘብ እና በስጦታ በመደለል በወሲባዊ ድርጊቶች እንዲሳተፉ የማስገደድ ድርጊቶችን ያካትታል። አኃዙ ከጠቅላላው የሕዝብ ብዛት አንጻር ሲሰላ፤ በአንድ ዓመት ውስጥ ብቻ 300 ሺህ የሚገመቱ ሕፃናት ከእነዚህ ጎጂ ድርጊቶች በአንዱ መጠቃታቸውን ያመለክታል።**

### መንግሥት

**1.1 በመጪው ዓመታት የበይነ-መረብ ትስስሩ (በተለይም በታዳጊ ወጣቶች ዘንድ) በእርግጠኝነት እያደገ የሚሄድ እንደመሆኑ ትስስሩ ሰፊ ደረጃ ከመድረሱ በፊት፤ የዲጂታል ቴክኖሎጂ ሊጫወት የሚችለውን ሚና ጨምሮ ስለ ሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ግንዛቤ ለመፍጠር አጋጣሚውን ይጠቀሙበት።** እነዚህ ፕሮግራሞች በማስረጃ ላይ የተመረኮዙ ሊሆኑ እና፤ አብዛኛውን ጊዜ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ፈጻሚዎች አስቀድሞ በሕፃኑ/ኗ የሚታወቁ ሰዎች መሆናቸውን ጨምሮ በይፋ ለመናገር የሚያስቸግሩ እና ስሱ (sensitive) ይዘት ያላቸውን የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ርእሰ-ጉዳዮች ፕሮግራሞቹ ያለማለባበስ በድፍረት ሊገልጹ ይገባል። በአሁኑ ወቅት እየተተገበሩ ያሉ ማስረጃን የተመረኮዙ ፕሮግራሞችን ከነባራዊ ሁኔታው አንጻር የማወረስ እና የመቃኘት ሥራ ቅድሚያ ሊሰጠው፤ ብሎም አሁን ያሉ በማስረጃ የተደገፉ ሰነዶችን እንደመንደርደሪያ መጠቀምን በእሳቤ ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል።

በትምህርት ቤቶች ለሚካሄዱ የግንዛቤ እና የትምህርት ፕሮግራሞች፤ እንዲሁም በመላ ሃገሪቱ ወዳሉ ማኅበረሰቦች በመድረስ ረገድ፤ የመሪነቱን ሚና የሚጫወተው የትምህርት ሚኒስቴር ነው። ከሕፃናት መብት ክበቦች እና የአቻ-ለአቻ አደረጃቶች ጋር የመገናኛ መድረክ መፍጠር የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ግንዛቤን ለመፍጠር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል (ይህም የአቤቱታ ማቅረቢያ መንገዶችን ጨምሮ ነው፤ ቁምነገር 3ን ይመለከቷል)። መረጃዎቹ ለወላጆች በሚሰጡ የትምህርት ፕሮግራሞች ውስጥም ሊካተቱ ይገባል።

ስለ በይነ-መረብ ስጋቶች ያሏቸውን አተያዮች እና ራሳቸውን ለመጠበቅ የሚጠቀሟቸውን ቴክኒኮች ወይም ስልቶች በፕሮግራሞቹ ውስጥ ለማንጸባረቅ እንዲቻል፤ ከሕፃናት እና ከተንከባካቢዎች ጋር አስቀድሞ በሚደረግ ምክክር መነሻነት፤ የግንዛቤ እና የትምህርት ፕሮግራሞች ሊዘጋጁ እና ሙከራ ሊደረግባቸው ይገባል። በቁልፍ ዓላማዎች ውስጥ ሊካተቱ የሚገቡ ነገሮች፡-

- ሕፃናት ስለ በይነ-መረብ ውሏቸው ከተንከባካቢዎቻቸው ጋር እንዲወያዩ የሚያስችላቸውን ውጥረት-አልባ እና ያልተቋረጠ ግንኙነት ለማዳበር ተንከባካቢዎችን በዕውቀት እና በክህሎት ማነጽ
- ስለ ወሲብ የሚደረግ ውይይትን የሚገድቡ፤ እንዲሁም ከመሳቀቅ እና ከኃፍረት ስሜት የተነሣ በሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ዙሪያ ሕፃናት እና አዋቂዎች ችግራቸውን ገልጠው ዕርዳታ ከማፈላለግ እንዲቆጠቡ የሚያደርጉ ወጎችን እና በልማድ የተነወሩ ብሂሎችን (taboos) መታገል፤
- ተንከባካቢዎች (ብዙዎቹ በይነ-መረብን ጨርሶ ተጠቅመው አያውቁም) በይነ-መረብን መጠቀም እንዲጀምሩ፤ እንዲሁም ሕፃናቶቻቸው እና ታዳጊ ልጆቻቸው ከሚጠቀሟቸው ፕላትፎርሞች ጋር ራሳቸውን ይበልጥ እንዲያላምዱ መደገፍ፤
- በበይነ-መረብ ላይ የሚያጋጥሙ አደገኛ ሁኔታዎችን ለማስቀረት እና በብልኀት ለማለፍ የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን እና ግንዛቤን እንዲጨብጡ የሕፃናትን የዲጂታል ዕውቀት ማጠናከር፤ ይህም አንድ ግለሰብን ማገድ እና ያልተገቡ ይዘቶችን ወይም ጥያቄዎችን ሪፖርት ማድረግ ስለሚቻልበት መንገድ የሚሰጡ ትምህርቶችን ሊያጠቃልል ይችላል። በተጨማሪም፤ በበይነ-መረብ መስተጋብር ላይ፤ እንዲሁም የግል መረጃዎችን፣ ምስሎችን፣ እና ቪዲዮዎችን በመለዋወጥ ሂደት ላይ መቼም ቢሆን አብረው ስለሚፈጠሩ ስጋቶች የሕፃናትን ዕውቀት መገንባት፤

**1.2 ሕፃናት ለዕድሜያቸው የተገባ እና የባህል ስሱነትን ያገናዘበ (የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን ጨምሮ) ጾታዊ ትምህርትን ካላገኙ፤ አጥፊዎች እንደ መልካም አጋጣሚ ይጠቀሙበታል።** ትምህርቱ ለሁሉም ሕፃናት መዳረሱን ማረጋገጥ አለብን፤ ይህም ስለ ወሲብ፣ ስለ ይሁንታ፣ ስለ ግል ድንበሮች፣ አዋቂዎች ወይም በሕፃናት ዙሪያ ያሉ ሌሎች ሰዎች በሕፃናት ላይ ማድረግ የሚችሉት ወይም የማይችሉት ነገሮች ምን እንደሆኑ፤ ወሲባዊ ምስሎችን በመቅረጽ፣ በመላክ፣ እና በመቀበል ሂደት ላይ ያሉ ስጋቶች እና ኃላፊነቶች ምን እንደሆኑ፣ እንዲሁም ለሰዎች እንዴት እምቢ ማለት እንደሚቻል የተመለከቱ መረጃዎችን ሊጨምር ይገባል። ይሄም በበይነ-መረብ ላይም ሆነ በአካል/በፊትለፊት መደረግ የሌለባቸውን አደገኛ ወይም ያልተገቡ ግንኙነቶችን ለይተው እንዲያውቁ ሕፃናትን ያግዛቸዋል። የዕድሜ-ገብ (age-appropriate) ሰነዶችን[111] በማዘጋጀት ረገድ እንደ ምርጥ ተሞክሮ ሊወሰዱ የሚችሉ እና እንደ ጥሩ መነሻ የሚገለግሉ አሁን ላይ ሊገኙ የሚችሉ ሪፖርቶች[112] እና ትግበራዎች[113] አሉ።

**1.3 ከሕፃናት ጋር ግንኙነት ያላቸው አዋቂ ሰዎች ስለ ወሲብ እና የወሲብ አማላይነት (sexuality) እንዳይወያዩ የሚያደርጋቸውን ምቾት የሚነሣ ስሜት ተቆጣጥረው፤ በበይነ-መረብ ወይም በአካል ስለሚካሄድ ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል በግልጽ ለመነጋገር እንዲደፍሩ ያበረታቷቸው።** ይህ ሲደረግ፤ እያደር በረዥም ጊዜ ተንከባካቢዎች ከሕፃናቶቻቸው ጋር ለማውራት እና ድጋፍ ለመስጠት እየቀለላቸው እንዲሄድ፤ ብሎም ዕርዳታ ሲያሻቸው ሕፃናት ወደ ተንከባካቢዎቻቸው የመሄድ ዝንባሌያቸው እንዲጨምር ያደርጋል። ተንከባካቢዎችን ለማገዝ ከተፈለገ፤ በበይነ-መረብ ላይም ሆነ ከበይነ-መረብ ውጪ በሁለቱም ከባቢዎች ውስጥ ያሉ የማኅበረሰቡ አባላት ሊያንጸባርቋቸው የሚችሉ የብዝበዛ እና የበደል አዝማማያዎችን/ጠባያትን ለይተው ለማወቅ የሚያስችላቸውን በማስረጃ የተደገፈ ትምህርት እና

111. UNFPA. (2021). My Body is My Own.
112. UNGEI. (2020). Bodily autonomy and SRHR.
113. NSPCC. (2017). Talk PANTS with Pantosaurus and his PANTS song #TalkPANTS - YouTube.

መረጃ ለተንከባካቢዎች እንዲሰጥ ያድርጉ። ይሄም እንዴት መሰል ጠባያትን መለየት እንደሚችሉ እና ደኅንነታቸውን እንደሚያስጠብቁ ሕፃናትንም ጭምር ለማስተማር ያስችላቸዋል። ከዚህ በፊት የተሠራባቸው ምርጥ ተሞክሮዎች[114] ስላሉ፤ እነዚህን እንደመነሻ ወስዶ እና ከአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ጥቅም ላይ ማዋል ይቻላል።

**1.4 ሕፃናት፣ ተንከባካቢዎች፣ መምህራን፣ እና ከሕፃናት ጋር አብረው የሚሠሩ ሰዎች፤ ወሲባዊ ምስሎችን ማጋራት ስለሚያስከትለው አደጋ በሁለንተናዊ አድማሱ እንዲገነዘቡ** እንዲሁም በዚህ የተነሣ ምናልባት ዐሉታዊ ጠንቆች ቢከሠቱ ጉዳቱን መቀነስ ስለሚቻልበት እርምጃዎች እንዲያውቁ ያግዟቸው። ወሲባዊ ይዘቶችን ለሌሎች ያጋሩ አብዛኞቹ ሕፃናት ድርጊቱን የፈጸሙት ፍቅር ስለያዛቸው ወይም ተቀባዩን ግለሰብ ስለሙኑት ነበር፤ ሆኖም ይህ ዓይነቱ ጠባይ ለከፋ ጉዳት ሊዳርግ ይችላል፤ ለምሳሌ ያለባለቤቶቹ ይሁንታ ይዘቱ ለሌሎች ሊተላለፍ እና ለወሲብ አስገድዶ-መጠቀም ሊውል ይችላል።

**1.5 የትምህርት እና የግንዛቤ ማሳደጊያ እንቅስቃሴዎችን በኢትዮጵያ ላሉ ለሁሉም ሕፃናት፣ ተንከባካቢዎች፣ እና መምህራን ማዳረስ ይገባል።** ከገጠር አቻዎቻቸው ይልቅ የከተማ ሕፃናት ከፍ ያለ የበይነ-መረብ ተደራሽነት ስላላቸው ለበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ይበልጥ የመጋለጥ ስጋት አላቸው የሚል እምነት አለ። አባባሉ የተወሰነ እውነትነት ቢኖረውም፤ ሙሉ ሥዕሉን ግን አይናገርም። በመላ ሃገሪቱ ተደራሽነቱ እየተሻሻለ በሄደ መጠን በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት በፍጥነት ትርጉም እያጣ እንደሚሄድ እሙን ነው።

**1.6 ሁሉም ተደራሲያን (ሕፃናት፣ መምህራን፣ እና አዋቂዎች) የሚሳተፉበትን ትምህርት መስጠት ያለባቸው ጉዳዩን እና መፍትሔዎቹን በቅጡ የተገነዘቡ ሰዎች ሊሆኑ ይገባል።** ከዚህ በፊት በተጨባጭ የደረሱባቸውን የበይነ-መረብ አደጋዎችን የሚቀርፍላቸው መሆኑን፤ ብሎም ሕፃናት ደኅንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችሏቸው ቴክኒኮች በትምህርቱ ውስጥ መካተታቸውን ለማረጋገጥ እንዲቻል፤ ከሕፃናት፣ ከተንከባካቢዎች፣ እና ከመምህራን ጋር በሚደረግ ደኅንነቱ በሚያስተማምን እና ሥነ-ምግባርን ጠብቆ በሚካሄድ ወይይት አማካኝነት የግንዛቤ እና የትምህርት ፕሮግራሞች ተዘጋጅተው ሊፈተሹ ይገባል። አሠልጣኞች ወሲብ እና ቴክኖሎጂን (ሁለት ውስብስብ ርእሰ-ጉዳዮችን) ባጣመሩ የትምህርት መርጃ ቁሳቁሶች እየተረዱ ለሌሎች ዕውቀታቸውን እንዲያካፍሉ ተግባር-ተኮር ሥልጠና እና ድጋፍ ሊያገኙ ይገባል፡
፡ ዓይነተኛ ትግበራዎቹ ጉዳተኛ ሕፃናት የመሳሰሉትን ጨምሮ አብዛኛውን ጊዜ መገለል የሚደርስባቸው ሕፃናትን ያካተቱ መሆኑን ያረጋግጡ።

## ተንከባካቢዎች፣ መምህራን፣ የሕክምና ባልደረቦች፣ እና የማኅበራዊ ድጋፍ ሠራተኞች[115]

**1.7 ተንከባካቢዎች እና ኃላፊነት-የተጣለባቸው አካላት ሕፃናት በበይነ-መረብ ላይም ሆነ ከበይነ-መረብ ውጪ ምን እየሠሩ እንደሆነ ማወቅ፤** ብሎም ከራሳቸው ሕፃናት ወይም በማኅበረሰባቸው ውስጥ ካሉ ሕፃናት ጋር ግንኙነት/ መስተጋብር ያላቸው ሰዎችን በንቃት መከታተል አለባቸው። እነዚህ መስተጋብሮች ለሕፃናት የሚገቡ ስለመሆናቸው ይገምግሙ። በይነ-መረብ ላይ ከበይተዋሮች የሚሰነዘሩ ጥቃቶች በዓይነታቸው ውስን ናቸው፤ ሌሎቹ በርካታ ስጋቶች የሚመነጩት ከአቻዎች፣ ከዘመድ፣ እና ከማኅበረሰቡ አባላት ነው።

**1.8 በዲጂታል ፕላትፎርሞች እና ቴክኖሎጂዎች ላይ ያለው ግንዛቤ እንዲሻሻል ያድርጉ።** የበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት ካሏቸው የኢትዮጵያ ተንከባካቢዎች ውስጥ 80 በመቶዎቹ በይነ-መረብን ፈጽሞ ተጠቅመው አያውቁም። ተንከባካቢዎች ራሳቸውን ከበይነ-መረብ ጋር ማላመድ እና የዲጂታል ክህሎታቸውን መገንባት ያሻቸዋል። ጎን ለጎንም፤ በበይነ-መረብ ምን ማከናወን እንደሚፈልጉ፣ እንዲሁም ጊዜያቸውን ለማሳለፍ የትኞቹን ፕላትፎርሞች ወይም ድረገጾች እንደሚመርጡ ከመጠየቅ ሊጀምሩ ይገባቸዋል። በልጆቻቸው የበይነ-መረብ አጠቃቀም ላይ ሲሳተፉ እና እገዛ ሲያደርጉ፤ እግረ-መንገዳቸውንም በይነ-መረብ ስላዘለው አደጋ እና ጠቀሜታ ለማወቅ፤ ብሎም ሕፃናቱ በበይነ-መረብ ላይ አደጋ ወይም ጉዳት በሚያጋጥማቸው ወቅት በሕፃናት እና በአዋቂዎች መካከል ይበልጥ ግልጽ የሆነ ውይይት የሚኖርበት ሁኔታን ይፈጥራል።

**1.9 ሕፃናት ከማንኛውም ዓይነት አካላዊ፣ ወሲባዊ፣ እና መንፈሳዊ በደሎች የመጠበቅ መብት እንዳላቸው፤** እንዲሁም ደኅንነታቸውን አስጠብቀው ለመቀጠል እንዲችሉ አንዴት ድንበራቸውን ማስመር እንዳለባቸው፣ ከአዋቂዎች እና በዙሪያቸው ካሉ ሰዎች የሚጠበቁ እና የማይጠበቁ ባሕርያትን፣ እና ያልተገባ ጠባይ ለሚያሳይባቸው ሰው እንዴት እንቢ ማለት እንዳለባቸው ያሳውቋቸው።

## ኢንደስትሪ

**1.10 ለሕፃናት በሚደርሱ የመረጃ ፈሰሶች ውስጥ ወሲባዊ ይዘቶች ሾልከው እንዳይገቡ ፕላትፎርሞች በራስ ተነሣሽነት መሥራት አለባቸው፤** ይህን ሲያደርጉም እንዳስፈላጊነቱ በመንግሥት ሕግጋት መገዛት ይጠበቅባቸዋል።

**1.11 የበይነ-መረብ አገልግሎት ሰጪዎች የሕፃናት ወሲባዊ በደል ቁሳቁሶችን ነቅሶ ለማውጣት እና ለማስወገድ የወጡ ሕግጋትን ማክበር አለባቸው።** የሕፃናት የበይነ-መረብ ቆይታ ደኅንነትን ለማረጋገጥ ይህንን ደንብ ተፈጻሚ ማድረግ ወሳኝ ነው።

114. See: the Australian eSafety Commissioner's programme'Start the Chat' to encourage caregivers to talk with their children about their lives online; and eSafety Commissioner's programme for seniors going online for the first time 'Be Connected.'

115. መንግሥት፣ የበይነ-መንግሥት ድርጅቶች፣ እና የሲቪል ማኅበረሰቡ እነዚህን መልእክቶች ተርጉመው ለተንከባካቢዎች፣ ለመምህራን፣ ለሕክምና ባልደረቦች፣ እና ለማኅበራዊ ድጋፍ ሠራተኞች ሊያዳርሱ ይገባል።

### ዲስረፕቲንግ ሀርም ከ‹ሃገር-አቀፍ ምላሽ አሠጣጥ ሞዴል› (Model National Response) ጋር ያለው ተጣጣሚነት

ብዙ ሃገራት፣ ኩባንያዎች፣ እና ድርጅቶች፤ የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት በእንግሊዝኛው የ‹ዊፕሮቴክት ግሎባል አሊያንስ› (WePROTECT Global Alliance) አባል ሆነዋል። አንድ አባል እንደመሆኗ ኢትዮጵያም (በእንግሊዝኛ ያለውን) የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን ለመከላከል እና ለመቅረፍ የሚውል ሃገር-አቀፍ የምላሽ አሠጣጥ ሞዴል ሰነድን በመጠቀም የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ምላሽ አሠጣጧን ለማደራጀት ትችላለች፡ ፡ ሞዴሉ መንግሥታት የምላሽ አሰጣጣቸውን ለማደራጀት እና ደረጃውንም ለማሻሻል የሚያግዝ ጠቃሚ መሣሪያ ነው።

በዚህ ሪፖርት የቀረቡት በርካታዎቹ የትግበራ ምክረ-ሐሳቦች፤ በ‹ሃገር-አቀፍ ምላሽ አሠጣጥ ሞዴል› ውስጥ ከተጠቀሱት ከ21ዱ ‹አቅሞች› ('capabilities') ጋር የሚጣጣሙ ቢሆንም፤ *ዲስረፕቲንግ ሀርም* ግን በተለይ የኢትዮጵያ ሁኔታን የሚመለከት ጥሬ መረጃን መሠረት በማድረግ የተቀመሩ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ የትግበራ አቅጣጫዎችን ለይቶ አስቀምጧል። በኢትዮጵያ ውስጥ የተገኘው ማስረጃ የሚያመለክተውነገር፤ ምንም እንኳ በ‹ሃገር-አቀፍ ምላሽ አሠጣጥ ሞዴል› ውስጥ የተጠቀሱ ጥቂቶቹ አቅሞች በኢትዮጵያ ውስጥም ያሉ ቢሆንም፤ አርኪ አገልግሎት እየሰጡ ግን አይደለም።

የ*ዲስረፕቲንግ ሀርም* ምክረ-ሐሳቦች በዋናነት ያተኮሩት በሕጎች[116]፣ ጉዳዩን በባለቤትነት የሚይዝ የሕግ አስከባሪ ስለማስፈለጉ[117]፣ በዳኝነት እና በዐቃቤ-ሕጎች[118]፣ እንዲሁም በትምህርት ፕሮግራሞች[119] ላይ ነው። ሁሉም ምክረ-ሐሳቦች ተግባር-ተኮር፣ ማስረጃ-አዘል፣ እና ተተግባሪ ናቸው። በተጨማሪም *ዲስረፕቲንግ ሀርም* የሰጣቸው ልዩ ልዩ ምክረ-ሐሳቦች ለእነማን እንደታለሙ ገልጿል (ማለትም መንግሥታዊ ኃላፊነት-ለተጣለባቸው፣ ለሕግ አስከባሪ ባለሥልጣናት፣ ለፍትሕ ባለሙያዎች፣ ለበይነ-መረብ እና ለቴክኖሎጂ ዘርፉ፤ አሊያም ለተንከባካቢዎች፣ ለማኅበረሰቡ፣ እና ለመምህራን)።

## ቁምነገር 2፡

### በኢትዮጵያ ለበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ከተዳረጉ ሕፃናት ውስጥ እጅግ ጥቂቶቹ ብቻ እንደ ዕርዳታ መጠየቂያ መስመሮች ወይም እንደ ፖሊስ ያሉ መደበኛ የአቤቱታ ማቅረቢያ አሠራሮችን ተጠቅመዋል።

#### መንግሥት

**2.1 የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን በብቃት ለማስተናገድ የተደራጀ ሃገር-አቀፍ** *የአደጋ ማሳወቂያ መስመር* **(hotline) መኖሩን ያረጋግጡ።** መስመሩ ከዓለም-አቀፍ መረቦች ጋር (ለምሳሌ ከ‹ኢንሆፕ› መረብ ጋር) ሊተሳሰር እና የሃገር ውስጥ የበይነ-መረብ አገልግሎት ሰጪዎች ጥፋት የፈጸመ ደንበኛቸውን አገልግሎት እንዲያቋርጡበት ትዕዛዝ የመስጠት ሥልጣን ሊኖራቸው ይገባል።

**2.2 የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን በብቃት ለማስተናገድ የተደራጀ ሃገር-አቀፍ** *የዕርዳታ መጠየቂያ መስመር* **(Helpline) መኖሩን ያረጋግጡ።** የመስመሮቹን ዘላቂነት፤ ብሎም ሁለቱንም አገልግሎቶች (ማለትም ሪፖርቶችን መቀበል እና ለሕፃናት የሥነልቦና-ወማኅበራዊ ድጋፍ) ለመስጠት የሚስችል አቅም እንዳላቸው ያረጋግጡ። በዕርዳታ መጠየቂያ መስመሮቹ ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞችን አቅም ለማሳደግ በሥልጠና ላይ ኢንቨስት ያድርጉ። የዕርዳታ መጠየቂያ መስመሮች በበቂ ሐብት እና የሰው ኃይል ሊደራጁ፤ ብሎም በዕርዳታ ፈላጊ ሕፃናት ዘንድ እንደ ሁነኛ አማራጭ ለመታየት የሚያስችላቸውን አመርቂ ጥራት ያለውን የክብካቤ እና የድጋፍ አገልግሎቶችን ማቅረብ አለባቸው። ሕፃናት ስለ ዕርዳታ መጠየቂያ መስመሮች እንዲያውቁ ተደርጎ እንኳ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ አቤቱታ ባቀረቡበት እና ዕርዳታ በጠየቁበት ወቅት ተሰጥቷቸው የነበረው ምላሽ ደካማ ከነበረ፤ ሕፃኑ/ኗ (እና ጉዳዩን የሚታዘቡ ሰዎች ጭምርም) ዕርዳታ ለማግኘት በድጋሚ የመመለስ ዕድላቸው የመነመነ ይሆናል።

**2.3 የማኅበራዊ አገልግሎት የሰው ኃይል አቅምን ለማሻሻል ኢንቨስት ያድርጉ፤** ስጋት ውስጥ የገቡ ወይም የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የደረሰባቸው ሕፃናትን በተሻለ ሁኔታ ለይቶ ለማወቅ እንዲቻል ከሕፃናት ጋር ግንኙነት ያላቸውን የግንባር ቀደም ሠራተኞችን አቅም ያዳብሩ። ይህም የሥነልቦና-ወማኅበራዊ ድጋፍ የሚሰጡትን ሁሉ አካትቶ መምህራንን እንዲሁም የትምህርት ቤት እና የጤና ሠራተኞችን ሊጨምር ይገባል፡ ፡ (ምክረ-ሐሳብ ቁጥር 2.11ን ይመለከቷል)

**2.4 የአደጋ ማሳወቂያ መስመሮች እና የዕርዳታ መጠየቂያ መስመሮች በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጉዳይ ላይ አቤቱታ የሚቀርብባቸው እና ዕርዳታ የሚጠየቅባቸው አሠራሮች መሆናቸውን ግንዛቤ የሚፈጥሩ እንቅስቃሴዎችን ያስፋፉ።** የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል-ነክ (እንዲያውም ስለ ማናቸውም ዓይነት የጥቃት፣ የብዝበዛ፣ እና የበደል ጉዳዮች) አቤቱታዎች ስለሚቀርብባቸው ስለእነዚህ አሠራሮች በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ያለው ግንዛቤ እጅግ አነስተኛ ነው። አንዱ ወሳኝ ቅድመ-ሁኔታ ለዕርዳታ መጠየቂያ መስመሮች በቂ ሐብት መመደብ፤ እንዲሁም መስመሮቹ አመርቂ ጥራት ያለው ክብካቤ እና ድጋፍ የሚሰጡ እንዲሆኑ ማድረግ የግድ ነው። ሕፃናት ስለ ዕርዳታ መጠየቂያ

116. ሃገር-አቀፍ ምላሽ አሠጣጥ ሞዴል ቁ. 3
117. ሃገር-አቀፍ ምላሽ አሠጣጥ ሞዴል ቁ. 4
118. ሃገር-አቀፍ ምላሽ አሠጣጥ ሞዴል ቁ. 5
119. ሃገር-አቀፍ ምላሽ አሠጣጥ ሞዴል ቁ. 13

መስመሮች እንዲያውቁ ተደርጎ እንኳ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ አቤቱታ በቀረበበት እና ዕርዳታ በተጠየቀበት ወቅት ተሰጥቶ የነበረው ምላሽ ደካማ ከነበረ፤ ሕፃኑ/ኗ (እና ጉዳዩን የሚታዘቡ ሰዎችም) ዕርዳታ ለማግኘት በድጋሚ የመመለስ ዕድላቸው የመነመነ ይሆናል።

### ሕግ አስከባሪ አካላት

**2.5 ለበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ነገረ-ጉዳዮች ግልጽ የአቤቱታ ማቅረቢያ ሂደቶችን መዘርጋት** እና የትግበራውን ሙሉነት ለማረጋገጥ እንዲቻል ለሁሉም የፖሊስ አባላት ሰፊ ሥልጠናዎችን ማዘጋጀት። በአሁኑ ሰዓት በበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎች እጅግ በጣም አስነተኛ የሚባሉ ብቻ ሳይሆን፤ ምንም የለም ወይም አንድም ጉዳይ ለማግኘት አልተቻለም። ሕፃናት ተጎጂ በሚሆኑባቸው አጋጣሚዎች ሁሉ ፖሊስ ለሕፃናት-ምቹ አሠራሮች መተግበሩን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥልጠና እና ክትትል ማድረግ። የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጉዳይን በአሁኑ ወቅት ስለ ሕፃናት ጥበቃ በሚዘጋጁ የሪፖርት ማቅረቢያ አሠራሮች ውስጥ እንዲካተት ማድረግ።

**2.6 በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እና በሕግ አስከባሪ አካላት መካከል በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ላይ ተኮረ የቅንጅታዊ አሠራሮችን ይፍጠሩ።** አስተማማኝ የመረጃ መለዋወጫ ፕላትፎርሞች የመሳሰሉትን ጨምሮ ማስረጃዎችን ለመለዋወጥ የሚያስችሉ ስልቶችን ያዘጋጁ።

### ተንከባካቢዎች፣ መምህራን፣ የሕክምና ባልደረቦች፣ እና የማኅበራዊ ድጋፍ ሠራተኞች[120]

**2.7** በሕፃናቱ የበይነ-መረብ ውሎ ዙሪያ በሕፃናት እና በሚታመኑ አዋቂዎች መካከል **ደኅንነቱ የተጠበቀ እና ያልተቋረጠ ግንኙነት እንዲዳብር ያድርጉ።** የበይነ-መረብ እንቅስቃሴያቸውን በተመለከተ ጤናማ ግንኙነት ካለ፤ ሕፃናት ማንኛውም ዓይነት አሳሳቢ ነገሮች፣ ስጋቶች፣ እና ጎጂ ክሥተቶች ቢያጋጥሟቸው ጉዳዩን የማሳወቅ ዝንባሌያቸውን ከፍ እንዲል ያደርገዋል።

**2.8 ሕፃናት የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ክሥተቶችን ሲያሳውቁ፤ ያደረጉት ነገር ምንም ሆነ ምን ጉዳዩ በፍጹም የሕፃኑ/ኗ ጥፋት አለመሆኑን በሚሰጣቸው ምላሽ ላይ ሊገለጽ ይገባል።** የሕፃናት ብዝበዛ እና በደል ድርጊት ጥፋቱ ሁሌም ቢሆን የአዋቂ ሰዎች ነው። ለበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የተዳረጉ ሕፃናት አብዛኛውን ጊዜ ጥፋቱን በራሳቸው ላይ እንደሚያላክኩ፤ እንዲሁም ተንከባካቢዎቻቸውን እና ሌሎች አካላትን እንዳሳጧቸው አሊያም በፖሊስ እንደሚፈረድባቸው የሚሰማቸው መሆኑን ጥናቱ ያሳያል። ምላሾቹ ከፍርድ ወይም ከቅጣት የራቁ ሊሆኑ ይገባል። ለምሳሌ እንግልት (maltreatment) ለደረሰበት ሕፃን ስለሚደረገው የመጀመሪያ ደረጃ ምላሽ የሚያብራራውን መመሪያ ይመልከቱ።

**2.9 ምናልባት ጉዳት እንዳያገኛቸው በሚል የሕፃናትን የበይነ-መረብ አጠቃቀም እምብዛም ለመገደብ አይሞክሩ፡** ፡ የቴክኖሎጂ ተደራሽነትን ማቀብ ለሕፃናት እንደ ቅጣት ሆኖ ይሰማቸዋል። ይህ መሰሉ ዕቀባ ሕፃናትን የሚያድናቸው ለጊዜው ብቻ እንጂ፤ ወደፊት ተመሳሳይ ነገር ሲገጥማቸው እንዴት ማለፍ እንደሚችሉ አያስተምራቸውም። ይህ ዓይነቱ ምላሽ ሕፃናት ስለደረሰባቸው ችግር ለአዋቂዎች ከመናገር እንዲቆጠቡም ያደርጋቸዋል። ከዚህ ይልቅ፤ ከበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ራሳቸውን እንዴት መጠበቅ እንደሚችሉ የሚመለከተውን ጨምሮ፤ ደኅንነቱን ያረጋገጠ የበይነ-መረብ አጠቃቀም ምንነት ዙሪያ ሕፃናትን እና ታዳጊዎችን ያስረዷቸው፤ ያስተምሯቸው።

**2.10 የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ስጋት ያጠላባቸውን ወይም ቀድሞውኑ ተጎጂ የሆኑ ሕፃናትን በተሻለ ለይቶ ለማወቅ እንዲቻል ከሕፃናት ጋር የሚገናኙ የግንባር ቀደም ሠራተኞችን አቅም ያዳብሩ።** ይህም የሥነልቦና-ወማኅበራዊ ድጋፍ የሚሰጡትን ሁሉ አካትቶ የትምህርት ቤቶች መምህራንን/ሠራተኞችን እንዲሁም የጤና ሠራተኞችን ሊጨምር ይገባል።

### ኢንደስትሪ

**2.11 ለሕፃናት ግልጽ እና ተደራሽ በሆኑ ፕላትፎርሞች የሚታገዝ መደበኛ የአቤቱታ ማቅረቢያ አሠራሮችን ያዘጋጁ፤** ብሎም ሕፃናት የአቤቱታ ሪፖርታቸውን ካስገቡ በኋላ ስላለው ሂደት ሕፃናት በሚገባቸው ቃላት የተዋቀሩ ማብራሪያዎችን ይስጡ። ፕላትፎርሞች እና አገልግሎት ሰጪዎች በሕፃናት ለቀረቡ አቤቱታዎች ፈጣን ምላሽ ሊሰጡ፤ ብሎም ግልጸኝነትን እና ተጠያቂነትን ሊያንጸባርቁ ይገባል። የበይነ-መረብ አገልግሎት ሰጪዎች፤ የሕፃናት ወሲባዊ በደልን የሚያሳዩ ይዘቶችን ነቅሶ የማስወገድ ተግባር እንዲያከናውኑ ሕጋዊ ግዴታ ሊጣልባቸው ይገባል። የሕፃናት የበይነ-መረብ ቆይታ ደኅንነትን ለማረጋገጥ ይህንን እርምጃ ማስፈጸም ወሳኝነት አለው።

## ቁምነገር 3.

**የፍትሕ ሥርዓቱ እስካሁን ድረስ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ሊባል የሚችል አንድም ነገረ-ጉዳይን አላስተናገደም። ለበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የተሻለ ምላሽ ለመስጠት እንዲቻል፤ የሕግ አስከባሪውን እና የዳኝነት ሥርዓቶችን ዕውቀት፣ አቅም፣ እና አደረጃጀት የሚያጎለብት ማርሽ ቀያሪ ኢንቨስትመንት ማድረግ ይደር የማይባል አስቸኳይ ጉዳይ ነው።**

### ሕግ አስከባሪ አካላት

**3.1 ሁሉንም የፖሊስ አባላትን እና ዐቃቤ-ሕጎችን ያሠልጥኑ፤** የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል በሚፈጸምባቸው በሁለቱ ስልቶች (ማለትም በበይነ-መረብ እና በአካል) መካከል ስላለው ቁርኝት በተለይም በቀበሌ እና በወረዳ እርከኖች ላይ ያሉትን ያሠልጥኑ። በበይነ-መረብ የሚፈጸሙ የበደል ድርጊቶች ላይ ክስ ለመመሥረት ስለሚያስችሉ የሕግ ድንጋጌዎች ያሳውቋቸው።

**3.2 በሕፃናት ጥበቃ ላይ ይበልጥ ያተኮሩ የሥራ ክፍሎችን ያቋቁሙ፤** የሥራ ክፍሎቹ ለሕፃናት-ምቹ ድጋፎችን ለመስጠት የሚችሉ የሠለጠኑ ወንድ እና ሴት ሠራተኞች ያሏቸው፤ ብሎም ለዚሁ የሚያስፈልገው በቂ ቦታ እና መሣሪያ የተሟሉላቸው ሊሆን ይገባል። የፌደራል ፖሊስ ኃይሉ ተጠሪነት ለሰላም ሚኒስቴር

120 መንግሥት፣ የበይነ-መንግሥት ድርጅቶች፣ እና የሲቪል ማኅበረሰቡ እነዚህን መልእክቶች ተርጉመው ለተንከባካቢዎች፣ ለመምህራን፣ ለሕክምና ባልደረቦች፣ እና ለማኅበራዊ ድጋፍ ሠራተኞች ሊያዳርሱ ይገባል።

እንደመሆኑ፤ የተጠቀሱትን ለማሟላት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል።

**3.3 የፖሊስ አባላት ለሕፃናት ቃለ-መጠይቅ ስለሚያደርጉበት አግባብ የሚደነግግ መመሪያ ያዘጋጁ።** ይህም ሕፃናት በተደጋጋሚ ቃለ-መጠይቅ እንዳይደረግላቸው እና ዳግም ተጠቂ የሆኑ መስሎ እንዳይሰማቸው ለማድረግ ያግዛል። ድጋፍ ፈላጊ ሕፃናት በቀላሉ ሊገነዘቧቸው የሚችሉ ስለ መብቶቻቸው የሚገልጽ መረጃን ጨምሮ፤ ሰነዶችን የማዘጋጀት ዕቅድ ይኑርዎት።

**3.4 በሚመለከተው የሕግ አስከባሪ መሥሪያ ቤት ሥር ያለው የሳይበር ወንጀሎች የሥራ ክፍል፤ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል-ነክ ነገረ-ጉዳዮችን የመለየት እና ለዓለም-አቀፍ የቴክኖሎጂ ፕላትፎርሞች የመምራት አቅሙን ያሻሽሉ።**

**3.5 ከኢንተርፖል የ‹ዓለም-አቀፍ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ› (International Child Sexual Exploitation (ICSE)) የመረጃ ቋት[121] ጋር ትስስር እንዲፈጠር ያድርጉ።** የተጠቀሰው ቋት ለመመረጅ (intelligence) እና ለመመርመር የሚረዳ መሣሪያ ሲሆን፤ ይህም ልዩ/ዓይነተኛ መርማሪዎች የሕፃናት ወሲባዊ በደል ነገረ-ጉዳዮችን የያዙ መረጃዎችን እንዲለዋወጡ ያስችላቸዋል፡ ፡ የሕፃናት ወሲባዊ በደል ይዘቶች የሚጠራቀሙበት ሃገር-አቀፍ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የመረጃ ቋት እንዲቋቋም ያድርጉ።

**3.6** በሕፃናት ላይ በወቅቱ እየደረሱ ያሉ ጉዳቶችን ለመቀነስ እንዲቻል፤ ከጠ/ብ/የ/ሕ/ብ/ማእከል የሚሰጡ የሳይበር ጥቆማዎችን ጨምሮ **ዓለም-አቀፋዊ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ምሪቶች በተገቢው የምርመራ ደረጃ ተገምግመው ማለፋቸውን የሚያረጋግጥ ብቁ አሠራር እና በቂ ሐብት እንዲኖር ያድርጉ።**

## የፍርድ ቤት ሥርዓቶች እና የፍትሕ ባለሙያዎች

**3.7 የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጉዳይ በፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ-ሕግ ጽሕፈት ቤት ሥር ባለው ‹የሃገር-አቀፍ ማስተባበሪያ አካል› (National Coordination Body) ውስጥ በአጀንዳነት እንዲካተት፤** እንዲሁም የሳይበር ወንጀል የሥራ ክፍልን እና የመረጃ መረብ ደኅንነት ኤጀንሲን ጨምሮ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጉዳይ የሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶችን በማስተባበሪያው ውስጥ በማካተት ተሳትፎውን እንዲሰፋ ያድርጉ።

**3.8 የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ነገረ-ጉዳዮች አያያዝ እና ለሕፃናት-ምቹ የሆነ ፍትሕ አሰጣጥ ላይ ያተኮረ ሥልጠናን ዐቃቤ-ሕጎችን እና ዳኞችን ጨምሮ ለሁሉም የፍትሕ ኃላፊዎች እንዲሰጥ ያድርጉ።**

**3.9** የበይነ-መረብ ንክኪ ያላቸውን ጨምሮ በማናቸውም የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ነገረ-ጉዳዮች ላይ **ለሕፃናት-ምቹ የሆነ የፍትሕ አሠጣጥ ሁኔታዎች ሁሌም ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጡ።** ይሄም ገንዘብን፣ የክዋኔ ደንቦችን (operating procedures)፣ እና ሥልጠናን ማቅረብ ይጠይቃል። ተጎጂ ሕፃናት ከፍርድ ቤት ሥነ-ሥርዓቶች እና ከሕግ ተዋንያን ጋር አስቀድመው እንዲለማመዱ እና ዝግጁ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን አዘጋጅተው ይተግብሩ። ተበዳይ ሕፃናት ከበዳያቸው ጋር ፊት ለፊት የማይገናኙበት አሠራር መዘርጋቱን ያረጋግጡ፤ ለምሳሌ የቪዲዮ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ማስረጃው ከሌላ ክፍል ሊሰጥ ይችላል፡ ፡ በ‹ባርንሀውስ ሞዴል›[122] (Barnahus model) የተጠቀሰው የችሎት አሠራር ዘዴን በመመርመር ጥቅም ላይ ማዋል ይቻላል። የተጠቀሱትን አማራጮች መጠቀም ካልተቻለ፤ ጥብቅ ምሥክሮች የሚቀመጡበትን ሳጥን መጠቀም ይቻላል (ምንም እንኳ ከሕፃኑ/ኗ ይልቅ ተከሳሹን በሳጥኑ ውስጥ ማስገባት ተመራጭ የነበረ ቢሆንም)። የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል-ነክ ነገረ-ጉዳዮች በሚታዩበት ችሎት ላይ በተጎጂው ላይ የደረሰው ጉዳት ወይም ጠንቅ እንዲገለጽ ጥያቄ ያቅርቡ። ይህም የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ድርጊት ስለሚያስከትላቸው ጉዳቶች ግንዛቤ ለመፍጠር፤ ብሎም ተበዳዩ ወገን በፍርድ ሂደቱ ላይ ‹የምር እየታየሁ እና እየተሰማሁ ነው› የሚል ስሜት እንዲፈጠርበት ያግዛል።

**3.10 የተጎጂ ፈንድ ከማቋቋም ጋር የተያያዙትን አራቱን መመሪያዎች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ያድርጉ።** እነዚህም ለሕፃናት ነጻ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ማቅረብን፤ ለሕፃናት እና ለተንከባካቢዎቻቸው ጊዜያዊ መጠለያ፣ ምክር፣ መጓጓዣ፣ ወይም የቤት ኪራይ አበል በመስጠት መደገፍን፤ እንዲሁም የሥነ-ልቦና ድጋፍ አገልግሎቶችን ያጠቃልላሉ።

**3.11** የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የደረሰባቸው ተጎጂዎች **የሕግ ድጋፍ፣ የሥነልቦና-ወማህበራዊ እና የሕክምና አገልግሎቶችን የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቹ።**

## መንግሥት

**3.12** በተለይም በወረዳ እና በቀበሌ እርከኖች ላይ ያሉ **የፖሊስ አባላትን፣ ዐቃቤ-ሕጎችን፣ ዳኞችን፣ የችሎት ሠራተኞችን፣ የሕፃናት ጥበቃ እና የግንባር ቀደም ሠራተኞችን** ስለ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ምንነት ብሎም በየሙያ መስካቸው ችግሩን መቅረፍ ስለሚቻልባቸው መንገዶች **ለማሠልጠን የሚያሻውን ወጪ በፍጥነት ይመድቡ።** የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን ጨምሮ የሕፃናት ጥበቃ ርእሰ-ጉዳዮችን በመሠረታዊ ሥልጠናዎች ውስጥ፤ ብሎም ለዓይነተኛ ባለሙያዎች በሚሰጡት ሥልጠናዎች ውስጥ ደግሞ በስፋት እንዲካተት ያደርጉ። የመነሻ ሥልጠናን እንዲሁም ትውስታን የሚያድሱ ተከታታይ ሥልጠናዎችን በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ላይ እንዲሰጥ ያድርጉ።

**3.13** አስቀድሞ እስከተደነገገው ዝቅተኛው የጊዜ ገደብ ድረስ መረጃዎችን ይዘው እንዲያስቀምጡ፣ የሕፃናት ወሲባዊ በደልን የሚያሳዩ ቁሳቁሶችን ነቅሰው እንዲለዩ እና/ወይም እገዳ እንዲጥሉ እና/ወይም እንዲያስወግዱ፣ እንዲሁም የሕግ አስከባሪ አካላት ለሚያቀርቡት የመረጃ ጥያቄ አፋጣኝ ምላሽ እንዲሰጡ የበይነ-መረብ አገልግሎት ሰጪዎችን የሚያስገድዱ **ሕጋዊ ድንጋጌዎች እንዲጣል ያድርጉ።**

**3.14 የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን ለመቅረፍ እንዲቻል ለሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች በሙሉ ለዚሁ ዓላማ ብቻ የሚውል ገንዘብ እንዲመደብላቸው ያድርጉ።** ኃላፊነት ያለባቸው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች - የሴቶች፣ ሕፃናት፣ እና ወጣቶች ሚኒስቴር፤ እንዲሁም የባህል እና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሊሆኑ ይችላሉ። የተጠቀሰውን የገንዘብ እገዛ እውን ለማድረግ፤ ዩኒሴፍ እና በሕፃናት ላይ በሚፈጸሙ ጥቃቶች ዙሪያ

121. የኢንተርፖልን ‹ዓለም-አቀፍ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ› (International Child Sexual Exploitation (ICSE)) የመረጃ ቋት የተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ይህንን ማስፈንጠሪያ በመጫን ማግኘት ይቻላል።

122. የባርንሃውስ ሞዴል፤ ጥቃት ለደረሰባቸው ተጎጂ ሕፃናት እና ለምሥክሮች የተፋጠነ ፍትሕን እና ክብካቤን ለማድረስ ጥቅም ላይ የሚውል መደበኛ የአሠራር ሂደት ነው።

የሚሠሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መንግሥትን እንዲደግፉ ማድረግ ይቻላል።

### ኢንደስትሪ

**3.15** የፍርድ ሂደቱን ርዝማኔ ለመቀነስ ሕፃናት-ቀመስ ነገረ-ጉዳዮችን አስመልክቶ **ከፍርድ ቤቶች ለሚቀርቡ የመረጃ ጥያቄዎች አፋጣኝ ምላሽ እንዲሰጥ ያድርጉ።**

### የማኅበራዊ ድጋፍ ዘርፍ

**3.16 በማኅበራዊ ድጋፍ አገልግሎቶች ላይ በግንባር ቀደምነት የተሠማሩትን ሁሉንም ሠራተኞች ያሠልጥኑ፤** ይህም በዓይነታቸው የተለዩ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ስጋቶችን እና ጉዳቶችን በብቃት ለመለየት ብሎም ውጤታማ እና በማስረጃ የተደገፈ ምላሽን ለመስጠት እንዲቻል ነው።

**3.17 የማኅበራዊ ድጋፍ አገልግሎቶች ለታዳጊዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ከተፈለገ ዘመናዊ እና ፈጠራ-አከል መንገዶችን መጠቀም አለባቸው።** ለሕፃናት ሰፊ ተደራሽነት ካላቸው መንገዶች መካከል አንዱ የዕርዳታ መጠየቂያ መስመሮች ሲሆኑ፤ ለይስሙላ መኖራቸው ብቻ በቂ ስለማይሆን፤ ዳጎስ ያለ ውሕሎተ-ንዋይን እና የሐብት ግብአትን ይጠይቃሉ። ሌላው ዓይነት የማኅበራዊ ድጋፍ አገልግሎቶች መስጫ መንገድ ደግሞ፤ የሕፃናትን የበይነ-መረብ ውሎ እና አጠቃቀም በቅጡ በተረዱ ወጣት እና ሥልጡን ሠራተኞች ታግዞ በበይነ-መረብ በኩል የሚሰጥበት አማራጭ ነው።

## ቁምነገር 4፡

### ሥራን ለማሣለጥ ወሳኝ የሆኑ ከበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጋር የተያያዙ የሕግ ማሻሻያዎችን ማድረግ

### መንግሥት

**4.1 በ‹ሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን› ውስጥ ያለው ‹የሕፃናት ሽያጭ፣ የሕፃናት የወሲብ ንግድ፣ እና የሕፃናት የብልግና ምስል-ወድምጽ [ፖርኖግራፊ] አማራጭ ፕሮቶኮል›[123] ላይ ከተቀመጡት ደረጃዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ፤ የሕግ ማሻሻያን እና የሕግ የማዘመን ተግባራትን ያከናውኑ፡** ፡ የሕፃናት ወሲባዊ በደልን ያዘሉ ቁሳቁሶችን እንዲሁም ከሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ ጋር የሚያያዙ ሌሎች ወንጀሎችን በመከላከል ረገድ የተጠቀሰው ፕሮቶኮል ፋይዳ አለው።

**4.2** እ.ኤ.አ. በ2014 የአፍሪካ ኅብረት የተቀበለውን **‹የሳይበር ደኅንነት እና የግላዊ መረጃ ጥበቃ› (Convention on Cyber Security and Personal Data Protection) ሃገሪቱ ተቀብላ እንድታጸድቅ ያድርጉ።** ከበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል አኳያ፤ ኮንቬንሽኑ በተለይ የሕፃናት ወሲባዊ በደል አዘል ቁሳቁሶችን ያካተቱ ድንጋጌዎችን ይዟል።

**4.3 የሕግ ማሻሻያዎችን ከዓለም-አቀፍ ኮንቬንሽኖች ጋር የማጣጣም ዕቅድ ይኑርዎት፤** ይህም ጉዳዩን ለመቅረፍ የሚያስችሉ አቅጣጫዎችን በእጅጉ ይሰጣል። ለምሳሌ ያህል በአውሮፓ ምክር ቤት የወጡት ‹ሕፃናትን ከወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ለመጠበቅ የወጣ ኮንቬንሽን› (የ‹ላንዛሬት ኮንቬንሽን›) እና ‹የሳይበር ወንጀል ኮንቬንሽን› (የ‹ቡዳፔስት ኮንቬንሽን›) ይጠቀሳሉ፡፡ ምንም እንኳ የእነዚህ ኮንቬንሽኖች ተፈጻሚነት በቀጣናው ማለትም በአውሮፓ ምክር ቤት አባል ሃገራት ላይ ብቻ የጸና ቢሆንም፤ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ላይ የሚከተሉት አቅጣጫ ግን ፋይዳቸውን በእጅጉ ከፍ እንዲል አድርጎታል። ከቀጣናው ውጪ ያሉ ሃገራት በእነዚህ ኮንቬንሽኖች እንዲገዙ ባይጠበቅባቸውም፤ በሃገር-አቀፍ ደረጃ ያሉ የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል-ነክ የሕግ ማእቀፎችን ለመገምገም ጠቀሜታ ያላቸው እና፤ የአውሮፓ ምክር ቤት አባል ያልሆኑ ሃገራትም ኮንቬንሽኖቹን ተቀብለው ለማጽደቅ የሚያስችል አማራጭን ያዘሉ ናቸው።

**4.4 ከሕፃናት ወሲባዊ በደል ቁሳቁስ ጋር የሚያያዙ ሁሉንም ድርጊቶች እንዲሁም የሕፃናት ወሲባዊ በደልን በቀጥታ-ሥርጭት ማስተላለፍን በማያሻማ ሁኔታ በማካተት፤ ብሎም በበይነ-መረብ ላይ የሚፈጸም ለወሲብ አስገድዶ-መጠቀምን እና ወሲባዊ ትንኮሳን ጨምሮ ሁለንተናዊነት በተላበሰ መልኩ የሕግ ማሻሻያዎችን ያድርጉ።** ምንም እንኳ የኮምፒዩተር ወንጀልን ለመደንገግ የወጣው አዋጅ፤ የሕግ አስከባሪ አካላት የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ነገረ-ጉዳዮችን ለመመርመር የሚያግዟቸውን የአካሄድ ሥነ-ሥርዓቶችን የሚደነግግ ይዘት ቢኖረውም፤ ድንጋጌዎቹ ግን የሕፃናት ወሲባዊ በደል አዘል ቁሳቁሶችን፣ ለወሲባዊ ዓላማ የአንድን ሕፃን ወሲብ ቀስቃሽ ብልቶች ማሳየትን፤ ኢ-ትእይንታዊ (non-visual) ቁሳቁሶችን፤ ብሎም በምናብ የተፈጠሩ ሕፃናትን እውን የሚመስል ገጽታ በማላበስ የተሰናዱትን ጨምሮ በዲጂታል ቴክኖሎጂ የተፈበረኩ የሕፃናት ወሲባዊ በደል ቁሳቁሶችን ምንነት ወይም ፍቺ የማይገልጹ እና የማያካትቱ ናቸው። አልፎ ተርፎም፤ አዋጁ የሕፃናት ወሲባዊ በደል አዘል ቁሳቁሶችን ሆን ብሎ ወይም በማወቅ የመቀበል ድርጊትን እንደ ወንጀል አድራጎት አይደነግግም።

**4.5 ለወሲብ ዓላማ በበይነ-መረብ የሚፈጸም የማሽኮርመም ወንጀል ላይ ያሉ ሁኔታዎችን በሚያካትት መልኩ የሕግ ማሻሻያ ያድርጉ፤** እነዚህም ወሲባዊ በደሉ የደረሰው የአካል ግንኙነት በመደረጉ የተነሣ ሳይሆን በበይነ-መረብ አማካኝነት የሚፈጸሙበትን ሁኔታዎች ጭምር ማለት ነው። (ለምሳሌ ሕፃናትን በማታለል ወሲባዊ በደል አዘል ይዘቶችን አዘጋጅተው ለወንጀለኛው እንዲልኩ የሚደረግበት ሁኔታ ይጠቀሳል።)[124]

123. OHCHR. (2000). Optional Protocol to the Convention on the Rights of the Child on the sale of children, child prostitution and child pornography.

124. የላንዛሬት ኮሚቴ እ.ኤ.አ. በ2015 በኮንቬንሽኑ አንቀጽ 23 ላይ በሰጠው አስተያየት፤ የኮንቬንሽኑ ፈራሚ ሃገራት ይህንን በሰፊው የሚተረጎመውን የበይነ-መረብ ማሽኮርመም ብያኔን ወይም አገላለጽን እንዲቀበሉት ምክረ-ሐሳብ አቅርቦላቸው ነበር፤ የአውሮፓ ምክር-ቤት የላንዛሬት ኮሚቴ (እ.ኤ.አ. 2015)፤ የላንዛሬት ኮንቬንሽን አንቀጽ 23ን የተመለከተ አስተያየት እና የማብራሪያ ሐተታ፤ ፓራግራፍ 20፤

# ዐማርኛ

| | |
|---|---|
| Child Sexual Abuse Material (CSAM) | የሕፃናት ወሲባዊ በደል-አዘል ቁሳቁስ (ሕ/ወ/በ/ቁሳቁስ) |
| Child Sexual Exploitation and Abuse (CSEA) | የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል (ሕ/ወ/ብ/በደል) |
| Helpline | የዕርዳታ መጠየቂያ መስመር |
| Hotline | የአደጋ ማሳወቂያ መስመር |
| Internet/online | በይነ-መረብ |
| Online Child Sexual Exploitation and Abuse (OCSEA) | የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል (በ/መ/ሕ/ወ/ብ/በደል) |
| Online gaming | የበይነ-መረብ የጨዋታ ግጥሚያ |
| Pornography | የብልግና ምስል-ወድምጽ |
| Sexual  assault | ወሲባዊ ጉንተላ |
| Sexual harassment | ወሲባዊ ትንኮሳ |
| Stigma | መጠቋቆሚያ (የመሆን ፍራቻ) |
| Website | ድረገጽ |

# ዕውቅና እና ምስጋና


ኢ/ሲ/ፒ/ኤ/ቲ/ ኢንተርናሽናል፣ ኢንተርፖል፣ እና የዩኒሴፍ የምርምር ጽ/ቤት-ኢኖሰንቲ በኢትዮጵያ ስላለው የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ነባራዊ ሁኔታ፣ ስጋቶች፣ እና የሕፃናት አተያይ/አረዳድ ላይ ተጨባጭ ማስረጃዎችን ለማግኘት እጅ-ለእጅ ተያይዘው ለመሥራት ያስቻላቸውን ዓይነተኛ ዕድል በማግኘታቸው የላቀ ደስታ ተሰምቷቸዋል። ይህ ሁለንተናዊ ሪፖርት፤ ለሁለት ዓመታት በዘለቀ የተቀናጀ ሥራ አማካኝነት ዕቅድ የወጣበት፤ እና የሚያስደንቁ መረጃዎች የተሰበሰቡበት እና የተተነተኑበት ነው። ያለ በርካታ ኢትዮጵያዊያን እና የኢትዮጵያ አጋሮች ተሳትፎ፤ እነዚህ ጥረቶች ስኬታማ ለመሆን ባልቻሉ ነበር።

የፕሮጀክቱ አጋሮች በ*ዲስረፕቲንግ ሀርም* ለተሳተፉት እና ቀጥሎ የተዘረዘሩትን አስተዋጽኦዎች ላበረከቱት ሁሉ ምስጋናቸውን ይገልጻሉ፦

- ግኝቶቹን በማጽደቅ እና ከነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በማዛመድ ረገድ፦ የአፍሪካ ኅብረት፣ የሳይንስ እና የከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር፤ የሴቶች፣ ሕፃናት፣ እና ወጣቶች ሚኒስቴር፤
- በጥሬ መረጃ አሰባሰብ ረገድ፦ አማኑኤል የልማት ማኅበር፣ የኢንተርፖል ‹ሃገር-አቀፍ ማእከላዊ ቢሮ› በአዲስ አበባ፣ ኢፕሶስ ሞሪ፣ ትሪቦንድ ሪሰርች ኤንድ ኮንሰልቲንግ ፒ/ኤል/ሲ/፣ የዩኒሴፍ ምሥራቃዊ እና ደቡባዊ አፍሪካ ክልላዊ ጽሕፈት ቤት፣ እና የዩኒሴፍ ኢትዮጵያ ጽሕፈት ቤት፤
- በቃለ-መጠይቆች እና መጠይቆችን በመሙላት ዕውቀታቸውን እና ተሞክሯቸውን በማካፈል ረገድ፦ የቀበሌ 06 የማህበረሰብ ጥምረት ኮሚቴ፣ የቀበሌ 08 የማህበረሰብ ጥምረት ኮሚቴ፣ ዓለም የሕፃናት መርጃ ድርጅት፣ አፍሪካን ሂዩማኑቴሪያን አክሽን፣ አፍሪካን ኔትዎርክ ፎር ዘ ፕሪቬንሽን ኤንድ ፕሮቴክሽን አጌይነስት ቻይልድ አቢዩዝ ኤንድ ነግሌክት፣ አሶሲየሽን ፎር ዘ ሪሃቢሊቴሽን ኦፍ ገርልስ፣ አራት ኪሎ የሕፃናት ክብካቤ እና የማኅበረሰብ ልማት፣ ቤዛ ፖስቸሪቲ ዲቨሎፕመንት ኦርጋናይዜሽን፣ ኬሪንግ ፎር ቨልነራብል ችልድረን ፕሮጀክት፣ ቻይልድ ኤይድ ኤንድ ዲቨሎፕመንት፣ ቻይልድ ዲቨሎፕመንት ተሬይኒንግ ኤንድ ሪሰርች ሴንተር፣ የሕፃናት ፍትሕ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት፣ የሳይበር ወንጀል ምርመራ ዲቪዥን፣ የሳይበር ወንጀል ክፍል፣ የደሴ ከተማ የወረዳ ፍርድ ቤት፤ የደሴ ከተማ የሴቶች፣ ሕፃናት፣ እና ወጣቶች ጽሕፈት ቤት፤ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር፣ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ-ሕግ ጽሕፈት ቤት፣ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ፍሪደም ፈንድ፣ ፎረም ኦን ሰስቴይነብል ቻይልድ ኢምፖወርመንት፣ የባህል እና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ የትምህርት ሚኒስቴር፣ የኢኖቬሽን እና የቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፤ የሴቶች፣ ሕፃናት፣ እና ወጣቶች ሚኒስቴር፤ ሚሽን ፎር ቻይልድ ዲቨሎፕመንት፣ ኖርዌጂያን ሪፊዩጂ ካውንስል፣ ፕላን ኢንተርናሽናል፣ ፕሮፌሽናል አሊያንስ ፎር ዲቨሎፕመንት፣ ሴፍ ማይግሬሽን ፕሮጀክት፣ ቴሬ ዴዝሆም ኢትዮጵያ፣ የዩኒሴፍ ኢትዮጵያ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት፤ የዩ/ኤን/ኦ/ዲ/ሲ/ ፕሮግራም ጽሕፈት ቤት በኢትዮጵያ፣ እና ወሎ ዩኒቨርስቲ

በዚህ ሪፖርት የተሳተፉት የሁሉም ሠራተኞች፣ አማካሪዎች፣ አስተርጓሚዎች፣ እና የሥራ ላይ ተለማማጆች ትብብር የተሞላበት ጥረት ባይኖር ኑሮ ይህ አመርቂ የምርምር ሥራ ለውጤት አይበቃም ነበር። በተለይም፤ የሚከተሉትን አካላት ለማመስገን እንወዳለን፦

**ከኢ/ሲ/ፒ/ኤ/ቲ/ ኢንተርናሽናል፡** ቲያጎ አፎንሶ፣ ዶ/ር ቪክቶሪያ ቤይነስ፣ አሊስ ቤቨን፣ ዊል ቤቨን፣ ዊሊ ቡሎሶ፣ የርሚ ብሬነር፣ ዶ/ር ማርክ ፒ. ካፓልዲ፣ ናርሲሶ ከምበ፣ ዶ/ር ዶሮቲ ዛርነኪ፣ ጃሬት ዴቪስ፣ ራንግሲማ ዴሳዋዴ፣ ጁሊያ ዱርስካ፣ ሶኒያ ኤስፓላርጋስ ቫል፣ አኔካ ፋሪንግተን፣ ቤያትሪስ ጋሴንጎ፣ ቲያጉ ጋንሳን፣ ዶ/ር ሱዛና ግሬጀር፣ ዚፖራህ ጎይትዜ፣ ጆሴፊን ሀንግስትሮም፣ አሊስቴር ሂልተን፣ ማሪያ ኢባኜዝ ቤልትራን፣ ዎራዋን ጂራታናፒዋት፣ ሱፕሪያ ካሳጁ፣ ዶ/ር ማርክ ካቬናግ፣ በርናንድ ኬነዲ፣ ዶሪን ቫን ደር ኮውር፣ ሱዛን ክሬስተን፣ ማሪ ሎውረ ሌመነር፣ ራፋኤሌ ሌክለር፣ ካትሪና ማሪስዋሚ፣ ጆን ማክጊል፣ ማርክ ማክኪሎፕ፣ ስቴላ ሞትሲ፣ ፍሎረንስ ሙዌኒ፣ ማኒዳ ኔብክላንግ፣ ካትሪን ናፔር፣ ሩምቢድዛይ ንጊንዲ፣ ፍሬዲ ኒኮልድስ፣ ሜጋን ኖርቴይ፣ ኤስተር ኦብዳም፣ ዶ/ር ናቲቪቲ ፔታላር፣ ዶ/ር ክሪስተን ፖንታሊ፣ ማሪ ጆይ ፕሪንግ፣ ዶ/ር ኤቴል ኩዋይሌ፣ ማሪታ ራድሜየር፣ ኬይራን ሩምስቢ፣ ጀኒፈር ሻትዝ፣ ጉንቻ ሻርማ፣ ኖንግ ሶሺያት፣ ቺትራፖን ቫናስፖንግ፣ አንድሬአ ቫሬላ፣ ክሪስተን ዋልኮም፣ ስካይለር ዌይት፣ ቲሞቲ ዊሊያምስ፤ **የዩኒሴፍ የምርምር ጽሕፈት ቤት - ኢኖሰንቲ፡** ዶ/ር ዳንኤል ካርዲፌልት-ዊንዘር፣ ማሪ ኖድዘንስኪ፣ መርየም ሰኢድ፣ ሮጀርስ ትዌሲጌይ፤

**የኢንተርፖል በሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች የሥራ ክፍል**

‹ደኅንነቱ የተጠበቀ በይነ-መረብ› በሚሰኘው ውጥኑ አማካኝነት ግሎባል ፓርትነርሺፕ ቱ ኢንድ ቫዮለንስ አጌይነስት ቺልድረን፤ በአማካሪዎች ቦርድ አማካኝነት ለሰጠው ምክር እና ለዚህ ፕሮጀክት ላበረከተው ከፍተኛ የገንዘብ ወጪ የፕሮጀክቱ አጋሮች ዕውቅና ለመስጠት ይወዳሉ። የ‹ሴፍ ኦንላይን› ቡድን የ*ዲስረፕቲንግ ሀርም*ን ጽንሰ-ሐሳቦች ቅርጽ በማስያዝ፣ የቴክኒክ አስተዋጽኦችን በማድረግ፣ እና የማያወላውል ድጋፍ በመስጠት ባደረገው አበርክቶ የ*ዲስረፕቲንግ ሀርም* አጋሮች ደስተኞች ናቸው።

ከሁሉ የላቀ ምስጋናችን፤ አስተዋጽኦ ላደረጉ ሕፃናት፤ በተለይም የበበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የደረሰባቸው እና  የደረሰባቸውን በድፍረት ለምርምር ቡድኖቹ ለገለጹ ታዳጊዎች ይድረሳቸው። የሕፃናቱ ተሞክሮዎች ቀጣዩን ጉዞ ለመወሰን ቁልፍ ሚና አላቸው።

